እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

ሚንነቱና መለኮታዊ ተልእኮው

1992 ዓ.ም.

1999 እ.አ.አ.

ከመለሰ ካሳ ወልደጻድቅ

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

ማንነቱና መለኮታዊ ተልእኮው

God The Holy Spirit: His Person and Divine Mission

ይህንን መጽሐፍ
ያለ ደራሲው ፈቃድ ሙሉ ለሙሉም ሆነ
በከፊል ግባት በሕግ የተከለከለ ነው።

Copyright © Melesse K. Woldetsadik 1999
First published in 1999

All rights reserved.
No part of this publication may be reproduced
or transmitted in any form or by any means without
the express written consent by the author.

Printed in the United States of America

For comments, questions or to order
additional copies write to:
Word of Peace Ministries
79-E Islay Lane
Columbia, SC 29210
USA
Tel. (803) 772-5293
Or
(919) 462-3298

እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑን ላሳየኝ: —

ከመንድሚ ተስፋዬ ተፈራ

እንዲሁም የእግዚአብሔርን ፍቅር በቃልም ሆነ
በኑሮው በስደተኛው ሕዝብ መካከል ለሚሰብከው: —

ከመንድሚ ሙሀሸት መንገሻ

የእግዚአብሔር መንፈስ መገኘት ሐሴትና ኃይል ይሁናችሁ
ስል ይህቺን መጽሐፍ ለእነርሱ ማስታወሻነት አበረክታለሁ።

ምስጋና

በመጀመሪያ ለወደደኝ፥ ስለ እኔም ራሱን አሳልፎ በመስጠት የዘላለም ሕይወትን ወራሽ አድርጎ በዚህ ዓይነት ሁኔታ እንዳገለግለው ያቆመኝን ጌታዬንና አምላኬን ኢየሱስ ክርስቶስን እጅግ እድርጌ አመሰግነዋለሁ። ከዚያም በመቀጠል ይህንን መጽሐፍ ልጽፍ ከተነሳሳሁበት ጊዜ አንስቶ በጸሎትና በድጋፍ አብረኝ በመቆም እንዲሁም ረቂቁን በማረም የረዳችኝን ውድ ባለቤቴ ራሔልን አመሰግናታለሁ። እንዲሁም በጸሎት፥ አስተያየት በመስጠትና በማበረታታት ካጠገቤ የቆመውንና በሥጋም በጌታም መንድሜ የሆነውን ታደሰ ካሳን አመሰግነዋለሁ። ረቂቁን እንብበው ደግሞ ጠቃሚ ሃሳብ በመስጠት መጽሐፉ በተሻለ መልክ እንዲቀርብ የረዱኝን ወንድሜ ደሳለው አዲስና ወንድሜ ጋሽ አሳየኸኝ በርኸን አመሰግናቸዋለሁ። ወንድሜ አስቻለው ተሾመና እህቴ ሙሉ ኃይለ ሚክያኤል ደግሞ ሁሉ በጸሎታቸው ስለሚያስቡኝ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

I would like to thank Dr. Craig S. Keener, a friend and mentor, whose prayers, encouragement, and wisdom always lift me up. At last but not least, I am grateful to my friend, Dr. Aaron Joungreise, for his unceasing prayers and encouragement that I have benefited through out the years.

ማውጫ

ምዕራፍ ገጽ

መቅድም 9

መግቢያ 12

1. ሥላሴ 17
2. መንፈስ ቅዱስ በፕንታቱክ ውስጥ 26
3. የመሳፍንት ዘመን ካሪዝማቲክ መሪዎች 34
4. መንፈስ ቅዱስ በነገሥታት ዘመን 38
5. መንፈስ ቅዱስ በነቢያት መጻሕፍት ውስጥ 45
6. መንፈስ ቅዱስ በጥንቱ ይሁዲ ሃይማኖት ውስጥ 56
7. መንፈስ ቅዱስ በወንጌላት ውስጥ 62
8. መንፈስ ቅዱስና የሐዋርያት ሥራ 88
9. መንፈስ ቅዱስና የሮሜ ሰዎች 95
10. መንፈስ ቅዱስና የቆሮንቶስ ሰዎች (1) 104
11. መንፈስ ቅዱስና የቆሮንቶስ ሰዎች (2) 114
12. መንፈስ ቅዱስና የገላትያ ሰዎች 122
13. መንፈስ ቅዱስና የኤፌሶን ሰዎች 137
14. መንፈስ ቅዱስና የፊልጵስዩስ ሰዎች 148
15. መንፈስ ቅዱስና የቆላስይስ ሰዎች 152
16. መንፈስ ቅዱስና የተሰሎንቄ ሰዎች (1&2) 154
17. መንፈስ ቅዱስ በመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ 160
18. መንፈስ ቅዱስና የዕብራውያን ሰዎች 166
19. መንፈስ ቅዱስ በጴጥሮስና በዮሐንስ መልእክቶች ውስጥ 170
20. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና አገልግሎት 176

መዝገቢያ 211

መቅድም

ይህ መጽሐፍ የተጻፈበት ዋና ምክን

ያት የሥላሴ ሦስተኛዉ አካል ስለሆነዉ ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ማን ነትና የርሱን መለኮታዊ ተልእኮ በሚገባ ስማብራራት ታስቦ ነዉ። እንደሚታ ወቀው ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ በአማኞች መካከል መገኘትና በአማኞች ውስጥ ማደር ማለት የእግዚአብሔር በሙላትና በኃይል መገኘት ማለት ነዉ። መንፈስ ቅዱስም የእግዚአብሔር በክብርና በሙላት መገኘት በመሆኑ ስለ እግዚአብሔር ማወቅ የሚገባንን እውነት እንድናውቅ ይረዳናል። በተጨማሪም በሕይወት ልምምዳችንም ውስጥ እግዚአብሔር በልጁ በኩል የሰጠንን የዘላለም ሕይወት እውን ያደርግልናል። ይህም ማለት በጉባኤያችን መካከልና በልባችን ውስጥ በመሆን በቅዱስ ቃሉ ውስጥ የተገለጠውን ዘላለማዊ እውነት በማስተማርና እንዲሁም በቃሉ የተደገፈ፣ ከቃሉ የተስማማና በቃሉ የነጠረ መንፈሳዊ ልምምድ እንዲኖረን ያደርጋል።

በመሠረቱ ይህ መጽሐፍ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ከዘፍጥረት እንስቶ እስከ ራእይ ድረስ ከሞላ ጎደል እካትቶ ይዞአል። ይህንንም ስል ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገሩትን ሁሉንም ጥቅሶች አቅርቤያቸዋለሁ ማለቴ አይደለም። ነገር ግን ለትምህርት ይጠቅማሉ ብዬ ያሰብኩትን በሙሉ አቅርቤ አቸዋለሁ ማለቴ ነው። በተጨማሪም የመጽሐፉ ይዘት ጥልቀት እንዲኖረዉ ተብሎ አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ላይ አንዳንድ ጠቃሚ አሳቦች በግርጌ ማስታወሻ [Footnote] መልክ ቀርበዋል። ስለዚህም አንባቢዉ እነዚህን የግርጌ ማስታወሻ

ዎች በማገናዘብ መረጃ ወይም ድጋፍ አሳቦችን ማግኘት ይችላል። የግርጌ ማስታወሻም እንድጠቀም ያነሳሳኝ ምክንያት እንባቢው የጠቀስኳቸው አሳቦች ከመነጩበት መጽሐፍ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እንዲኖረው በማሰብ ነው። በመሆኑም እንባቢው ስለተጠቀሱት አሳቦች በስፋት እና በጥልቀት ለማንበብ ከፈለገም የመጻሕፍንደራሲ፣ የመጽሐፉን ርዕስ እና አሳታሚውን ድርጅት በመ ውሰድ ፈልጎ ለማንበብይረዳዋል።

ሌላው መጥቀስ የምፈልገው ነገር ቢኖር ይሂንን መጽሐፍ እንድጽፍ ያነሳሳኝ ዋናው ምክንያት ሲሆን ይኸውም እንደሚከተለው ይሆናል — አንደኛ፣ ከሥላሴ አካላት ውስጥ ብዙውን ጊዜ አማኞች በደንብ ያልተረዳነው አካል ቢኖር መንፈስ ቅዱስ ነው። አብን የወሰድን እንደሆነ በአባት እንመስለዋለን፣ ወልድን ደግሞ ሥጋ በመልበስ ሰው ሆኖ፡ ስለ መጣ እርሱንም መመሰል አያስቸ ግረንም። ዮሐንስ በመልእክቱ ላይ «ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያ የነበረው ንና የሰማነውን በዓይኖቻችን ያየነውን የተመለከትነውን እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፤ ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል አንመሰክርማለን፣ ከአብ ዘንድ ለእ ኛም የተገለጠውን የዘላለም ሕይወትን እናወራላችኋለን» በማለት ስለ ኢየሱስ ሥጋ በመልበስ ሰው ሊረዳው በሚችለው መንገድ መገለጡን ይናገራል (1ዮሐ 1፤1-2)። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መመሰል በጣም ያስቸግራል። ለምሳሌ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ከርስቶስ ለኒቆዲሞስ «ነፋስ ወደሚወደው ይነ ፍሳል ድምጹንም ትሰማለህ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንደሚሄድ አታውቅም» (ዮሐ 3፤8) በማለት ስለ መንፈስ ቅዱስ ረቂቅነት ይነገረዋል። ምንም እንኳን በተለያየ ጊዜያት መንፈስ ቅዱስ በእሳት፣ በርግብ፣ በውኃ፣ በነፋ ስ፣ በዘይት ወዘተ ተመስሎ ቢቀርብም ይህንን የመሰለ አካል [Imagery] አለው ብሎ ለመናገር ያዳግታል።

ሁለተኛ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ትምህርቶች መንፈስ ቅዱስን ከኃይልነቱ ባሻገር ለአምላክነቱ የሚገባውን ክብር በመስጠት አሳቡን

1

አምላክ ግለትም እግዚአብሔር ወልድ ሥጋን በላዩ ላይ በመደረብ ሰው ሆኖ ወደ ዚህች ምድር መጣ። ይሁን እንጂ አምላክነቱን ሰላልተወ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው እንደሆነ መታወቅ አለበ ት።

እንደፈቃዱ እንድናገለግል ያበረታቱናል፣ ያስተምሩናልም። ይህም ደግሞ በፍቅር፣ በአኩሪሮትና በፍርሃት ሆነን ስጦታዎቹን እንድንጠቀም ይረዳናል።

ሦስተኛ፣ የርሱን ማንነት፣ መለኮታዊ ባሕርይውንና ተልእኮውን በስፋ ትና በጥልቀት ማወቃችን መንፈሳዊ ስጦታዎቹን በአግባብ እንድንያዛቸውና እን ድንጠቀምባቸው ሲረዳን የክርስቶስ አካል በሆነችውን በቤተክርስቲያን ግንባታ ሥራ ላይ ደግሞ አብረነው እንድንሠራ አመቺ ሁኔታዎች ይፈጥራል።

አራተኛውና የመጨረሻው ደግሞ አንዳንድ አማኞች እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱሱ በኩል በዘመናችን የሚሠራውን መለኮታዊ ድንቅና ተአምራት በመወሰን የመንፈስ ቅዱስስጦታዎች በዛሬ ጊዜ እንደማይሠሩ አድርገው ስለሚወ ሰዱ እግዚአብሔር ከዘጋጀላቸው ብረክት ማለትም አብ ከሰጠው የተሰፋ ቃል ራሳቸውን ሲነፍጉ ይታያሉ። በመሆኑም ይህ መጽሐፍ ልባቸውን ለጌታ መንፈስ ቅዱስ በመክፈት በበረከት እንዲጥለቀለቁና አይተውት በማያውቁት ኃይ ልና መንገድ ቤተክርስቲያንን እንዲያገለግሉ ያበረታታል።

በተጨማሪም በመጽሐፉ ውስጥ አንዳንድ የሳረፍተ ነገር ግድፈት አንዲሁም ከምርመራ ያመለጡ ባዕዳን ቃላት ሊኖሩ ስለሚችሉ በዳግም ኅትመት እስኪስተካከሉ ድረስ እንባቢውን ይቅርታ እጠይቃለሁ። በመጨረሻም በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት ጥቅሶች ከቀድሞው የአማርኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን የዘመን አቆጣጠሩ ደግሞ እንደ አውሮጳውያን ዘመን አቆጣጠር ነው።

በዘላለም ኪዳን ደም ለቦነች ትልቅ አረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከሙታን ያስነሳውና ይህንኑ መንፈስ በልባችን ውስጥ በማስቀመጥ አባዬ ብለን እንድንጠራው፣ ወደርሱም እንድንጮህ ያደረገ የምሕ ረትና የፍቅር አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን በእኛ እያደረገ ፈቃዱን እንፈጽም ዘንድ በመልካም ሥራ ሁሉ ፍጹማን ስለሚያደር ገን፣ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።

መለሰ ካሳ ወልደጻድቅ
ኮሎምቢያ፣ ሳውዝ ካሮላይና
ዩ ኤስ ኤ

«ክርስቶስ በለ እኛ አርግማን ሆኖ ከሕግ አርግማን ዋጀን፤ የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል፣ የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ።»

ገላትያ 3፡14

መግቢያ

ወደ ዕረፍት የሚያመጣ የእግዚአብሔር መንፈስ

መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዉስጥ በአብዛኛው ቦታ «የእግዚአብሔር መንፈስ» ወይንም «መንፈስ» በመባል ይጠራል። ይህም በአብራይስጡ ቋንቋ «ሩአሽ ኤሎሂም» እና «ሩአሽ አዶናይ/ ሩአሽ ያህዌ» የሚባለዉ ነው። መንፈስ የሚለው ቃል በአብራይስጡ «ሩአሽ» ሲሆን በግሪኩ ደግሞ «ፕኦማ» ተብሎ ይጠራል። በተጨማሪም «መንፈስ ቅዱስ» የሚለዉ ቃል በብዛት ተጠቅሶ የምናየዉ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዉስጥ ነዉ። በዚሁ በአዲስ ኪዳን ውስጥም መንፈስ ቅዱስ «የክርስቶስ መንፈስ» (ሮሜ 8፡9)፤ «በክርስቶስ ኢየሱስ ያለ የሕይወት መንፈስ» (ሮሜ 8፡2)፤ «የዘላለም መንፈስ» (ዕብራ 9፡14)፤ «የኢየሱስ መንፈስ» (ሐዋ16 ፡7)፤ «አጽናኙ» (ዮሐ 15፡26፤ 16፡7)፣ «የእውነት መንፈስ» (ዮሐ 16፡13) ወዘተ. በመባልም ይጠራል።

በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስ ከዘፍጥረት አንስቶ እስከ ራእይ ድረስ መለኮታዊ ሥራዉን ሲሠራ በግልጽ ይታያል። ስለዚህም በዘፍጥረት ምዕራፍ

አንድ ላይ «የእግዚአብሔር መንፈስ በዉኃ ላይ ሰፍፎ ነበር» ሲል፣ በራእይ ምዕራፍ ሀያ ሁለት ቁጥር አሥራ ሰባት ላይ ደግሞ «መንፈሱና ሙሽራይቱ ና ይላሉ የሚሰማም ና ይበል፤ የተጠማም ይምጣ የወደደም የሕይወትን ዉኃ እንዲያዉ ይዉሰድ።» በማለት ሲነግረን መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ዓላማ ናአቅድ ለማስፈጸም ያለዉን ሰፍራ ያሳየናል። ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ ጌታ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረው ሰፍራና ይጫወት የነበረው መለኮታዊ ሚና በብዙ አንባብያንና በሥነመለኮት ምሁራን ዘንድ መዘንጋቱ በጣም የሚያሳዝን ሆኖ ቆይቶአል። አንደ አውነቱ ከሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ በብሉይ ዘመን ባይሠራ ኖሮ አዲስ ኪዳን የሚባል ነገር ሊኖር ባልቻለም ነበር፣ ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጥላ ነውና[2]።

አስራኤላውያንን ከግብፅ አውጥቶ በምድረበዳ ይመራቸው ስለ ነበረው መንፈስ ነቢዩ ኢሳይያስ ሲጽፍ – በጭንቀታቸው ሁሉ ተጨንቆ በፍቅሩና በርሕራሄው የተቤዣቸውንና የተሸከማቸውን እግዚአብሔርን ስለ አስቆጡትና ቅዱስ መንፈሱንም ስለ አስመረሩት እርሱም ተመልሶ ጠላት እንደ ሆናቸው ገልጸአል (ኢሳ 63፡9-10)። ስለዚህም ጉዳይ አስመልክቶ ጳውሎስ «ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፣ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና» (1ቆሮ 10፡1-5) በማለት የክርስቶስ መንፈስ ይከ ተላቸው እንደነበር ይናገራል። የመንፈስ ቅዱስን መገኘትና ምሪት በሕይወቱ የተለማመደው ንጉሥ ዳዊትም ደግሞ «አቤቱ፣ ንጹህ ልብን ፍጠርልኝ፣ የቀና ውንም መንፈስ በውስጤ አድስ። ከፊትህ አትጣለኝ፣ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ።» (መዝ (51)፡10-11) በማለት ልቡን አፍስሶ ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሔር ሲጮህ እንመለከታለን።

2

አግዚአብሔር አምላክ በኃጢአት የወደቀውን የሰው ልጅ ለማዳን አቅዱን የጀመረው ከብሉይ ኪዳ ን ዘመን ጀምሮ ነው። አዳምና ሄዋን በኃጢአት ከወደቁ በኋላ ናግን በመጥራት ጠኃ አዳን ው። ከዚያም በመቀጠል አብርሃምን በመጥራት ከወገናቹ ለይቶ አወጣው። ስርሱም «አሕዛብ በእን ተ ይባረካሉ» በማለት ተስፋን ሰጠው። ከርሱም አብራክ የእስራኤልን መንግሥት መሠረተ። መሲን ም በመጥራት ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት ነፃ አወጣቸው። በርሱም እድ ሕግንና የአምልኮ ሥርዓትን ሰጣቸው። ከዚያም በመቀጠል በነቢያቱ እና ስለሚመጣው ባርኮት (መሢሑ) ተናግሮ ነበር። ሐዋር ያው ጳውሎስና የብሪውያን ጸሐፊም በብሉይ ኪዳን ዘመን የተሰጠው ሕግ የነገር ዋላ እንዳለው ጠትሰውታል። ይህም ማለት እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ትእዛዝትን የሰጠው የዘሙኑ ፍጻ

መጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔር ቃል ያደረገው ነገር ቢኖር በእግዚአብሔር መንፈስ መጻፉ ወይም የእግዚአብሔር አስትንፋስ [Inspired] መሆኑ ነው። ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስ ለቅዱሳን ነቢያት መገለጥን በመስጠት ወይንም በመንዳት ቃሉን እንዲጽፉ ማድረጉ ነው (2 ጴጥ 1፥21 ፤ 2ጢሞ 3፥16 -17)። ሌላዉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ደግሞ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር በመሆን ኃይልን እየሰጠ፥ የቃሉን ፍቺ በልባቸው እያበራ፥ እየመራ፥ እየግለጸና እየጸለየ ሰዎች የጽድቅን ፍሬ እያፈሩ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲኖሩ በማድረግ ከርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያጠናክሩና በሕይወታቸውም እርሱን እንዲለማመዱት ያደርጋል።

ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ማለት የእግዚአብሔር በኃይልና በሙላት መገለጥ ማለት እንደሆነ ማወቅ ያስፈልገናል። የእግዚአብሔር ቃልና የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚነግረን ከሆነ የአንደኛው ክፍለ ዘመን እማኞች የመንፈስ ቅዱስን መገኘት የእግዚአብሔር በሙላት መገኘት እንደሆነ የተረዱ ስለ ነበሩ ልባቸውን ከፍተው ለርሱ በመስጠታቸው እርሱም በሚገባ ተጠቅሞባቸው አልፈዋል። መንፈስ ቅዱስ ባለበት ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔር በኃይል መገለጥ እንዳለ በደንብ የተረዱና በሕይወታቸውም የተለማመዱት ስለ ነበሩ በተቀደሰው ኑሮአቸው የጠላትን ኀይል እያወኩና እያሸበሩ፥ በቃሉ ብርሃን ደግሞ ጨለማውን እየሰነጠቁ በመንፈስ ኃይልና ጉልበት የሰላምን ወንጌል ይዘው ሮጡ፤ ድምጻቸውም በምድር ሁሉ ላይ ቃላቸውም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ወጣ። የምሥራቹንም ቃል በኑሮአቸው ብቻ ሳይሆን በሞታቸውም ጭምር ሰበኩት።

በተጨማሪም በዚህ መጽሐፍ ጨለጥ ከቀኖና መጻሕፍት[3] አንዳንድ አባቦችን ጠቅሻለሁ። ይህ ማለት እነዚህ መጻሕፍት እንደ እግዚአብሔር ቃል

ፍጻሜ ደርሶ ልጁን በመሳክ እስኪያድነን ድረስ ነበር (ዘጸ 20 ፤ ቆላ 2፥17፤ እብ 9፡ 11፤ 10፥1፤ 1 ሳ 4፥1-7)። ስለሆነም ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጠቋሚ ነው ማለት ይቻላል።

[3] ቀኖና መጻሕፍት በመባል የሚታወቁት ሰማኒያ አሐዱ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ያሉት አሥራ ሰምንቱ መጻሕፍት ናቸው። ማለትም ሰማንያ አሐዱ የመጽሐፍ ቅዱስን በድሳ በደህቱን መጻሕፍትና አሥራ ስምንቱን ቀኖና መጻሕፍት ይዘአል። እነዚህ ቀኖና መጻሕፍት የተጻፉትም ከክደት መልስ እስከ ክርስቶስ ትውልድ ድረስ ባለው የአራት መቶ ዓመታት የዝምታ ጊዜ ጨለጥ ነው። ይህ ጊዜ የዝምታ ጊዜ የተባለበትም ምክንያት የእግዚአብሔር ድምጽ የጠፋበት ወቅት በመሆኑ ነው፤ ስለሆነም ምንም ዓይነት መንፈሳዊ መነዳት [Prophetic inspiration]

ተመስጦዋል ማለት አይደለም ምክንያቱም በእግዚአብሔር መንፈስ ቀጥታ ምሪት የተጻፉ ስለ አይደሉ የእግዚአብሔር አስትንፋስ የለባቸውምና ነው። እንደዉም እነዚህ መጻሕፍት የተጻፉት በሁለቱ ኪዳናት መካከል ባለው ወይም በእንግሊዝኛው [Intertestamental times] በመባል በሚታወቀው ጊዜ ዉስጥ ነው። ይህም ማለት አይሁዳውያኑ ከባቢሎን ስደት ከተመለሱ በኋላ ባለው የአራት መቶ የዝምታ ዓመታት ውስጥ የተጻፉ ናቸዉ። ቢሆንም ቅሉ እነርሱ በተጻፉበት ጊዜ የነበረዉን የማኅበረ ምዕመናን ሥነመለኮት አስተሳሰብ፥ መንፈሳዊ ደረጃ፥ ባሕላዊና ታሪካዊ ገጽታን ስለሚያንጸባርቅ እንዳንድ አባቦችን ለመደገፍ ስል እንደ መረጃ በመጠቀም ጠቅሼአቸዋለሁ።

በመጨረሻም የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ውስጥ በምንመለከትበት ጊዜ በብሉይ ኪዳን ዘመን ልክ እንደ አዲስ ኪዳኑ ዘመን መንፈስ ቅዱስ በሥጋ ሰዓሹ ሁሉ ላይ አልፈሰሰም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ሰዎችን እየመረጠ የመቤዠቱን ሥራ በታሪክና በሁኔታዎች ውስጥ ያከናውን ነበር። እሰራኤልን ታሪክ ብንመለከት የእግዚአብሔር መንፈስ ሁል ጊዜና ካለማቋረጥ በግልጽ ሲሠራ አይታይም።[4] የእግዚአብሔር መንፈስ በግልጽ ሲሠራ የሚታየው ውሸኝ በሆኑ አምስት የሃይማኖትና የፖለቲካ ወቅቶች ነበር። እነዚህም እንደሚከተሉት ናቸው — 1ኛ የእሰራኤል መንግሥት በምድረበዳ ሲቋቋም (በሙሴ አማካኝነት)፤ 2ኛ በመሳፍንት ዘመን (የተስፋይቱን ምድር ከወረሱ በኋላ)፤ 3ኛ የንጉሣዊ አገዛዝ ሲመሠረት (ሳኦል የመጀመሪያው ንጉሥ ሆኖ ከተቀባበት ጊዜ አንስቶ)፤ 4ኛ በነቢያት ኤልያስና ኤልሳዕ ዘመን፤ 5ኛ በሰደት ዘመንና ከሰደት በኋላ ባለው የመታደስ ዘመን (የቤተመቅደሱ እድሳት እስከ አለቀበት ጊዜ ማለትም ነቢያቱ ሐጌ፥ ዘካርያስ እና ሚልክያስ የመጨረሻ ነቢያት ሆነው እስከገለገሉበት ጊዜ ድረስ ማለት ነው)።

ባለመኖሩ ሰዎች በራሳቸው አነሳሽነት እነዚህን መጻሕፍት ሲጽፉ ችለዋል። መጻሕፍቶቹም Pseude pigraphal እና Apocriphal መጻሕፍት በመባል ይታወቃሉ።

[4] በርግጥም የእግዚአብሔር መንፈስ ሁልጊዜ በሥራ ላይ ነዉ። እዚህ ላይ ለመግለጽ የሞከርኩት የእግዚአብሔር መንፈስ በድንቅና በታምራት በግልጽ ሲሠራ የታየባቸዉን ጊዜያቶች ነዉ [Prophetic empowerment with wonders and miracles] ይህም በፍጥረት ላይ ከሰው ተአምራት ሌላ ማለቴ ነዉ።

ይሄ ምንን ነው የሚያሳየን ብንል በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር መንፈስ በመረጣቸው ሰዎች ውስጥ እና በጉባኤው መካከል በማደር ሲሠራ ቆየ፣ በአዲስ ኪዳን ዘመን ግን በአማኞች ውስጥና በጉባኤ መካከል በማደር ከስማቂረጥ ይሠራል (በአማኞች የግል ሕይወትና በሕብረት ውስጥ) ። ይህም ሊሆን የቻለው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ በመሞት የአብርሃምን በረከት እርሱም የመንፈስን ተሰፋ በእምነት እንድንቀበል በማድረጉ ነው (ዘፍ 17፥1-8፤ ገላ 3፥14)።

እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን መንፈሴን በሥጋ ለባሹ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ ብሎ በነቢያቱ በተናገረዉ መሠረት (ኢዩ 2፥28-32) ኢየሱስ ወደ አብ ካረገ በኋላ በበዓለ ኀምሳ ቀን መንፈሱን አትረፍርፎ አፈሰሰዉ (ሐዋር 2፥1-4)። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ስጦታዉ አሸበረቀች። የመንፈስ ቅዱስም በሙላት መውረድ የመጨረሻውን ዘመን ጎህ ቀደደ። ይህ የመጨረሻዉ ዘመን ተብሎ የሚታወቀዉም ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ከፈሰሰበት ጊዜ እንስቶ እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድረስ ያለዉ ጊዜ መሆኑ በዚሁ በትንቢተ ኢዩኤል ላይ እንመለከታለን። ስለዚህም ጌታ መንፈስ ቅዱስ ትናንት እንደሠራዉ ሁሉ ዛሬም ይሠራል፤ ቤተክርስቲያንንም ለጌታ ዳግም ምጽአት እያዘጋጀች በመሆኑ በዚያ ደስ ይለናል።

በመጨረሻም መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገኘት ነዉ ብለን ከመንን ዘንዳ የርሱን መገኘት ከመለኮታዊ ሥራው ነጥለን ማየት አይገባንም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከመፍጠር ሥራዉ አረፈ እንጂ ሰዉን ከማዳን ተገ ባሩ አላረፈምና ነው። ከፍጥረት በፊትም፥ በመፍጠሩ ተግባር ላይም (በዉኃ ላይ ከመስፈፍ እንስቶ እስከ ፍጥረት ድረስ ማለት ነው፥ ዘፍጥ 1፥2) ከዚያም በኋላ በምሪትና በመቤዠት ሥራ ላይ የነበረዉ የሕያው እግዚአብሔር መንፈስ አሁንም እንደቀድሞው ይሠራል፤ ከክርስቶስ አካልም (ከቤተክርስቲያን) ጋር በመሆን ጌታ ኢየሱስ ና ይላል። እኛም ይህንን ዳግም የመምጣቱን የምሥራች ድምጽ በቃሉ በኩል ከመንፈስ ቅዱስ የሰማን — «አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና» እንላለን (ራእይ 22፥17፤ 20)።

እኔ ሁሉን በሚችል በማይገና ምድርን የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ አን ድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ። እርሱ ብቻ የአብ ልጅ በሚሆን ዓለም ሳይፈጠር ከአብ በተወለደ፤ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ በሚሆን በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ፤ በሕ ልውናው ከአብ ጋር በተካከለ ሁሉ በእርሱ በሆነ ለሰ እኛ ለሰዎች ስለ ደህንነ ታችን ከሰማይ በወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም ሥጋ ነስቶ ሰው በሆነ፤ በጲላጦስ ዘመን ስለኛ በተሰቀለ፤ መከራ በተቀበለ፤ በተቀበ ረም በቅዱሳት መጻሕፍትም እንደተጻፈው በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሳ፤ ወደ ሰማይ በወጣ በአባቱ ቀኝ በተቀመጠ፤ በሕያዋንና በሙታን ሊፈር ድ ዳግመኛ በክብር ሊመጣው ለመንግሥቱ ፍጻሜ ስለሌው በእንድ ጌታ በኢ የሱስ ክርስቶስ አምናለሁ። ከአብና ከወልድ ጋር በሚሰገድለት ከአብና ከወል ድ በሚመጸዉ በነቢያት በተነገረ፤ የሕይወት ጌታና ሰጪ በሆነ በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ። የሙታንንም ትንሣኤና ገና የሚመጣውንም ዓለም ሕይወት እጠባበቃለሁ።

— የኒቅያ የሃይማኖት መግለጫ

1

ሥላሴ

በዚህ ርእስ ስር ስለ እግዚአብሔር ሦስትነትና አንድነት እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስን መለኮታዊ ባሕርይ እንመለከታለን። በቀጥታ ወደ መንፈስ ቅዱስ ትምህርት ከመግባታችን በፊት ስለ እግዚአብሔር አንድነት መመልከቱ መሠረታዊ የሆነ ትምህርት ስለሚሰጠን ከዚህ በመቀጠል እንነጋገራለን። እንደሚታወቀው ሁሉ ከሥነመለኮት [Theology]

ትምህርት ውስጥ ለመረዳት የሚከብደው የሥላሴ ዶክትሪን [Theology proper] ነው። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ማንነት፣ ጥልቀቱና ስፋቱ በሰው አዕምሮ ሊመረመርና ሊደረስበት ስለማይቻል ነው። በርግጥም ማወቅ የምንችለው እርሱ እንድናውቀው የፈቀደልንን ያህል ብቻ በመሆኑ ይህንኑ እውነት በእምነት መቀበል ይኖርብናል (አሁን በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደሚያይ ስለሆንን፣ 1ቆሮ 13፣12)። ነገር ግን ሊላውን ማወቅ የማንችለውን ምስጢር ሁሉ ለእርሱ እንተ ወዋለን። ምክንያቱም ጌታችንን ፊት ለፊት ስናየው አሁን ምስጢር የሆነብን ነገር ሁሉ ግልጥልጥ ብሎ ይታወቀናል (ማለትም የሚያውቀንን ያህል እናውቀዋ ለን፣ 1ቆሮ13፣12፤ ዘዳግም 29፣29)።

ወደ ዋናው ነጥባችን ስንመጣ «ሥላሴ» የሚለውን ቃል በመጀመሪያ የተጠቀመበት የአራተኛው ክፍለ ዘመን የሃይማኖት መሪ የነበረው ጠርጡሊን [ተርቱሊያን] የተባለው ሰው እንደሆነ እናያለን። በዚያን ወቅት አሪዮስ የተባለ መናፍቅ በመነሳት «አብ ወልድን ከመለደው እንግዲህ ወልድ በአብ ተፈጥሮ አል ማለት ነው» በማለት የስሁተት ትምህርቱን ማስፋፋት በመጀመሩ የኒቅያ የሃይማኖት ስብሰባ በንጉሥ ቆንስጣንጢን [ቆንስታንቲኖስ] በ325 ዓ.ም. ላይ በቢ ታንያ በምትሆነው በኒቅያ፣ ከዚያም በሲሪሚየም በ357 ዓ.ም. ስብሰባ ተጠራ። በስብሰባውም ላይ አሪዮስና ተከታዮቹ «ኢየሱስ ፍጡር ነው» በማለታቸው ተወገዙ[5]። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንግዲህ «ሥላሴ» የሚለው ቃል የእግዚአብ ሔርን ሦስትነትና አንድነት ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ሆኖ ቀረ።[6]

እንግዲህ ስለ ሥላሴ ስናጠና ማወቅ ያለብን ነገር ቢኖር ምንም እንኳን እግዚአብሔር ሦስት አካል ቢኖረውም በአምላክነቱ አንድ መሆኑን ነው (ዘዳ 6፣4)። ይህም ማለት ሕልውናውን ሳንከፋፍልና አካላቱን ሳንደባልቅ ነው። አምላካችን አንድነቱ በሦስትነቱ፣ ሦስትነቱ ደግሞ በአንድነቱ ተጠቃሎ የሚኖር አምላክ ነው፤ ወይንም በሌላ አነጋገር በመለኮታዊ ባሕርይው አንድ ነው።

---

[5] ማርክ ኢ. ኖል፣ *ተርኒንግ ፖይንትስ* (ግራንድ ራፒድስ፣ ዌስር ቡክስ፣ 1997) 48-55።

[6] ስለ ሥላሴና የሐዋርያቶች የእምነት መግለጫ በስፋትና በጥልቀት ለማንበብ ከፈለጉ በዶ/ር አልስተር መክገራዝ የተጻፈውን *ሉይ ቢሊቭ፤ ሉክሀፐሉሪንግ ዚ ሉፖስትልስ ክሪድ* (ዳውነርስ ግሮቭ፣ ኢን ተርቫርሲቲ ፕረስ፣ 1997)። ዶ/ር መክገራዝ መግለጫውን በሚገባ በማብራራት የእግዚአብሔርን አን ድነትና ሦስትነት ለእንባቢው በሚዋም መልኩ አዘጋጅቶ አቅርቦልናል።

1. አንድነቱ

ሁሉንም በመቻል፣ ሁሉንም በማወቅ፣ በሁሉም ቦታ በመገኘት፣ በዘላለ ማዊነት፣ በሥልጣን፣ በአገዛዝ፣ በኃይል፣ በሕልውናና በክብር ነው።

2. ልዩነቱ ደግሞ

በአካል፣ በግብርና በሰም ነው (ለምሳሌ አብ ዓለም ሳይፈጠር ያቀደውን እቅድ ወልድ ፈጹም ታዛዥ በመሆን የሰውን ሥጋ ለብሶ የባሪያን መልክ በመያዝ በሞቱና ትንሣኤው አዳነን፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ይሄ ንን ክርስቶስ የሠራውን ሥራ አውን የሚያደርግና የሚያስፈጽም አካል ነው)።


ማጠቃለያ

- አብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ በአካል ይለያል
- ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ በአካል ይለያል
- መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ በአካል ይለያል
- ነገር ግን በመለኮት ሦስቱም አንድ ናቸው
- ስለዚህም እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብለን እንጠራቸዋለን።
- ሆኖም አምላክ አንድ እንጂ ሦስት አይደለም።[7]

---

[7] የአትናቴዎስ የሃይማኖት መግለጫ ስለ እግዚአብሔር አካላቱና ሕልውናው እንዲሁም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነትና ሰውነት (ተፈጥሮው) በሚገባ አብራርቶታል። ስለዚህም መግለጫው የክርስትና ችን መሠረት በመሆኑ አንባቢው ፊልጳ አንዲያኑስና ቢቻልስ ጠንቅቆ ቢያጠናው መልካም ነው በማ ለት አበረታታለሁ። መግለጫውም ቢጀምር «ለመዳን የሚፈልግ ሰው ሁሉ ከሁሉም ነገር አስቀድሞ የሁሉ የሆንች የቤተክርስቲያንን ሃይማኖት እውነተኛ አድርጎ ሊቀበለው ያስፈልገዋል» ካለ በኋላ «የሁሉም የሆነ የክርስቲያኖች ሃይማኖት ይህ ነው፤ በጽኑ እምነት ይህንን ሃይማኖት ያልያዘ ሰው ሊድን አይችልም።» ብሎ በመደምደም መግለጫውን የማወቅ አስፈላጊነት ታላቅ ምስጢር እንደሆ ነ አስቀመታል። እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባን ነገር ቢኖር የሃይማኖት አባቶች ይህንን መግለጫ ቢያወ ጡ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተውና በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተመርኩዘው በመሆኑ የመዳንን መንገድ ግልጥ አድርጎ ያሳያል። በአብዛኛው ጊዜ እኛ የወንጌላውያን አብያተክ ርስቲያናት ጉባኤያችንን ስለ ሥላሴና ስለ ኢየሱስ አምላክነትና ሰውነት ደስትሪን በቂ ጊዜ መሰደን ባለማስተማራችን ወይም ደግሞ በቂ ትኩረት ባለመስጠታችን አባላቶቻችን የስህተት ትምህርትን ለመ ቋቋም ወይም ፊት ለፊት ለመነጋገር ሲቸገሩ እንመለከታለን።

ይህም ከዚህ በታች የምናየው ሦስት ማዕዘን [ትራያንግል] በዶ/ር ኖር መን ጋይስለር የቀረበ የሥላሴ ስእላዊ መግለጫ ነው።[8] ከዚህ በፊት ብዙ ዎች በተለያየ ዓይነት መንገድ ስለ ሥላሴ ለመግለጥ ሞክረዋል። እንደሚታወ ቀው ሁሉ የእግዚአብሔርን ማንነት በስእል መልክ ሙሉ ለሙሉ ማሳየት መቼም የማይቻል ነገር ነው። ነገር ግን እስከ አሁን ካየኋቸው ስእላዊ መግለ ጫዎች ውስጥ ይሄኛው ሥላሴን በመጠኑም ቢሆን ይገልጸል። እንግዲህ በስእሉ ላይ እንደምናየው አንድ የሦስት ማእዘን ቅርጽ (ትራያንግል) ሦስት ጫፎች ሲኖሩት፥ ሦስቱ ጫፎች ደግሞ ሦስቱን አካላት ይወክላሉ። የትራያንግሉ የው ስጡ ክፍል ደግሞ የአካላቱን የመለኮታዊ ባሕርይ አንድነት ይዞአል። ይህም አንድ እግዚአብሔር እንዳለ ያሳየናል።



ሥላሴ (ስእላዊ መግለጫ ቁ. 1)

[8] ኖርመን ጋይስለር ኢንድ አብዱል ሳሲብ፥ *አንሸሪንግ ኢስላም* (ግራንድ ራፒድስ፥ ቤከር ቡክ ሃው ስ፤ 1993) 265-67።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ተገልጦ የምናየው የእግዚአብሔር ሦስ ትነትና አንድነት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ማለትም በሁለተኛው አካል በኩል ያገኘነው ደህንነት የሥላሴ ሥራ መሆኑንም ጭምር ነው (ሮሜ 5፡ 18፤ 2ቆሮ3፥1-6፤ ገላ4፥4-6፤ ኤፌ1፥3-14)። እንዲሁም በ 2ቆሮ13፥14፤ 1ቆሮ12 ፥4-6፤ ኤፌ4፥4-6፤ ማቴ28፥18 ያሉት ጥቅሶች ስለ እግዚአብሔር ሦስትነትና አን ድነት ይናገራሉ።

እንደሚታወቀው ሁሉ የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የሚተበል የክርስትና እምነት ብቻ ነው። ይህም ዶክትሪን (ትምህርት) የእምነታችን ቁልፍ በመሆኑ የአምላካችንን ማንነት፥ ምን እንደሚመስል፥ እንዴት እንደሚ ሠራ እና እርሱንም እንዴት እድርገን መቅረብ እንዳለብን ያስተምረናል። በተለ ይ ደግሞ የጌታችንን የኢየሱስንና የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት እንድንረዳ ስለ ሚያደርገን ለደህንነታችን መሠረት ነው ማለት ይቻላል።

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናነብ የተለያዩ የሚመስሉ ነገር ግን መሠረታዊ አሳባቸው አንድ የሆነ ሦስት እውነታዎችን እናገኛለን፤ እነዚህም —

1. *እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ* (ዘዳግም 6፥1-6፤ 3፥13-15፤ ዘጸ 20፥2-3፤ 15፥ 11፤ ዘካር 14፥9፤ 1ቆሮ 8፥4-6፤ 1ጢሞ 2፥5-6)።
2. *ሦስት አካላት እንዳሉት* (2ቆሮ 13፥14፤ 1ቆሮ 12፥4-6፤ ኤፌ 4፥4-6፤ ማቴ 28፥18)።
3. *ሦስትነቱ በአንድነቱ የተጠቀለለ መሆኑን ነው፤ ይህም ማለትም ሦስት አካላ ት ነገር ግን አንድ አምላክ ብቻ መኖሩን ነው (ዘዳ 6፥4፤35፥39፤ ዮሐ 17፥3 ዘዳ 8፥10፤ 9፥14፤ ኢሳ 44፥6፣8፤ 45፥5-6፤ 46፥9)።*[9]

[9] ስለ ሥላሴ ዐየልቀት ስማቅ የፈለገ ሰው የዶ/ር ኢሪክሰንን መጽሐፍ ቢያንብ ጠቃሚ የሆነ እውቀ ትን ያገኛል ብዬ አስባለሁ ይህም እንደሚከተለው ነው፤ ሚላርድ ጄ ኢሪክሰን፥ *ክሰቲያን ቲኦሎጂ* (ግራንድ ራፒደስ ምሺጋን፥ ቤከር ቡክ ሃውስ፤ 1994) 321-341።

ሀ/ አብ አምላክ ነው

አብ አምላክ ነው (1ቆሮ 8፥4,6፤ 1ጢሞ 2፤5-6፤ ማቴ 6፥4,6,8, 18,26,30፤ 11፥25፤ 19፥23-26፤ 27፥46፤ ማር 12፥17,24-27፤ 14፥36፤ ሉቃ 11፥2፤ 22፥42፤ 23፥34,46፤ ዮሐ 17፥11)፤ ኢየሱስ አብ ወይም አባት እያለ ይጠራዋል (ማቴ 11፥25፤ ሉቃ 11፥2፤ 22፥42፤ 23፥34፤46፤ ዮሐ 11፥41)፤ ኢየሱስም ሲናገር አብ ቅዱስ እንደሆነ (ዮሐ 17፥11)፥ ጻድቅ እንደሆነ (ዮሐ 17፥25)፥ ፍቅር እንደሆነ (ዮሐ 16፥27)፥ ሕያው እንደሆነ (ዮሐ 6፥57)፥ ኃያል እንደሆነ (ማር 14፥36)፥ ይቅር ባይ እን ደሆነ (ማቴ 6፥14፤ ሉቃ 15፥21-23)፥ መሐሪ እንደሆነና (ሉቃ 6፥36) ሁሉን እንደሚያውቅ (ማቴ 6፥4፣ 6፣ 8፣ 18) ገልጸታል። በአጠቃ ላይ ስለ አብ አማላክነት በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ብዙ ቦታዎች ተጠቅሶ እናነኛለን። አንዳንድ ቦታዎች ላይም በቀጥታ እግዚአብሔር በማለት ይጠራዋል። ቡተለይ ደግሞ የአብን አምላክነት ለመረዳት ብዙም ችግር ሰለሌለብን ይህንን ክፍል በማለፍ ስለ ኢየሱስና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሰፋ ባለ መልኩ እንነጋገራለን።

ለ / ወልድ አምላክ ነው

ሐዋርያው ዮሐንስ ወንጌሉን ሲጀምር «በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በርሱ ሆነ፥ ከሆ ነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።» (ዮሐንስ 1፥1-3) በማለት በኢየሱስ አምላክነት የምሥራቹን ያበሰራል። በሌላም ቦታ በፊልጵስ ዩስ መልእክት ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ «በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ[10] ከእግዚአብሔርጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆ ጠረውም ... ነገር ግን በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ» (ፊል 2

[10] የገሪኩ ቃል በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር የሚለውን ምርፊ ይለዋል ትርጉሙም እውነተኛ መልክ ወይንም ቅርጽ ማለት ነው። ከዚህ የምንረዳው ነገር ሲኖር ምንድነው ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሙን የእግዚአብሔር መልክ ይሆ ሲኖር ሳለ ራሱን ለማዋረድ ወይንም ባዶ ለማድረግ መምረጡን ነው። ስለዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ (ወልድ) እግዚአብሔር ነው ማለት ነው።

፥6-7) በማለት አምላክነቱን ይነግረናል። ራሱንም ባዶ ያደረገው በአ ምላክነቱ ላይ ሥጋን በመደረቡ መሆኑንም አስቀምጦታል (አምላክነቱን ትቶ አልመጣም ነገርግን ሥጋ ሲለብስ ራሱን ባዶ አደረገ (ተዋረደ)። ወይም በሌላ አነጋገር መለኮታዊ ባሕርይዉን በመቀነስ ሳይሆን ነገር ግን ሰብእናን በመደረብ ነው ራሱን ያዋረደው)።

በዕብራዉያን ምዕራፍ አንድ ላይ እግዚአብሔር ከጥንት ጀም ሮ በተለያየ መንገድና ሁኔታዎች ለአባቶቻችን ለነቢያት ከተናገረ በኋላ አሁን ግን «የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርይው ምሳሌ» በሆነው በልጁ በዚህ በመጨረሻው ዘመን ለእኛ ተናገረን ይላል (1፥1-3)። በመቀጠል ም ከመላእክት ይልቅ እጅግ የከበረ በመሆኑ እግዚአብሔር አባቱ — «አምላክ ሆይ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል»፥ «ጌታ ሆይ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማዮችም የእጆችህ ሥራ ናቸው» (1፥8፣10) አያለ እንደሚጠራው በመንገር የኢየሱስን አምላክነት ያሳየና ል። ይህ «ጌታ ሆይ» የሚለው ቃል የዕብራይውን *ያሕዌ/አዶናይና* የእንግሊዝኛውን LORD ለሚባሉት ቃላት ትርጓሜ ነው። በመሠረቱ *ያሕዌ/አዶናይ* የሚለዉ የእግዚአብሔር መጠሪያ ስም እርሱ ከእስራኤ ል ቤት ጋር የገባውን ቃልኪዳን የሚያስታውስ ስም ነው። ስለዚህም ይህንን የእግዚአብሔር የቃልኪዳን ስም አብ ራሱ ለልጁ ለኢየሱስ መጠቀሙ አምላክነቱን ግልጽ አድርጎ ያሳየናል።

ኢየሱስም ራሱ «እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ 10፥30) ሲል በዮሐንስ 17፥5 ላይ ደግሞ «ዓለም ሳይፈጠር ባንተ ዘንድ በነበረኝ ክብ ር እንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ» በማለት ለአባቱ በጸለየው ጸሎት ላይ አምላክነቱን አሳይቶናል። በሌላም ቦታ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መለእክት «የእኔ» ብሎ ይጠራቸዋል (ማቴ 13፥41)፣ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ምርጦች የራሱ እንደሆኑ ይናገራል (ማቴ 12፥28፤ 19፥14፤24፤ 21፥31፣ 43፤ ማር 13፥20)፣ ኃጢአትን እንደሚያስተሰርይ ተናግሮአ ል (ይህም የሚቻለዉ በእግዚአብሔር ብቻ ነው (ማር 2፥8-10))፣ ዓለማ ት በርሱ ተፈጥረዋል (ዮሐ 1፥3፤ ቆላ 1፥16፤ ዕብ 1፥2) እና የመፍረ ድ ሥልጣን እንዳለውም ተናግሮአል (ማቴ 25፥31)።

ንጉሰ ያዝያን በሞተበት ዓመት ነቢዩ ኢሳይያስ እግዚአብሔር
ን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ፥ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን
ሞልቶት እንዳየው ጽፎአል (ኢሳ 6፥1)። ይህንን መገለጥ አስመልክቶ
ሐዋርያው ዮሐንስ ሲጽፍ «ክብሩን ስለ አየ ኢሳይያስ ይህን አለ፥ ስለ
እርሱም (*ክርስቶስ ኢየሱስ*) ተናገረ» በማለት ነቢዩ ኢሳይያስ ያየው
የክርስቶስ ኢየሱስን ክብር እንደሆነ ያመለክተናል። ስለዚህም ይህ
ክፍል እንደገና ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደሆነ ይነግረናል ማለት
ነው (ዮሐ 12፥37-41)።

በመጨረሻም ኢየሱስ የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው (ቆላ 1፥
15)፤ የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርይው ምሳሌ ነው (ዕብ 1፥3)፤ የእግዚ
አብሔር ሙላት በርሱ ይኖራል (ቆላስ 1፥19፤ 2፥9)፤ የእግዚአብሔር
ክብር በርሱ ተገልጸአል (ዮሐ 1፥14፤ 1ቆሮ 4፥6፤ ዕብ 1፥3)፤ የእግዚአ
ብሔር ምሳሌ ነው (2ቆሮ 4፥4)፤ እርሱን ማየት አብን ማየት ነው (ዮሐ
12፥45፤ 14፥8-11)፤ እርሱን ማክበር አብን ማክበር ነው (ዮሐ 5፥23)፤
እርሱን መጥላት አብን መጥላት ነው (ዮሐ 15፥23)።

ሐ / መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው

መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔርም ስለሆነ
ዓለማት በርሱ ተፈጥረዋል (ዘፍጥረት 1፥2፤ መዝሙር (104)፥30)። በሐ
ዋርያት ሥራ ላይ እርሱን መዋሸት እግዚአብሔርን መዋሸት እንደ ሆነ
ተጠቅሶአል (5፥3-4)። አምላክም ስለሆነ ዓለምን ስለ ኃጢአት ይወቅሳ
ል (ዮሐ 16፥8-11)፤ አዲስ ሕይወትን ይሰጣል (ዮሐ 3፥8)፤ ሁሉን ይመ
ረምራል (1ቆሮ 2፥10)፤ የእግዚአብሔርን አሳብ ያውቃል (1ቆሮ 2፥11)፤
የወንጌልን ይዘት ለአማኞች ያስተምራል (1ቆሮ 2፥13)፤ በአማኞች ውስ
ጥና በጉባኤ መካከል ያድራል (1ቆሮ 3፥16፤ ሮሜ 8፥11፤ 2ጢሞ1፥14)፤
ሁሉንም ነገር እንደፈቃዱ ይሠራል (1ቆሮ 12፥11)፤ ልባችን ውስጥ ሆኖ
ስለ እኛ ይቃትታል (ሮሜ 8፥26፤ ገላ 4፥6)፤ በእግዚአብሔር መንገድ
እንድንሄድ ይመራናል (ገላ 5፥18፤ ሮሜ 8፥14)፤ ኃይልን ይሰጠናል
(ኤፌ 3፥16)፤ እንዲሁም በኃጢአታችን ያዝናል (ኤፌ 4፥30)።

የእግዚአብሔር መገለጥ የመጣው በርሱ በኩል ነው[11] (1ቆሮ
2፥10፤ ኤፌ 3፥5)፤ የተሰሎንቄ አማኞች መለወጥ እውን የሆነው በሚ
ቀድሰው በመንፈስ ቅዱስ ነው (2ተሰሎ 2፥13)፤ ትንቢትና በልሳን መና
ገርም የመጣው በርሱ በኩል ነው (1ቆሮ 12፥3፤ 14፥2፣16)፤ የሮሜ አማ
ኞች የኃጢአትን ሥራ በርሱ እንዲገድሉ ተነግሮአቸዋል (ሮሜ 8፥13)፤
የኤፌሶን አማኞች ደግሞ በርሱ ኃይል እንዲጠነክሩ የጳውሎስ ጸሎቱና
ምኞቱ ነው (ኤፌ 3፥16)፤ የፊልጵስዩስ አማኞች እግዚአብሔርን የሚያ
መልኩት በመንፈስ አማካኝነት ነጪ (ፊልጵ 3፥3)፤ የቆላስያስ ሰዎች
ፍቅራቸው ከመንፈስ ቅዱስ የተነሳ ነው (ቆላ 1፥8)፤ የምንኖረውና የምን
መላለሰው በመንፈስ ነው (ገላ 5፥16፤ 25)፤ በመጨረሻም የዳንነውም
በመንፈስ በሚሆን አዲስ መታደስና መታጠብ ነው (ቲቶ 3፥5)።

11

በመሠረቱ እግዚአብሔርን የገለጠው አንድያ ልጁ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዮሐ 1፥14፤ 18)
። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ኢየሱስን በመገለጥ አብን ያሳየናል። ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስ የእግዚ

2

መንፈስ ቅዱስ በፔንታቱክ[12] ውስጥ

መጽሐፍ ቅዱስ ሲጀምር «በመጀ መሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበር፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በዉኃ ላይ ሰፍፎ ነበር።» በማለት የሥላሴ ሦስተኛዉ አካል የሆነዉ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ተግባር ላይ ዋናዉን ቦታ ይዞ እንደነበር ያሳየናል።

ከላይ እንደጠቀስኩት መንፈስ የሚለው ቃል በዕብራይስጡ ሩአሽ ሲባል ይህም *የእግዚአብሔር መንፈስ፡ የሰዉ መንፈስ፡ መንፈስ፡ እስትንፋስ* እና *ነፋስ* የሚለዉን ትርጉም ይሰጠናል።[13] በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥም በተለያዩ ቦታዎች ላይ ሩአሽ የሚለው ቃል የተለያየ ትርጉም ይዞ እናገኘዋለን። እነዚህም –

1. *የእግዚአብሔር መንፈስ* (ዘኁ 11፡17፤ 25-29፤ 1ሳሙ 10፡6-10፤ 19፡20፡23፤1 6፡15-16፣18-10፤ 1ነገሥ 22፡21-24፤ 2ዜና 18፡20-22)።
2. *መንፈስ* (1ነገ 10፡5፤ 2ዜና 9፡4፤ 1ነገሥ 21፡5፤ ዘፍ 45፡27፤ ሕዝቅ 11፡19፤ 18፡31፡36፤ ኢሳ 59፡21፤ 65፡14፤ መክብብ 7፡8፤ ምሳሌ 16፡19)።
3. *እስትንፋስ* (ኢዮብ 4፡9፤9፡18፤15፡30፤16፡13፤ ሰቆቃ 4፡20፤ ኢዩኤ 10፡14፤ ዕብ 2፡19፤ ኢሳ 30፡28፤ 34፡16፤ 59፡19፤ ዘፍ 6፡17፤ 7፡15፤ ሕዝቅ 37፡5)።
4. *ነፋስ* (ዘፍ 8፡1፤ ዘጸ 15፡10፤ ዘኁ 11፡31፤ 1ነገሥ 18፡45፤ ኢዩ 10፡13፤ ሆሴ 13፡15፤ ኢሳ 40፡7) ናቸው።

የእግዚአብሔር መንፈስ በመፍጠር ሥራ ላይ እንደነበረ የሚያሳዩን ብዙ መረጃዎች አሉ። ለምሳሌ በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ይንቀሳቀስ እንደነበር ይናገራል። «ሰፍፎ» ነበር የሚለውን ቃል በዕብራይስጡ «መራሼፈት» ይለዋል። ይህም ግሥ የፒየል ቦዝ አንቀጽ /ፒየል ፓርቲሲፕል/ በመባል ሲታወቅ የሚያሳየውም መንፈስ ቅዱስ የነበረውን የማያቋርጥ እንቅስቃሴን ነው። በዘዳግም 32፡11 ላይ እግዚአብሔር ስለእስራኤል ልጆች ያለውን ፍቅርና ጥበቃ ሲናገር «መራሼፈት» የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ይጠቀማል — «ንስር ጫጩቶቹን እንደሚያወጣ በእነርሱ ላይ እንደሚሰፈናፍ ክንፎቹን ዘርግቶ ወሰዳቸው» በማለት ይህ ቃል እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ካለ ማቋረጥ አብሮአቸው እየሄደ እንደጠበቃቸው ያሳየናል።

ስለዚህም ከላይ እንዳየነው መንፈስ ምድር ባድማ በነበረች ጊዜ በውኃ ላይ ሰፍፎ እየተንቀሳቀሰ የዝግጅት ሥራውን ያጠናክር እንደነበር እንረዳለን። ይህንንም አስመልክቶ ሊሳይያስ በምዕራፍ አርባ ላይ «የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ፣ ወይስ አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማን ነው? ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ?

እብሔርን ጥልቅ ነገር እየመረመረ ይገለጥልናል። ይህንንም ልናሸ የቻልነው በጌታችን ኢየሱስ ምትና ትንሣኤ ነው።

12

ፔንታቱክ የሚባሉት አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ናቸው ሲሆኑ እነርሱም — ኦሪት ዘፍጥረት፣ ኦሪት ዘጸአት፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኁልቁና ኦሪት ዘዳግም ይባላሉ።

13

ቢ.ዲቢ፣ ሉ ሂበሩ ሊንድ ሊንሊሽ ለክሲከን ኦቭ ዚ ኦልድ ቴስታመንት (አክሰፎርድ፡ክላረንደን ኦሰቃሚ ድርጅት) 924።

ወይስ ማን መከረው?» በማለት ሉዓላዊነቱንና ሁሉንቻይነቱን ይገልጻል። በዘፍ ጥረት 1፥26-27 ላይ «ሰዉን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር» በማለት የሦስቱንም አካላት ተሳትፎ ሲያሳየን መንፈስ ቅዱስ (ሶስተኛው አካል በመሆኑ) ሰውን በመፍጠር ሥራ ላይየነበረውንም ተሳትፎ በዚያው እንመለከታለን።

እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ብቻ ሳይሆን የፈጠረው የራሱንም እስት ንፋስ [ራሐሽ] ባፍንጫው ውስጥ እፍ ብሎበታል (ዘፍ2፥7)። በኢዮብ መጽሐፍ ላይም «የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ ሁሉንም የሚችል አምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ» (ኢዮብ 33፥4) ሲል በመዝሙረ ዳዊት (104)፥30 ላይ ደግሞ «መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም» በማለት የመንፈስን ፈጣሪነት ይናገራል።

አብርሃም የእግዚአብሔር ነቢይ ስለሆነ የእግዚአብሔርን መንፈስ ድም ጽ መስማት የተለማመደ ሰው ነበር። እግዚአብሔር በኃጢአት የወደቀውን የሰውን ልጅ የማዳን እቅዱን ሲያወጣ አብርሃምን በመጥራት ከከለዳውያን ዑር ወደ ደቡብ ከነዓን አመጣው። አብርሃም በዚያን ጊዜ ከእባቱና ከአገሩ ሰዎች ጋር የጨረቃን አምላክ ያመልክ ነበር፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ድምጽ በሰማ ጊዜ በእምነት ታዝዞ ወጣ።[14] እግዚአብሔርም አብርሃምን በራዕይና በድምጽ ያነጋገረው ነበር። በዚህም መሠረት እግዚአብሔር ስርዉ በማለጥ የልጅ ልጆቹ ወደ ግብፅ ምድር እንደሚወርዱና ባሪያዎች እንደሚሆኑ ተናገረው፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ አሕዛብ በርሱ እንደሚባረኩ የምሥራቹን ቃል አበሰረው (ዘፍ 12-15)።

ይህም የአሕዛብ ባርኮት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ተፈጸመ። ስለዚህ ም የተሰፋ ቃል ቅድስት ማርያም በመንፈስ ሆና «ለአባቶቻችን እንደተናገረ ለአ ብርሃምና ለዘሩ ለዘላለም ምሕረቱ ትዝ እያለው እስራኤልን ብላቴናውን ረድቶ አል» በማለት ተናገረች። ጳውሎስ ደግሞ በገላትያ መልእክት ላይ ስለዚህ ባርኮት «የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል የአብርሃም በረከት ወደ አሕ ዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርሳቸው ዘንድ።» (3፥14፤18) ነው እያለ ይናገራል። ስለሆነም ለአብርሃም የተገባለት ይህ የተሰፋ በረከት ከዘላለም ሕይወት አንሰቶ እስከ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ጭምር ነው።

[14] ሲዮን ውድ፣ *ሉ ሰርቪይ ኦቭ ኢዝራኤል ሂስትሪ* (ግራንድ ራፒድስ፣ ሚንዶርሽን I 1986) 30።

ሌላው የእግዚአብሔር መንፈስ በግልጽ ሲሠራ የምናየው በዮሴፍ ሕይ ወት ዉስጥ ነው። ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም የተረጎመው በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ ነበር (ዘጸ 42፥16፤ 37-38)። ፈርዖን ራሱ በመገረም «በውኑ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትን እንደዚህ ያለ ሰው እናገኛለንን?» (42፥37-38) ሲል ተናግሮአል።

መንፈስ ቅዱስ በምድረበዳው ጉዞ

እግዚአብሔር ሕዝቡን በድንቅና በተአምራት ከግብፅ ምድር ካወጣ በኋላ በሲና ምድረበዳ ሕጉን በመሰጠት በመካከላቸው ያድር ዘንድ መቅደስን እንዲሠሩለት ባዘዛቸው ጊዜ (ዘጸ 25፥8)፤ ሕዝቡ ሥጦታዎችን እንዲያመጡለት ለሙሴ ነገረው። ከዚያም ውስጥ አሮን ቅዱስ ይሆን ዘንድ ልብስ እንዲሠሩለ ት ሰዎችን የጥበብ መንፈስን ሞላባቸው (ዘጸ 28፥1-5)። የኡሪ ልጅ ባስልኤል የጥበብን ሥራ ያስተውል ዘንድ፤ በወርቅና በብር በናስም ይሠራ ዘንድ፤ ስፈርጥ የሚሆነውን የዕንቁ ድንጋይ ይቀርጽ ዘንድና ሥራውን ሁሉ ይሠራ ዘንድ በሥራ ሁሉ ብልሃት በጥበብም በማስተዋልም በእውቀትም የእግዚአብሔርን መንፈስ ተሞላ (ዘጸ 31፥1-5)። የአሂሳሚክን ልጅ ኤልያብም ከባስልኤል ጋር በጥበብ አብሮት እንዲሠራ መንፈስን ተሞላ (ዘጸ 31፥6)። እነርሱም የመገናኛውን ድን ኳን፤ የምስክሩን ታቦትና በርሱ ላይ ያለውን የስርየት መክደኛ እና የመሠዊያ ዕቃዎችን እንዲሠሩ ነበር።

በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር መገኘት እውን የሆነበት በመገ ናኛው ድንኳንና በቤተ መቅደሱ ውስጥ ነበር። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለሙሴ በሲና ተራራ ላይ ተገለጠለት ግለትም ሙሴ በስደት በምድያም ምድር በነበረበት ወቅት(ዘጸ 3)። ከዚያም በኋላ ግለትም ከግብፅ በጸናች እጅ ከወጡ በኋላ በዚሁ በሲና ተራራ ላይ ሕግ ለእስራኤል ተሰጠ (ዘጸ 20)። በመቀጠልም ሙሴ ትእዛዝን ተቀብሎ ለእግዚአብሔር ማደሪያ ሠራ (ዘጸ 25-31)። በዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር እቅድ ከተራራው ላይ ወርዶ በሕዝቡ መካከል ለማደር

ነበር። ማደሪያውም ተሰርቶ ባለቀ ጊዜ ደመናውም የመገናኛውን ድንኳን ከደነ፥ የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላ (ዘጸ 40፥34)።

ሙሴ በተራራው ላይ ከእግዚአብሔር ጋር በነበረ ጊዜ ሕዝቡ ጣዖትን ሰርተው በማምለክ እግዚአብሔርን በደሉ (ዘጸ 32፥1-6)። በዚህም ምክያት የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደ፤ ከሕዝቡም መካከል ብዙዎችን ቀሰፈ፥ እግዚአብሔርም ከሕዝቡጋር ላለመውጣት ወሰነ። ለሙሴም ካንተ ጋር አልወጣም ምክንያቱም አንተ ደንዳና ሕዝብ ስለሆንህ አጠፋሃለሁ። ነገር ግን ለአባቶችህ የማልሁላቸውን ምድር እንድትወርስ መላእክቴን ከአንተ ጋር አልካለሁ ብሎ በነገረው ጊዜ ሙሴ በጣም ነበር ያዘነው (ዘጸ 32፥34፤ 33፤2-5)። ሙሴም እንዲህ ብሎ እግዚአብሔርንተናገረ – «እነሆ አንተ-ይሆን ሕዝብ አውጣ ትለኛ ለህ ከእነም ጋር የምትልከውን አላስታወቅኸኝም ... ከእኛ ጋር ካልወጣህስ ከዚህ አታስወጣን በምድርፊት ካለው ሕዝብ እኔና ሕዝብህ የተለየን እንሆን ዘንድ» (ዘጸ 33፥12-16)። እግዚአብሔርም የሙሴን ልመና አዳመጠ፥ ተለመነ ውም። በዚህም ምክንያት ከእርሱ ጋርም እንደሚወጣ አረጋገጠለት።

እዚህ ላይ እንደምንመለከተው እግዚአብሔር አብሮት እንደማይወጣ ነገር ግን መላእክቱን እንደሚልክ ለሙሴ በነገረው ጊዜ የሙሴ መልስ በጣም የሚያስገርም ነበር። ሙሴ የመንፈስ ቅዱስን አስፈላጊነት በደንብ የተረዳ ሰው ስለ ነበር ምኞቱ ራሱ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲከተላቸው ነበር እንጂ መላእክት አልነበረም። እዚህ ላይ በግልጽ እንደምናየው እግዚአብሔር የተስፋ ይቱ ምድር አትገቡም አላላቸውም፥ ነገር ግን እርሱ ያላቸው ነገር ቢኖር መላ እክቱን በፊታቸው እንደሚልክና ወደ ተስፋይቱም ምድር እንደሚያስገባቸው ነበር (32፥34፤ 33፥3)። የሙሴ መልስ ግን «አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህ እንግዲህ ከሌላው ሕዝብ በምን እንለያለን» የሚል ነበር። ምክንያቱም ካለእግዚአብሔር መንፈስ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሞገስ የለውምና ነው (ዘጸ 33፥16)። በርግጥም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከሌላው አሕዛብ የሚለያቸው የመሰብሰቢያ አዳራሻቸው ማማሩ፥ የቁጥራቸው መብዛቱ ወይንም ዝማሬን ማወቃቸው ሳይሆን

የእግዚአብሔር መንፈስ በመካከላቸው ማደሩ ነው[15]።

እስራኤላውያንን ይከተል ስለ ነበረው መንፈስ ኢሳይያስ ሲናገር «በጭንቀታቸው ሁሉ ተጨነቀ፤ የርሱ መገኘት አዳናቸው[16] (የፊቱ መልአክ አዳናቸው) ... እነርሱ ግን አመፁ ቅዱስ መንፈሱን አስመረሩት ስለዚህም ተመልሶ ጠላት ሆናቸው ... የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ዕረፍት አመጣቸው» (63፥9-14) ይላል። ነህምያም «ያስተምራቸው [Instruct] ዘንድ መልካሙን መንፈስ ሰጠሃቸው» (ነህም 9፥20) በማለት ይከተላቸው ስለነበረው መንፈስ ቅዱስ ይናገራል። ጸውሎስም በቆሮንቶስ መልእክት ላይ ይሆንን አስመልክቶ ሲናገር «አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ፤ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ፤ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፥ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና» (1ቆሮ 10፥1-5) በማለት ሕይወታቸው በመንፈስ ቅዱስ ታድሶና ለምልሞ እንደቆየ ይናገራል።

ነገር ግን እስራኤላውያን በምድረበዳው ጉዞአቸው እግዚአብሔርን በተለያየ ጊዜያት በተደጋጋሚ አሳዝነውታል። በእግዚአብሔርና በባሪያው በሙሴ ላይ ማመጻቸውን በመቀጠል ቃዴስ በርኔስ ሲደርሱ ይሆንኑ አመጻቸውን ካለእነ አበዙት (ዘኁ 10-14)። ይህንንም አመጻቸውን በግልጽ በማውጣት የግብፅን ዱባና ምግብ በመምኘት (ዘኁ 11)፣ አሮንና ማርያም ደግሞ በሙሴ ላይ ክፉ በመናገር (ዘኁ 12) እና ምድሪቱን ሊሰልሉ የሄዱት ተመልሰው ዝናውን በነገሩለ

15

በዚህ ክፍል የሚገኘውን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በማስተዋል እንድመለከት የረዳኝ ዶ/ር ነርደን ፊ ናቸው። አሳቸውም ስለ መንፈስ ቅዱስ በጻፉት መጻሕፍታቸው ውስጥ ይህንን ክፍል አብራርተውታል። ስለዚህም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አባቶቻን ዘመንተም የብዙዎችችንን ልብ ስለ አበራ አጅግ አድርጌ አመሰግነዋለሁኝ።

16

«የፊቱ መልአክ» የሚለው አባባል «መልአኩ» እና «የርሱ ፊት» የሚለውን ታላት የያዘ ነው። የዚህ ኃይለት አባባል በሌለ ቦታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሶ እናየውም። መልአኩም እግዚአብሔር ራሱ ነው (ዘጸ 20፥21-23፤ 33፥2፤ 14፥15፤ ዘኁ 20፥16፤ ኢያሱ 5፥13፤ መሳፍ 13፥6፤ 21-22)። ስለዚህም ትርጉሙ እግዚአብሔር ራሱ (የርሱ ፊት) ነበር የሚከተላቸው። አባባቡንና ኢሳይያስ 63 ትን ስንመለከት «በጭንቀታቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ... በፍቅሩና በርህራሄውም ተቤዣቸው በቀ ደመውም ዘመን ሁሉ አነሰቶ ተሸከማቸው።» በማለት ራሱ እግዚአብሔር አብሮአቸው እንደወጣ ይናገራል። የእግዚአብሔር የፊቱ መገኘት በአዲስ ኪዳን ውስጥ «የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ» (ዕብ 1፥3) «የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ ክርስቶስ» (2ቆር 4፥4) «የማይታይ አምላክ ምሳሌ» (ቆላ 1፥15) በማለት ያም የፊቱ መገኘት ክርስቶስ እንደሆነ ይነገረናል። ጆን ኢን አዝዋልት፤ *ዘ ቡክ ኦቭ ኢዝራያ* (ግራንድ ራፒድስ፥ ኤርድመንስ አሳታሚ ድርጅት፤ 1998) 607።

ቸው ጊዜ በሙሴና በአሮን ላይ በማጕረምረም፥ በእግዚአብሔር ውሳኔና ኃይል ባለመታመን አመፃቸውን አብዝተው ጨመሩት (ዘኍ 14)። በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደ፥ አርሱም አለ — «በግብፅ ምድርና በምድረበዳ ያደረግሁትን ተአምራቴንና ክብሬን ያዩ እነዚህ ሰዎች ሁሉ አሥር ጊዜ ስለተፈ ታተኑኝ፥ ነገሬንም ስላልሰሙ፥ በእውነት ለአባቶቻቸው የማልሁላቸውን ምድር አያዩም፤» (ዘኍል 14፥22-23)። በዚህም ምክንያት ከግብፅ ሲወጡ ለአቅመ አዳም የደረሱ (ከ20 ዓመትና ከዚያም በላይ የሆኑት ሁሉ) ከኢያሱና ከካሌብ በስተቀር ሁሉም በምድረበዳ ሞቱ (ዘኍል 14፥29) ። ስለዚህም እግዚአብሔር የተስፋውን ምድር እንዲወርሱ ካወጣላቸው አቅድ ለሠላሳ ሰምንት ዓመታት ያህል ዘገዩ። የሚያሳዝነው ነገር ከባርነት አውጥቶ በመሸከም በምድረበዳ ሲመግባቸውና ሲመራቸው የነበረው መንፈስ ቅዱስ ተመልሶ ጠላት ሆናቸው፥ ተዋጋቸውም (ኢሳ 63፥10-11፥ 1ቆሮ 10፥1-13፤ ዕብራ 3፥7-11)።

መጽሐፈ ኢያሱ

ሙሴ በምድረበዳ ውስጥ የእያንዳንዱን ሰው አቤቱታ ማዳመጥ ሸክም በሆነበት ጊዜ፥ አማቱ ዮቶር በመከረው መሠረት ሰባ ሽማግሌዎችን መረጠ። ከእነዚህም ከተመረጡት ውስጥ አንዱ ኢያሱ ነበር (ዘጸ 24፥13፤ 32፥17)። ኢያሱ ከግስተዳደርም ባሻገር የእስራኤል የጦር አዝማችም ነበር (ዘጸ 17፥9-13)። ነገር ግን ሙሴ ከሞተ በኋላ እርሱን ተክቶ ሕዝቡን የመምራት ተጨማሪ ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር (ዘኍ 27፥16-23)። ይህም የመሪነት ሥራ ዋናው ተግባር ሕዝቡ እግዚአብሔርን መታዘዛቸውንና ማምለካቸውን መከታተል፥ እስራኤልን በቅዱስ ጦርነት መምራትና ማስተዳደር እንዲሁም የተስፋው ምድር ለሁሉም ነገዶች በትክክል መከፋፈሉንም ማረጋገጥ ጭምር ነበር (ኢያሱ 1፥2-5፤ ዘዳ 1፥37፤ 3፥28፤ 31፥7)።

እንደሚታወቀው ኢያሱ መንፈስን የተቀበለው ከሰባዎቹ ጋር ቢሆንም ይህን የአገልግሎት ሥጦታ የተሰጠው ግን ሙሴ እጁን በጫነበት ጊዜ ነበር (ዘዳግ 34፥9)። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ ከሙሴ ጋራ እንደነበረው ሁሉ ከኢያሱም ጋር ነበር (ኢያሱ 1፥5፤ 3፥7)። ሙሴ ቀይ ባሕርን እንደከፈለ ሁሉ ኢያሱም ዮርዳኖስን ከፍሎአል (ዘጸ 14፥21-23፤29፤ ኢያሱ 3፥17)። እግዚአብሔር ሙሴን በተቀደሰ ስፍራ እንደተገናኘው ሁሉ ኢያሱንም ተገናኝቶታል (ዘጸ 3፥5፤ ኢያሱ 5፥15)። እንግዲህ ከላይ እንደተመለከትነው ኢያሱ ተአምራትን ያደርግ የነበረውና ሕዝቡን እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀላቸው ምድር ይመራ የነበረው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር።

«እነሆም የእንበላ ደቦል አያገላ ወደ እርሱ ደረሰ። የእግዚአብሔርም መንፈስ በእርሱ ላይ በኃይል መረደ፤ ጠቦትን እንደሚቆራርጥ በእጁ ምንም ሳይኖር ቆራረጠው።»

መጽሐፈ መሳፍንት 14፤5-6

3

የመሳፍንት ዘመን ካሪዝማቲክ[17] መሪዎች

የመሳፍንት ዘመን በመባል የሚታወቀው ከኢያሱ ሞት በኋላ እስከ ሳኦል ንግሥና (መቀባት) ያለው ከሦስት መቶ ዓመት በላይ የሚሆነው ጊዜ ነው።[18] እንዲህ ሆነ፤ ከኢያሱ ሞት በኋላ አዲሱ ትውልድ ከእምላኩ ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ ፈቀቅ አለ። ይህም — 1ኛ. ከነዓንን ሲይዙ እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት በዚያ አገር ይኖሩ የነበሩ

17

ካሪዝማቲክ የሚለው የግሪክ ቃል «ካሪስ/ካሪስቶስ» ትርጉሙም ጸጋ እና «ካሪስማ/ካሪስማቶስ» ትርጉሙም የጸጋ ሥጦታ ከሚለው የመጣ ነው፤ ስለዚህም ካሪዝማቲክ የሚለው በጸጋ ሥጦታ ወይንም መስክታዊ ሥጦታ ግለትም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞላ ለግለት ነው የምንጠቀምበት።

18

ምንም እንኳን ከሙሴና ነቢያ ሳሙኤል በመሳፍንት ዘመን ቢኖሩም የነበሩበት ጊዜ ከመሳፍንት ዘመን ወደ ንጉሣዊ አገዛዝ ባለው የሽግግር ወቅት ስለነበር ብዙ ሰዎች በመሳፍንት ዘመን ውስጥ አይጠቀሱአቸውም።

ትን አሕዛብ ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት ሲገባቸው እነርሱ ግን ቸል በማለት የርሱን ትዕዛዝ ናቁ፤ 2ኛ. አሕዛብ ከሆኑት ከከነዓናውያን ጋር ተጋቡ፤ 3ኛ. የአሕዛብን አማልእክት በማምለክ ከግብፅ ምድር በጸናች እጅ ያወጣቸውን የአብርሃምን አምላክ እግዚአብሔርን ተዉት። በዚህም ምክንያት ለጠላቶቻቸው ባሪያ በመ ሆን እገለገሉ።

እዚህ ላይ ልብ ማድረግ የሚገባን ነገር ቢኖር በዘዳግም ውስጥ ከእግ ዚአብሔር ጋር በገቡት ቃልኪዳን መሠረት እርሱን ከተውት እርሱም ይተዋቸ ዋል (ዘዳግ 28-30)። ነገር ግን ንስሐ በገቡና በተመለሱ ጊዜ እርሱ ደግሞ መሪ የሚሆንን ሰው እያስነሳ በመንፈሱ በመሙላት (አብዛኛዎቹን መሪዎች) ይታ ደጋቸው ነበር። ይህም ቃልኪዳን *የዘዳግሙ ቃልኪዳን [Duetronomic Coven ant]* በመባል ይታወቃል። ቃልኪዳኑም በተፈጥሮው *ግዴታዊ* ሲሆን በይዘቱ ደግሞ *በረከትና መርገምን* የያዘ ነው። ስለዚህም በቃል ኪዳኑ መሠረት እግዚ አብሔር ያዘጋጀላቸውን በረከት የሚያገኙት ሲታዘዙት ሲሆን ባይታዘዙት ግን መርገምን ያጭዳሉ።

እንግዲህ ወደ ዋናው ነጥባችን ስንመጣ በዚህ በመሳፍንት ዘመን በስድ ስት የተለያዩ ጊዜያት ስጠላቶታቸው ባሪዎች ሆነዋል። ነገር ግን ንስሐ በመ ግባት ወደ አባቶቻቸው አምላክ ሲመለሱ ስድቱንም ጊዜ መሪና ፈራጅ የሚሆን ንሰው በማስነሳት ነፃ አውጥቶአቸዋል። ከላይ እንደተነጋገርነው እነዚህን የመሳፍንት ዘመን መሪዎች ልዩ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር መንፈስ ቅዱስን የተሞሉ ሲሆኑ፥ መንፈስም በኃይል ሲወርድባቸው ጦሮኞች ይሆናሉ፥ ጠላታቸው ንም በመምታት ድል ይነሳሉ[19]። እነዚህም መሪዎች እንደሚከተሉት ናቸው -

- ❖ እግዚአብሔር ጎቶንያልን በማስነሳት በመንፈሱ ሞልቶ ከመስጴጦምያ ንጉሥ የስምንት ዓመት የባርነት አገዛዝ ነፃ አወጣቸው (መሳፍንት 3፤7-11)።

19

ከእነዚህም መሪዎች መካከል ቢያንስ በአራቱ ላይ መንፈስ ቅዱስ ግልጽ በሆነ መንገድ በኃይል ሲሰ ራባቸው ይታያል። እነርሱም — ጎቶንያል (3፤10)፥ ጌዴዎን (6፤34)፥ የፍታሔና (11፤29) ሳምሶን ናቸው (13፤25፤ 14፤6፣19፤ 15፤14)።

- የእስራኤል ልጆች እንደገና በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ስለ ሠሩ እግዚአብሔር ለሞዓብ ንጉሥ አሳልፎ ሰጣቸው። እርሱም አሥራ ስምንት ዓመት ገዛቸው። እነርሱም ወደ እግዚአብሔር እንደገና በጮሁ ጊዜ ናዖድን አስነሳላቸው፤ ከጠላታቸውም እጅ ታደጋቸው (መሳፍንት 3፤12-31)።
- ናዖድ ከሞተ በኋላ የእስራኤል ልጆች እንደገና በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ። እግዚአብሔርም በከነዓናውያን እጅ ለሀያ ዓመታት ያህል አሳፍሮ ሰጣቸው። እነርሱም ወደ እግዚአብሔር በጮሁ ጊዜ በመንፈስ የተሞላችውን ነቢይቱን ዲቦራንና ባርቅን አስነሳላቸው፤ ከጠላታቸውም እጅ አዳናቸው (መሳፍንት 4-5)።
- የእስራኤልም ልጆች እንደገና በእግዚአብሔር ፊት ክፉን ሥራ ስለሠሩ በምድያም እጅ ለሰባት ዓመት ያህል አሳልፎ ሰጣቸው፤ ነገር ግን ወደርሱ በጮሁ ጊዜ ጌዴዎንን አስነስቶ በኃይሉ በመሙላት ነፃ አወጣቸው (መሳፍንት 5፤34 ፤6-9)።
- እስራኤላውያን አሁንም እግዚአብሔርን ተዉት እርሱም ለአሥራ ስምንት ዓመታት ያህል ለአሞራውያን አሳልፎ ሰጣቸው። ነገር ግን ወደርሱ በተመለሱ ጊዜ ዮፍታሄን በማስነሳት (የእግዚአብሔርም መንፈስ በዮፍታሄ ላይ መጣ ይላል) ነፃ አወጣቸው (መሳፍንት 11፤29፤ 10-12)።
- የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ፊት እንደ ገና ክፉ ሥራ ሠሩ፤ እርሱም በፍልስጥኤማውያን እጅ አርባ አመት አሳልፎ ሰጣቸው። ወደ እርሱ በጮሁ ጊዜ ሳምሶንን አስነሳላቸው። ሳምሶንን ከእናቱ ማሕጸን በመለየት በመንፈሱ ምልቶ እስራኤልን ለመታደግ ተጠቀመበት። ሳምሶንም በተለያዩ ጊዜያት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ታላላቅ ተአምራትን አድርጎአል። የእግዚአብሔርም መንፈስ በኃይል በወረደበት ጊዜ ታላላቅ ድንቆችን ያደርግ ነበር— ሀ/ የአንበሳን ደቦል በእጁ ቆራርሶአል (መሳፍ 14፤5-9)፤ ለ/ ሠላሳ ሰዎችን ገድሎአል (መሳፍ 19-20)፤ ሐ/ የአገሩ ሰዎች አስረውት ለፍልስጥኤማውያን አሳልፈው ሊሰጡት ሲሉ የመንፈስ ኃይል ከርሱ ጋር ስለነበረ ከገመዱ የታሰረበት ገመድ በእሳት እንደተበላ እንደ ተልባ እግር ሆነ፣ በእህያም መንጋጋ አንድ ሺህ ሰው ገደለ (መሳፍ15፤14-16)፤ መ/ የጋዛን በር መዝጊያ ይዞ ከውስቱ መቃኖችና ከመወርወሪያው ጋር በመንቀል በትከሻው ላይ አድርጎ በኬብሮን ፊት ወዳለው ተራራ ላይ ተሸክሞት ከወጣ በኋላ በዚያ ጣለው (መሳፍ 16፤1-3)፤ ሠ/ የቤቱን ምሰሶ ይዞ በሙሉ ኃይሉ በመግፋት ቤቱን በመናዱ ራሱንና ብዙ ሰዎችን ገደለ (መሳፍ 16፤ 28-31)።

«ይሁንም ነገር በሰማ ጊዜ በሳኦል ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወረደ፥ ቁጣውም እጅግ ነደደ።»

መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 11፥6

4

መንፈስ ቅዱስና የነገሥታት ዘመን

በመሳፍንት ዘመን ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የሚታየውን ያደርግ በነበረበት ጊዜ ካህኑ ዔሊ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ካሆነና ፈራጅ ሆኖ ያገለግል ነበር። በዚያን ወቅት እግዚአብሔርም ለሐና ወንድን ልጅ ሰጣት (በጠየቀችው መሠረት)፤ ስሙንም ሳሙኤል አለችው (1ሳሙ 1-2)። ሳሙኤልም በዓሊ ፊት እግዚአብሔርን በማገለገል አደገ። የዔሊ ልጆች ግን «ምናምንቴዎች» ነበሩ፥ እግዚአብሔርንም አያውቁትም ነበርና ኃጢአትን በመሥራት ይበድሉት ነበር (1ሳሙ 1-2)። እግዚአብሔር ግን ሳሙኤልን አስነሳው። እግዚአብሔርም ከሳሙኤል ጋር ስለ ነበረ ከቃሉ አንዳች በምድር ላይ አይወድቅም ነበር። ሳሙኤልም ከዔሊ በኋላ የእስራኤል ነቢይና ፈራጅ ሆነ (1ሳሙ 3፥19-21)።

ነገር ግን እርሱ በሸመገለ ጊዜ ልጆቹ ጉቦን እየተቀበሉ ፍርድን ያጣምሙ ነበር። የአሰራኤልም ልጆች ለሳሙኤል መጥተው — «እነሆ፥ አንተ ሸምግለሃል፥ ልጆችህም በመንገድህ አልሄዱም፤ አሁንም እንደ አሕዛብ ሁሉ የሚፈርድልን ንጉሥ አድርግልን» ብለው በጠየቁት ጊዜ ነገሩ ሳሙኤልን አስከፋው። ይህንንም በማድረጋቸው እግዚአብሔርን ናቁት (1ሳሙ 8፥ 1-9)። ታዲያ በዚሁ በጠየቁት መሠረት እግዚአብሔር ከብንያም ነገድ የሆነውን የቂስን ልጅ ሳኦልን ንጉሥ አድርጎ ሰጣቸው (1ሳሙ 9)። ሳኦልም በሳሙኤል ከተቀባ በኋላ ወደ እግዚአብሔር ኮረብታ በመጣ ጊዜ የነቢያትን ጉባኤ አገኘ። እዚያም የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ስለ ወረደበት ትንቢትንም ተናገረ (1ሳሙ 10፥ 1-13)።

ከእንድ ወር በኋላ አሞናውያን የኢያቢስን ሰዎች ማስጨነቁን ሳኦል በሰማ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወረደበት፥ ቁጣውም እጅግ ነደደ። ጥምዱንም በሬዎች ወስዶ ቆራረጣቸው፥ ሕዝቡንም ሁሉ ሰብስቦ አሞናውያንን ወጥቶ መታቸው (1ሳሙ11፥1-11)። በሌላ ጊዜ ደግሞ ሳኦል በዳዊት ስለ ቀና ሊገድለው ስለሚፈልግ ያሳድደው ነበር (ዳዊት ለንጉሥነት ከተቀባ በኋላ ጎልያድን በመግደሉ ሕዝቡ «ሳኦል ሺህ፥ ዳዊትም አልፍ ገደለ» በማለት ይዘምሩ ነበር፤ ይህም ሳኦልን እጅግ አስቆጣው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በዳዊት ላይ ይቀና ጀመር፥ 1ሳሙ 18፥6-9)። ዳዊትም ከርሱ ሸሽቶ ወደ አርማቴም ወደ ሳሙኤል መጣ።

ሳኦል የዳዊትን ወደ አርማቴም መምጣት በሰማ ጊዜ ዳዊትን ያመጡት ዘንድ መልእክተኞችን ቢልክም እነርሱ ግን መንፈስን ስለተሞሉ ወደ እርሱ ከመመለስ ይልቅ እዚያው በመቅረት ትንቢትን ይናገሩ ጀመር። መልእክተኞችን በተደጋጋሚ ቢልክም ስላልተሳካለት ሳኦል ራሱ ተነስቶ ሄደ። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በርሱም ላይ ስለ ወረደበት ትንቢተ ይናገር ጀመር። ልብሱንም

አውልቆ በሳሙኤል ፊት ትንቢት ይናገር ነበር፤ ራቁቱንም ወድቆ ቀንና ለሊት በዚያ አደረ (1ሳሙ19፥18-24)።

ዳዊትም ለንጉሥነት በሳሙኤል በተቀባበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል መጣበት (1ሳሙ 16፥13)። የእግዚአብሔር መንፈስ ግን ከሳኦል ሰለራቀ ክፉም መንፈስ ያሰቃየው ነበር። ነገር ግን መንፈስ ከዳዊት ጋር ስለ ነበር በገና ሲደረድር ሳኦልን ደስ ያሰኘውና ያሳርፈውም ነበር (1ሳሙ 16 ፥14)። ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ የተመራ ሰው ስለ ነበር ወደጦርነት ከመውጣቱ በፊት የእግዚአብሔርን መንፈስ ይጠይቅ ነበር፥ እንደዛም በማድረጉ በጠላቶቹ ላይ ድልን ይቀዳጅ ነበር። በመንፈስም የሚመራ ስለ ነበር በመውጣት በመግባቱ ማስተዋልን የሚያደርግ ሰው ነበር — በመንፈስም በመመራት ቅኔን ይደረድር ነበር (2ሳሙ 223፥2)፤ እስራኤልንም ያስጨነቀውን ጎልያድን በመግደል ክብርን ለእግዚአብሔር ድልን ደግሞ ለእስራኤል ሕዝብ ያመጣ የእግዚአብሔር ባሪያ ነበር (1ሳሙ 17፥46-49)።

ነገር ግን ዳዊትም በፍትወት ተነድቶ በቤርሳቤህ በመድረስና ባልዋ ኦርዮ በጦር ሜዳ እንዲሞት በማድረጉ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ሠራ። በዚህም ምክንያት ነቢዩ መጥቶ በገሰጸውና እግዚአብሔር በቀጣው ጊዜ (2ሳሙ 11-12) ዳዊትን በጣም አድርጎ ያሳሰበው ነገር ቢኖር መንፈስ ቅዱስ ከንጉሥ ሳኦል (እግዚአብሔርን በመበደሉ ምክንያት መንፈስ እንደራቀው ሁሉ) እንደራቀው ሁሉ ከእርሱም የሚርቀው መሰሎት ነበር። ዳዊትም በነገሩ ላይ እንዲህ ሲል ጸለየ–«አቤቱ ንጹህ ልብን ፍጠርልኝ የቀናውን መንፈስ በውስጤ አድስ። ከፊትህ አትጣለኝ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ አትውሰድብኝ» (መዝ (51፥10-11)።

ከላይ እንደተነጋገርነው ዳዊት በመውጣትና በመግባቱ ማስተዋልን የሚያደርግ ሰው ስለ ነበር በተለያዩ ጊዜያት ሳኦል በእግዚአብሔር ላይ በማመጹ ምክንያት መንፈስ ቅዱስ ሲርቀውና ክፉ መንፈስ ሲያሰቃየው የተመለከተ ሰው ነበር። ስለዚህም ነው «መንፈስህን ከእኔ አትውሰድ» እያለ ይጸልይ የነበረው ምክንያቱም ዳዊት ከመንፈስ ቅዱስ መገኘትና ምሪት ሕይወቱም ሆነ ንግሥናው ዋጋ እንደሌለው ጠንቅቆ ያወቀ ሰው ነበር።[20] ዳዊት በመዝሙር (139፥7) ላይ «ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ» ሲል፥ በምዕራፍ (143)፥10 ላይ ደግሞ «አንተ አምላኬ ነህና ፈቃድህን ለማድረግ አስተምረኝ፤ ቅዱስ መንፈስህም በጽድቅ ምድር ይምራኝ» እያለ ይጸልያል። ከሸመገለ በኋላ እንኳ ምስክርነቱን ሲሰጥ ይህንን የመሰለ ታላቅ ሥራ በዘመኑ ሊሠራ የቻለው በእግዚአብሔር ኃይል እንደሆነ ተናግሮአል (2ሳሙ 22፥1-51)።

ሌላው የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ የታየበት ጊዜ ደግሞ በንጉሥ ሰሎሞን ዘመን ነበር። የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ቤተመቅደሱን ሠርቶ እንደጨረሰ የእግዚአብሔር ክብር ቤቱን እንደሞላው መጽሐፍ ቅዱሳችን ይናገራል (2ዜና 7፥1-3)። እንደምናስታውሰው በዘዳግም ምዕራፍ 12 ላይ ለእስራኤል ልጆች የተሰፋውን ምድር በወረሱ ጊዜ እግዚአብሔር ስርሱ ቤትን በመሥራት እንዲያመልኩት ተና ግሮአቸው ነበር፤ ይህም ትዕዛዝ በንጉሥ ሰሎሞን ዘመን ተፈጸመ።

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን ሰሎሞንም በምረቃው በዓል ላይ ጸሎቱን በፈጸመ ጊዜ እሳት ከሰማይ ወርዶ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና ሌላውንም መሥዋዕት በላ። ከግቢዕ የባርነት ቀንበር አውጥቶ በምድረበዳ ይከተላቸው የነበረው መንፈስ ቤቱን ሞላው። እግዚአብሔርም ክብር የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶት ነበርና ካህናቱ ወደ ውስጡ ገብተው ማገልገል እንኳን አልቻሉም። የእስራኤል ልጆች በወለሉ ላይ በግምባራቸው ተደፍተው «እርሱ ቸር ነውና ምሕረቱም ለዘላለም ነውና» እያሉ አመለኩት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቤተመቅደሱ የእግዚአብሔር ማደሪያና የእስራኤል ሕልውና መሠረት ሆኖ ቆየ[21] (2ዜና 7፥1-10፥ 1ነገሥ 8፥11)።

በመዝሙርም ላይ ስለዚሁ ስለ እግዚአብሔር መንፈስ መገኘት ሲናገር «የመራዊት አምላክ ሆይ ማደሪያዎችህ እንደምን የተወደዱ ናቸው፤ ነፍሴ የእግዚአብሔርን አደባባዮች ትወድዳለች ትናፍቅማለች።» (መዝ (84)፥ 1-2)፥ «ኃይ

---

20 ሂልፍ ሂልደርብራንድት፤ ለን ሌልድ ትስተመንት ቲኦሎጂ ሉቸ ዘ ሰፒሪት ሉቸ ጎድ (ፐበዲ፤ ሄንድሪክሰን አሳታሚ ድርጅት፤ 1995) 127።

21 ኸርደን ፊ፥ ፖል ዘ ስፒሪት ኢንድ ዘ ፒፕል ሉቸ ጎድ (ፐበዲ፥ ሄንድሪክሰን አሳታሚ ድርጅት፤ 1996) 11።

ልሆንና ክብርህን ሊይ ዘንድ እንዲሁ በመቅደስ ውስጥ ተመለከትሁ» (መዝ(63)፤ 12) ይላል። እንዲሁም ሕዝቡ በዓመት አንድ ጊዜ ለበዓል ወደ ኢየሩሳሌም መቅደሱ ሲመጡ የከተማዋ መግቢያ ሲደርሱ መቅደሱን በሚያዩት ጊዜ — «ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ አቤቱ፥ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች» እንዲሁም «ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ» የሚሉትን መዝሙር እያለቀሱና እየፈነደቁ ይዘምሩ ነበር (መዝ (42)፤1፤ (122) ፤1)።

ኤልያስና ኤልሳዕ

አንደኖና ሁለተኛ ነገሥት መጻሕፍትን ልዩ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር የእግዚአብሔር መንፈስ በኤልያስና በኤልሳዕ እጅ ታላላቅ ተአምራትን ማድረጉ ነው። ቃሉም ግልጽ አድርጎ እንደሚያሳየን ከሆነ የሁለቱ ነቢያት አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ሥልጣን የተሞላ ነበር። አገልግሎታቸውም ነገሥታቱ አክዓብ (874-853)፥ አካዝያ (853-852)፥ ኢዮርብዓም (842-840)፥ ኢዩ (841-814)፥ ኢዮአካዝና (814-798) ኢዮአስ (798-782) በነገሡበት ጊዜ ሲሆን ወቅቱም የእስራኤልን ምድር የበዓል አምልኮ ሞለቶት ነበር[22]። በተለይ ደግሞ የንጉሥ አክዓብ ሚስት የሆነችው ሲዶናዊትዋ ኤልዛቤል የበዓልን አምልኮ በምድሪቱ አሰፋፋች። አክዓብም አርሱዋን በመከተል በዓልን ማምለክ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የማምለኪያ አጸድን በመትከል የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን አስቆጣው (1ነገ 16፤31-34)። በዚህን ጊዜ ነበር ቱሰቢያዊው ኤልያስንና በኋላም ኤልሳዕን በማስነሳት በመንፈሱ ሞልቶ እስራኤልን ወደ በአምላካቸው እንዲመለሱ የተጠቀመባቸው። እነርሱም የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ስለነበረባቸው ደፋሮች ከመሆናቸው የተነሳ ነገሥታትን እንኳን ሳያቀር ይገስጹ ነበር (1ነገሥ 17-20)።

22

ሊዮን ውድ፥ *A Sacrificial Slain Lamb* (ግራንድ ራፒድስ፥ ዞንደርቫን፤ 1986) 260-277።

አገልግሎታቸውም ኃይልን በመግለጥ ብቻ ሳይሆን ተጋፍጠው ድል በማድረግ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ከሌሎች አማልክት የሚበልጥ ኃይለኛና እውነተኛ አምላክ እንደሆነ አሳይተዋል። ኤልያስ ከኤልዛቤል ማዕድ የሚበሉትን 400 የማምለኪያ አጸድ ነቢያትንና 450 የበዓል ነቢያትን በመራት ውደ ቀርሜሎስ ተራራ እንዲሰበሰቡ አድርጎ እውነተኛው አምላክ የትኛው እንደሆነ ይታወቅ በማለት ታላቅ ተአምራትን አድርጎ ሃሰተኛ ነቢያቱንና ተከታዮቻቸውን ሲያሳፍር፥ የእግዚአብሔርንም እውነተኛነትና ታላቅነት አሳይቶአል። የበዓል ነቢያቱንም ወደ ቂሶን ወንዝ ወሰዶ በዚያ በማረድ የእግዚአብሔርን ኃያልነት በማሳየት ሕዝቡንም ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር መለሰ (1ነገ 18፤16-48)።

በርግጥም የነቢዩ ኤልያስ አገልግሎቱ ኃይልን መግለጥ ብቻ ሳይሆን ትንቢትንም በመናገር ጭምር ነበር። ለአክዓብ ዝናብ በምድሪቱ እንደሚዘንብ ትንቢትን ከነገረው በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው «የእግዚአብሔርም እጅ በርሱ ላይ ስለነበረች ወገቡን አሸንፍሞ ወደ ኢይዝራኤል እስኪገባ ድረስ የአክዓብን ሰረገላ ቀድሞ ይሮጥ ነበር» (1ነገሥ 18፤41-46)። ኤልያስ በእግዚአብሔር ኃይል ሰራጥታንና ቤተሰብዋን ከረሃብ ታድጎአታል (1ነገ 17፤1-16)፤ የሰራጥታን ልጅ ከሞት አስነስቶአል (1ነገ 17፤17-23)፣ እሳት ከሰማይ አውርዶአል (1ነገ 18፤30-40፤ 2ነገ 1፤7-18)፣ የዮርዳኖስን ውኃ በሁለት ከፍሎአል (2ነገ 2፤7-8)፤ በመጨረሻም ኤልያስ በአውሎ ነፋስ ወደሰማይ ተወስዶአል (2ነገ 2፤11)።

ኤልሳዕም ኤልያስን በለመነው መሠረት የኤልያስን መንፈስ በሁለት እጥፍ ተቀብሎአል[23] (2ነገ 2፤9-11)፣ የዮርዳኖስን ውኃ በሁለት ከፍሎአል (2ነገ 2፤14)፤ የነቢያትም ልጆች ባፕቡት ጊዜ የኤልያስ መንፈስ በርሱ ላይ ማረፉን አወቁ (2ነገ2፤15)፤ የኢያሪኮ ውኃ ክፉ ስለነበረ አርጥዝ ሴቶችን ያስወርድ ነበርና ኤልሳዕ በእግዚአብሔር ኃይል ውኃውን ስለ ፈወሰው ከዚያ በኋላ ሞትና ጭንገፋ አልሆነም (2ነገ2፤19-22)። የእስራኤል የይሁዳና የኢዶምያስ ነገሥታት

23

ኤልሳዕ የኤልያስን መንፈስ በሁለት እጥፍ ተቀበሎአል ሲባል ኤልያስ የነበረውን ጸጋና ኃይል በሁለት እጥፍ ተቀበሎአል ማለት ነው።

ሞዓብን ስመውጋት በወጡ ጊዜ ሰባት ቀን ዞረው ስእነርሱና ስሠራዊታቸው ውኃ አልተገኘም። በዚህም ምክንያት ሰለ ተጨነቁ ነቢዩ ኤልሳዕን አስጠሩት። እርሱም ባለበገና አስመጥቶ ባስደረደረው ጊዜ የእግዚአብሔር እጅ መጣችበት ትንቢትም ተናገረ። እግዚአብሔርም ውኃ አፈስቀላቸው፥ ምዓዛውያንንም በእጃቸው አሳልፎ ሰጣቸው (2ነገ 3፥4-27)።

ኤልሳዕ ከነቢያት ሚሰቶች አንዲቱ ለነበረችው ዘይቱን በማትረፍረፍ አዳዋን አንድትከፍል በማድረግ ከባርነት አድኖአታል (2ነገ 4፥1-7)፤ ታስተናግዳው የነበረችውን ሱናማይቱን ወንድ ልጅ እንደምትወልድ በነገራት ትንቢት መሠረት ወንድ ልጅን ወለዳለች (2ነገ4፥12-16)፤ ሕጻኑም ካደገ በኋላ ታሞ ቢሞት ኤልሳዕ ከሞት አስነስቶታል (2ነገ 4፥ 18-37)፤ በምድር ላይ ራብ በነበረ ጊዜ የነቢያትን ልጆች መግቦአል (2ነገ4፥38-41)፤ ሀያውን የጉበሰ እንጀራና የእህል እሸት በመባረክ በልተው እንዲያተርፉ አድርጎአል (2ነገ 4፥42-44)፤ የሶርያ የጦር አለቃ ንዕማንን ሰባት ጊዜ ዮርዳኖስ እንዲታጠብ በማድረግ ከለምጹ ፈውሶታል (2ነገ 5፥1-14)። ባጠቃላይ ኤልሳዕ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሌላ ሌላም ብዙ ድንቆችን አድርጎአል።

«ወደ ዘለቶ እንደሚወርዱ ከጠቶች፣ እንዲሁ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ዕረፍት አመጣቸው።»

ኢሳይያስ 63፥14

5

መንፈስ ቅዱስ በነቢያት መጻሕፍት ውስጥ

ትንቢተ ኢሳይያስ

ፍርድና ገዥህና (4፥4፤ 34፥16)

ኢሳይያስ የኢየሩሳሌም ኃጢ

አት ስለበዛ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚመጣ ይናገራል። ይህንንም ፍርድ የሚያመጣው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። ኃጢአቱዋን በፍርድና በሚያቃጥል መንፈስ ያነጻዋል፤ በፍርዱም እውነተኞነቱንና ጻድቅነቱን ያሳያል። በእውነትና በቅንነት በመፍረድ ክፋትን አስወግዶ ስርሱ የሆኑትን በዚያው መንፈስ ይቀ

ድሳቸዋል (ኢሳ 28፥6 ተመልከት) ግለትም በፍርድ መንፈስ ኃጢአተኛ ላይ ቢፈርድ፥ በሚያቃጥል መንፈስ ደግሞ ቅዱሳኑን ከኃጢአተኛ ከለየ በኋላ ይቀድሳቸዋል ወይንም ያነጻቸዋል (ኢሳ 30፥33፤ 42፥25)።

ጌታን መታመንና በመንፈሱ መደገፍ

(ኢሳ 31፥1-3)

ሴናክሬም የተባለው የአሦር ንጉሥ የተመሸጉትን የይሁዳ ከተሞች ለመውሰድና ኢየሩሳሌምን ለመውጋት ፊቱን ባቀና ጊዜ (701 ዓ.ዓ)[24] የይሁዳው ንጉሥ ሕዝቅያስ በእግዚአብሔር መንፈስ ላይ ከመታመን ይልቅ ከሰው ዘንድ እርዳታን ለመፈለግ ፊቱን ወደ ግብጽ አቀና። የእግዚአብሔርን ከንድ ከመደገፍ ይልቅ በግብፅ ፈረሶች ተደገፈ። እግዚአብሔርም ይህንን አስመልክቶ ግብግውያን ሰዎች እንጂ አምላክ አይደሉም፥ ፈረሶቻቸውም ሥጋ እንጂ መንፈስ አይደሉም ስለዚህም የእስራኤልን ቅዱስ ስማይመለከቱ እግዚአብሔርንም ስማ ይፈልጉ ወዮላቸው በማለት የማስጠንቀቂያ ቃልን ይናገራል።

አዚህ ላይ «አምላክ» እና «መንፈስ» የሚሉትን ቃላቶች እናያለን — ግብጻውያን አምላክ አይደሉም ለምን ከነርሱ እርዳታን ትፈልጋላችሁ? ፈረሶቻቸው ሥጋ እንጂ መንፈስ አይደሉም ስለምንስ በነርሱ ተደገፋችሁ? በማለት እርሱ ሁሉን ቻይ አምላክ ስለሆነ በርሱ በመታመን በክንፎቹ ጥላ ሥር እንዲጠለሉ ይነግራቸዋል። ከግብጻውያን ፈረሶች ይልቅ ደግሞ በጌታ መንፈስ ቢደገፉ ኃይልና ምሪት ይሆንላቸዋል።

የመታደስ ተስፋ

(ኢሳ 32፥15-20)

እግዚአብሔር ሲናገር ምድሪቱ የምትፈወሰውና ሰውም ተዘልሎ የሚኖረው መንፈስን ከላይ በሚፈስስበት ጊዜ ነው ይላል በዚህ ክፍል ውስጥ። መንፈስ ከላይ በሚፈስስበት ጊዜ ግን ምድረ በዳውም ፍሬያማ፥ የጽድቅም ሥራ ስላም፥ የጽድቅም ፍሬ ለዘላለም ጸጥታና መታመን ይሆናል እያለ የተስፋ ቃል ይሰማቸዋል።

መንፈሳዊ ባርኮት

(ኢሳ 44፥3)

ከዚህ ምዕራፍ በፊት ባሉት ምዕራፎች ውስጥ እግዚአብሔር እስራኤልን በኃጢአት ይወቅሳል። በመቀጠልም ኃጢአትህንና በደልህን እደመሰወስሁ ሁኝ በማለት ከተናገረ በኋላ በዚህ ክፍል ደግሞ ባርኮትን ይናገራል። ይህም ባርኮት የሚመጣው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው። «መንፈሴን በዘርህ ላይ በረከቴንም በልጆችህ ላይ አፈስሳለሁ» ካለ በኋላ በመቀጠልም «በፈሳሽ ችም አጠገብ እንደሚበቅሉ እንደ አኻያ ዛፎች በሣር መካከል ይበቅላሉ» (ቁ. 4) በማለት መንፈስ ቅዱስ ዘራቸውን ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ጭምርእንደሚባርክ ይናገራል። ይህም የመንፈሳዊ ሕይወት ባርኮት የርሱ መሆናቸውን ስለሚያረጋግጥላቸው «እኔ የእግዚአብሔር ነኝ» እያሉ በኩራት እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል።

መንፈስና ቃሉ

(ኢሳ 59፥21)

እግዚአብሔር የሕዝቡን ሰቆቃና ለቅሶ ተመለከተ፥ ፍርዱም እንደሌለ ስለ አየ ተከፋ (16-19)፤ ነገር ግን በዚህ ሁሉ ጭንቀት ወደ እርሱ የሚማልድ ባለማግኘቱ ተደነቀ። ስለዚህም «የገዛ ክንዱ መድኃኒትን አመጣለት፥ ጽድቁም አገዘው» በኋላ ከዚያም በመቀጠል ከኃጢአት ስሚርቁ ያለውን ቃልኪዳን ይናገራል። ይህም ከእነርሱ (ከኃጢአት ከራቁት) ጋር ያለው መንፈሱንና በአፋችው ያደረገው ቃሉ ከአፋቸው እንዲሁም ከዘር ዘራቸው አፍ ከዘላለም እስከ ዘላለም ይኖራል። ይህም የተስፋ ቃል መንፈሱና ቃሉ በአንድነት እንደሚሠሩ ይናገራል — ቃሉ እርሱን እንዲያውቁትና እንዲወዱት ሲያደርጋቸው፥ መንፈሱ ደግሞ ኃይልን በመስጠት በቃሉ እንዲኖሩ ስለሚያደርግ ይህ ቃል ኪዳን ከትውልድ ወደ ትውልድ መሸጋገሩን እውን ያደርጋል።

[24] ሊዮን ውድ፥ *ሉ ሰርቢይ ኦብ ኢዝራዕል ሂስትሪ* (ግራንድ ራፒድስ፥ ዞንደርቫን፤ 1986) 306-307።

ካህኑ ሕዝቅኤል ወደባቢሎን ሲጋዝ የሀያ አምስት ዓመት ልጅ ነበር። ይህም የሆነው በ597 ዓ.ዓ ሲሆን ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደስዋን ከዘረፈ በኋላ ነው (ማለትም በሁለተኛው ዙር ዝርፊያ ጊዜ መሆኑ ነው፤ 2ነገሥ 24፤13)። ሕዝቅኤል ከ593-571 ባለው ጊዜ ውስጥ ነቢር የእግዚአብሔርን ቃል ይናገር የነበረው። ቦታውም በከለዳውያን አገር በሚገኘው በኮቦር ወንዝ አጠገብ ነበር (ንጉሡ ዮአኪን በተማረከ በአምስተኛው ዓመት 1፤2)። ሕዝቅኤል ስለ እግዚአብሔር መንፈስ የተናገረውን እንመልከት —

«እርሱም የሰው ልጅ ሆይ በእግርህ ቁም እኔም እናገርሃለሁ አለኝ በተናገረኝም ጊዜ መንፈስ ገባብኝ በእግሬም አቆመኝ የሚናገረኝንም ሰማሁ» (2፤1-2)

«መንፈስም አነሳኝ በኋላዬም — የእግዚአብሔር ክብር ከቦታው ይባረክ የሚል የጽኑ ንውጥውጥታ ድምጽ ሰማሁ» (3፤12)

«መንፈስም አንስቶ አስወገደኝ እኔም በምሬትና በመንፈሴ መቀት ሄድሁ የእግዚአብሔርም እጅ በላዬ በርትታ ነበር» (3፤14)

«መንፈስም ገባብኝ በእግሬም አቆመኝ ተናገረኝም» (3፤24)

«እጅ መሳይንም ዘረጋ በራስ ጠጉሬም ያዘኝ መንፈስም በምድርና በሰማይ መካከል አነሳኝ» (8፤3)

«መንፈስም አነሳኝ ወደ ፀሃይ መውጫ ወደሚመለከት ወደ እግዚአብሔር ቤትም ወደ ምስራቁ በር አመጣኝ» (11፤1)

«የእግዚአብሔርም መንፈስ ወደቀብኝ እንዲህም አለኝ» (11፤5)

«መንፈስም አነሳኝ በእግዚአብሔርም መንፈስ በራእይ ወደ ከላውዴዎን ምድር ወደ ምርኮኞቹ አመጣኝ» (11፤24)

«የእግዚአብሔርም እጅ በላዬ ነበረ እግዚአብሔርም በመንፈሱ አወጣኝ አጥንቶችም በሞሉባቸው ጠለቀ መካከል አኖረኝ» (37፤1)

«መንፈስም አነሳኝ ወደ ውስጥም አደባባይ አገባኝ» (43፤5)

ሕዝቅኤል ያየው ትንቢት የቀድሞው ቤተ መቅደስ እንደሚያበቃለትና አዲስ የሆነ ክብር ያለው ቤተ መቅደስ እንደሚሠራ ነበር። «ከአሕዛብ ምድር አወጣችኋለሁ ከየአገሩም አሰባስባችኋለሁ ወደገዛ ምድራችሁም አመጣችኋለሁ ጥሩ ውኃንም አረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ ከርኩሰታችሁም ሁሉ ከጣኦቶቻችሁም ሁሉ አጠራችሁአለሁ» (36፤25)። ከዚህ ትንቢት እንደምንመለከተው በመጀመሪያ እግዚአብሔር በምርኮ አገር የነበሩትን አይሁዳውያን ሊቀድሳቸው ይፈልጋል። ከዚያም በኋላ አዲስን ልብና አዲስን መንፈስ እንደሚሰጣቸው ቃል ይገባል — «አዲስም ልብ አሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ አሰጣችኋለሁ። መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትእዛዜም አሰሄዳችኋለሁ፥ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ ታደርጉማላችሁ» (11፤19-20፤36፤26-27)።

ከዚህ በፊት እንደተነጋገርነው አሰራኢላዊያኑ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን መጠበቅ ስላልቻሉ (ይህም ከዚህ በፊት እንዳየነው «የዘዳግሙ ቃልኪዳን» በመባል የሚታወቀው፤ ዘዳግ 27-29) ወደ ስደት ተጋዙ። ኢየሩሳሌምም ተቃጠለች፥ ቤተ መቅደሱዋ ደግሞ ተዘረፈ። አሁን ደግሞ እግዚአብሔር በራሱ አነሳሽነት ሊረዳቸው ስለፈለገ አዲስን ልብና መንፈስ ይሰጣቸዋል። ይህም በርሱ ትእዛዝ አንዲሄዱ ያደርጋቸዋል። የዚህ ትንቢት የቅርብ ተፈጻሚነቱ ለእስራኤል ቢሆንም የርቀት ተፈጸሚነቱ ደግሞ ለሁሉም ሕዝቦች ነው (ነቢዩ ኤርምያስም እንዲሁ ተመሳሳይ ትንቢትን ተናግሮአል)። ትንቢቱም ሙሉ ለሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተፈጸመ፤ በርሱም ሥራ ሁሉችንም አዲስን ልብና መንፈስን ተሰጠን (ኤር 24፤7፤31፤31)። ይህንንም ትንቢት ጌታ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችንና በጉባኤያችን (በግኅበረ ምዕመናን) መሐል በማደር ተፈጸሚነቱን እውን አደረገው (ዕብራ 8፤8-12፤ 10፤15-16፤ ሮሜ 7፤6፤ ቆላስ 3፤10፤ ቲቶ 3፤5)።

በሕዝቅኤል ምዕራፍ 37 እና 39 ላይ ስንመለከት መንፈስ በአጥንቶቹ ላይ ስለነፈሰ አጥንቶቹ ሕያው ሆኑ። ይህም ትንቢት የእስራኤልን መንግሥት ከስደት መልስ መመሥረት የሚያበስር ነበር — «መንፈሴንም በውስጣችሁ አሳድራለሁ፥ አናንተም በሕይወት ትኖራላችሁ በገዛ ምድራችሁም አኖራችኋለሁ፤ እኔም እግዚአብሔር እንደ ተናገርሁ እንዳደረግሁም ታውቃላችሁ፥ ይላል እግዚ

አብሔር» (ሕዝቅ 37፥14)። የእግዚአብሔር መንፈስ ምድሪቱንም እንደሚያቆ ማትና እንደሚመሰርታት በመንገር «መንፈሴን በነርሱ ላይ አፍስሻለሁና ፊቴን ከእነርሱ አልሸሽግም» እያለ የማጽናኛ ቃሉን ይሰጣቸዋል (ሕዝቅ 39፥29)።

ትንቢተ ኢዩኤል

ለዲስ ሕይወት

የትንቢተ ኢዩኤል መጽሐፍ ሁለት መልእክቶችን የያዘ ነው። አንደኛው 1፥-2፥12 ያለው ሲሆን እርሱም የፍርድን ቃል ያዘለ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ከ 2፥13-3፥21 ያለው ሲሆን የያዘውም የደህንነትንና የማጽናኛን ቃል ነው። በምዕራፍ ሁለት ላይ ያለው ትንቢት መንፈስ ቅዱስ በሥጋ ለባሹ ላይ መፍሰሱን የሚያበስር በመሆኑ ጴጥሮስ በዘጓስ ንጥላ ቀን እንደጠቀሰው በሐዋር ያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት ላይ እናገኛለን። ቃሉም እንዲህ ይላል —«ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሹ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥ ጎበ ዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፤ ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ።» (ኢዩ 2፥28-32)።

እግዚአብሔር መንፈሱን ሳይሰፍር እንደሚሰጥና በሥጋ ለባሹ ሁሉ ላይ (በኢየሱስ በኩል ከርሱ ጋር እርቅን ላደረጉ ሁሉ) መንፈሱን በማፍሰስ በዘ መናቸው ሁሉ እርሱን በመውደድና በርሱ ደስ በመሰኘት እንዲኖሩ ያደርጋል። ይህንን ትንቢት ልዩ የሚያደርገው ነገር ቢኖር እግዚአብሔር መንፈሱን በሥጋ ለባሹ ሁሉ ላይ ሲያፈስ አሠራሩም የእድሜ ገደብ ሳይኖረው፥ የጸታገደብ ሳይኖ ረው፥ የዘር ገደብ ሳይኖረውና የመደብ ገደብ ሳይኖረው (ጨዋ ወይም ባሪያ ይሁን) መሆኑ ነው። ይህም የተሰፋ ቃል ነቢያቱ ከተነበዩት ጋር ተመሳሳይነት አለው (ኤር 31፥33-34፤ ሕዝቅ 36፥26-27)።

ከላይ እንደተነጋገርነው መንፈስ ቅዱስ በመፍሰሱ አራት ነገሮች እንደ ሚከናወኑ ተናግሮአል፤ እነርሱም – 1) ልጆች ትንቢተ ይናገራሉ 2) ሽማግሌዎች ሕልምን ያልማሉ 3) ጎበዞች ራእይ ያያሉ 5) የመጨረሻው ቀን ምልክት ይሆ ናል [Eschatological signs]።

ትንቢተ ሐጌና ዘካርያስ

የጊዜ መገኘት

የነቢያቱ የሐጌና የዘካርያስ መልእክቶች የመጡት ከባቢሎን ስደት ለተመለሱት እስራኤላውያን፥ ለመሪው ለዘሩባቤልና ለካህኑ ለኢያሱ ነው። እግዚአብሔር የፋርስን ንጉስ የቂሮስን ልብ ስላነሳሳ ምርኮኞቹ የይሁዳ ልጆች ወደ አገራቸው ተመልሰው ቤተ መቅደሱን እንዲሠሩ ትእዛዝን ሰጠ (ዕዝራ 1፥1-4)። እነርሱም ወደ ኢየሩሳሌም በመጡ በሁለተኛው ዓመት ሥራውን ጀመሩ (ይህም በ536 ዓ/ዓ መሆኑ ነው[25]፥ ዕዝ 3፥8)። ይሁን እንጂ «የይሁዳና የብን ያም ጠላቶች» ምርኮኞቹ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር አምላክ መቅደስ እንደ ሠሩ ስለ ሰሙና ስላዩ ሥራውን ተቃወሙ። ደብዳቤም ለንጉሥ አርጤ ክስስ በመጻፍ ሥራው እንዲተጓጎል አደረጉ (ዕዝ 4)።

በዚህም በሰማርያውያን ተቃውሞ ምክንያት ሥራውን በማቆም ሁሉም ወደ የራሱ የግል ሕይወት ሄደ። የእግዚአብሔር ሰዓት ገና ነው፥ ይሄ የርሱ ጊዜ ቢሆን ኖሮ ተቃዋሚዎቻችንን አጥፍቶ ሥራውን እንድንጨርስ ያደርገን በር በግለት ሁሉም ወደ ገዛ ቤቱ ሮጠ (ዕዝራ 4፥23-24፤ ሐጌ 1፥1-3)። በዚህ ጊዜ ነበር ነቢያቱ ሐጌና ዘካርያስ ሰው የቤተ መቅደሱን ሥራ እንዲቀጥል በእስ ራኤል አምላክ ስም ትንቢትን የተናገሩት (ከእግዚአብሔር በተቀበሉት ቃል መሠረት)። በትንቢቱም መሠረት መሪዎቹ ዘሩባቤልና ኢያሱ ተነስተው በኢየሩ ሳሌም ያለውን የእግዚአብሔርን ቤት መሥራት ጀመሩ (ይህም በ520 ዓ/ዓ ገደማ መሆኑ ነው[26]፥ ዕዝራ 5፥1-2)።

---

[25] ዊልሞ ዝን ገመረነ፥ *ኢንተርፕሪተርስ ዲ ፐርፌቲስ ወርድ* (ግራንድ ራፒደስ፥ ዞንደርቫን፤ 1990) 187።

[26] ዝን ገመረነ፥ 187።

ነቢዩ ሐጌ በመልእክቱም «በውኑ ይህ ቤት ፈረሶ ሳለ እናንተ ራሳችሁ በተጀለሙ ቤቶቻችሁ ለመኖር ጊዜው ነውን?»፥ «እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ ይላል እግዚአብሔር» (ሐጌ 1፡4፣13) ብሎ ተናገረ። እንደገናም እግዚአብሔር «መንፈስም በመካከላችሁ ይኖራልና አትፍሩ» ይላል በማለት አበረታታቸው።

ይህ በዚህ እንዳለ በነቢዩ በዘካርያስ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔር መልእክት እንዲህ ሲል መጣ – «ለዘሩባቤል የተባለው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው — በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። ታላቅ ተራራ ሆይ አንተ ምንድር ነህ ? በዘሩባቤል ፊት ደልዳላ ሜዳ ትሆናለህ» (ዘካር 4፡6)። በሰማርያውያን በኩል ስለደረሰባቸው ታላቅ ተቃውሞና ተስፋ መቁረጥ (ተራራው) ሲያጽናናቸው፥ መሪ በሆነው ከዘሩባቤል ጋር በመሆን በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ይህንን ተራራ እንደሚያስወግድላቸው ይነግራቸዋል። ይህም ደግሞ የቤተመቅደሱን ሥራ ሠርተው እንዲጨርሱ ኃይልና ብርታት ሆናላቸዋል።

እንግዲህ ከላይ እንደተመለከትነው ሁለቱም ነቢያት ያመጡት መልእክት ግልጽ ነው – ይኸውም መንፈሱ ከእነርሱ ጋር ስለሚሆን የሚያጽናና ኃይል የሚሰጥ ነው። ስለዚህም መንፈሱ ከእነርሱ ጋር ስለሚሆን ታላቁ ተራራ ማለትም የቤቱን ሥራ ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ የገታው ተቃውሞ ደልዳላ ሜዳ ይሆናል የሚል ነው። ምንም እንኳን ቤቱን መሥራት ሲጀምሩ ተቃዋሚዎቻቸውም ሥራው እንዲቆም ደብዳቤ ወደ ንጉሥ ዳርዮስ ቢልኩም እግዚአብሔርም በተናገረው መሠረት ዳርዮስ ሥራው እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጠ። የአምላካቸው እጅና መንፈስ ከእነርሱ ጋር ስለ ነበረ ሥራው ሰለጠ።

ይህም መንፈስ በእግዚአብሔር ላይ እንዲደገፉ በማድረግ ዕረፍትን፥ ሞገስንና የጸሎትን ኃይል ሰጣቸው (ዘካር 6፡8)። እግዚአብሔርም ሲያጽናናቸው ቤቱን በክብር እንደሚሞላው፥ ሰላምን እንደሚሰጣቸውና ከፊተኛው ቤት ይልቅ (ንጉሥ ሰሎሞን ከሠራው) የዚህ የሁለተኛው ቤት ክብር እንደሚበልጥ ይነግራቸዋል (ከፊተኛውም ቤት የሚበልጠው በሕንጻው ማማር ሳይሆን እግዚአብሔር መንፈሱን ስለሚያፈስበት ብቻ ነው፤ ማለትም በመንፈስ የተዋበ ይሆናል፥ ሐጌ 2፡7-9)።

በጣም የሚደንቀው ነገር ቢኖር የእግዚአብሔር መንፈስ በመካከላቸው ስለ ነበር በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሥራውን ሰርተው ጨረሱ፤ ቤተ መቅደሱንም ሁሉ እደሱት (ይህም በ515 ዓዓ መሆኑ ነው)[27]። ይህንንም አስመልክቶ ዕዝራ ሲናገር «የአይሁድም ሽማግሌዎች በነቢዩ በሐጌና በአዶ ልጅ በዘካርያስ ትንቢት ሠሩ ተከናወንላቸውም። እንደ አስራኤልም አምላክ ትእዛዝ እንደ ቆሮስና እንደ ዳርዮስ እንደ አርጤክስስም ትዕዛዝ ሠርተው ፈጸሙ።» በማለት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተጽናንተውና ከንዶቻቸውን አበርትተው ጠላቶቻቸውን በማሸነፍ ሥራውን እንደጨረሱ ይናገራል (ዕዝ 6፡14)።

ታዲያ እኛም እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይና አገልግሎት «ከብንያምና ከይሁዳ» ጠላቶች በሚነሱብን ውጊያ ምክንያት ተስፋ ከመቁረጥ የተነሳ ችል እንል አይገባንም። እግዚአብሔር አምላካችን ከፊታችን የተጋረጠብንን «ተራራ» በመንፈሱ ደልዳላ ሜዳ ማድረግ የሚችል ብርቱ ጦረኛ ስለሆነ ራሳችንን ስርሱ ሙሉ ለሙሉ በመስጠት መንፈሳዊ ውጊያን እንዋጋ ይገባናል። ትናንትና «እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ» ደግሞም «መንፈሴ በመካከላችሁ ይኖራልና አትፍሩ» ብሎ ለዘሩባቤልና ለኢያሱ የተናገረ አምላክ አሁንም ለእኛ ይህንኑ የሚያበረታታና የሚያጽናና ቃል ይነግረናል። ስለዚህም መንፈስ በሚያስተጥቀን ኃይል የዛሉትን ክንዶች አበርትተን፥ የተሰጠንን አገልግሎት በታማኝነት እንወጣው ይገባናል። ምክንያቱም ከእነ ዘሩባቤል ጋር የነበረው የክርስቶስ መንፈስ አሁንም ከእኛ ጋር ነውና።

ትንቢተ ዳንኤል

ዳንኤልና ባልንጀሮቹ ወደ ባቢሎን ምርኮ የተወሰዱት የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም በነገሠ በሦስተኛው ዓመት ሲሆን ይህም በ 605 ዓዓ ገደማ ነው[28] (ዳን 1፡1፤ 2ነገሥ 24፡1-2፤ 2ዜና 36፡5-7)። የተወሰዱትም በመጀመሪያው የባቢሎናውያን ከበባ ጊዜ ነው። ዳንኤልና ባልንጀሮቹ ከመሳፍንቱና ከነገሥታቱ

[27] ሽን ጉመረን፥ 193።
[28] ጆን ዋልቮርድ፥ ዳንኤል (ቺካጎ፥ ሙዲ ፕረስ፤ 1971) 29።

ዘር ውስጥ ተመርጠው ወደ ባቢሎን ቤተመንግሥት እንዲመጡ የተመረጡበት ምክንያት በጥበብ ሁሉ የሚያስተውሉ፣ እውቀትም የሞላባቸው፣ ብልሃኞችና አስተዋዮች ስለ ነበሩ ነው። በስደትም ምድር ራሳቸውንም በአሕዛብ መጠዋ ና መብል እንዳይረክሱ በማድረጋቸው[29] እግዚአብሔር በትምህርትና በጥበብ ሁሉ እውቀትንና ማስተዋልን ሰጣቸው[30]። ንጉሡም ባነጋገራቸው ጊዜ በጥበብና በማ ስተዋል በግዛቱ ሁሉ ካሉት የሕልም ተርጓሚዎችና አስማተኞች አሥር እጅ በል ጠው ተገኙ። በተለይ ደግሞ ዳንኤል በራእይና በሕልም አስተዋይ ሰው ነበር (ዳን 1፤3-6፤ 17-21)።

ንጉሥ ናቡከደነፆር ሕልም አልሞ ሕልሙ በጠፋበት ጊዜ የከለዳ ውያንን አስማተኞችና ሕልም ተርጓሚዎችን አስጠርቶ እንዲነግሩት በጠየቃቸ ው ጊዜ ሊነግሩትም ሆነ ሕልሙን ሊፈቱለት አልቻሉም። ነገር ግን ዳንኤል መንፈስ ቅዱስ ስለነበረው ሕልሙንም ሆነ ፍቺውን ለንጉሡ አስታወቀው (ዳን ምዕ 2)። መንፈስም ቅዱስ ስለነበረበት ከሁሉም በላይ ከፍከፍ አለ፣ በባቢሎን ጠቢባን ሁሉ ላይ ዋነኛ አለቃ ሆኖ ተሾመ (ዳን 2፤1-49፤ 5፤29፤ 6፤3)።

ንጉሡ ብልጣሶር የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ የወርቁንና የብሩን ዕቃዎች አስመጥቶ በግብዣው ላይ እንዲጠጣበት በማድረጉ እንዲሁም እግልሉ ከቶቻቸውን እያመሰገኑ እግዚአብሔርን ስለ አሳዘኑት፣ የሰው እጅ ጣቶች የሚ መስሉ ወጥተው በግንቡ ላይ በተጻፉ ጊዜ ፍቺውን የከለዳውያን ጠቢባን ሊፈቱ ት አልቻሉም። ነገር ግን «የቅዱሳን አማልክት መንፈስ ያለበት» ሰው ዳንኤል የቃሉን ፍቺ አስታወቀው (ዳን. ምዕ 5)።

ንጉሡ ዳርዮስ መቶ ሀያ መሳፍንት በመንግሥቱ ሲሾም ሦስት አለቆችን ደግሞ በላያቸው ሾሞ ነበር። ከእነዚህ ከሦስቱ ሹማምንት አንደኛው ዳንኤል ነበር። ዳንኤልም መልካም መንፈስ ስለ ነበረው ከአለቆችና ከመሳፍንት ሁሉ በልጦ ተገኘ (ዳን 6፤1-3)።

ዳንኤል የመንፈስ ቅዱስ ስጦታም ስለ ነበረው በመጨረሻው ዘመን ስለ ሚከናወኑት ነገሮች ራእይን ተቀብሎአል (ምዕ 7-12)። ባጠቃላይ ዳንኤል የእግዚአብሔር መንፈስና ስጦታው ስለ ነበረው በአራት ነገሥታት ሥር ክብርን በማግኘት በሥልጣን ላይ ቆየ። እነዚህም ነገሥታት ናቡከደነፆር፣ ብልጣሶር፣ ዳርዮስና ቂሮስ ናቸው።

---

29 እነ ዳንኤል ምግቡንና መጠጡን ላለመብላት የፈለጉበት ምክንያት 1ኛ. ሥጋው በሙሴ ሕግ የተከለ ከለ አንስሳ ሥጋ ነበር፣ 2ኛ. መጠጡና ምግቡ ለባዚሉናውያን አማልክት ከተሰዋ ዕቃ ነበር የሚ ባላው። ይህ ደግሞ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይቃረናል። ዋልቬርድ፣ ዳንኤል I 37-38።

30 ዳንኤልና ባልደረቦቹ በንጉሡ ፊት እንዲቆሙ የተመረጡበት ምክንያት «በጥበብ ሁሉ የሚያስተውሉ እውቀትም የሞላባቸው ብልሃተኞችና አስተዋዮች» በመሆናቸው እንደነበር በ1፤3-4 ላይ እንመለከ ታለን። እነርሱም ከንጉሥታቱና ከመሳፍንቱ ዘር ስለ ነበሩ ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ ነበሩ። እግዚአ ብሔርን በመታዘዛቸውና በማክበራቸው ደግሞ የጸጋ ስጦታ ተሰጣቸው። ይህም ደግሞ ሰማያዊ የሆ ነ «በትምህርትና በጥበብ ሁሉ እውቀትንና ማስተዋልን» የሚሰዋ ነው።

«ከንጉሥ አርጤክሰስ በኋላ ምንም ዓይነት ዘሪይ አልነበረም። ስለዚህም ነው የአገዚአብሔር አስትንፋስ ያለበት መጽሐፍት ያልተጻፈው።»

ጆሲፈስ (አጌንስት ኢፒየን 1.41)

6

መንፈስ ቅዱስ በጥንቱ ይሁዲ ሃይማኖት ውስጥ

እይሁዳውያኑ ከባቢሎን ስደት ከተመ ለሱበት አንስቶ እስከ መሢሁ መምጣት ማለትም እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ድረስ ያለው ጊዜ የመከከለኛው ዘመን በመባል ይታወቃል (በሁለቱ ኪዳናት መካከል ስለሚገኝ ነው)። ይህም ዘመን አራት መቶ ዓመታትን የያዘ ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ ከዘሩባቤል[31] በኋላ ምንም ዓይነት ከዳዊት ግንድ የሆነ መሪ አልተነሳም።

31

ይህ ዘመን አንደ አግዚአብሔር ፍቃድ በንጉሥ ቂሮስ አነሳሽነት ዕገዛ፣ ዘሩባቤል፣ ኢያሱና ብዙ ሕዝብ ወደ ኢየሩሳሌም በመምጣት ቤተ መቅደሱን ሠሩ። በመቶጠልም ከህሞያ ጋርም ሌላኛው ቡድን ቅጥርን ለመሥራት መጥቶአል። ቢሆንም ቅሉ ከዘሩባቤል በኋላ በእስራኤል ምድር ከእሴይ ግንድ የሆነ መሪ አልተነሳም ነገር ግን በምድሪቱ ብዙ የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎች ነበሩ።

የዝምታ ጊዜም ስለ ነቢረ የመንፈስ ቅዱስ መነዳት [Prophetic inspiration] አልነበረም። ከዚህም የተነሳ ብዙ ሰዎች በራሳቸው አነሳሽነት መጻሕፍትን ጽፈዋል። አን ዳንዶቹም መጻሕፍት ተቀባይነትን እንዲያገኙ በማሰብ በታዋቂ የአግዚአብሔር ሰዎች ስም ተጽፈዋል። ከላይ እንደተጠቀሰው እነዚህ መጻሕፍት በአግዚአብሔር መንፈስ መነዳት ወይም ምሪት [Inspiration] ስለአልተጻፉ እውነተኛነት [Authenticity] ይጎድ ላቸዋል። በሰዎች ስም የተጻፉት ደግሞ የብዕር ስም መጻሕፍት [Pseodonymous litrature] በመባል ይታወቃሉ።[32]

የአይሁድ ታሪክ ጸሐፊ የሆነው ጆሲፈስ አጌንስት ኢፒየን በተባለው መጽሐፉ ላይ ከንጉሥ አርጤክሰስ እስከ አሁን ድረስ ያለው ታሪክ ተጠቃሎ ቢጻፍም ከዚያ በፊት የነበሩትን መጻሕፍት አያክልም ምክንያቱም ከአርጤክሰስ በኋላ የተጻፉት መጻሕፍት በነቢያት የተጻፉ አይደሉም በማለት የዝምታው ጊዜ ነቢያት የጠፉበት ጊዜ መሆኑን ተናግሮአል።[33] የአይሁድ መምህራን በጻፉዋቸው ሥነጽሑፍም ውስጥም ስለ መንፈስ ቅዱስ በዘመኑ በኃይልና በመገለጥ ሰላለመ ሥራቱ ሲናገሩ – የመጨረሻዎቹ ነቢያት ሐጌ፣ ዘካርያስና ሚልክያስ ከሞቱበት ጊዜ አንስቶ መንፈስ ቅዱስ በግልጽ ሲሠራ አለመታየቱንና ነገር ግን በተለየና በግልጽ በማይታይ መንገድ በሕዝቡ ውስጥ ይሠራ እንደነበረ ገልጸውታል።[34]

ከዚህ የምንረዳው ነገር ቢኖር በዝምታው ወቅት ምንም የመንፈስ መነዳት [Inspiration] ስለሌለ የተጻፉት የብዕር ጽሑፎችም ሆኑ ቀኖና መጻሕፍት አንደ አግዚአብሔር ቃል ሊወሰዱ አይገባቸውም። ምክንያቱም የሕያው የአግዚአብሔር አስትንፋስ የለባቸውምና ነው።

32

የአነዚህ የብዕር መጻሕፍት ጸሐፊዎች መጽሐፍቶቻቸው ተቀባይነትን አንዲያገኙ በማሰብ በታዋቂ የአግዚአብሔር ሰዎች ስም ጽፈዋል። ባጠቃላይ ሲሉቹም ያልጠቀስኳቸው አሥራ ስድስቱ መጻሕ ፍትም ቢሆኑ አንዲሁ በሌሎች ሰዎች የተጻፉ በመሆናቸው አይሁዳውያኑ የአግዚአብሔር ቃል ወይ ም የአግዚአብሔር አስትንፋስ አድርገው አይወስዱዋቸውም ነበር። ስለዚህም በአብራይስጡ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ [ማሶሬቲክ ቴክስት] ውስጥ ተካተው አይታዩም ምንም አንኳን ወደ ግሪክ የ ተተረጎመው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ [ሰፕቱጀንት] ውስጥ አንዳንዶቹ ተተርጉመው ቢገኙም ቅሉ። ይህም ሰፕቱጀንት የተተረጎመው በዚሁ የዝምታ ወቅት ሲሆን (283-245 ዓ.ዓ. ባለው ጊዜ ውስጥ ነው) ቦታውም በግብጽ ዘምትሮው በአሌክሳንደሪያ ውስጥ ነው።

33 ጆሲፈስ (አጌንስት ኢፒየን 1.41)።

34 (ቶስ ቦት 842) *ስፕሪት ኢን ዘ ኦስፕልስ* አንድ አስትሰ ውስጥ ተጠቅሶአል።

ስለዚሁ ድጋፍ መረጃ የሚሆነን ኢየሱስ በማቴዎስ ምዕራፍ ሀያ ሦስት ላይ ያስተማረው ነው —

> «እነሆ፣ ነቢያትንና ጥበበኞችን ጻፎችንም ወደ እናንተ እልካለሁ፤ ከእነርሱም ትገድላላችሁ ትሰቅሉማላችሁ፣ ከእነርሱም በምኵራባችሁ ትገርፋላችሁ ከከተማም ወደ ከተማም ታሳድዳላችሁ፤ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ ይደርስባችሁ ዘንድ።»
>
> (ማቴ 23፣34-35)

የአቤል መሞት በመጀመሪያው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ በሆነው በዘፍጥረት ውስጥ ሲገኝ የዘካርያስ መሞት ደግሞ በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ካለፅ ውስጥ ይገኛል (ዘፍ 4፣8፤ 2ዜና 24፣15-22)። እንደሚታወቀው ሁሉ የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት ይጀምርና የሚደመደመውም በዜና መዋዕል ካለፅ ነው። ይህም ማለት የነቢያት መጻሕፍትና መዝሙራት በመጽሐፉ የመካከለኛው ክፍል ውስጥ ነው የሚገኙት። ኢየሱስ በምድር በነበረበት ጊዜም የነበረው የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና/የብዕር መጻሕፍትን በውስጡ ያካተተ አይደለም። እንግዲህ ይህንን ካየን ኢየሱስ የሚነግረን ነገር ቢኖር የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከ «ሀ» እስከ «ፐ» ድረስ ስለተገደሉት ነቢያት እንደሚናገሩ ነው። እነዚህ የብሉይ መጻሕፍት ደግሞ የተጻፉት ከዝምታው ዘመን በፊት እንደሆነ የታወቀ ነው። ስለዚህም ኢየሱስ በትምህርቱ ውስጥ እነዚህን የቀኖና መጻሕፍት ያልጠቀሰበት ምክንያት የእግዚአብሔር ቃል ባለመሆናቸው ሲሆን ለእኛም ደግሞ ጥሩ መረጃ ሆኖ ቀርቦልናል።[35]

አዲሁም በሰሜን አፍሪካ የምትገኘው የካርቴጅ ቢሾፕ የነበረው አትናቴዎስ በ367 ዓም ላይ የፋሲካን በዓል አስመልክቶ ለአብያተክርስቲያናት በጻፈው ደብዳቤ ላይ የቀኖና መጻሕፍት የመሰራጨታቸው ጉዳይ ስላሳሰበው ክርስቲያኑ ሕዝብ እንዲጠነቀቅ በመንገር እነዚህ መጻሕፍት የእግዚአብሔር አስትንፋስ እን

35

ዎልተር ሲ. ካይዘር፣ *ቅዎርድ ሪዲስከቨሪንግ ዚ ኦልድ ቴስተመንት* (ግራንድ ራፒድስ፣ ዞንደርቫን አሳታሚ ድርጅት፣ 1991) 44-45።

ደሌለባቸውም ጠቅሶአል። በደብዳቤውም ላይ ሀያ ሰባቱን የእግዚአብሔር አስትንፋስ ያለባቸውን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በዝርዝር አስቀምጦዋቸዋል።[36]

ይህ የዝምታ ወቅት የመንፈስ ቅዱስ መገለጥና ምሪትም የጠፋበት[37] ጊዜ ስለነበር የሚመጣውን የመታደስ ዘመን በተሰፋ እንዲጠባበቁ በማድረግ መልካም አስተዋጽኦ ነበረው። ስምሳሌ መቃብያኑ ይሁዳ ቤተ መቅደሱን በኃይል አሸንፎ ከሶርያውያን እጅ በማረከበት ጊዜ (164 ዓዓ ገደማ ማለት ነው[38]) ቀሳውስቱ በእሕዛብ የረከሰውን መሠዊያ ካፈረሱት በኋላ በምትኩ ሌላ በመሥራት ድንጋዮቹን በመቅደሱ ግቢ ውስጥ ደህና ቦታ አስቀመጡት። ይህንንም ያደረጉበት ምክንያት በዚያን ጊዜ ቀጥተኛ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ስላላገኙ ነበር። ስለዚህም ነቢይ ይመጣል፣ እርሱም ምን ማድረግ እንደሚገባን ይነግረናል በማለት ይጠባበቁ ነበር[39]። እንግዲህ ከዚህ ክፍል የምንመለከተው በዚያን ወቅት ቀጥተኛ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት እንዳልነበረ ነው።

በተጨማሪም በዚሁ በዮንቱ ይሁዲ ሥነመለኮት አስተሳሰብ መሠረት ሰዎች መንፈስ ቅዱስን የንጽህና መንፈስና የትንቢት መንፈስ ነው ብለው ያምኑ ነበር (ስመቀደስና ትንቢትን ስመስጠት)።[40] የንጽህና መንፈስ በመሆኑም ሰዎችን ሲቀድስ የትንቢት መንፈስ በመሆኑ ደግሞ ሰማያዊ የሆኑ መገለጦችን ይሰጣል።

36

ግርሀ ኤ. ኖል፣ *ተርኒንግ ፖይንትስ፣ ዲሳይሲቭ ሞመንትስ ኢን ዘ ሂስትሪ ኦቭ ክርስቲያኒቲ* (ግራንድ ራፒድስ፣ ቤከር ቡክ ሃውስ፤ 1997) 37.

37

ይሄንን ሰል መንፈስ ቅዱስ ስልነበረም ማለቱ አይደለም፤ አርሱ እግዚአብሔር እንደመሆኑ መጠን በሁሉም ሰፍራ የሚሠራና ሁሉ በመለኮታዊ ሥራ ላይ ነው (ሰዎችን በትድስና እንዲናሩ ያስችላቸው እንደነበረም ተጠቅሶአል)። ነገር ግን ለመገለጽ የሞከርኩት በሰዎች ሕይወትም ሆነ በጉባኤ መሐል የሚታይ ግልጽ የሆነ መገለጥና ተአምራት እንዲሁም ታሪን እንዲጽፉ የሚያስችላቸው የመነጻት አገልግሎት ሲያከናውን አለመታየቱን ነው። በርግጥ በኩምራን ማኅበረሰብ ውስጥ በብዛትም ባይሆን አልፎ አልፎ የትንቢት አገልግሎት እንደነበረ የሚጠቁሙ አንዳንድ ሥነጽሑፎች ነበሩ። — ክሬግ ኪነር፣ *ዘ ስፒሪት ኢን ዘ ኅስፐልስ ኢንድ አስትስ* (ፒበዲ፣ ሄንድሪክሰን አሳታሚ ድርጅት፤ 1997) 10-11።

38 ኢየን ውድ፣ *ኤ ሰርቪይ ኦቭ ኢዝራልስ ሂስትሪ* (ግራንድ ራፒድስ፣ ዞንደርቫን፤ 1986) 359።

39

ዊልያም ላርኪን ኢንድ ጆል ዊልያምስ፣ *ሚሽን ኢን ዘ ኔው ቴስታመንት* (ሜሪኖል፣ ኦርቢስ ቡክስ፤ 1998) 22። ክሬግ ኪነር፣ *ዘ ስፒሪት ኢን ዘ ኅስፐልስ ኢንድ አስትስ* (ፒበዲ፣ ሄንድሪክሰን፤ 1997) 14።

40 ክሬግ ኪነር፣ *ዘ ስፒሪት ኢን ዘ ኅስፐልስ ኢንድ አስትስ* I 1።

በተለይ ደግሞ የሙት ባሕር የተቸበለለ ብራና [Dead Sea Scroll][41] የኩምራን ማኅበረሰብን መንፈሳዊ ይዘትንም ያዘለ ሲሆን በዚሁ ጽሑፍ ውስጥ የንጽህና መንፈስ ሰዎችን በጥሩ ግብረገብ እንዲኖሩ እንደሚያስችላቸው ተጠቅሶአል። ይህም ደግሞ በአዲስ ኪዳን ላይ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ተብሎ ከተጠቀሰው ጋር ይስማማል (ገላት 5፤16-23)።

እነዚሁ በእንደኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊትና በኋላ ይኖሩ የነበሩት ኢሰንስ[42] ይባሉ የነበሩት የሃይማኖት ሰዎች (የኩምራን ማኅበረሰብ) በቅድስና መኖር ላይ በጣም ስለሚያተኩሩ (በሙሴ ሕግና በማንጻት ተግባር ላይ) ብዙ መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ የጻፉአቸው ጽሑፎች በእርሱ የማንጻት አገልግሎት ላይ ያተኮረ ነው። በቀኖና መጻሕፍት ውስጥም ስለ እግዚአብሔር የማንጻት አገልግሎት እንዲህ ተብሎ እናገኛለን «ከዚያች ቀን ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ እኔን ከመከተል ወደ ኋላ እንዳይመለሱ አነጻቸዋለሁ ልቡናቸውም እኔን ትከተላለች ትእዛዜንም ሁሉ ይፈጽማሉ።» (መጽሐፈ ኩፋሌ 1፤22)።

በሌላም በኩል የጥንቱ የይሁዲ ሐይማኖት የሥነመለኮት አስተሳሰብ የትንቢትን መንፈስ ከመለኮታዊ መገለጥና ጥበብ ጋር ያያይዋል።[43] የአይሁድ መምህራንንም እንዲሁ መንፈስ ቅዱስን ከትንቢት አገልግሎት ጋር ያያይዙታል። ጆሲፈስ የተባለው የጥንቱ የአይሁድ የታሪክ ጸሐፊ እንዲህ በማለት ጽፎአል – «መለኮታዊ መንፈስ በዳዊት ላይ በመጣ ጊዜ ትንቢት መናገር ጀመረ» (ጆሲፈስ ስ አንቲኪዩቲ 6.166)። ፋይሎ የተባለውም የታሪክ ጸሐፊ እንዲሁ መንፈስ ቅዱስን ከትንቢት መንፈስ ጋር ያያይዘዋል። በመጽሐፈ ሲራክ ውስጥም

41

የሙት ባሕር የተቸበለለ ብራና [ዶድ ሲ ስክርል] በመባል የሚታወቀው ሥነ ጽሑፍ የዕብራይስጡን ብሉይኪዳን መጻሕፍትን የያዘ ነው፤ የተገኘውም 1947 ነው በሙት ባሕር አቅራቢያ ሲሆን ያገኘው ም አንድ እረኛ ነው። እነዚህ መጻሕፍት የተቀበሩት ኢሲንስ በሚባሉት በኩምራን ማኅበረሰብ ሲሆን ይህንን ዋቅል በመመልከት እሁን ያለንን መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ እንደሆነ ማረጋገጫና በሁለቱ ኪዳናት መካከል ባሉት ጊዜያት ያለውን የመንፈሳዊ አንቅስቃሴ ማወቅ ይቻላል።

42

እነዚህ ኢሲንስ በመባል የሚታወቁት የሃይማኖት ክፍሎች ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ጋር የሚተካከሉ አንድ ቡድን ናቸው። በብዙ ይኖሩ የነበሩትም በይሁዳ ግዛት ውስጥ ሲሆን አሕዛብ ይኖሩበት የነበረውን የእስራኤል ክፍል ውስጥ አይኖሩም ነበረ ምክንያቱም አንዳይረክሱ ስለሚፈሩ ነበር። ባጠቃላይ በቅድስና ላይ በጥብቅ ያተኮሩ በስ ነበር ስብቻቸው ተለይተው የሚኖሩ አይሁዳውያን ነበሩ። የተወሰደው ከ *ዘ ኦንደርሽን ኘሽቶሪያል ኢንሳይክሎፒዲያ ኦቭ ዘ ባይብል ቮልም ፲* ሚሪል ቴኒ (ኤዲተር) (ግራንድ ራፒድስ፡ ሬጅነሲ ረፍረንስ ሳይብሪሪ)

43 ኪነር *ዘ ሰፒሪት ኢን ዘ ኘስፐልስ ኤንድ አክትስ* 11

«ኢሳይያስ የወደፊቱን በታላቁ መንፈስ አየ» ብሎ ይናገራል (48፤22-24)። በአጠቃላይ ከላይ እንደተመለከትነው የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በተመለከተ በጥንቱ የይሁዲ ሃይማኖት ውስጥ እነዚህ ሁለት ዓይነት አመለካከቶች ነበሩ ማለት ነው (የትንቢትን ቃል መስጠትና መቀደስ ናቸው)።

«እኔስ ሰንሰሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ ከማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታልኤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል፤ መንቹም በእጁ ነው፥ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፥ በንፋሩ ያከታል፥ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል።»

የማቴዎስ ወንጌል 3፥11-12

7

መንፈስ ቅዱስ በወንጌላት ውስጥ

በነቢዩ በአሞጽ እንደተጻፈው

እግዚአብሔር ምስጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ ምንም ነገር ስለማያደርግ የመሢሑን መምጣት የምሥራች አብሳሪና መንገድ ጠራጊ ይሆን ዘንድ መንፈስ ዮሐንስን ከእናቱ ማሕፀን ለየው (አሞጽ 3፥7)። መጥምቁም ከምድረበዳ «ለእግዚአብሔር መንገድ አዘጋጁ እያለ» የአራት መቶውን ዓመት የዝምታ ጊዜ በመደምደም አዲሱን የመንበሮ ጊዜ ጎህ መቅደዱን አበሰረ።

የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በዮሐንስ ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ ስንመለከት የእግዚአብሔር የማዳን እጅ መቃረቡን እንረዳለን። ዮሐንስ ገና በእናቱ ማሕፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ሞላበት (ሉቃ 1፥15)፤ የኤልያስን ሚና ይጫወታል[44] (ሉቃ 1፥17፤ ሚልክ 3፥1፤ 4፥5-6)፤ የምሥራች ነጋሪ ነው (ሉቃ 1፥19፤ ኢሳይ 40፥9)፤ መንፈስ ቅዱስ ስለሚያድርበት የወይን ጠጅ አይጠጣም (ሉቃ 1፥15፤ ዘኍል 6፥3፤ ዘሌዋ 10፥9፤ መሳፍ 13፥3-4)። ከእስራኤልም ልጆች ብዙዎችን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳል፤ የተዘጋጁትንም ሕዝብ ለጌታ እንዲያበጅ ናዳ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፥ የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ (በመሢሑ) ይሄዳል (ሉቃ 1፥16-17)።

እናቱ ኤልሳቤጥ የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ጽንሱ (ዮሐንስ) በማሕፀንዋ ዘለለ፥ መንፈስንም ተሞላች (ሉቃ 1፥41)። አባቱ ዘካርያስ መንፈስ ቅዱስ ሞልቶበት እንዲህ በማለት ስለ ዮሐንስ ተናገረ – «አንተ ሕጻን ሆይ፥ የልዑል ነቢይ ትባላለህ፥ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና፤ እንደ ዚህም የኃጢአታቸው ስርየት የሆነውን መዳን እውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ፤» (ሉቃ 1፥76)።

ዮሐንስም እድጎ በመንፈስ ከጠነከረ በኋላ ለእስራኤል እስከ ታየበት ቀን ድረስ በምድረበዳ ኖረ። እዚያም የእግዚአብሔር ቃል መጣለት፤ ይህም በነቢዩ በኢሳይያስ እንደተጻፈው ይፈጸም ዘንድ መንገድን ለመሢሑ ሊጠርግና ሊያዘጋጅ መጣ (ሉቃ 3፥3-6፤ ኢሳ 40፥3-5፤ ሚልክ 3፥1)። ዮሐንስም የንስሐን ጥምቀት እያጠመቀ ቡበዙ ምክርም እየመከረና እየገሰጸ መጣ። እርሱም በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ስለ ነበር የሕዝቡን ኃጢአት በግልጥነትና በድፍረት እየተቃወመና እየገሰጸ ለንስሐ እንዲመጡ ይጋብዝ ነበር። ፈሪሳውያን፥ ሰዱቃውያን፥ የሔሮድስ ወታደሮች፥ ቀራጮችና ጸሐፍት እንዲሁም ሕዝቡ ወደ

44

ኤልያስ ከጌታ ቀን በፊት በመምጣት የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፥ የልጆችን ደግሞ ወደ አባቶች ይመልሳል ተብሎ ተጽፎአል (ሚልክ 2፥6-7፤ 3፥1፤18፤ 4፥5)። ስለዚህም ዮሐንስ ይህን የኤልያስን አገልግሎት ሊፈጽም በስ መጣ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በመሢሑ ፊት እንደሚሄድ ተገልጾአል። ኤልሳዕ የኤልያስን መንፈስ እንደተቀበለ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሶአል (2ነገ 2፥9-15)። ሙጥ ምቁ ዮሐንስ ምንም እንኳን «በኤልያስ መንፈስና ኃይል» ቢመጣም እንደ ኤልያስ ደንቅና ተአምራትን አላደረገም። ነገር ግን እንደ ኤልያስና ኤልሳዕ በግልጽነትና በድፍረት ኃጢአትንና አመጸን

እርሱ ሲመጡ ባየ ጊዜ «እናንት የእፉኝት ልጆች[45]፥ ከሚመጣው ቁጣ እንድት ሸሹ ማን አመለከታችሁ? እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤ በልባችሁም — አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ፤ እላችኋለሁና ከነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሳለት እግዚአብሔር ይችላል።» እያለ ይገሰጻቸው ነበር (ማቴ 3፥7-8)።

ዮሐንስም በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ «እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃ ችኋለሁ፤ ከኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል ፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል፤» እያለ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አጥማቂነት በግልጽ በመንገር የሕዝቡን ልብ ለኢየሱስና ለመንፈስ ቅዱስ ያዘጋጅ ነበር (ማቴ 3፥11፤ ሉቃ 3፥16፤ ማር 1፥8፤ ዮሐ 1፥33)። ከዚያም በመቀጠል «መንሹም በእጁ ነው፥ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፥ ስንዴውንም በጎተራ ይከታል፥ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል።» በማለት የኢየሱስን አገልግሎትና ሥልጣን አመልክቶአቸዋል።

እዚህ ላይ እንደምንመለከተው ዮሐንስን ልዩ የሚያደርገው ነገር ቢኖር የነቢዩ መንገድን ጠራጊ ብቻ ሳይሆን ራሱም የብሉይ ኪዳን የትንቢት ፍጻሜ ስለ ነበር ነው (ኢሳ 40፥3-5፤ ሚልክ 3፥1፤ 4፥5)። ከዚያም ባሻገር ዮሐንስ የኢየሱስ ምስክር ነበር — ይህም ኢየሱስን በዮርዳኖስ ወንዝ ባጠመቀ ጊዜ ሰማያት ተከፍተው የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ርግብ ወርዶ በኢየሱስ ላይ ሲመጣና «በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» የሚል ድምጽ ከአብ ዘንድ ሲመጣ ተመልክቶአል፥ በኋላም ደግሞ የዚሁ እውነት ምስክር ሆኖ አል (ማቴ 3፥15-17፤ ማር 1፥9-11፤ ሉቃ 3፥21-23)።[46]

ሁሉ አየተታወሙና አየገሸጸ ሕዝቡን ወደ ንስሐ ጠራ። ከዚያም የሕዝቡን ልብ ለሚመጣው መሢሕ አዘጋጀ።
45

«የአፋኝት ልጆች» የሚለው አባባል በጣም ትልቅ ስድብን ያዘለ ቃል ነው። ምክንያቱም በጥንቱ ሜዲትራንያን አካባቢ እንደሚታመነው ከሆነ የአፋኝት ልጆች ሲወለዱ የእናታቸውን ማህፀን እየበሉ ስለሚወጡ እናታቸውን ይገድላሉ ተብሎ ነው። ስለዚህም እንድን ሰው «የአፋኝት ልጅ» ብሎ መጥራት «እናትና አባትህ ክፉ ሲሆኑ አንተ ደግሞ ከእናትህና ከአባትህ የባሰክ ክፉ ነህ» ደግሞም «ለመጪጅ አናትህ አንቧን የማትብጅ ነህ» ብሎ እንደ መሳደብ ያህል ነው የሚቆጠረው። — ከሬ ግ ኪነር፣ ማቴው (ዶውንርስ ግሮቭ፣ ኢንተርቫርሲቲ ፕረስ፣ 1997)79።
46

ዮሐንስ ሕዝቡን በውኃ ያጠምቅ የነበረው ስንስሐ ጥምቀት ነበር። እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባን ነገር ቢኖር የኢየሱስን ጥምቀት ከሉቃ ለየት የሚያደርገው ነገር ኢየሱስ ኃጢአትን ስላላደረገ ምን

እንግዲህ የዮሐንስ ጥምቀት የተመለከትን እንደሆነ ዋና ዓላማው ሕዝቡን ለሚመጣው መሢሕ ከዘጋጀና እርሱን ካሳያቸው በኋላ ለርሱ ቦታ ለመልቀቅ ነበር። ከመልቀቁም በፊት እርሱ መንገድን ያዘጋጀለት መሢሕ (ኢየሱስ ክርስቶስ) በርሱ እጅ ተጠመቀ። ስለሆነም የኢየሱስ አገልግሎት በዮሐንስ ጥምቀት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በግልጽ ተጀመረ። ዮሐንስም ሲመሰክር «እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል» (ዮሐ 3፥30) በማለት ለኢየሱስ ቦታውን መልቀቅ እንዳለበት ያመለከታቸው ተፈጸመ።

የኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት

መልአኩ ገብርኤል ስቅድስት ማርያም ተገልጦ የምትወልደው ልጅ በመንፈስ ቅዱስ የተፀነሰ መሆኑን ባበሰራት ጊዜ፥ መንፈስ ቅዱስ በርሱዋ ላይ እንደሚመጣና የልዑልም ኃይል እንደሚጸልላት ነግሮአታል (ሉቃ 1፥335)። አጨናዋ ዮሴፍ ደግሞ ማርገዙዋን ባወቀ ጊዜ በሰውር ሊተዋት አስቦ ነበር ፤ነገር ግን የጌታ መልአክ በሕልም ተገልጦለት የተፀነሰው ሕጻን በመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ነገረው (ማቴ 1፥20)። ይህም በነቢዩ የተጻፈው «እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል» የሚለው ይፈጸም ዘንድ ነው (ኢሳ 7፥14)።

ኢየሱስም ከተወለደ በኋላ እንደ ሙሴም ሕግ የመንጻታቸው ወራት በተፈጸመ ጊዜ፥ በጌታ ሕግ የእናቱን ማሕፀን የሚከፍት ሁሉ ለጌታ የተቀደሰ ይባላል ተብሎ እንደተጻፈ በጌታ ፊት ሊያቆሙት ወደ ኢየሩሳሌም ይዘውት መጡ (ዘጸ 13፥2፤12፤ ዘሌዋ 5፥11፤ 12፥8፤ ሉቃ 2፥24-25)። ይህ በንዲህ እንዳስ በኢየሩሳሌም ደግሞ ስምዖን የሚባል አንድ ሰው ነበር። ይህም ሰው የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር። መንፈስ ቅዱስም በርሱ ላይ ስለ ነበር

ም ዓይነት ንስሐ አያስፈልገውም ነገር ግን በመጠመቁ ራሱን ጌት አድርጎ ሕዝቡን መለስ፣ ወሊያው ም ጽድቅን ፈጸመ። ሮበርት ቶማስ ሰታንሊ ፕንድሪ ፤ ኤ ሃርመኒ ኦቭ ዘ ስፐንስስ (ሳንፍራንሲስኮ፣ ሃርፐርስ ሳንፍራንሲስኮ፣ 1978) 36 ፤ ኪነር፤ ዘ ሰርሪት ኢን ዘ ስፐንስስ ኢንድ ስስትስ I 65።

መሢሑን ሳያይ እንደማይሞት በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር። በመንፈስም ተመርቶ ወደ መቅደስ መጥቶ ኢየሱስን አየ፥ እርሱንም ከወላጆቹ ተቀብሎ በማቀፍ እግዚአብሔርን ባረከ (ሉቃ 2፥21-35)።

ሀ. በመንፈስና በእሳት አጥማቂው ኢየሱስ

መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመሰክር «እኔ በውኃ እጠም ቃችኋለሁ ነገር ግን የሚማውን ጠፍር መፍታት የማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ ይመጣል እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል።» (ሉቃ 3፥16፤ ማር 1፥8፤ ማቴ 3፥11) እያለ ይነግራቸው ነበር። እንግዲህ ከላይ እንደምናየው ሦስት ዓይነት ጥምቀቶች አሉ ማለት ነው፤ እነርሱም የውኃ፥ የመንፈስና የእሳት ጥምቀቶች ሲሆኑ ከዚህ በመቀጠል በዝርዝር እንመለከታቸዋለን።

1) *የውኃ ጥምቀት*

ይህ ዓይነቱ ጥምቀት ዮሐንስ እያጠመቀ የመጣው ዓይነት ነው። የዚህ ዓይነቱ የማንጻት ተግባር በአይሁዳውያኑ ዘንድ የተለመደ ሲሆን እነርሱም ሰዎችን ለማንጻት ኩሬዎችን ይጠቀሙ ነበር።[47] የኩምራንም ማኅበረሰብም ይህንኑ ዓይነት የማንጻት ተግባር ሰዎችን በውኃ በማጥመቅ ያከናውኑ ነበር።[48] አሕዛብም ደግሞ ወደ ይሁዲነት ሲለወጡ ከማኅበረ ምእመናኑ ጋር ከመቀላቀላቸው በፊት ማለትም ከግርዘት በተጨማሪ በውኃ መጠመቅ ነበረባቸው።[49] ነገር ግን የዮሐንስን ጥምት ከእነዚህ የሚለየው ነገር ቢኖር ጥምቀቱ ለሚመጣው መሢሕና ለመንግሥቱ የንስሐና ልብን የማዘጋጀ ጥምቀት ነበር እንጂ ወደ ምንም ዓይነት ሃይማኖት ውስጥ የሚያስገባ አልነበረም[50]። ለምሳሌ ያህል በዚያ ዘመን በመ

---

47 ያዲን፣ *መሳፍ* (ኒውዮርክ፤ ራንደም ሃውስ፣ 1966) 164፤ ፒርሴን፣ *ዘ ጺስትስ ኦቭ መሳፍ* (ኒውዮርክ፤ ስክራይብነርስ፣ 1967) 179።

48 ቢ. ኢ. ቲሪንግ፣ «ኢነር ኤንድ አውተር ከንሺንግ ኦት ኩምራን አዝ ኤ ባክግራውንድ ቱ ኒው ቴስታመንት ባፕቲዝም,» <u>ኤን ቲ ኢቭ</u> (1981) 615-631።

49 ኪነር፣ *ሰፒሪት ኢን ዘ ጎስፐልስ ኢንድ ኦክትስ* I 62።

በመሠረቱ የጥምቀቱ ዋና ዓላማ ሰዎችን በማዘጋጀት በመሢሑ እንዲያምኑና እርሱ ይዞት ወደ ጥምቁ የተጠመቁትን ሰዎች ብንመለድ ሁሉም ወደ ክርስትና ሲመጡ እንደገና በእብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ሰም መጠመቅ ነበረባቸው።

2) *የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት*

አብ መንፈሱን ይልካል፥ ዮሐንስም በተደጋጋሚ እንደ መሰከረው ኢየሱስ ሕዝቡን በመንፈስ ያጠምቃል ((ዮሐ 14፥7፤ ማር 1፥8)። መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ ወረደበት ጊዜ ኢየሱስ ሕዝቡን በመንፈስ እንደሚያጠምቅ አብ ለዮሐንስ ገልጸለታል (ማር 1፥10፤ ዮሐ 1፥33)። ኢየሱስም በዮሐንስ ጥምቀት ከተጠመቀ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ወደ ምድረበዳ አወጣው (ማር 1፥12)። አጥማቂው ራሱ በመንፈስ ተመርቶ ተፈተነ፥ ፈተናውንም በድል አሸንፎ ወጣ፥ በመንፈስም ኃይል ተሞልቶ ወደ ገሊላ ተመለሰ (ሉቃ 4፥14)። ኢየሱስ ሊያጠምቅ የቻለበትም ምክንያት የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ሲሆን በቃሉም ላይ «እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀበልን በጸጋ ላይ ጸጋተሰጥቶናልና» በማለት በርሱ በኩል ስለምናገኘው ባርኮት ይናገራል (ዮሐ 1፥16፤34)።

«የመንፈስ ቅዱስ» ጥምቀት የሚለው አባባል ሁለት ነገሮችን የያዘ ሲሆን፥ ይህም መንፈስ ቅዱስና ጥምቀት የሚሉትን ነው። ከታሪክ እንደምንረዳው አይሁዳውያኑ ወደ ይሁዲነት የሚገቡትን አሕዛብ በውኃ ያጠምቋቸው ነበር። ይህንንም የሚያደርጉት በውኃ ውስጥ በመንከር ነበር። ስለሆነም «ጥምቀት» የሚለው ቃል ሁለት አሳቦችን ያዘለ ነው፤ እነርሱም መለወጥ [Con version] እና መነከር [Imersion] የሚሉት ናቸው። ነገር ግን አዲስ ኪዳንን በአጠቃላይ ስንመለከት 1ኛ. በወንጌላት ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ማለት የጸጋ ስጦታ ሙላት ሲሆን 2ኛ. የጳውሎስ መልእክቶች ደግሞ መለወጥንም (መዳንን) ጭምር ነው የሚያሳዩት።[51] እንዲህም ሲሆን የቻለበት ምክንያት

መጣው መንግሥት እንዲገቡ ነው። ቢሆንም ቅሉ የዮሐንስ ጥምቀት የሕዝቡን ልብ ለሚመጣው መሢሕ በንስሃ ለማዘጋጀት ነበር እንጂ ወደ አንድ ሃይማኖት ውስጥ በቀጥታ የሚያስገባ አልነበረም (ለምሳሌ ወደ ይሁዲነት የሚለወጡት አሕዛብ እንደሚጠመቁት ዓይነት ማለት ነው)።

51 ጎርደን ዲ. ፊ፣ *ጎድስ ኢምፓወሪንግ ፕሬዘንስ፥ ዘ ሆሊ ሰፒሪት ኢን ዘ ሌተርስ ኦቭ ፖል* (ፒበዲ፤ ሄንድሪክሰን አሳታሚ ድርጅት፣ 1994) 1-36።

ምናልባት ጳውሎስ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው አናንያ እጁን በጫነበትና ጌታን በተቀበለበት ጊዜ አንድ ላይ በመሆኑ ሊሆን ይችላል (ሐዋ 9፥17)።

ከዚህም በመነሳት እንዳንዶቹ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ማለት የሕይወት ለውጥ ወይም ዳግም ውልደት ነው ይላሉ። ወይም በሌላ አነጋገር ሰዎች ጌታን ሲቀበሉ የሚሞሉት መንፈስ ነው ይላሉ። ሌሎች ደግሞ የለም የመንፈስ ጥምቀት ሰንል ከደህንነት የሚቀጥል ነገር ግን ከዚያ በኋላ የሚመጣ የጸጋ ስጦታ ሙላት ነው። ይህም ደግሞ የቅድስና ኃይል ስለሆነ በዘመናችን ሁሉ በጽድቅና በቅድስና እንድንኖር ያስችለናል ይላሉ። ይህም ከደህንነት ቀጥሎ የሚመጣው ባርኮት ጥብረ መንፈስ ቅዱስ ካልዕ [The second works of the Spirit] በመባል ይታወቃል[52]። ለማንኛውም ስለዚህ ነገር ወደ ፊት ባሉት ምዕራፎች ውስጥ በጥልቅ እንነጋገራለን።

3) የእሳት ጥምቀት

የእሳት ጥምቀት የሚለው አባባል ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ተለይቶ ቀርቦልናል። የምዕራፉን አገባብ [Context] ከተመለከትንና እንዲሁም የብሉይና የአዲስ ኪዳናት መጻሕፍት ትርጉም እንደሚያሳዩን ከሆነ ዮሐንስ ያሰጠነቅቅ የነበረው ስለሚመጣው የመጨረሻው የፍርድ ቀን ነበር። አርሱም ሲናገር «ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ»፥ እንደገናም «አርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል» ካለ በኋላ በመቀጠልም (ምንም እንኳን ሁለቱ ጥምቀቶች በተለያየ ጊዜ ወይም ባንድ ጊዜ ይፈጸሙ አይፈጸሙ ባይናገርም) «መንሹም በእጁ ነው፥ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፥ ስንዴውን በጎተራ ይከታል፥ ገለባውን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል።» ይላል (ማቴ 3፥8-12)።

52

ከላይ እንደተነጋገርነው ደህንነትና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንድ ላይ ይከናወናል ብለው የሚያምኑ ሰዎች ሁለተኛ ጊዜ የሚመጣ ባርኮት ወይም ጸጋ የለም ይላሉ። ነገር ግን በጸጋ ስጦታዎች የሚያምኑ ሰዎች ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከደህንነት የሚቀጥልና የተለየ አሠራር ነው ስለሚሉ ጥምቀቱም ሁለተኛው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ [ጥብረ መንፈስ ቅዱስ ካልዕ] ተባለ። ይህም ማለት ከመንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያው የደህንነት ሥራ (መለወጥ፥ መቀየር፥ በመንፈስ በሚሆን አዲስ አተያየትና ኅትመት፥ 2ተሰሎ 2፥13፤ ቲቶ 3፥5፤ ዮሀ 3፥8፤ ኤፌ 1፥13፤ 4፥30፤ 1ቆሮ 6፥11፤) ቀጥሎ የሚመጣ ባርኮት ነው።

እንግዲህ እዚህ ላይ «የማይጠፋ እሳት» የሚለው ስለሚመጣው የመጨረሻው ቀን ፍርድ የሚያሳይ ነው (ኢሳ 1፥31፤ 66፥24፤ ኤር 7፥20)።[53]


በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ እሳት ፍርድን ለማሳየት በብዙ ቦታዎች ተጠቅሶ እናገኛለን (መዝ 1፥4፤ ኢሳ 17፥13፤ 66፥15-16,24፤ ሆሴ 13፥3፤ ኢዩኤ 3፥13፤)። ኢየሱስም ራሱ በማቴዎስ 13፥39-43 ላይ በመጨረሻው የፍርድ ቀን እንከርዳዱ ማለትም ኃጢአተኞች ተለቅመው በእሳት እንደሚቃጠሉና በዚያም ጥርስ ማፋጨት እንደሚሆን ተናግሮአል። ዮሐንስም እንዲሁ እሳቱ የማይጠፋ ነው ሲል ኃይለኝነቱንና ዘላለማዊነቱን ተናግሮአል።

ነቢያቱም ደግሞ በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር መንግሥቱን ሲመሠርት መንፈስ ቅዱሱን እንደሚያፈስስ በመተንበይ (ኢሳ 44፥3፤ ሕዝቅ 39፥29፤ ኢዩ 2፥28)፤ እንደገናም እግዚአብሔር እሳቱን በኃጢአተኞች ላይ እንደሚያመጣ አስጠንቅቀዋል (ኢሳ 26፥1፤ 65፥15፤ 66፥24፤ ኤር 4፥4፤15፥4)። ስለዚህም እግዚአብሔር መንግሥቱን ሲመሠርት ሁለት ነገሮች ይከናወናሉ ማለት ነው — 1ኛ. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት 2ኛ. የእሳት ጥምቀት (የፍርድ ቀን የሚከናወን) ናቸው።

የእግዚአብሔር መንግሥት ደግሞ በኢየሱስ መምጣት ጎህ ቀደደ እንጂ ሙሉ ለሙሉ ተዘርግቶ አላበቃም [Cosummation]። ሙሉ ለሙሉ ተመሥርቶ የሚያበቃው የመንግሥቱ ንጉሥ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ዳግም ሲነግሥ በአካል በሚመጣበት ጊዜ ነው። ስለዚህም በዚያን ጊዜ የእሳት ፍርድ ይከናወናል ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ከወረደበት ቀን አንስቶ እስከ ምጽአቱ ድረስ ያለው ጊዜ ደግሞ የመጨረሻው ዘመን በመባል ይታወቃል። ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ስለላዊ መግለጫ እንመለከት—

53

ጆርጅ ላድ፥ ሉ ቲኦሎጂ ኦቭ ዘ ኒው ትስታመንት ሪቫይዝድ ኤዲሽን (ግራንድ ራፒድስ፥ ውልያም ኤርድማን፤ 1996)34።



በአሳዊ መግለጫ ቁ. 2

በተጨማሪም ደግሞ ነቢያቶች የፍርድን ቀን ከመከር መሰብሰብ ጋር ያመሳስሉታል (ኤር 51፥33፤ ኢዩ 3፥12-14)። ገበሬው እህሉን ሲወቃ ገለባውን ከእህሉ እንደሚለየው ሁሉ እግዚአብሔርም እንዲሁ ምርቱን ከገለባው ይለየዋል፥ በእሳትም ያቃጥለዋል። ስለሆነም ኃጢአተኞች ደግሞ እንደ ገለባ ሰለ ሚመሰሉ (ኢሳ 17፥13፤ ኤር 13፥24፤ 15፥7) በፍርድ ቀን ከጻድቃን ተለይተው ወደ እሳት እቶን ውስጥ ይጣላሉ። ይህንን ክፍል በተመለከተ አንዳንድ ሰዎች የእሳቱ ጥምቀት እግዚአብሔር ልጆቹን ለማጥራት የሚጠቀምበት ነው ብለው ያምናሉ።[54]

ነገር ግን አገባቡ እንደሚያሳየን ከሆነ የእሳት ጥምቀት የተለየ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም፤ ምክንያቱም በአይሁዳውያኑ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የትንቢትና የማንጻያ መንፈስ ነው ብለው ሲያምኑ፥ የእሳትን ጥምቀት ግን ከፍ

54

አንዳንድ ሰዎች የእሳት ጥምቀት እንደተከናወነ አድርገው ያስባሉ፤ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የሆኑት ዶ/ር ጆል ግሪን ስለ ሉቃስ ወንጌል በጻፉት ማብራሪያ መጽሐፋቸው የመንፈስ ጥምቀትና የእሳት ጥምቀት ጥንድ ጊዜ ሊከናወን የሚችል ነገር አድርገው አቅርበውታል። እንዴት ሁለቱ ጥምቀቶች ጥንድ ጊዜ ሊከናወኑ ይችላሉ ለሚሉት ጥያቄዎች የርሳቸው መልስ ግን በጥምቀቱ እግዚአብሔር በመንፈሱ ኃይልን ሲሰጥ በእሳቱ ደግሞ ያጠራል ብለው ያምናሉ። ነገር ግን የክፍሉ አገባብ እንደ ሚያሳየንና አብዛኛው የአዲስ ኪዳን ምሁራንና በተለይም ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ዋናት ታዋቂ የሆኑት እንደነ ዶ/ር ጎርደን ፊ፣ ዶ/ር ጀምስ ደን፣ ዶ/ር ክሬግ ኪነር እንዲሁም ሌሎች ያልጠቀስኳቸው ጠበብት እንደሚስማሙበት ከሆነ የመንፈስ ጥምቀትና የእሳት ጥምቀት የተለያዩ መሆናቸውን ነ

ርድ ጋር ነው የሚያይዙት[55]። እግዚአብሔር ልጆቹን ከኃጢአትና ከበደል ሊያነጻ ያዘጋጀበት መንገድ በልጁ ደም ነው። ስለዚህም መጥምቁ ዮሐንስ ራሱ ኢየሱስን ባየው ጊዜ «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስተሰርይ የእግዚአብሔር በግ» (ዮሐ 1፥29) በማለት መናገሩ — 1ኛ. የኃጢአት ይቅርታ የሚሰጠውና የሚያነጻው የኢየሱስ ደም መሆኑን 2ኛ. በቅድስና በጽድቅ እንድንኖር የሚያደርገን ደግሞ መንፈስ ቅዱስ እንጂ የእሳት ጥምቀት አለመሆኑን ለመረዳት ያስችለናል (ለእግዚአብሔር በመለየት ኃይልን እየሰጠን፥ የመንፈስን ፍሬ አፍርተን ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀን እንድንሆን ያስችለናል)።

ለዚህም ዋሩ መረጃ ሆኖ ሊቀርብ የሚችለው መጥምቁ ዮሐንስ በእስር ቤት በነበረበት ጊዜ መልእክተኞችን ወደ ኢየሱስ በመላክ የሚመጣው መሢሕ እርሱ እንደሆነና እንዳልሆነ ለማወቅ መፈለጉ ነው። ከዚህ እንደምንረዳው ዮሐንስ የሁለቱን ጥምቀቶች ጊዜያት በውን ያወቀ አይመስልም (ማለትም ኢየሱስ ዳግም እንደሚመጣ አያውቅም ነበር ለማለት ይቻላል)። ስለዚህም ከአብ ምስክርነትን የተቀበለውና እርሱ ራሱ የመሰከረለትና ያጠመቀውን መሢሕ «የሚመጣው አንተ ነህ ወይስ ሌላ እንጠብቅ» (ማቴ 11፥2-3) ብሎ መጠየቁ ጠበቅ ያለ ምክንያት እንዳለው አያጠያይቅም። ኢየሱስ ወዲያውኑ መንግሥቱን በምድር መሥርቶ ኃጢአተኞችን፥ ተቃዋሚዎችንና ሮማውያንን በእሳቱ አጥምቆ ለእስራኤል መንግሥትን የሚመልስ ሳይመስለው አልቀረም[56] (ከኢየሱስ ጋር ከሦስት ዓመት በላይ አብረውት የነበሩት ደቀመዛሙርት እንኳን የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ነበራቸው፥ ሉቃ 19፥11፤ 21፥7፤ ሐዋ 1፥6)። ነገር ግን ኢየሱስ ይህንን ሲያደርግ ሰላላየው (የሰው ልጅ ሊኮንን አልመጣምና፥ ዮሐ 3፥17) ነገሩን ለማጣራት ሲል መልእክተኞችን በመላክ «የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ

ው። ጆል ግሪን፥ *ዘ ጎስፔል ኦቭ ሉክ* (ግራንድ ራፒድስ፥ ውልያም ኤርድመን አሳታሚ ድርጅት፤ 1997) 180-181።

55 ጂምስ ደን፥ *ባፕቲዝም ኢን ዘ ሆሊ ስፒሪት* (ናፐርቪል፥ ኤስ ሲ ኤም ፕሬስ፤ 1970) 12።

56

አይሁዳውያኑ የእስራኤልን መንግሥት መመሥረት የሚያበሰሩትን የብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች በመመርኮዝ እግዚአብሔር በመሢሑ በኩል መንግሥትን ለእስራኤል በመመለስ በዘላለም ተዘልለን እንድንቶ መኖ ያስችለናል ብለው ያምኑ ነበር። ስለዚህም የመሢሑ መምጣት የእስራኤል መንግሥት የነጻነት ና የብልጽግና ዘመን የሚመጣበት ጊዜ እንደሆነ ያስባሉ (ኤር 16፥15፤ 23፥8፤ 50፥19፤ ሆሴ 11፥11 ፤ ኢዩ 3፥17)። — ዊልያም ላሮኒን ፥ *ኢንሳይድ ቪው ኦቭ ሰንስ* (ዶውነርስ ግሮቭ፥ ኢንተርቫርሲቲ ፕሬስ፤ 1995) 40።

ሌላ እንጠብቅ?» በማለት እንደጠቀው እናያለን (ማቴ 11፥2-6፤ሉቃ 7፥18-23)።[57]

ኢየሱስ ራሱ ወደ አብ ከማረጉ በፊት ለደቀመዛሙርቱ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡና ከርሱ የሰሙትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል እንዲጠብቁ ካዘዛቸው በኋላ እንዲህ በማለት ተናገራቸው – «ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ...መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ።» (ሐዋ 1፥5፤ 8)። እዚህ ላይ እንደምንመለከተው ኢየሱስ የዮሐንስን ጥምቀት ከጠቀሰ በኋላ የሚጠመቁት በአንዱ ዓይነት ጥምቀት ብቻ መሆኑን ነግሮአቸዋል — እርሱም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። በማይጠፋው እሳት እንደሚጠመቁ ግን አልነገራቸውም ምክንያቱም የርሱ ዓይነት ጥምቀት እርሱን ላልተቀበሉት (ለገለባው) የተዘጋጀ የመጨረሻው ቀን ፍርድ ነውና።

ስለሆነም ከዮሐንስ ትንቢት የምንረዳው ይህን ይመስላል — የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች። ይህችም መንግሥት 1ኛ. ያመኑትን ስሰማያዊ ባርኮት ትሰበስባለች (የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው) 2ኛ. ያላመኑትን ደግሞ ለእሳት ፍርድ (ለእሳት ጥምቀት) ትሰበስባለች (ይህም የሚሆነው ኢየሱስ ዳግም ከመጣ በኋላ በፍርድ ቀን የሚከናወን ነው)።

ለ. ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ

ኢየሱስ አገልግሎቱን በግልጽ የጀመረው በውኃ ተጠምቆ በመንፈስ ቅዱስ ከተቀባ በኋላ ነበር (ማር 1፥10-11፤ ሉቃ 3፥21-23፤ 4፥17-19፤ ዮሐ 1፥31-32፤ ኢሳ 61፥1-2)። ሐዋርያቱም የኢየሱስ አገልግሎት ከዮሐንስ ጥምቀት (በዮሐንስ ከተጠመቀበት) ጀምሮ እስከ አረገበት ድረስ እንደሆነ ተረድተውታል (ሐዋ 1፥21)። ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም እንኳን ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ቢሆንም በመንፈስ ቅዱስ መቀባትና መደገፍ ነበረበት። ምክንያቱም ለአባቱ በነበረው ፍጹም ፍቅርና መታዘዝ የሰውን ሥጋ በላዩ በመደረብ ራሱን አዋርዶ ሰው ሆኖ ስለመጣ ነው (ፊል 2፥5-8)። ስለዚህም ምንም እንኳን አምላክነቱ

57

ጆርጅ ላድ፣ ኤ ቲኦሎጂ ኦቭ ዘ ኒው ቴስታመንት ረቫይዝድ ኤዲሽን (ግራንድ ራፒደስ፡ ውልያ

ከርሱ ጋር ቢሆንም በአባቱ ላይ ፍጹም መደገፍ ነበረበት፤ ይህንንም የሚያደረገው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነበር። ይህንንም መንፈስ እግዚአብሔር አት ረፍርፎ ሰጥቶታል፥ እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ ስለጂ አይሰጥምና (ዮሐ 3፥34)።

በአብ ላይ ስለመደገፍ አስመልክቶ ኢየሱስ ሲናገር ከአባቱ ከሚያየውና ከሚሰማው በስተቀር ከራሱ አንዳች እንደማያደርግ ከገለጸ በኋላ (ዮሐ 5፥19፤ 7፥16፤ 8፥28-29፤ 10፥37-38፤ 12፥49) የላከውን ፈቃድ ስመፈጸም እንጂ ራሱን ሊያስደስት እንዳልመጣ ግልጽ አድርጎ ተናግሮአል (ዮሐ 5፥30፤ 6፥38)። ራሱን በማዋረድ ሰው ሆኖ በመምጣቱ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከአባቱ በሚያገኘው መመሪያ መሠረት የተሰጠውን ተልእኮ በሚገባ ሊያከናውን ችሎአል (ዮሐ 17፥4)።

ኢየሱስ በመንፈስ የተሞላ ብቻ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ሙሉ ለሙሉ የተመራም ነበር (ማቴ 4፥1፤ ሉቃ 4፥1)። በመንፈስ ቅዱስም ኃይል ታላላቅ ድንቅና ተአምራትን አድርጎአል፣ ደዌና ሕማምን ሁሉ እየፈወሰ በአጋንንት የታሰሩትን እየፈታ በኃይልና በሥልጣን ያስተምር ነበር። ተአምራቱንም ያዩት ሕዝብ ታላቅ ነቢይ ተነስቶአል በማለት አንዳንዶቹ ዮሐንስ ከሞት ተነስቶአል ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ ኤልያስ ተገለጠ ሌሎቹም – ከቀደሙት ነቢያት አንዱ ተነስቶአል ይሉ ነበር (ሉቃ 9፥7-9)።

ም ኤርድመን አሳታሚ ድርጅት፤ 1996) 35።

ከዚህ በታች ኢየሱስ የሠራው ተአምራት ኤልያስና ኤልሳዕ ከሠሩት ጋር በማነጻጸር እንመለከታለን —

ኤልያስ	ኤልሳዕ	ኢየሱስ
የመበለቱዋን ልጅ ከሞት አስነሥቶአል 1ነገ 17፥17-24	የሱናማዊቱዋን ልጅ ከሞት አስነሥቶአል 2ነገ 4፥34-37	የመበለቱዋን ልጅ ከሞት አስነሥቶአል ሉቃ 7፥11-17
ምግቡን አትረፈረፈው 1ነገ 17፥13-16	ምግቡን አትረፈረፈው 2ነገ 4፥42-44	ምግቡን አትረፈረፈው ሉቃ 9፥10-17
ወደ አሕዛብ ተላከ 1 ነገ 17፥8-16	አሕዛብን ፈወሰ 2ነገ 5፥1-14	አንደነ ኤልያስና ኤልሳዕ ወደ አሕዛብ እንደሚዞር ተናገራቸው ሉቃ 4፥23-27፤ 5፥12

ሰላሳዊ መግለጫ ቁ. 3

ኢየሱስ የመሪነት ባሕርይው እንደ ሙሴ ነው፤ — ሙሴ ሕዝቡን ከግብፅ ባርነት አውጥቶ በምድረበዳ በድንቅ ታምራት እንደመራ ሁሉ፥ ኢየሱስም እንዲሁ ሕዝቡን ከኃጢአትና ከሰይጣን ባርነት ነጻ አውጥቶ ወደ አዲሲቱዋ ኢየሩሳሌም ይመራል። ሙሴ በምድረበዳ ለሕዝቡ እግዚአብሔር «እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፤ እርሱንም ታደምጣለህ።» ብሎ ተናግሮአቸው ነበር (ዘዳግ 18፥15)። ኢየሱስም ደግሞ ሙሴ የተናገረው ስለ እርሱ እንደሆነ ጠቅሶአል (ዮሐ 5፥45-47)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ዮሐንስን፥ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ይዞአቸው ወደ ረጅም ተራራ በወጣ ጊዜ ሙሴና ኤልያስ ተገልጠውላቸው ነበር። በዚያን ጊዜም ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር፤ ድምጽም ከሰማይ መጣ «በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት» አለ (ማቴ 17፥1-8፤ ማር 9፥7፤ ሉቃ 9፥35፤ ዘዳግ 18፥15)። ይህ የሚያሳየን ኢየሱስ ልክ እንደ ሙሴ፥ ኤልያስና ኤልሳዕ በጸጋ ኃይል የተሞላ (ካሪዝማቲክ) መሪ እንደሆነ ነው።[58]

ሐ. መንፈስ ቅዱስን መሳደብ

(ሉቃ 11፥17-18፤ ማቴ 12፥15-37፤ ማር 3፥20-30)

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ ወደ ገሊላ በመጣ ጊዜ ሰዎችም ሁሉ ይከተሉት ስለር። ፈሪሳውያኑም እርሱን በመቃወም ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እርሱን ተከትለው ወደ ገሊላ መጡ። ሕዝቡም ጋኔን ያደረበትን አውርና ዲዳ የሆነውን ልጅ ወደ እርሱ እንዲፈውሰው አመጡት፤ ኢየሱስም ሙሉ ለሙሉ ፈወሰው። ሕዝቡም ተገርመው «እንኳ ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆንን?» አሉ። መሢሑ የሚመጣው ከዳዊት ዘር ነው ተብሎ ስለሚጠበቅ «የዳዊት ልጅ» የሚለው አባባል መሢሕ ስማለት ነው የሚጠቀሙበት።

እንግዲህ ፈሪሳውያኑም «የዳዊት ልጅ» የሚለውን በሰሙ ጊዜ ተበሳጩ፥ ይህ በብዔልዜቡል[59] በአጋንንት አለቃ ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም አሉ። እንደሚታወቀው ሁሉ የዚህ ዓይነቱ ክስ በሙሴ ሕግ መሠረት የሞት ፍርድ የሚያመጣ ክስ ነው።[60] ኢየሱስም መልሶ ሰይጣን እንዴት ራሱን እየተቃወመ ሊሠራ ይችላል? ካለ በኋላ እርስ በርሱዋ የምትለያይ መንግሥት ሁላ እንደምትጠፋ በመንገር ርስ በርሱ የሚለያይ ከተማም ሆነ ቤት አይቆምም (ማቴ 12፥26) በማለት አፋጠጣቸው።

እንደገናም በመቀጠል «እኔስ በብዔልዜቡል አጋንንትን የማወጣ ከሆንኩ

---

58 ሮጀር ስትሮንስታንድ፥ *ዘ ካሪዝማቲክ ቴሎሎጂ ኦቭ ሉንት ሉክ* (ፒዐዲ፣ ሄንድሪክሰን አሳታሚ ድር ጅት፤ 1994) 44-45።

59 ኤፍ ኤፍ ብሩስ፥ *ሃርድ ሴይንግስ ኦቭ ጀሰስ* (ሾውነርስ ፕሮቭ፥ ኢንተርቫርሲቲ ፕረስ፤ 1983) 89። ብዔልዜቡል ዓንድ ወቅት የከነዓናውያን አማልዕክት ስም ነበር ትርጉሙም «የተከበረ ጌታ» ማለት ሲሆን አይሁዳውያኑ ደግሞ ይህንን ቃል «የአጋንንት አለቃ» ለማለት ይጠቀሙበታል። ምክንያቱም የአሕዛብ አምላክ ጣዖታት ናቸው። እንደሚታወቀው ከማንኛውም ጣዖት በስተጀርባ አጋንንት አሉ ምክንያቱም የአሕዛብ አምላክ ሰይጣን ስለሆነ ነው።

60 ደን፥ *ጀሰስ ኤንድ ዘ ሰፒሪት* (ለንደን፣ ኤስ ሲ ኤም፤ 1975) 53። ጆን ማየር፥ *ማቲው፣ ኑው ቴስታመንት ሜሲጅ* (ዊሊንግተን፣ ግይክል ፕሴዘርፐ 1980) 134 ፥ ኪነር፤ *ማቲው* I 230።

ልጆቻችሁ በማን ያወጡዋቸዋል? ስለዚህ እነርሱ ፈራጆች ይሆኑባችኋል» በማለት ከብሎቹን ሰንጣቃ እንጨት ውስጥ አስገባቸው። ምክንያቱም በእስራኤል አገር ብዙ አስማተኞች አጋንንትን እናወጣለን በማለት ይታወቃሉ ወይንም ሕዝቡን ያታልላሉ። ስለዚህም ኢየሱስን በአጋንንት አለቃ ነው አጋንንትን የሚያወጣው ካሉ ሌሎቹንም አጋንንት እናወጣለን የሚሉትን አጋንንት አለባችሁ ማለታቸው ስለሆነ እንዳይወግሩአቸው ሕዝቡን ፈሩ። ኢየሱስም በመመለስ «እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ ወይም ጣት አጋንንትን የማወጣ ከሆንኩ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቀርባለች ማለት ነው» በማለት የእውነትን ቃል አበሰረላቸው።

ከዚያም በመቀጠል ኢየሱስ በሰይጣን ላይ ኃይል እንዳለው ከነገራቸው በኋላ ለእስራኤል መሪዎች ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ማስጠንቀቂያ ተናገረ — «ስለዚህ አላችኋለሁ፥ ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል፥ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ስለደበ አይሰረይለትም። በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሰረይለትም።» (ማቴ 12፥31-33፤ ማር 3፥27-30)።

እንደሚታወቀው ሁሉ ኢየሱስ የተፀነሰው፥ የተቀባውና አገልግሎቱ የጀመረው እንዲሁም ታምራትን በማድረግ መሢሕ /የዳዊት ልጅ/ መሆኑን ያረጋገጠበት ወይም ሊሕገሙ ያሳወቀበት በመንፈስ ቅዱስ ነው። ስለሆነም የኢየሱስን እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅነትና የእግዚአብሔር መንግሥትን ይዞ መምጣቱን ያበሰረውን መንፈስ ቅዱስ መሳደብና መቃወም የኢየሱስን መሢሕነትና የሳከውን አብ መቃወም፥ እንዲሁም እርሱ ይዞት የመጣውን የምሥራች ወንጌል ውድቅ ማድረግ ነው።[61] እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባን ነገር ቢኖር መሳደብ የሚለው ቃል በግሪኩ «*ብላስፌሚኦ (ብላስፌሚያ)*» ሲሆን ትርጉሙም ስም ማጉደፍ፥ ስም ማጥፋት፥ ሃሜትና ዝናን ማጉደፍ ነው[62]። ስለዚህም ይህ የሚያሳየን

61

ውልያም ሌን፥ *ዘ ጎስፔል አኮርዲንግ ቱ ማርክ* (ግራንድ ራፒድስ፥ ኤርድመን አሳታሚ ድርጅት፤ 1974) 145። ብሩስ፥ *ሃርድ ሲዩንግስ ኦቭ ጀሱስ* ፤ 92።

62

ዎልተር ባወርስ፥ *ኤ ግሪክ-ኢንግሊሽ ለክሲከን ኦቭ ዘ ኒው ቴስተመንት* (ቺካጎ፥ ዘ ዩኒቨርሲቲ ኦቭ ቺካጎ ፕረስ፤ 1979) 142-143.

ከጥላቻ የመነጨ ወይንም የመጣ እግዚአብሔርን መሳደብ፥ ዝናውን (እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን) ማጉደፍና መቃወምን ነው እንጂ የመንፈስ ቅዱስ ሥራን ከመጠራጠር ወይንም ካለመረዳት የመጣ አሉታዊ ምላሽን አይደለም።

የእግዚአብሔርን መንግሥት መምጣት ያበሰረውን መንፈስ ቅዱስ የማይቀበል ኢየሱስን የማይቀበል ነው። ኢየሱስን ደግሞ የማይቀበል የላከውን አብን የማይቀበል ነው (ማቴ 10፥40)። ስለዚህም የአይሁድ መሪዎች በቅናትን በጥላቻ በመነዳት አሰበውበትና መክረውበት የሚያድነውን፥ በልጁ የተገለጸውንና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እውን የሆነውን የእግዚአብሔር ጸጋና ምህረ ከራሳቸው ጣሉ። በዚህም ምክንያት ለኃጢአታቸው ፈውስን አጡ። ምክንያቱም ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ ልጁ የሌለው ግን ሕይወት የለውምና ነው (1ዮሐ 5፥10-12)።

በመጨረሻም ከዚህ መገንዘብ ያለብን ነገር ቢኖር አንዳንድ ሰዎች በቤተክርስቲያናችን የሚደረገውን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ስለአልተቀበሉ ወይም ስለተቃውሞ የኃጢአት ይቅርታ አያገኙም ብለን መደምደም የለብንም። እንደሚታወቀው ሁሉ ሰዎች በተለያየ ምክንያት በተለይ ደግሞ ባንዳንድ ቦታዎች የሚያዩትን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ለመቀበል ይቸገራሉ። የማይቀበሉበትም ምክንያት ምናልባትም የበሀተትን አመራር በመፍራት ሊሆን ይችላል፤ ወይም አንዳንዶቹ ደግሞ ጥሩ የሆነ መረዳት ሳያገኙ ቀርተው ሊሆን ይችላል። ስለዚህም በነርሱ ላይ የፍርድን ቃል ከመስንዘራችን በፊት ለምን መንፈሳዊውን እንቅስቃሴ ሊቀበሉ እንዳልቻሉ ለመረዳት ብንሞክር በብዙ መንገድ ልንጠቅማቸው እንችላን።

ነገር ግን አንድ ሰው በኢየሱስ ስም የሚደረገውን ተአምራትና ድንቅ እያየ «ኢየሱስ አምላክ አይደለም። በርሱ ውስጥና በእናንተ የሚሠራው መንፈስ የሰይጣን ነው» በማለት እግዚአብሔርን በመጥላት ተነሳስቶ ቢሳደብና ቢቃወም ልጁንና የደህንነቱ ወንጌል አክፋፍቶ ጥሎአልና ለኃጢአቱ ፈውስ የለውም። ምክንያቱም ልጁ የሌለው የዘላለም ሕይወት አይኖረውምና ነው።

መ. ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ያስተማረው

(ይህ ምልክት ይከተላቸዋል)

ኢየሱስ በማርቆስ ወንጌል ላይ በርሱ የሚያምኑ ሁሉ ተአምራትና ድንቅ እንደሚያደርጉ ተናግሮአል። ይህም ተአምራት የሚደረገው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑንም ገልጸታል። በዚህም መሠረት በርሱ ያመኑት በስሙ አጋንንት ያወጣሉ፥ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥ የሚገድልንም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፥ እንዲሁም በድውዮች ላይ እጃቸውን ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ (ማር 16፥17-20)። እግዚአብሔር እነዚህን ሰጦታዎች ለአማኞች የሰጠበት ምክንያት የልጁን የደህንነት ወንጌል ለማሰፋፋት ነው። ይህንን ከፍል ያነበቡ አንዳንድ ሰዎች «እምነት ካላችሁ እባብ ያዙና ወይንም መርዝ ጠጡና አሳዪን» በማለት በአማኞች ላይ የፌዝን ቃል ሲሰነዝሩ ይታያሉ። እኛም ደግሞ የነርሱን ቃል ወስደን እባቡንም የማንይዝበትና መርዙን የማንጠጣበት ምክንያት እግዚአብሔርን መፈታተን እንደማይገባን ጌታችን ኢየሱስ ስለሚያስተምረን ነው (ማቴ 4፥7፤ ሉቃ 4፥12)።

እንደ እውነቱ ከሆነ ኢየሱስ እነዚህን ሰጦታዎች የሰጠን የእምነታችን መለኪያ ወይንም መመዘኛ መሳርያ አድርገን እንድንጠቀምባቸው አይደለም። ነገር ግን ወንጌል ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብሮ ስለታደለን የምሥራቹን ለፍጥረት ሁሉ ስናበስር የእግዚአብሔር ኃይል አብሮን ይወጣል፥ ሰዎችንም እየወቀሰ ወደ ደህንነት ያመጣቸዋል (ሮሜ 1፥16፤ ዕብ 2፥4)። አብሮንም ስለሚወጣ የጠላትን ኃይልና የሞትን ደጃፍ ሁሉ እየሰባበረ በሕይወታቸው ሁሉ ስለሞት ፍርሃት በባርነት ታስረው የነበሩትን አርነት ያወጣል (ዕብራ 2፥14-15፤ ቆላ 1፥20፤ 2፥14-15፤ 1ቆሮ 15፥55-57፤)።

ሠ. ኢየሱስና ኒቆዲሞስ

(ዮሐንስ ምዕራፍ ሦስት)

ከፈሪሳውያን ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበር። ይህም ሰው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ያደረጋቸውን ድንቅና ተአምራት ካየ ወይም ከሰማ በኋላ በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጣ። ኒቆዲሞስም ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣ ነገረው (ዮሐ 2፥13-25)። ኢየሱስ ግን መልሶ «እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በሰተቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» አለው። ኒቆዲሞስን የሚያህል የአይሁድ መምህር «የእግዚአብሔር መንግሥትና ዳግም ልደት» የሚለውሱትን ቃላት ሊረዳ ያልቻለበት ምክንያት በወቅቱ በነበረው በአይሁዳውያኑ የሥነመለኮት ትምህርት መሠረት የእግዚአብሔር መንግሥት የምትመጣው በሙታን ትንሣኤ ጊዜ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነበር።[63]

ስለዚህም ኒቆዲሞስ እንዴት ከሽምግልና በኋላ ዳግም ውልደት ይኖራል? በማለት ግራ መጋባቱን አሳየ። ኢየሱስም መልሶ «እውነት እውነት እልሃለው ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» አለው። በመቀጠልም «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ፥ ነው ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው ... ነፋስ ወደ ሚወደው ይነፍሳል ድምጹንም ትሰማለህ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንደሚሄድ አታውቅም» በማለት በሰው ልጅ ሞት ምክንያት ዳግም ውልደትን አውን አድርጎ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያሰገባው የእግዚአብሔር መንፈስ መሆኑን ነገረው።

አንዳንድ የአዲስ ኪዳን ምሁራን ሲናገሩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ጠንቅቆ ለሚያውቅ እንደ ኒቆዲሞስ ላለ መምህር«ከውኃና ከመንፈስ» የሚለው አባባል የሕዝቅኤልን ትንቢት ያስታውሰዋል ይላሉ። ይህም — «ጥሩ ውኃን አረጭባችሁአለሁ አናንተም ትጠራላችሁ... አዲስንም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ» (ሕዝቅ 36፥25-27) የሚለው ነው[64]። እንግዲህ የኢየሱስ መልእክት ምንድነው ቢባል — የሃይማኖት ሰው ብቻ መሆን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አያስገባም። የሚያስገባው ዳግም መወለድ (የሕይወት ለውጥ) ሲሆን ይህም ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ የታጠበ፥ ያቆጠቆጠ፥ የተቀደሰና የተለወጠ [Regenerate] ሕይወት ነው የሚለው ይሆናል።[65]

እዚህ ላይ ደግሞ «ከውኃ መወለድ»ና «ከመንፈስ መወለድ» የሚለው አባባል የተመለከትን እንደሆነ ሁለቱም የመንፈስ ቅዱስን የማንጻትና የመለወጥን

---

[63] ብሩስ፥ *ዘ ጎስፔል ኦቭ ጆን* (ግራንድ ራፒድስ፥ ኤርድመንስ አሳታሚ ድርጅት፤ 1983) 83።
[64] ከሬግ ኪነር፥ *ዘ ሰፒሪት ኢን ዘ ጎስፔልስ ኢንድ አክትስ፤* 151።

ሥራ ያሳየናል። በዚሁ መንገል ውሰጥ በምዕራፍ ሰባት ከቁጥር ሰላሳ ሰባት እስከ ሰላሳ ዘጠኝ ድረስ ያለው ቃል መንፈስ ቅዱስን በውኃ ሲመስለው እንመለ ከታለን። በተጨማሪም የምንመለከተው ነገር መንፈስ ቅዱስ በነፋስ ተመስሎ መቅረቡ ነው — «ነፋስ ወደ ሚወድደው ይነፍሳል» በማለት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሰው ጥበብና እውቀት የሚለካና የሚወሰን ሳይሆን በራሱ መለኮታዊ ፈቃ ድ፣ ጥበብና መንገድ እንደሚሠራ ይናገራል።

ረ. ኢየሱስና ሳምራዊቱዋ ሴት

(ዮሐንስ ምዕራፍ አራት)

ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ ከይሁዳ ወደ ገሊላ ሲሄዱ የሳምራውያን መን ደር በደረሱ ጊዜ ኢየሱስ ደክሞት ስለነበር በያዕቆብ ጉድጉዋድ አጠገብ አረፍ አለ፤ ደቀመዛሙርቱ ግን ምግብ ሊገዙ ወደ ከተማ ሄዱ። በዚህን ጊዜ ነው ከሳ ምራዊትዋ ሴት ጋር የተነጋገረው። ንግግራቸውም የተጀመረው በኢየሱስ አነሳሽ ነት ሲሆን፣ ርሱም «ውኃ አጠጪኝ» አላት። እርሱዋ ግን መልሳ «አንተ የይ ሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠዋ እንዴት ትለምናለህ?» አለችው፤ አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና።[66] እርስ በርስ አለ መግባባታቸውና ጠባቸው እንዳንድ ጊዜም ወደ ጦርነት ይመራቸው እንደነበረ ጆሲፈስ ገልጸታል።[67]

[65] ኪነር፡ *// ስፔሪት ኢን // ንስፐልስ ኤንድ ለስትስ* ፤151።

[66] ሰማርያውያን የኢይሁድና የእስዛብ ድብልቅ ደም ያላቸው ናቸው። ይህም የሆነው በ721(2) ዓዓ ሶር ያውያን የሰዜኑን ግለትም የእስራኤልን መንግሥት ወረው ከያዙ በኋላ የተወሰኑትን ነዋሪዎች በማፍ ለስና በምትኩ የራሳቸውን ሰዎች በማምጣት ሰፈራ ስላዜዱ። በዚህም ምክንያት የእይሁዳውያን ዘር ከሶርያውያን ጋር ተደባለቀ። እነዚህ ድብልቅ ዘር ያለባቸው ሰዎች ሰማርያውያን በመባል ይታወቃ ሱ። ሰማርያውያንም በእይሁዳውያን ዘንድ ተቀባይነት ስላጡና አንዳንድ የአምነት ልዩነት በመከሰላ ቸው ስለነበረ በ400 ዓዓ ገደማ ላይ የራሳቸው የሆነ ቤተ መቅደስ በገሪዜም ተራራ ላይ ሥሩ። እነር ሱም ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውሰዋ አምስቱን የኦሪት (የፔንታቱክ) መጻሕፍት ብቻ ሲቀበሉ ሌሎ ቹን መጻሕፍት አይቀበሉም ነበር። በ108 ዓዓ ሳይም አይሁዳውያኑ ጆን ሂርካነስ በሚባል ሰው መሪነ ት ይህንን ቤተ መቅደስ አፈረሱት። ስለዚህም በዚህና በተለያየ ምክንያት አይሁድና ሰማርያውያን አይተባበሩም ነበር። የበለጠ ማብራሪያ የሚፈልግ ሰው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መጽሐፍ ማንበብ ይችላል፤—

ዴቪድ ዶብ፡ *// ሂው ቴስተመንት ኤንድ ፊዚኒክ ጁዳይዝም* (ለንደን፡ 1956) 382።

[67] ጆሲፈስ፡ ጄዊሽ ዎር (2.232-240)፤ አንቲከዩቲ (20.118-136)።

ኢየሱስም መልሶ «የእግዚአብሔርን ስጦታና ውኃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑንስ ብታውቂ እንቺ ትለምኚው ነበርሽ የሕይወትም ውኃ ይሰጥሽ ነበር» አላት። የእይሁድ መምህራን በመጨረሻው ዘመን ከአዲሲቱዋ ኢየሩሳ ሌም ውኃ ይፈስሳል ብለው ያምኑ ስለነበር[68] አባባሉ የእግዚአብሔር መንግሥት መቃረቡን ያመለክታል፤ ይህም ውኃ መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህ «የሕይወት ውኃ» ንጹህ፣ ትኩስና ሕይወትን የሚሰዋ ሲሆን ንጹህነቱ ደግሞ የሚጠቅመው ለማንጻትና ለመቀደስ ነው።[69]

እንደገናም «ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደገና ይጠማል፤ እኔ ከምሰ ጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆ ናል» (ቁ. 14) አላት። በኤርምያስም ላይ የእስራኤል አምላክ «ሕያው ውኃ ምንጭ» እንደሆነ ተጠቅሶ እናገኛለን። ስለሆነም የኢየሱስ መልእክት ለሰማር ያዊቱዋ ሴት — እኔ የምሰዋሽ መንፈስ ይቀድስሽና ሕይወት ይሰዋሻል፤ የዘላለ ም የሕይወት ውኃ ምንጭ ስለሆነም መንፈሳዊ ጥማትሽን ያረካልሻል። ከእን ግዲህ ወዲህ በገሪዜምም (የሰማርያውያን ቤተመቅደስ የሚገኝበት ቦታ) ሆነ በኢ የሩሳሌም ለአብ ለመስገድ መሄድ አያስፈልግሽም። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ በእውነትና በመንፈስ እንድታመልኪው ያደርግሻል ብሎ እንደ ማለት ነው።

ሴቲቱ ኢየሱስን «አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ እናንተም – ሰው ሊሰግድለት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ» አለችው። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላት «እንቺ ሴት አመኚኝ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል። እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን። ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣ ል፤ አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደእነዚህ ያሉትን ይሻልና። እግዚ አብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባ ቸዋል።» እርሱ የሚሰጠው ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ ውኃ ምንጭ ስለ ሆነ አምልኮው ሁሉ በዐታና በጊዜ የተወሰነ አይደለም። ምክንያቱም ኢየሱስ

[68] ዲ ሲ አሊሰን፣ <u>ዛ ሲጂንን ዋተር</u> ኢስ ጂ ቲ ኪው 30(1986) 143-157።

[69] ኪነር፡ *// ስፔሪት ኢን // ንስፐልስ ኤንድ ለስትስ* 153።

ክርስቶስ የእግዚአብሔርን መንግሥት በመንፈስ ቅዱሱ ወደ ሕይወታችን አም ጥቶ የርሱ ቤተ መቅደስ አደረገን። መንፈሱንም በማፍሰስ የማያቋርጥ የሕይ ወት ውኃ ምንጭን በውስጣችን አፈለቀ። መንፈሱም ስለ አብና ስለ ኢየሱስ ማወቅ የሚገባንን በቃሉ ውስጥ የተገለጠውን እውነት ተረድተን፣ በርሱ ኃይል የተመራ መንፈሳዊ ምልክን እንድናቀርብ ይረዳናል። ስለሆነም አምልኮአችን የሚወሰነው የት እናምልከው በሚለው ሳይሆን እንዴት አድርገን ወይም በምን ዓይነት ሁኔታ እናምልከው በሚለው ይሆናል።

ሰ. ከሆድ የሚፈልቅ ውኃ

(ዮሐንስ ምዕራፍ 7፤37-39)

«ከበዓሉ በታላቁ ቢኋለኛው ቀን ኢየሱስ ቆሞ — ማንም የተጠማ ቢኖ ር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ። ይህን ግን በርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለመንፈስ ቅዱስ ተናገረ፣ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወ ረደም ነበርና።» ወቅቱ የአይሁድ የዳስ በዓል ሲሆን የሚከበረውም በኢየሩሳ ሌም ባለው ቤተ መቅደስ ነበር። የበዓሉም ዋና ዓላማ እግዚአብሔር ከግብፅ ምድር ባወጣቸው ጊዜ የእስራኤልን ልጆች በዳስ ውስጥ እንዳስቀመጣቸው የልጅ ልጆቻቸው ያውቁ ዘንድ ነው። የሚከበረውም በሰባተኛው ወር በአሥራ አምስተኛው ቀን ነበር። ኢየሱስም በዓሉ እኩሌታ ጀምሮ ወደ መቅደስ ወጥቶ ያስተምር ነበር። ይህ የዳስ በዓል ለሰባት ቀናት ያህል የሚቆይ ሲሆን ሕዝቡም ለሰባት ቀን በዳስ ይቀመጣሉ ስምንተኛው ቀን ግን የተቀደሰ ጉባኤ ይሆንላቸዋል (ሌዋ 23፤36፤ ዘኁ 29፤1-40፤ ነህም 8፤18)።

የመጀመሪያው ቀንና የስምንተኛው ቀን የዕረፍት ቀን ነው። በመጀመሪ ያው ቀን ዘካርያስ ምዕራፍ አሥራ አራት ቁጥር ስምንት ላይ ያለው «በዚያም ቀን የሕይወት ውኃ ከኢየሩሳሌም ይወጣል» የሚለው ይነበብና በመቀጠልም ቁጥር አሥራ አራትን በማንበብ እግዚአብሔር ስለ ሰጣቸው ዝናብና መከር ያመ ሰግኑታል። እንዲህ ዓይነቱ ምስጋናውም ሁሌ ጠዋት ጠዋት ለመጀመሪያዎቹ ሰባት ቀናት ይደረጋል።

ሕዝቡም ቀሳውስቱን በመከተል ጠዋት ጠዋት ወደ ሰሎኤም ኩሬ ይሄ ዳል። እዚያም እንደደረሱ የወርቅ እቃው በውኃ ይሞላና ወደ ቤተ መቅደሱ ይመጣል፤ ከዚያም በመቀጠል መሥዋዕቱ ይቀርባል። ውኃው ግን በምዕራብ በኩል በሚገኘው የመሠዊያ ቀዳዳ እንዲፈስስ ይደረጋል። ከዚያም የቤተ መቅ ደሱ መዘምራን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከመዝሙር (113) - (118) ድረስ ያለ ውን የምስጋና መዝሙር ይዘምራሉ። ነገር ግን ስምንተኛው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ ስለሆነ ምንም ዓይነት ሥራ መሥራት አይፈቀድም፤ ውኃ መቅዳት እንኳን አይቻልም። በዚህም ቀን ስለ ዝናብ ጸሎት ይደረጋል፤ ስለግዚአብሔር ጣፋጭ ሸታ የሚሆን በእሳት የሚቃጠል መሥዋዕትና እንስሳ ይቀርባል (ዘኁ29 ፤3)።[70]

በዚህ በስምንተኛው ቀን («ከበዓሉም በታላቁ ቀን») ነበር ኢየሱስ ቆሞ በታላቅ ድምጽ «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣ» በማለት የጋበዛ ቸው። ይህ ቀን ከላይ እንደተነጋገርነው ውኃ የማይቀዳበት ሲሆን፤ ኢየሱስ ይህችን ቀን ጠብቆ የተናገረው ንግግር — ውኃ እንዳትቀዱ እግዚአብሔር አዞአ ችኋል። ምክንያቱም ይህች ቀን ተጠብቃ የቆየችው እኔ የዘላለም የሕይወት ውኃ እንድሰጣችሁ ነው፤ ውኃውም እኔ ነኝ። ይህን ውኃ የጠማ ሁሉ እርሱ ተባርኮ ሌሎቹንም ይባርካል። ስለዚህም ወደ እኔ ኑ ብሎ እንደማለት ነው።

ከላይ ቀደም ብሎ እንደተመለከትነው ለሳምራዊቲዋ ሴት ኢየሱስ «ይህ ንን ውኃ የሚጠጣ ዳግም አይጠማም» ሲላት፤ እዚህ ደግሞ ዳግም አለመጠ ማት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ይህን ውኃ የጠጣ ሁሉ ባርኮቱ ከርሱ ውስጥ ምልቶ ሌሎቹንም እንደሚያረሰርስ ይናገራል። ምክንያቱም ኢየሱስ የሕይወት ውኃ ምንጭ ስለሆነ በርሱ የሚያምን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወቱ ረስርሶ ሌሎች ንም ይባርካል።

---

[70] ብሩስ፣ *F. THTAS አቭ ጽን* I 181-182።

ሸ. ሌላው አጽናኝ

(ዮሐ 14-20፤ ማቴ 10-19፤ ማር 13-11)

ኢየሱስ ከርስቶስ ከአብ ዘንድ ወጥቶ የመጣ፣ ወደ አብ ተመልሶ በክብር ያረገና በርሱም ቀኝ ተቀምጦ ለኃጢአታችን ይቅርታ የሚሰጠን አጽናኖችን ወይም ጠበቃችን ነው (1ዮሐ 2፥1)። ነገር ግን ኢየሱስ የመጨረሻውን ራት ከደቀመዛሙርት ጋር ከበላ በኋላ ቢመዱትና ትእዛዙንም ቢጠብቁ ለዘላለም ከእነርሱ ጋር እንዲሆን ሌላ አጽናኝ አብ እንዲልክላቸው እንደሚሰማን ነገራቸው (ዮሐ 14፥17)። ይህ አጽናኝ ዓለም ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው።

ኢየሱስ በዚህ ክፍል ያለውን እውነት ሲያብራራው ርሱን የሚወድዱትን ሁሉ አርሱም ይወድዳቸዋል፣ አባቱም ደግሞ ይወድዳቸዋል። ስለሚወድዳቸውም ራሱን ይገልጥላቸዋል፣ አርሱና አብም ወደ እነርሱ መጥተው በውስጣቸው መኖሪያ ያደርጋሉ (ዮሐ 14፥21-23)። እንግዲህ ኢየሱስ ለሚወድዱትና ትእዛዙንም ለሚጠብቁ ሁሉ ራሱን የሚገልጠውና በአማኝ ውስጥ የሚያድረው በመንፈስ ቅዱሱ አማካኝነት ነው። ይህ አብ በስሙ የሚልከው መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ ሁሉንም ነገር ያስተምራል፣ ኢየሱስ የተናገረውን ሁሉ ያሳስባል፣ ሰላምን ይሰጣል ስለ ኢየሱስም ይመሰክራል (ዮሐ 14፥25-27፤ 15፥267)።

አጽናኝ ወይም ጸራቅሊጦስ የሚለው ቃል በግሪኩ «*ፓራክሊቶስ*» ሲሆን ትርጉሞቼውም ሁለት ቃላትን ያዘለ ነው— «*ፓራ*» ከአጠገብ የሚቆም ማለት ሲሆን «*ክሊቶስ*» ደግሞ የተጠራ ማለት ነው። ሁለቱ ቃላት ባንድ ላይ ሲጋጠሙ የሚሰጡት ትርጉም «ከአጠገብ እንዲቆም የተጠራ» የሚለውን ነው። ይህ ቃል በጥንት ግሪኮች ዘንድ ለጠበቆችና በፍትህ ላይ ተሰማርተው ሰዎችን ለሚረዱ ሰዎች የሚሰጥ መጠሪያ ስም ነው። ለምሳሌ ያህል በማቴዎስ 10፥19 ላይ «አሳልፈው ሲሰጡአችሁ የምትናገሩትን በዚያች ሰዓት ይሰጣችሁአልና አንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ አትጨነቁ፣ በአናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነውእንጂ የምትናገሩት አናንተ አይደላችሁም» በማለት የመንፈስ ቅዱስን በመከራቸን ጸራቅሊጦስነት በሚገባ አስቀምጦታል። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ ጸራቅሊጦስ ስለሆነ በመከራና በችግራችን፣ እንዲሁም በስደታችን ሁሉ ከአጠገባችን በመሆን ታላቅ የሆነን መጽናናት ይሰጠናል።

በዮሐንስ ምዕራፍ አሥራ ስድስት ከቁጥር 7-15 ላይ ደግም «እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ እኔ አንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ አይመጣምና እኔ ብሄድ ግን አርሱን አልክላችኋለሁ።» በማለት የሚመጣው አጽናኝ (መንፈስ ቅዱስ) ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ዓለምን እንደሚቀስ ጠቅሶታል። ዓለምን የሚወቅስበትም ምክንያት —

- ስለ ኃጢአት፣ በኢየሱስ ስለማያምኑ ነው። ይህም እግዚአብሔር የላከውን ልጁን ዓለም ስለአልተቀበለችውና ሞት ስለተፈረደበት ነው። በዚህም ምክንያት መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ በመሆን ይወቅሳታል፣ ስህተቱዋንም ያጋልጣል።
- ስለ ጽድቅ፣ ዓለም በራሱዋ ሕግ ብትፈርድበትም እንኳን እርሱ ግን ከሞት በመነሳት በክብር ወደ አባቱ ተመልሶ ጻድቅ መሆኑን አረጋገጠ። በዚህም ምክንያት ዓለም ተከሳች።
- ስለ ፍርድ፣ የዚህ ዓለም ገዢ የሆነው ሰይጣን በመስቀል ላይ ስለተቀጠቀና ስለተጣለ ነው (ኢየሱስም ዮሐንስ 12፥3 እና 16፥3 ላይ ሰይጣን የሚጣልበት ጊዜ እንደተቃረበ ተናግሮ ነበር)። ስለዚህም የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ከላይ ተነጋገርናቸውን እውነታዎች ያረጋግጣል።[71]

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ገሊነግራቸው የፈለገው ብዙ ነገር ነበረ ነገር ግን ካለ መንፈስ ቅዱስ አርዳት መቋከም ስለማይችሉ አልነገራቸውም። አርሱ የአውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ግን ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራቸው፣ የሚሰማውን ሁሉ እንደሚናገር፣ አርሱን እንደሚያከብረውና ከአብና ከአርሱ ወስዶ እንደሚነግራቸው አስተማራቸው (12-15)።

ኢየሱስ እውነት ስለሆነ መንፈሱ የእውነት መንፈስ ተባለ (ዮሐ 14፥6)፣ የእውነትም መንፈስ ስለሆነ እውነት ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ ይመራናል። ኢየሱስ ከአብ የሰማውን ይናገራል፣ ከርሱም ያየውንም ያደርጋል (ዮሐ 5፥19፤ 30፤ 8፥28፤ 12፥49) እንዲሁም ለአብ ያለው ሁሉ የርሱ ነው (ዮሐ 13፥3፤ 16፥1

---

[71] ብሩስ፣ *ዘ ኅበፕል ኦቭ ጆን* ፤ 319።

5)። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ ወስዶ ነገረን ማለት ከአብ ወስዶ ነገረን ማለት ነው። ወልድ በሠራቸው ሥራዎች አብን እንዳከበረው ሁሉ መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ የኢየሱስን ተልእኮ፥ ሥራና ማንነት ገልጦ በማሳየት ወልድን ያከብረዋል (ዮሐ 7፥18፤ 17፥4) ።

ከላይ እንደተመለከትነው መንፈስ ቅዱስ የሚከተሉትን ነገሮች በአማኝ ሕይወት ውስጥ ይሠራል –

- ከአማኝ ጋር አማካሪ፥ ጠበቃና አጽናኝ ሆኖ ይሠራል
- በአማኞች ውስጥ ያድራል
- ኢየሱስንና አብን ለአማኞች ይገልጻል
- የእውነትም መንፈስ ስለሆነ ወደ እውነት ሁሉ ይመራል፥ ስለ እግዚአብሔርም መታወቅ የሚገባውን ሁሉንም ነገር ያስተምራል
- ኢየሱስ ያስተማረውንና የተናገረውን ሁሉ ያሳስባል፥ ከኢየሱስ የሚሰማውን ይናገራል
- ኢየሱስ ራሱ እግዚአብሔር እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነና ኢየሱስም ካቆመበት በመቀጠል መዳን በርሱ እንደ ሆነ ይመሰክራል።
- ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች ስለማይተወን ሰላሙን በአጽናኙ በኩል ይተውልናል። ይህም ሰላም ዓለም እንደሚሰጠው ያለ ሳይሆን በእግዚአብሔር እርቅ ላይ የተመርኮዘ ኃይል ያለው ዘላለማዊ ሰላም ነው። ይህ ሰላም አእምሮን ሁሉ ስለሚያልፍ ጭንቀትንና ፍርሃትን አውልቆ በመጣል በልባችን ውስጥ የሚገዛ ነው (ፊል 4፥7፤ ቆላ 3፥15)።
- ኃይልን ይሞላናል፥ እንዴትና ምን እንደምንናገር ይሰጠናል፥ ሰላሙንም በልባችን በማፍሰስ ያጽናናናል።
- ስለ ኃጢአት፥ ስለጽድቅና ስለፍርድ ዓለምን ይወቅሳል
- ኢየሱስን ያከብረዋል [Glorification]

በመጨረሻም በዮሐንስ 20፥21 ላይ ደግሞ እንደምንመለከተው ኢየሱስ ስደቀመዛሙርቱ አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ አልካችኋለሁ በማለት እፍ አለባቸው መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ይህ የሆነው ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ነበር። ደቀመዛሙርቱ አይሁድን ስለፈሩ ተሰብስበው በነበሩበት ቦታ በመሄድ አብ እርሱን እንደላከው ሁሉ እርሱም በዚያው ሥልጣንና ኃላፊነት ሾማቸው፥ የርሱም መልእክተኛ ሆኑ። ወልድ የእግዚአብሔርን መንፈስ ካለልክ ሰስ ተቀበለ እርሱ ደግሞ ካለው መስዶ እፍ አለባቸውና መንፈስን ተሞሉ (እግዚአብሔር መንፈሱን ስፍሮ ለልጁ አልሰጠውም፥ ዮሐ 1፥32-34፤ 3፥34)። ከዚህ በፊት ይህንን መንፈስ ያልተሞሉበት ምክንያት ኢየሱስ ስላልከበረ ነበር (ዮሐ 7፥39)፤ አሁን ግን ሞትን ድል በማድረግ ስለ ከበረ ከርሱ ጋር አንድ መሆን ነበረባቸው [Union with the risen Christ]።

ከላይ እንዳየነው ኢየሱስ መንፈሱን ሲሰጣቸው እፍ ነው ያለባቸው። «እፍ» የሚለው ግሥ በግሪኩ «ኢምፊሳለ» ሲባል ይህ አባባል በዘፍጥረት 2፥7 ላይ እግዚአብሔር በአዳም አፍንጫ የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት ከሚለው ጋር አንድ ዓይነት ቃል ነው። ከከበረው ክርስቶስ የተቀበሉት እስትንፋስ ሕወትን የሚለውጥ ስለሆነ ከርሱ ጋር አንድ ያደርጋቸዋል። ይህ ዓይነቱ የሕይወት ለውጥና ኩመት በበዓለ ኀምሳ ቀን ሲመጣ ላለው የተስፋ ቃል (የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት) አስፈላጊ ነበር። በመሆኑም እፍ ያለባቸው መንፈስ የትንሣኤ ውን ኃይል ሲያሳይ፥ በበዓለ ኀምሳ ቀን የተጠመቁት ደግሞ የማረጉን ኃይል ያሳያል። በሌላ አነጋገር የፊተኛው ጌታ ድል መነሳቱን ሲያሳይ፥ በኋለኛው ደግሞ ከሹመት ወደ ሙላት በማሸጋገር ሉዓላዊ [Sovereign] መሆኑን አሳይቶአል።[72]

«ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፤ ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ።»

የሐዋርያት ሥራ 1፥5

8

መንፈስ ቅዱስና የሐዋርያት ሥራ

ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ለተከታዮቹ እየታያቸውና ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት እየሰበከ አርባ ቀናት ቆየ። ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት ከርሱ የሰሙትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል በኢየሩሳሌም ሆነው እንዲጠብቁ አዘዛቸው፤ ይህም የተስፋ ቃል የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነበር። ጥምቀቱም ኃይልን ስለሚሞላቸው ከኢየሩሳሌም እንስቶ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ የርሱ ምስክሮች ያደርጋቸዋል (ሉቃ 24፥49፤ ሐዋ 1

72

ፀ. ኢፍ ፄስትዮት፥ *// ንስፐል ለክርዲንግ ቱ ሴንት ጆን* (ግራንድ ራፒድስ፥ ኤርድመንስ አሳታሚ

፥5-8)። ይህም የተስፋ ቃል በበዓለ ኀምሳ ቀን ሐዋርያቱ ተሰብስበው እንዳሉ መንፈስ ቅዱስ በመውረዱ ተፈጸመ።

«በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥ ድንገት እንደሚነጥቅ ኀውሎ ነፋስ ከሰማይ መጣ፥ ተቀምጠውም የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።»

(ሐዋ 2፥1-4)

«...ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎአልና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምት ሰሙትን አፈሰሰዉ።»

(ሐዋ 2፥33)

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከኢየሱስ የሰሙት አብ የሰጠው የተስፋ ቃል ሲሆን ይህም በበዓለ ኀምሳ ቀን ተፈጸመ፤ ኢየሱስም መንፈስን ከአብ ተቀብሎ እነርሱን አጠመቃቸው። አብ መንፈሱን ስለጄ ሰፍሮ እንዳልሰጠዉ ሁሉ እን ደዚሁም ልጄ ደግሞ የሚወዱትን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ አረሰረሳቸው፤ በመንፈ ሱም ተጠመቁ (ዮሐ1፥32-34)። በመጠመቃቸውም የርሱን ኃይል ተሞሉ፥ አርሱንም ለበሱት። በእርሱም መንፈስ ስለተሞሉ እርሱ ያደርገውና ያስተ ምረው ዘንድ የጀመረውን አገልግሎት ቀጠሉ። ከኢየሩሳሌም እንስቶ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ በየከተማው፥ በየዱራና በየገደሉ የርሱ ምስክሮች በመሆን ሞቱንና ትንሣኤውን ተሸክመው ዞሩ፤ እስከ ሞትም ድረስ የታመኑ ሆኑ።

ኢየሱስ የሰጣቸው ሦስት ተስፋዎች (አሳባቸው አንድ የሆነ) በዚህ በዐ ዓለ ኀምሳ ቀን ሲፈጸሙ እንመለከታለን። እነርሱም 1ኛ. በሉቃስ 24፥49 ላይ የሚገኘው «እነሆም፥ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ አልክላችሁአለሁ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ።» የሚለው ሲሆን፤ 2ኛ. በሐዋርያት ሥራ 1፥5 ላይ «ነገር ግን ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን

ድርጅት I 1973) 292-295።

የተሰፋ ቃል ጠብቁ፤ ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን ከዋቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አለ።» 3ኛ. በሐዋርያት ሥራ 1፥8 ላይ «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ።» የሚሉት ናቸው።

በሉቃስ 9፥1-6 ባለው ክፍል እንደምናየው ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ጠርቶ በአጋንንት እንዲያወጡና በሽታን እንዲፈውሱ ኃይልንና ሥልጣንን ሰጣቸው። ይህንንም በማድረጉ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ተሳታፊ አደረጋቸው። በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ደግሞ በሞቱና በትንሣኤው ያተመውን የደህንነት ወንጌል በሙሉ ኃይልና ሥልጣን እንዲቀጥሉ ኃይልን አስታጠቃቸው፥ በጸጋ ሰጦታም ተሞሉ። ይህም ማለት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ውስጥና በመካከላቸው ሊያድር ወረደ። መጥምቁ ዮሐንስም «እርሱ በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችሁአል» ብሎ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ።

በኃይል መሞላትና በልዩ ልዩ ሥጦታዎችም መባረክ የሰላሙን ወንጌል ለመሰበክ አስፈላጊ ነበር። ወይም በሌላ አነጋገር ለተጠሩበትና ለተሰየሙበት አገልግሎት አስታጠቃቸው። ይህም የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ኃይልን በማሰታጠቅ በግል ሕይወታቸው የቅድስና (የመንፈስ) ፍሬ እንዲያፈሩና[73] በአገልግሎታቸው ደግሞ የወንጌሉ ምስክሮች እንዲሆኑ ረዳቸው። በመጨረሻም የኢየሱስ አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በይፋ እንደተከፈተው ሁሉ የሐዋርያት አገልግሎትም እንዲሁ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ተመርቆ በበዓለ ኀምሳ ቀን በይፋ ተከፈተ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወንጌል በመንፈስ ኃይል ሰለጠ።[74]

73

አንዳንድ አንደነ ዶ/ር ጎርደን ፊ ያሉ ምሁራን በመንፈስ የመሞላታችን ተቀዳሚ አላማ በኃይሉ አንድንታጠቅና ፍሬ አንድናፈራ አንዲሁም በአግዚአብሔር ደስ እንዲለን ነው ሲሉ ሌሎቹ አንደነ ዶ/ር ክሬግ ኪነር ያሉት ምሁራን ደግሞ የመሞላታችን ተቀዳሚ አላማ በኃይል ተሞልተን ወንጌልን አንድንሰብክ ነው ይላሉ። ነገር ግን ሁለቱም ተቀዳሚና አስፈላጊዎች ናቸው፤ — መንፈስ ቅዱስ ኃይልን በማስታጠቅ ወንጌልን እንድንሰብክ ሲረዳን ሕይወታችንንም ደግሞ በመስመር ፍሬ አንድናፈራ በማድረግ ወንጌልን በአንደበታችን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በሁሉአችንም ቋምር እንድንሰብክው ይረዳናል።

74

ሮጀር ስትሮንስታንድ፡ *ዘ ክሪዝማቲክ ቲኦሎጂ ኦቭ ሉቃስ* (ፒዐዲ፡ ሄንድሪክሰን አሳታሚ ድርጅት፤ 1994) 52።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በአሁኑ ዘመን

አንድ ሰው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙና የሕይወቱ ጌታ አድርጎ ሲቀበል ኃጢአቱ ይቅር ይባልለታል፥ መንፈስ ቅዱስም ወደ ሕይወቱ በመምጣት ይለውጠዋል። ይህ ዓይነቱ ለውጥ ዳግም መወለድ ይባላል። ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሰንል ከዳግም መወለድ የተለየ ሲሆን ይህም በመንፈስ መሞላትና መጥለቅለቅ ማለታችን ነው። በዛሬዋ ቤተክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምንድነው? የምንጠመቀውስ መቼ ነው? እንደ በዓለ ኀምሳ ቀን ያለ ጥምቀት አሁንም ሊኖር ይችላል ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች ከማወዛገባቸው የተነሳ የክርቲያኑን ጎራ በሁለት ከፍለውታል።

አንደኛው ወገን ይህም ወስሊያን፥ ፔንቴኮስታልስ፥ የሆሊነስ አማኞች፥ ካሪዝማቲክና ሌሎችም ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ከዳግም መወለድ በኋላ የሚመጣ ራሱን የቻለ ሂደት ነው ይላሉ። ሌሎቹ ደግሞ ማለትም በሪፎርምድ ትራዲሽን ሥር ያሉት አማኞችና እነርሱን የመሰሉት ደግሞ የለም፥ አንድ ሰው ዳግም ሲወለድ በመንፈስ ቅዱስ አብሮ ይጠመቃል እንጂ ሌላ ሁለተኛ ጊዜ የሚሰጥ ጸጋ የለም ይላሉ። የመጀመሪያዎቹ የሚያቀርቡት መረጃ በሐዋርያት ሥራ ላይ የተጠቀሱትን የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ሲሆን፥ ሁለተኞቹ ደግሞ የሐዋርያት ሥራ ታሪካዊ እንጂ ትምህርት አዘል [Didactic] ስላል ሆነ እርሱን እንደ መመሪያ በመውሰድ የዚያን ዓይነት ጥምቀት አሁንም ሊኖር ይችላል ብለን መውሰድ አንችልም በማለት አሁን ያለውን የመንፈስ ቅዱስ አንቅስቃሴና ሰጦታዎችን ይቃወማሉ ወይም አይቀበሉም።[75]

ነገር ግን በሉቃስ ወንጌልና በሐዋርያት ሥራ ላይ ጠለቅ ያለ ጥናት ያካሄዱት ሮጀር ስትሮንስታንድ ሲጽፉ በሐዋርያት ሥራ ላይ የምናየው ሰለ ክርስቶስና መንፈስ ቅዱስ የተጻፉት የብሉይ ኪዳናት ትንቢት ሲፈጸሙና የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይልና በድንቅ ሲሠራ መሆኑን ገልጸዋል። በመቀጠልም

75

ጆን ስቶት፡ *ዘ ባፕቲዝም ኢንድ ፉልስ ኦቭ ዘ ሆሊ ስፒሪት* (ዶውነርስ ግሮቭ፡ ኢንተርቫርሲቲ፤ 1964) 8። አንተኒ ስትሮንስታንድ፡ 5-9።ሆክማ፡ *ሆሊ ስፒሪት ባፕቲዝም* (ግራንድ ራፒድስ፡ አር ድማን አሳታሚ ድርጅት፤ 1972) 23-24።

የሐዋርያት ሥራ የመንፈስ ቅዱስን ተአምራዊ ሥራ የሚያሳይ ታሪካው መጽሐፍ ቢሆንም ገና ለገና ታሪካዊነት እንጂ ትምህርት አዘልነት [Didactic] የለውም በማ ለት መንፈስ ቅዱስ በቤተክርስቲያን የጀመረውን መለኮታዊ ሥራ መጣA እንች ልም[76] ብለዋል።

በርግጥም ወንጌላትንና የሐዋርያት ሥራን ስንመለከት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከዳግም መወለድ በኋላ የሚመጣ መሆኑን እንመለከታለን። ምክንያቱም 1ኛ. ኢየሱስ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ተፀንሶ በመንፈስ የተሞላውና የተቀባው ሠላሳ ዓመት ሲሞላው ነው። 2ኛ. ደቀመዛሙርት የተለወጡት ወይም አዲስ ሕይወትን ያገኙት ኢየሱስ እፍ ባለባቸው ጊዜ ሲሆን በመንፈስ ቅዱስ የተጠመ ቁት ግን በበዓለ ኀምሳ ቀን ነው። 3ኛ. የሰማርያ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን የተ ሞሉት ከዳኑ በኋላ ነው (ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃA እን ጂ መንፈስ ቅዱስን እንዳልተቀበሉ በሰሙ ጊዜ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ላኩላቸው፤ ሐዋ 8)። 4ኛ. ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን በመጣ ጊዜ አንዳንድ ደቀመዛሙርትን አገኘና «ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀብላችሁ? አላቸው፤ እነርሱም አልተቀበልንም መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ሰንኩዋ አልሰማንም» አሉት (በዮሐንስ ሞምቀት ተጠምቀዋል ነገር ግን ኢየሩሳሌምን ለቀው ራቅ ወዳለ ቦታ ከወጡ ሳይ ቆይ እንደግይቀር ይገመታል። ምክንያቱም በበዓለ ኀምሳ ቀን የተከናወነውን ነገር ሰንኳን ጭራሽ አልሰሙም)። እርሱም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተሞሉ በልሳኖችና ትንቢት ተናገሩ (ሐዋ 19)።

ነገር ግን እንዳንዶቹ ደግሞ ጌታን ሲቀበሉ እዚያው በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አሉ። ለምሳሌ ጳውሎስን ብንመለድ ኢየሱስ በደማስቆ መንገድ ከተ ገለጠለት ቡኋላ ወደ አናንያ ቤት ወሰዱት። እዚያም አናንያ እጁን በጫነበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተሞላ (ሐዋ 9፤10-18)። ጴጥሮስ ከእግዚአብሔር በተቀበ ለው ራእይ መሠረት ወደ ቂሳርያ በመሄድ ለቆርኔሊዎስና ለቤተሰዎቹ ወንጌልን በሚሰብክበት ጊዜ ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ በልሳኖችም ተናገሩ (ሐዋ10)።

[76] ለትሮንስታንድ፣ 5-9።

ማጠቃለያ

እንግዲህ ከላይ እንደተመለከትነው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከዳግ ም ውልደት የተለየ ሲሆን፤ ይህም —

- ሰዎች ጌታን ሲቀበሉ በመንፈስ ቅዱስ ሊጠመቁ ይችላሉ (ወዲያ ውኑ)።
- ሌሎች ደግሞ ከዳኑ በኋላ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በቂ መረዳ ትን ሲያገኙ ልባቸውን በመክፈት ይጠመቃሉ።

በልሳን መናገርና የጸጋ ስጦታዎች

በልሳን የመናገር ጉዳይ ነገር በዘመናችን ባለችው ቤተክርስቲያን ዘንድ አወዛጋቢ ጉዳይ ሆኖ ይታያል። ከዚህ ቀጥሎ መንፈስ ቅዱስን የተሞሉ ሁሉ በልሳን መናገር አለባቸው ወይ? ወይም ደግሞ ይናገራሉ ወይ? የሚለውን ጥያ ቄ ለመመለስ እንሞክራለን። እንደሚታወቀው በልሳን መናገርን አስመልክቶ ሁለት ዓይነት አስተሳሰብ አለ — አንደኛው ክፍል መንፈስ ቅዱስን የተሞሉ ሁሉ በልሳን መናገር አለባችው ሲል፤ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የለም፤ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሁሉ የግድ በልሳን መናገር የለባቸውም ይላል።

በልሳን መናገር የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት መሆኑን በሐዋርያት ምዕራፍ ሁለት ላይ እንመለከታለን። ጴጥሮስም በልሳን መናገር መንፈስ መውረ ዱንና የነቢዩ ኢዩኤል ትንቢት መፈጸሙን እንደሚያሳይ ተናግሮአል (ሐዋ 2፤ 19-21)። በሌላ ጊዜ ደግሞ ጴጥሮስ ወደ ቂሳርያ ሄዶ ለቆርኔሎዎስና ይሰሙት ለነበሩት ሰዎች ወንጌልን በሰበከ ጊዜ ቃሉን በሚሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ወረደ ባቸው፤ በልሳኖችም መናገር ጀመሩ (ሐዋ 10)። ጳውሎስ ስለ መንፈስ ቅዱስ መውረድ ፈጽሞ እውቀት የሌላቸውን ተከታዮች ባገኘ ጊዜ እጁን ጫነባቸውና መንፈስን ተሞሉ፤ በልሳኖችም ተናገሩ (ሐዋ 19)። ጳውሎስ ራሱ ጌታን በተቀ በለ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞላ ቃሉ ይነግረናል (በልሳን መናገሩን ባይገል ጽም ፤ሐዋ 9)። ነገር ግን ወደ መልእክቶቹ ዘወር ያልን እንደሆነ በአንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ አሥራ አራት ላይ ከግናቸውም ይበልጥ በልሳን ስለሚናገር

እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግን ተናግሮአል (1ቆሮ 14፥18)። ከዚህ የምንረዳው ነገር ቢኖር በልሳን መናገር የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት (ሙላት) ውጤት ስለ ሆነ ያገኘውም በደግሰቀ መንፈስን በተሞላበት ጊዜ ስመሆኑ መገመት ይቻላል።

ነገር ግን የሰማርያ ሰዎች መንፈስ በወረደባቸው ጊዜ በልሳኖች ይናገሩ አይናገሩ የተገለጸ ነገር የለም – «እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ» የሚለውን ብቻ እናያለን። በዚያን ጊዜም ሲሞን የሚሉት ሰው በሐዋርያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጥ ባየ ጊዜ ገንዘብ ይዞ ወደ ሐዋርያት መጣና — «እጄን የምጭንበት ሰው ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ለእኔ ደግሞ ይህንን ሥልጣን ስጡኝ አለ» (በነገራችን ላይ የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ ሊገዛ በመሞከሩ ተገስጸአል፤ 8፥14-20)። በርግጥ እነዚህ ሰዎች በልሳን እንደተናገሩ የተገለጸ ነገር ባይኖርም መመለስ የሚገባን ጥያቄ ቢኖር - ሲሞን በሰዎቹ ላይ በግልጽ የሚታይ ማረጋገጫ ካላየ በስተቀር በመንፈስ መሞላታቸውን በምን አወቀ? የሚለውን ነው።

ማጠቃለያ

ከላይ ባየናቸው ድጋፍ መረጃዎች መሠረት ሦስት ነገሮችን እንረዳለን —

- ❖ በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቁ ብዙዎች በልሳኖች ተናግረዋል
- ❖ በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቁ አንዳንዶቹ መሞላታቸውን የሚያሳይ ግልጽና ተጨባጭ የሆነ ለውጥ ታይቶባቸዋል (ምንም እንኳን በልሳኖች ተናገሩ ብሎ በግልጽ ባይናገርም)
- ❖ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና በልሳን መጸለይ ምንም ዓይነት ሰው ሰራሽ ዘዴ አያስፈልገውም። አንዳንድ አገልጋዮች ለሰዎች በሚጸልዩበት ጊዜ ሰዎቹ የተወሰኑ ቃላቶችን በተደጋጋሚ እንዲሉ ያበረታቱዋቸዋል (ለምሳሌ ያህል «ሃሌ ሉያ» ወይም «አሜን» ወዘተ. የሚሉትን ቃላት በተደጋጋሚ እንዲሉ ያደርጋሉ)። በመሠረቱ በልሳን የመጸለይ ስጦታ የእግዚአብሔር መለኮታዊ አሠራር በመሆኑ በእምነት ሆነን መጸለይ እንጂ መንፈስ ቅዱስን ለመርዳት መሞከር በቃሉ የተደገፈ አይደለም።

«እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ደካማችንን ያግዘዋል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደ ሚገባን አናውቅምና፤ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።»

ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥26-27

9

መንፈስ ቅዱስና የሮሜ ሰዎች

ጳውሎስ መልእክቱን ወደ ሮሜ ሰዎች ሲጽፍ በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ስለጠው ስለ እግዚአብሔር ወንጌል ሐዋርያ ሊሆን እንደተጠራ በመግለጽ ይጀምራል (1፥1)። በመቀጠልም ወንጌሉም «እንደ ቅድስና መንፈስ ከሙታን መነሳት ስለተነሳው፥ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለተገለጠው» ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመሰክር እንደሆነ ይናገራል (1፥3-4)። በመቀጠልም ወደ ሮሜ ለመሄድ ብዙ ጊዜ

እንደሚያስብ ይናገራል። ለመሄድ የሚፈልግበት ዋናው ዓላማ ደግሞ «ትጸኑ ዘንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳከፍላችሁ» ነው፤ ምክንያቱም «በሌሎቹ አሕዛብ ደግሞ እንደ ሆነ በእናንተም ፍሬ አገኝ ዘንድ ... በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቻለሁ።» (1፥11-15) በግለት መንፈሳዊ ስጦታ የሕይወት ፍሬን ለማፍራት አስፈላጊ መሆኑን ያሳየናል። ስለሆነም የሐዋርያው ስሪነገር መንፈሳዊ ስጦታን እንዲያገኙና ፍሬ እንዲያፈሩ ሲሆን ይህም ደግሞ ለነርሱ ያለው የልብ ቅንዓት ያሳያል።

በምዕራፍ ሁለት ላይ ደግሞ ሲናገር «በግልጽ በሥጋ የሚደረግ መገረዝ መገረዝ አይደለምና፤ ዳሩ ግን በስውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው፥ መገረዝ በመንፈስ የሚደረግ የልብ መገረዝ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም፤ የርሱ ምስጋና ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ከሰው አይደለም።» (2፥29) በግለት የሚለውጠው መንፈስ ቅዱስ እንጂ በሕግ የተጻፉትን ፊደላት በመጠበቅ እንዳልሆነ ይናገራል። ሙሴ በምድረበዳው ጉዞ ላይ ለአዲሱ ትውልድ ሲናገር – «በሕይወትም አንድትኖር አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ እንድትወድ አምላክህ እግዚአብሔር ልብህን የዘርህንም ልብ ይገርዛል» በማለት እግዚአብሔር በራሱ ሰዓት እንደሚለውጣቸው ተናግሮ ነበር (ዘዳግ 30፥6)። በትንቢተ ኤርምያስም ላይ ተመሳሳይ የሆነ መልእክት እናያለን —

> «እነሆ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር ከግብፅ አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና፥ እኔም ቸል አልኋቸው፥ ይላል እግዚአብሔር። ከእነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና፥ ይላል እግዚአብሔር፤ ሕጌን በአእምሮአቸው አኖራለሁ፥ በልባቸውም እጽፈዋለሁ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል።»
>
> (ኤር 31፥31-33)

በትንቢተ ሕዝቅኤልም ላይ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል —

> «በትእዛዜም ይሄዱ ዘንድ ፍርዴንም ይጠብቁና ያደርጉ ዘንድ አንድ ልብ አሰጣቸዋለሁ፥ በውስጣቸውም አዲስ መንፈስ አሰጣለሁ፥ ከሥጋቸው ውስጥ የድንጋዩን ልብ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ አሰጣቸዋለሁ፤ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ።» (11፥19-21)
>
> «አዲስም ልብ አሰጣችኋለሁ አዲስን መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ አሰጣችኋለሁ። መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትዕዛዜም አሰሄዳችኋለሁ፥ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ ታደርጉማላችሁ።»
>
> (ሕዝቅ 36፥26-27)

ይህም በነቢያት የተተነበየው የልብ ግርዘት በመንፈስ ቅዱስ በኩል ተፈጸመ። ግርዘቱም ደግሞ በእጅ የሚሆን ሳይሆን በመንፈስ የሚሆን ነው (2ቆር 3፥1-18)። እግዚአብሔር መንፈሱን በውስጣችን በማድረግ ገረዘን፥ የድንጋዩን ልብ አውጥቶ በመላእ የሥጋን ልብ ሰጠን። በዚህም ምክንያት መንፈስ ቅዱስ ትዕዛዛቱን በመጠበቅ እርሱን ደስ እንድናሰኘው ይለውጠናል።

መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ስለ ሚኖር የእግዚአብሔርን ፍቅር በልባችን ያፈስልናል፤ ይህም ብቻ አይደለም ነገር ግን ተስፋን በመስጠት በመከራችን እንድንመካ ያደርገናል። ተስፋውም የሚመጣውን የእግዚአብሔርን ክብር ስለ ምናይና ከርሱ ጋር ከዘላለም እስከ ዘላለም ስለ ምንነግሥ ሲሆን፥ ፍቅሩ ደግሞ ተስፋውን ያጸናልናል (5፥1-5)።

6፥4፤ 7፥4-6

«እንግዲህ ክርስቶስ በእብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።»

«እንዲሁ ወንድሞቼ ሆይ እናንተ ደግሞ በክርስቶስ ሥጋ ለሕግ ተገድላችኋል፤ ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ እናንተ ለሌላው ከሙታን ለተነሳው ለርሱ ትሆኑ ዘንድ። በሥጋ ሳለን በሕግ የሚሆን የኃጢአት መሻት ለሞት ፍሬ ሊያፈራ በብልቶቻችን ይሠራ ነበርና፤ አሁን ግን ለርሱ ለታሰርንበት ሰለ ሞትን ከሕግ ተፈትተናል ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም።»

ክርስቶስ ከሞት የተነሳው የእብ ክብር በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ሲሆን እኛንም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ የሚያደርገን ይሄው መንፈስ ቅዱሱ

ነው። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባደረገው መሥዋዕትና በትንሣኤው ኃይል ምክ ንያት እኛ አማኞች አሁን በምንኖረው ኑሮና ወደፊት በሚመጣው ሙታን ትንሣ ኤም ጭምር በሞቱና በትንሣኤው አብረን እንባተፋለን። ይህንንም እውነት የወሰድነው የውኃ ጥምቀት በተምሳሌነት ሲያረጋግጥልን፣ የምንኖረውም በትንሣ ኤው ኃይል ነው።[77] ጳውሎስ ሲናገር «አሁን ግን ለርሱ ለታሰርንበት ስለ ሞትን ከሕግ ተፈትተናል» በማለት የብሉይ ኪዳንንና አዲስ ኪዳንን ያነጻጽ ራል። ምንም እንኳን «አርጌው ፈደል» (በሙሴ የተሰጠው ሕግ) በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፈ ቢሆንም ከርሱ ጋር አብሮ ስላልታደለ ሰዎች ሕጉን ሙሉ ለሙሉ ሊጠብቁት አልቻሉም።

እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባን ነገር ሕጉ ቅዱስ፣ ትእዛዙም ደግሞ ቅድ ስት እንደሆነች ነው። ምክንያቱም ሕጉ የተሰጠው በእግዚአብሔር ስለሆነ የእግዚአብሔር እስትንፋስ አለበትና ነው (7፣12)። ነገር ግን ሰው ሕጉን ሊጠ ብቅ ስላልቻለ ኃጢአት ምክንያት አግኝቶ በውስጣችን ነገሠ። ሕጉን የማይጠ ብቅና በርሱ ጸንቶ የማይኖር ደግሞ የተረገመ እንደሆነ ተገልጸአል (ዘዳ 27፣ 26)። በዚህም ምክንያት ማንም ሰው ሕጉን ሙሉ ለሙሉ ሊጠብቅ ስላልቻለ ሁሉም ሰው ከሕግ እርግማን በታች ተዘጋ። ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ምክንያት ከሕግ አስራት ተፈትተን በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን። ይህም ከላይ እንደተገለጸው በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ የተገኘ አዲስ ሕይወት ሲሆን እውን የሆነውም በመንፈስ ቅዱስ ነው (ዕብ 2፣4)።

8፣1-39

ይህ ክፍል በክርስቶስ ኢየሱስ ላለን አሁን ኩነኔ እንደሌለብን ይነ ግረናል። ምክንያቱም በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃ ጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቶናልና ነው። እንደሚታወቀው ሁሉ ሕጉ ሞት ፈርዶብን ነበር (ቁ1)። እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመ ላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት ኃጢ አትን በሥጋ ኮነነ (5)። በ7፣13-25 ላይ «እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ስለዚህ

[77] ሙ፣ 384-388።

ሞት ከተሰጠ ሥጋ ግን ያድነኛል» ካለ በኋላ በዚህኛው ምዕራፍ ደግሞ የክርስ ቶስ መንፈስ ብቻ አርነት ሊያወጣ እንደሚችል የምሥራች ይናገራል።

ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፣ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው (6)። ምክንያቱም በመንፈስ ፈቃድ ስንኖር እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰ ኘውን ነገር ስለምናደርግ ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቅ ያገኘነውን ሰላም እጥብ ቀን እንይዛለን። ከርሱ ጋር በመታረቃችንም ደግሞ ሕይወት ሆኖልናል። እንግ ዲህ ከርስቶስም በእኛ ውስጥ ስላለ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደለንምና መንፈ ሳችን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው (9-10)። ስለሆነም ኢየሱስን ከሞት ያስነሣው እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ በአሰቀመጠው በመንፈሱ (ማለትም ልጁን በአስነሣበት በዚያው መንፈስ) በሙታን ትንሣኤ ጊዜ ለሚሞተው ሰውነታችን ሕይወትን በመስጠት ከሞት ያስነሳናል[78] በማለት ታላቅ የሆነን ተስፋ ይሰጠናል (ቁ. 11፤ 1ቆር 6፣14፤ 15፣12-58)።

በክርስቶስ ኢየሱስ መንፈስ ከሞትና ከኃጢአት ባርነት ነጻ ከወጣን ዘንድ አሁን ደግሞ በመንፈሱ የሰውነትን ሥራ እንድንገድል እዳ አለብን እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ እንኖር ዘንድ አይደለም (12)። የእግዚአብሔርም ልጆች ስለሆንን በመንፈስ በመመራትና የሰውነትን ሥራ በመንፈስ ኃይል እየገደልን በሕ ይወት እንኖራለን። አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበ ልን እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ ስላልተቀበልን ለኃጢአት ልን ገዛ ከቶ አይገዛንም (15-16)።

ከአገባቡ እንደምንረዳው «ሥጋ» በግሪኩ «ሳርክስ» ሲባል የሚያሳየን የዓለምን ክፉ ተጽእኖና ኃጢአትን ሲሆን፣ «የሥጋ ሥራ» ስንል ደግሞ ለዓለ ምና ለሰይጣን ያደረ ክፉ አመራር ማለታችን ነው። በጌታ ኢየሱስ የዳነ ሰው ከሥጋ ሥራ ተላቋልና በጽድቅ ይኖራል (ተመልሶ ወደ ኃጢአት ባርነት ካልተ መለሰ በስተቀር)። በተጨማሪም «ሰውነት» በግሪኩ «ሶማ» ሲለው የሚያሳየ

[78] «ሕይወትን ይሰጠዋል» የሚለው ቃል በግሪኩ «ዞፖዬሴይ» የሚለው ሲሆን ይህም ትንቢታዊ ግሥ (ፊዩቸር ቴንስ) ነው። ስለዚህም አረፍተ ነገሩ የሚያሳየን መንፈስ ቅዱስ አሁን በሕይወታችን እየ ሠራ ያለውን ወይንም የሠራውን የደህንነት ሥራ ባይሆን ወደ ፊት በሙታን ትንሣኤ ጊዜ የሚያከና ውነውን ተግባር ነው። እግዚአብሔር ልክ ልጁን ከሞት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዳስነሣው እንዲ ሁ እኛንም በውስጣችን በሚኖረው በመንፈሱ ከሞት ያስነሳናል። ዳግለስ ሙ፣ *ሮማስ 1-8* (ቺካ ጎ፣ ሙዲ ፕረስ፤ 1991) 525-526።

ውም ሰውነትን ወይንም የሰው አካልን ነው። የተለወጠ ክርስቲያን ዕለት ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመረዳት በአዕምሮው መታደስ እየተለወጠ ሰውነቱን ቅዱስና ሕያው መሥዋዕት በማድረግ (የሰውነትን ሥራ እየገደለ) ለእግዚአብሔር ያቀርባል።[79]

የእግዚአብሔር ልጆች በመንፈስ ቅዱስ ላይ በመደገፍና በመመራት የሰውነት ሥራን እየገደሉ ዕለት ዕለት የድል ሕይወትን ይኖራሉ። ይህ የሚኖሩትም በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተደገፈ የድል ሕይወት እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ያደርሳቸዋል። የእግዚአብሔርን ምሪት በተመለከተ ዳዊት በመዝሙሩ «ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ» (መዝ (23)፡3) ሲል፥ በምሳሌ ላይ ደግሞ «በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፥ እርሱም ጎዳናህን ያቃናልሃል።» (ምሳ 3፡5) በማለት ስለ እግዚአብሔር መሪነት ይነግረናል።

የክርስትና ጉዞአችንን በተመለከተ መንፈስ ቅዱስ መምራት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ለውርስም ያበቃናል። የእግዚአብሔርም ልጆች ስለሆንን በዕለተ ምጽአት እርሱ ጋር አብረን ወራሾች ነን። የእግዚአብሔር ልጆች ስለመሆናችን ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ከመንፈሳችን ጋር በመሆን ይመሰክርልናል። ወራሾችም ስለሆንን በዚያን በጌታ ቀን ከክርስቶስ ጋር አብረን እንከብራለን። ታዲያ አብረን የምንከብር ከሆንን ደግሞ ክርስቶስ የተቀበለውን መከራ አሁን በምንኖረው ኑሮ መቀበል ይኖርብናል (ቁ. 14-17፤ ፊል 1፡29)።

ለእኛ ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ሲመዛዘን ያሁኑ ዘመን ሰቃይ እንደምንም አይቆጠርምና በመከራችን መጽናት ይኖርብናል (ቁ. 18)። በሚደር ስብን በማናቸውም ዓይነት ስደትና መከራ ስናልፍ መንፈስ ቅዱስ አብሮን ስለሆነ ኃይልን መስጠት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ልጅ ወደ አባቱ እንደሚጮኸው ሁሉ እኛም ወደ እግዚአብሔር አባታችን እንድንጮህ፥ አባዬ ብለን እንድንጠራውና ከርሱ ጋር እንድንነጋገር ይረዳናል። ስለዚህም በሚደርስብን በማናቸውም መከራ ልንመካ ይገባናል። ምክንያቱም የማያሳፍረን የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን በመንፈስ ቅዱስ ፈስሶአልና ነው (5፡5)።

[79] ሙ ፥ 529።

የመንፈስ በኩራት ያለን ግለትም በምጽአት ሰዓት የሚሆንን ማጎተም በልባችን የተቀበልን በዚህ አስከፊ ዓለም ስንኖር ልጅ ሆነን የምንከብርበትን ቀን እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን። ምክንያቱም የዳንነው ቤተሰፋ ስለሆነ አሁን የምንኖረው ኑሮ ከችግርና ከመከራ ሙሉ ለሙሉ ነፃ የሆነ አይደ ለምና ነው (ቁ. 22-25)[80]። የምንቃትተው ብቻችንን ሳይሆን ነገር ግን መንፈስ ቅዱስም ራሱ ደግሞ ድካማችንን ያግዛል፥ እንዴትም አድርገን እንድንጸልይ እና ውቅምና ልባችንን እየመረመረ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል (26-27)። እግዚአብሔርን ስለምንወደውና እንደ አሳቡም ስተጠ ራነው የሚደርስብን ማንኛውም ዓይነት መከራና ችግር ወይም ስደት እግዚአብ ሔር ራሱ አስቀድሞ የወሰነው በመሆኑ ለበጎ ነው። ዘንነቱም ይህ በሕይወታችን የሚደርስብ ነገር ሁሉ የልጁን የኢየሱስን መልክ እንድንመስል ስለሚያደርግ ነው። ታዲያ መከራውንም ከርሱ ጋር ከተቀበልን ደግሞ ከርሱ ጋር አብረን ስለ ምንከብር በዚህ ታላቅ ተስፋ እንጽናናለን (28-30)።

ከላይ እንደተነጋገርነው የአማኞችን ከክርስቶስ ጋር መከራን መቀበልን እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰነው ነገር ስለሆነ መንፈስ ቅዱስ በድካማችን በማ ገዝና ስለ እኛ በመቃተት ይማልድልናል። መንፈስ ብቻ አይደለም የሚማል ድልን ነገር ግን ከሙታን የተነሣውና በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ክርስቶስ ኢየሱስም ራሱ ይማልድልናል። ስለሆነም በዚህ ዓለም ስንኖር የሚደርስብን መከራ፥ችግር፥ ስደት፥ ጭንቀት፥ ራቁትነት፥ ሰይፍ፥ ሞትም ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ማንኛውም ነገር ቢሆን በክርስቶስ ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም። ምክንያ

80

በተሰፋ ድነናል ሲል አሁን ገና አልዳንም ማለቱ አይደለም። ደህንነታችን የተረጋገጠ ነው።። በሆ ንም ቅሉ እግዚአብሔር በልጁ በኩል ያዘጋጀልን የደህንነትና ሰማያዊ በረከት ቀመሰነው እንጂ ሙሉ ለሙሉ አልተቀበልነውም። ይህም አባባል በእንግሊዝኛው The already and the not yet በመባል ይታወቃል። በዚህም ምድር ስንኖር በችግርና በመከራ ውስጥ እናልፋለን። መከራውንም አብረን በመቀበላችን ጌታ ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ እኛም ከርሱ ጋር እንከብራለን፤ እግዚአብሔርም ያዘጋጀልን ሰማያዊ በረከት አብረን እንወርሳለን። እስከ እዛ ድረስ ግን ራሳችንን እግዚአብሔርን በመምሰል እያስማመድን ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት እናድጋለን። ስለዚህም ይህን የልጅነታችንን ቤዛ ግለትም እግዚአብሔር ለልጆቹ ያዘጋጀውን ታላቅ ባርኮት አምኖቶ በፍጹም ሙላት እስኪያረ ሰርሰን [Consumate] ድረስ ያንን ቀን በውስጣችን ባለውና ተስፋውን በሚያጸናልን በመንፈስ ቅዱስ እንጠባበቃለን።

ቱም በወደደን በኢየሱስ ክርስቶስ ካሸናፊዎች ሁሉ እንበልጣለንና ነው (31-39)።

14፥16-18

«የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ በመብልና በመጠጥ አይደለችም።»

የዚህን ምዕራፍ ጠቅላላ ይዘት የተመለከትን እንደሆነ ሐዋርያው ምግብን በተመለከተ በእምነት የደከመውን ሰው በአሳቡ ላይ ሳንፈርድ እንድንቀበለው ያሳስበናል (ቁ 1)። በሮሜ ያሉ ክርስቲያኖች አንዳንዶቻቸው ሁሉን ይበሉ ዘንድ እንተፈቀደላቸው ስለሚያምኑ ሁሉንም ነገር ሲበሉ፥ አንዳንዶቹ ደግሞ አትክልት ብቻ ይበላሉ (ቁ 2-4)። ስለዚህም በተረዳንበት መረዳት የራሳችንን እምነት ለራሳችን በማድረግ፥ እርስ በርሳችን ሳንፈራረድና ለወንድሞቻችን እንቅፋትን ሳናኖር ተሸክመን መኖር እንደሚገባን ይነግረናል። ማናችንም ብንሆን የራሳችንን ጽድቅ ልናቆም አይገባንም። ምክንያቱም ጽድቃችን የተገኘው በሠራነው ሥራ ሳይሆን በጌታ ሞትና ትንሣኤ የተገኘ ነው። በመሆኑም እርስ በርስ ከመፈራረድ ይልቅ በአንድነትና ቢሕብረት ልንኖር ይገባናል (ቁ 5-15)።

ከዚያም በመቀጠል «የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ደስታ ናት እንጂ በመብልና በመጠጥ አይደለችም» በማለት ከላይ የተጠቀሰውን አንድነትና ኅብረት የሚጠብቅ አማኝ እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኝ ይነግረናል። ስለዚህም በመንፈስ ቅዱስ በመመራት፥ በርሱ ከሚገኝ ደስታና ሰላም እርስ በርሳችን የምንተናነጽበትን መንገድ መከተል አለብን። ስለዚህም በመብል ምክንያት እርስ በርሳችን እየተፈራረድን እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያቆመውን ሰላምና አንድነት ማፍረስ ተገቢ እንዳልሆነ ይነግረናል (16-20)።

15፥13

«የተስፋ አምላክም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላምን ይሙላባችሁ።»

በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ሐዋርያው ቅድም የጀመረውን ምክር በመቀጠል ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድክም ልንሸከም እንደሚገባን ይናገራል። ክርስቶስ

ራሱን ደስ ለማሰኘት እንዳልመጣ ሁሉ እኛም ደግሞ ሌሎች ወንድሞቻችንን ለናገለግል እንደሚገባን ያሳስባል። ስለዚህም አይሁዳዊም ሆነ አሕዛብ በመብል ሥርዓት ምክንያት እርስ በርስ ከመፈራረድ ይልቅ አንድ ልብ በመሆንና በአንድ አፍ እግዚአብሔርን አክብሩት ይላል (1-6)። ይሆንን አንድነትና ሕብረት ሊሰጣቸውም የሚችለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመሆኑ ሰላምና ደስታን እየሞላ ለእግዚአብሔር ክብር ያቆማቸዋል (7-13)።

ወንጌል የሚያድን የእግዚአብሔር ኃይል የሆነበትም ምክንያት በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ታትሞ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብሮ ስለታደለ ነው። ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ አሕዛብን ለወንጌል እንዲታዘዙ በማድረግ ለእግዚአብሔር ይለያቸዋል (ይቀድሳቸዋል)። አሕዛብ እንዲታዘዙ ሲባል ወንጌል ለእነርሱ የተሰበከው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሆነው ምልክትና ድንቅ ታምራት ነበር (15፥15-18)። በመጨረሻም ወደፊት የሚጠብቀውን አገልግሎት በመቀበል ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር እንዲጸልዩ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በልባቸው በፈሰሰው በመንፈስ ቅዱስ ፍቅር ያሳስባቸዋል (15፥30፤ 5፥5)።

«ፍቅርን ተከታተሉ፥ መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን በዛርቱ ፈልጉ።»

1ቆሮንቶስ 14፥1

10

መንፈስ ቅዱስና የቆሮንቶስ ሰዎች (1)

ጳውሎስ በመልእክቱ ላይ የቆሮንቶስ ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ በማመናቸው ምክንያት ስለ ተሰጣቸው የጸጋ ስጦታ ሁሌ እግዚአብሔርን ያመሰግናል። የርሱን ምስክርነት እግዚአብሔር ያጸናለት በቃልና [ሎጎስ] በእውቀት [ግኖሲስ] ሲሆን ይህም ደግሞ በጸጋ ስጦታዎች [ካሪዝማ] ባለጸጋዎች እንዲሆኑ በማድረግ ነው (1፥1-6)። የቃል ስጦታ [ሎጎስ] የሚባለው ትንቢትን፥ ማስተዋልና ጥበብ እንዲሁም በልሳን መናገርን ሲያጠቃልል

ይሆንንም በምዕራፍ አሥራ ሁለት ላይ በሰፋት እንመለከታለን።[81] ታዲያ ይህ የተሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታ የሚጠቅማቸው አሁን ለሚኖሩበት ዘመን ካለ ነቀፋ ለእግዚአብሔር እንዲኖሩ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የኢየሱስን ዳግም ምጽአት ሲጠባበቁ ለዚያች ለጌታ ቀን ያጸናቸዋል (7-9)።[82]

2፥4-7

ጳውሎስ በእነርሱ ዘንድ በነበረበት ጊዜ ኢየሱስን ከመስበክ በቀር ስለራሱ ስመመስከር አልሞከረም፤ ነገር ግን ወደ እነርሱ የሄደው በድካምና በብዙ መንቀጥቀጥ ነበር። በመሆኑም እምነታቸውም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን ቃሉም ስብከቱም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ። ደግሞም እርሱ የሚሰብከውን የመሰቀሉን ቃል እግዚአብሔር የሚያጠናለት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር። በተቃራኒው ደግሞ በቆሮንቶስ የነበሩ አንዳንድ «መንፈሳውያን» በኃይልና በድንቅ ተአምራት የሚሰበክ ሰው ምንም ዓይነት ሕመም ወይንም የሰውነት ድካም ሊኖረው አይገባም ይላሉ። በእነርሱ አባባል ሐዋርያው መልስ ሲሰጥ የእግዚአብሔር ኃይል በሰው ድካም ውስጥ እንደሚገለጥ እንጂ በሰው ጥበብና በሚያባብል ቃል ውስጥ እንዳልሆነ ይናገራል።

---

[81] ፊ፥ ጎደሰ ሊምፓወረንግ ፕሬዘንስ፥ ዘ ሆሊ ስፒሪት ኢን ዘ ሊተርስ ኦቭ ፖል፤ 85።

[82] የጌታ ቀን በአብራይስጡ [ዮም ኣዶናይ/ያህዌ] በመባል የሚታወቅ ሲሆን ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ ትርጉም ይዞ አናገኘዋለን። ይህም የጌታ ቀን የሚያሳየው እግዚአብሔር የሚፈርድበት፥ የሚያጠራበት፥ ለራሱ የሆኑትን ቅሬታዎች የሚሰበስብበት፥ ለሰሙ የሚበቀልበት፥ ለሕዝቡ በትንቢት የሚፈርድበት፥ ፍጥረትን የሚያድስበት፥ ሙሉ ነጻነትን የሚሰጠበትና ግዛቱንና ሥልጣኑን በምድር ላይ የሚያቋቁምበትና የሚያስፋፋበት ነው። ይህ «የጌታ ቀን» የሚለው ሃሳብ በመጀመሪያ የተገለጸው በነቢዩ በአሞጽ መጽሐፍ ላይ ሲሆን እግዚአብሔር በወቅቱ ይኖሩ የነበሩትን እስራኤላውያን ንስሃ ካልገቡ መጥቶ እንደሚቀጣቸው ይገልጻል። ከዚያም በመቀጠል በትንቢት ሆሴዕ ላይ ደግሞ የጌታ ቀን የሚለው አባባል የሰው ልጅ ለእግዚአብሔር የሚመልሰበት የመለኮታዊ ቅጣት ቀን እንደሆነ ይገልጻል። በትንቢተ ሚክያስ ደግሞ የጌታ ቀን ከእግዚአብሔር መገለጥ [ቲዮፋኒ] ጋር ያያይዘዋል። ትንቢተ ሶፎንያስ ደግሞ የጌታ ቀንን በመጨረሻው ሰዓት እግዚአብሔር መጥቶ እንደሚፈርድ በመግለጽ አስቀምጦታል። ይህኑ ዓይነት የመጨረሻው ሰዓት ፍርድን የሚያመለክት ከፍል በሌሎችም ነቢያት ተገልጸአል (ኢሳ 2፥12-18፤ 13፥6-9፤ 22፥5፤ 26፥21፤ ናሆም 1፥3-6፤ እንባቆም 2፥20፤ ኤርም 29፥23፤ 42፥5፤ ሚልኪ 3፥5፤ ማቴዎስ 25፥31-46)። በዚህ በቆሮንቶስ መልእክት ላይም ሐዋርያው «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቀን» በማለት የመጨረሻውን የፍርድ ቀን ማለትም የጌታ ቀንን ያሳያል— ዊልም ቩን ገመረን፥ ኢንተርፕሪቲንግ ዘ ፐርፈክት መርደ (ግራንድ ራፒድስ፥ ዞንደርቫን፤ 1990) 214፤

ፊ፥ ዘ ኔው ኢንተርናሽናል ኮሜንታሪ ኦን ዘ ኔው ቴስታመንት፥ ዘ ፊርስት ኢፒስትል ቱ ዘ ኮሪንቲያንስ (ግራንድ ራፒድስ፥ ኤርደመን አሳተሚ ድርጅት፤ 1987) 43።

ይህም የእግዚአብሔር ኃይል በድካም የሚገለጥ (4፥9-13)፥ ሕይወትን የሚለውጥና ቅድስናን የሚሰጥ (5፥3-5) እንጂ ዝም ብሎ በልሳን በመናገር ብዛት ወይም አዋቂ ልሁን ባይነት አይደለም (በልሳን መናገርን አይቃወምም ነገር ግን አንዳንድ የቆሮንቶስ አማኞች በልሳን በመናገራቸው ብዛት ከሁሉም የበለጡ መንፈሳውያን አድርገው ራሳቸውን ስለ ወሰዱ ነው)። በዚህ በምንኖርበት ዘመን መንፈሱ ጸጋንና ኃይልን በመስጠት በቃላችንና በሕይወታችን የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ አዋጅ ነጋሪዎች ያደርገናል። በመሆኑም የመሰቀሉ ቃል ለምንድነው ለእኛ ሞኝነት ነው። ምክንያቱም በሞኝነት ውስጥ የራሳችንን ቃልና ጥበብ ብልጫ ስለምንጥል የእግዚአብሔር ማስተዋል በዚያ ውስጥ ይገለጣል። ስለዚህም አማኞች ሁሉ በእግዚአብሔርን ጥበብና እውቀት ልንመካ ይገባናል እንጂ በራሳችን ልንመካና ራሳችንን ልንሰብክ አይገባንም።

2፥6-3፥2

እኛ በበሰሉት መካከል የምንናገረው ጥበብ የሚሻሩትን የዚችን ዓለም ጥበብ አይደለም። ነገር ግን ይህ ጥበብ አይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወድዱት ያዘጋጀው ነው። ይህ ጥበብ ከዘመናት በፊት እግዚአብሔር ለክብራችን የወሰነው ሲሆን እርሱም ደህን ነታችን ወይም የመሰቀሉ ቃል ነው (ዮሐ 17)። እግዚአብሔርም ይህንን ጥበብ በመንፈሱ በኩል ለእኛ ገለጠው፥ ወንጌል በመገለጥ ኃይል መጥቶአልና።

ይህም ጥበብ የሚገኘው በመንፈስ ሲሆን መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ አሳብ ይመረምርና ለእኛ ይነገረናል። የተቀበልነው የእግዚአብሔርን መንፈስ ስለሆነ መንፈሳዊዉን ነገር ከመንፈሳዊ ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ጥበብን እንናገራለን። እዚህ ላይ የምንመለከተው ነገር ቢኖር የእግዚአብሔር ጥበብ (የመሰቀሉ ቃል) የሚታወቀው በእግዚአብሔር ሕዝብ ብቻ መሆኑ ነው (2፥6-13)።

አንዳንድ ራሳቸውን «የላቁ መንፈሳዊ» ያደረጉ ሰዎች ሐዋርያትን እንመርምር በማለት ራሳቸውን ከፍ ከፍ ያደርጋሉ። ሐዋርያው አነርሱን አስመልክቶ ሲናገር ስፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት በመሆኑ ፍጥረታዊ ሰው ሊያውቀው አይችልም ብሎአል። ምክንያቱም መንፈሳዊ ነገር

በመንፈስ የሚመረመር ስለሆነ የመንፈስ ነገር ያልገባው ወይም መንፈስ ቅዱስ የሌለው ሰው (ፍጥረታዊ ሰው) ሊያውቀው አይችልም። «መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል እርሱ ግን በማንም አይመረመርም» ምክንያቱም የሚያስተምረው መንፈስ (የክርስቶስ ልብ) ስለ አለው ነው (14-17)። በመቀጠልም ቅናትና ክርክር እንዲሁም መከፋፈል በመካከላቸው ስለ አለ መንፈሳውያን ሳይሆኑ ሥጋውያን መሆናቸውን ይናገራል። ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆኑት ሰላምና ፍቅር አይታይባቸውምና ነው (3፥1-4)።

በመቀጠልም ጳውሎስ መሪ ነን ስሚሉት ሲናገር — «አንዱ እኔ የጳውሎስ ነኝ» ሲል ሌላኛው ደግሞ «እኔ የአጵሎስ ነኝ» ቢል ምንድነው የሚጠቅመው? በማለት እርሱ ቢተክልና አጵሎስ ደግሞ ቢያጠጣ የሚያሳድገው እግዚአብሔር ስለሆነ መከፋፈል እንደማያስፈልግ ይናገራል። በመቀጠልም አናንተ የእግዚአብሔር እርሻና ሕንፃ ናችሁ፥ እኛ ደግሞ ከርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነን በማለት ሕዝቡን ከፋፍሎ መግዛት ተገቢ እንዳልሆነ ይናገራል።

ስለሆነም መሪዎቹ እግዚአብሔር የሕዝቡ ባለቤት እንደሆነ አውቀው ሕዝቡን በፍቅርና በጎብረት መምራት እንዳለባቸው በብርቱ ቃል ይመክራቸዋል (3፥5-9)። ስለዚህም ይህንን ሕንፃ እንዴት እንደሚያንጽ ሁሉም መጠንቀቅ አለበት (3፥10)። ምክንያቱም ከኢየሱስ በቀር ሌላ መሠረት የለምና ነው (ቁ 11)። ሥጋዊው ጥበብ በእንጨት፥ በአገዳና በሣር ቢያንጽም (በመከፋፈል ማለት ነው) ቅሉ ሁሉም በጌታ የሚፈተንበት ጊዜ ይመጣል (ቁ 12)። ስለዚህም በሥጋዊ ጥበብ በመመራት ቤተክርስቲያንን በመከፋፈል የሚያጠፉትን ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ያስጠነቅቃል (ቁ 13-15)። አንደገናም «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?» ሲል ይህንን ቤተ መቅደስ የሚያፈርሰውን እግዚአብሔር እንደ ሚያፈርሰው ይናገራል (16-17)። በሌላ አነጋገር ከላይ እንደተመለከትነው በእገዳና በሣር የሚያንጹ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ የሚያፈርሱ ስለሆኑ ታላቅ የሆነን ፍርድ ይጠብቃሉ።

በዚህ ክፍል ማጎበረ ምዕመኑ «የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ» ተብሎ ተጠርቶአል። ምክንያቱም ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ እንደተነጋገርነዉ እግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችንና በመካከላችን በመገኘቱ የርሱ ቤተ መቅደስ

ስለ አደረገን ነው። ከዚህ በፊት እንደተነጋገርነው ሁሉ በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ የለያቸው ነገር ቢኖር የእግዚአብሔር በመካከላቸው መገኘት ነበር።[83] ቢሆንም ቅሉ ሕዝቡ «ቤተመቅደስ» በመባልተጠርተው አያውቁም። በአዲስ ኪዳን ዘመን የምንኖር እኛ ግን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተብለን ተጠርተናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር በመካከላችን ብቻ ሳይሆን በውስጣችንም ጭምር ስለሚያድር ነው። የቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ደግሞ ከዚህ በፊት እንደተነጋገርነው በትንቢት ሕዝቅኤልና ኢዩኤል ላይ ያለው ራእይ ፍጻሜ ነው (ሕዝቅኤል ምዕራፍ 40-48፤ ኢዩ 2፥28-32)።

6፥11

የዚህን ክፍል ቅድመ አገባብ ስንመለከት ጳውሎስ «ከእናንተ አንዱ ከባልንጀራው ጋር ሙግት ቢኖረው በቅዱሳን ፊት በመፋረድ ፋንታ እንዴት በአመፀኞች ፊት ሊፋረድ ይደፍራልን?» በማለት ዓለም በእኛ ላይ እንድትፈርድ ሳይሆን እኛ ቅዱሳን በዓለም ላይ ለመፍረድ ሥልጣን እንዳለን ይናገራል። በትዳር ጉዳይና እርስ በርስ ሙግትን በተመለከተ የፍርድ ቤት ቢያስፈልገን ወደ ዓለም ሄደን ከመከሰስ ይልቅ በቤተክርስቲያን ውስጥ ጉዳያችንን መጨረስ ይኖርብናል። እንዲያውም ቢቻልስ ተበድሎ ይቅር በማለት ነገርን ሁሉ መተው ይሻላል። ምክንያቱም እኛ በኢየሱስ የዳንን፥ በመንፈስ ቅዱስ የታጥብንና የተቀደሰን የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች ነን። በዓለም ያሉቱ ግን አመጸኞች ስለሆኑ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች አይደሉም። ስለዚህም መከሰስ፥ መለያየት፥ ሙግትና አመጸኛነት ከእነርሱ ዘንድ ናቸውና። በመሆኑም በኢየሱስ ሰም የዳነውንና በመንፈስ ቅዱስ የተቀደሰውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የእግዚአብሔርን መንግሥት የማይወርሱ አመጸኞች ሊዳኙት አይችሉም።

---

83 ፊ፥ ጎደስ ኢምፓወረንግ ፕረዘንስ፡ ዘ ሆሊ ስፒረት ኢን ዘ ሴተርስ ኦቭ ፖል ፤ 114። ይህን አሳብ ከዚህ በፊት ተገልጸ አናተሞስን (በምአራፍ 2)። የእግዚአብሔርን ሕዝብ የለያቸው የእግዚአብሔር መንፈስ መገኘት ነው ሲባል ሕጉና የአምልኮ ሥርዓቱ ምንም ቦታ እንደሌለው መቁጠር አይደለም። ነገር ግን ስለነዚህ ሁሉ ዋናው ምክንያትና ምክንያት የሆነው የእግዚአብሔር መገኘት ነው። ስለሆነም የሰጪው (የእግዚአብሔር) መገኘት ነው ሕዝቡን ከሌላው አሕዛብ የለየው።

6፥12-20

በዚህ ክፍል ደግሞ ምንም እንኳን ሁሉም ነገር ቢፈቀድልን (ማለት ም አትንካ አትቅመስ ከሚል ከሕግ ባርነት ነፃ ብንሆንም) አንድ ነገር ስንኳን ሊሰለጥንብን አይገባንም ምክንያቱም ሰውነታችን የክርስቶስ ነውና (ቁ. 12፤ ገላት 5፥1 ተመልከት)። የርሱም የሆነበት ምክንያት — 1ኛ. ክርስቶስ በመስቀል ላይ በዋጋ ገዝቶናል። 2ኛ. ከጌታ ጋር በመተባበር አንድ መንፈስ ሆነናል። 3ኛ. በመንፈስ ቅዱስ ታጥበን፥ ተቀድሰን እንዲሁም ጸድቀናል። 4ኛ. የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ሆነናል። ስለዚህም እግዚአብሔር ጌታችንን ኢየሱስን ከሞት በአስነሣበት መንፈስ የእኛንም ሥጋ በመጨረሻው ቀን ከሞት ያስነሣዋል። በመሆኑም ሰውነታችን የእግዚአብሔር አንጂ የእኛ ስላልሆነ ራሳችንን እየቀደስን፥ ከዝሙትም እየራቅን በሥጋችን እግዚአብሔርን ልናከብር ይገባናል (11-20)።

ምዕራፍ 12-14

በዚህ ክፍል ከምዕራፍ አሥራ ሁለት እስከ አሥራ አራት ድረስ ስለ መንፈስ ቅዱስና መንፈሳዊ ስጦታዎች ከየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይልቅ ተብራርቶ እናገኛለን። ሐዋርያውም ምዕራፉን ሲጀምር «ስለ መንፈሳዊ [ፐኦማቲኮን] ነገርም ወንድሞች ሆይ፥ ታውቁ ዘንድ አወዳለሁ።» (12፤1) በማለት ከመዳናቸው በፊት ድምጽ የሌላቸውን ጣዖታት በማምለክ ጠፍተው እነደነበር ያስታውሳቸዋል። ከዚያም በመቀጠል ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ሆኖ «ኢየሱስ የተረገመ ነው» የሚል እንደሌለ፥ እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በተቀር «ኢየሱስ ጌታ ነው» ሊል ማንም እንደማይችል ይነግራቸዋል። የቆሮንቶስ ሰዎች ወደ ጌታ ከመምጣታቸው በፊት፥ ጣዖታትን በሚያመልኩበት ጊዜ በተለይ ደግሞ በአምልኮ ፍንደቃ [Ecstacy] ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ ኢየሱስን መርገም አንዱ የሥርዓቱ ባሕርይ ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል።

አሁን ግን በጌታ መንፈስ በመሞላታቸው ኢየሱስ ጌታ ነው ይላሉ እንጂ አይራገሙም።[84]

ስለዚህም በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ያለው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በመንፈስ ቅዱስ ከተሰጠ ስጦታ የመነጨ በመሆኑ የኢየሱስን ጌታነት የሚያጎላ ነው። ታዲያ ይህንን ስጦታ ከእግዚአብሔር ነው ብለው ለመቀበል ላቃታቸው ለአንዳንድ የቆሮንቶስ አማኞች ሐዋርያው — «በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ በስተቀር — ኢየሱስ ጌታ ነው» የሚል የለም በማለት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከሚሰጡ ወይም ከሚመጡ መልእክቶች [*Prophetic utterances*] በስተቀር የማያታት አም ልኮ የኢየሱስን ጌትነትና አምላክነት ሊያጎሉ እንደማይችሉ በመንገር ያረጋጋቸዋል። በመቀጠልም የጸጋ ስጦታዎች አንድነታቸውና ልዩነታቸውን በዝርዝር አቅርቦላቸዋል —

የጸጋ ስጦታዎች (ስአላዊ መግለጫ ቁ. 4)

ልዩነታቸው	አንድነታቸው
የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነው	መንፈስ ግን አንድ ነው
አገልግሎት ልዩ ልዩ ነው	ጌታ ግን አንድ ነው
ለአያንዳንዱ መገለጥን	እግዚአብሔር ግን አንድ ነው
ለአንዱ ጥበብን መናገር	ሰጪው መንፈስ ነው
ለአንዱ እውቀትን መናገር	በዚያው መንፈስ
ለአንዱም እምነትን	በዚያው መንፈስ
ለአንዱ የመፈወስ ስጦታን	በአንዱ መንፈስ
ለአንዱ ትንቢትን መናገር	በአንዱ መንፈስ
ለአንዱም መናፍስትን መለየት	በአንዱ መንፈስ
ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር	በአንዱ መንፈስ
ለአንዱም በልሳን የተነገረውን መተርጎም	በአንዱ መንፈስ

84

ዲ. ኤ. ካርሰን፣ *ፆዊንግ ዘ ስፒሪት*፣ ኤ. ቲኦሎጂካል ኤክስፖዚሽን ኦቭ ፈርስት ኮረንቲያንስ 12-14_

ከላይ የተጠቀሱትን ስጦታዎች በመዘርዘር ሰጪው መንፈስ ቅዱስ፣ ጌታ ኢየሱስ (ወልድ) ና እግዚአብሔር (አብ) አንድ ነው በማለት የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት ያሳየናል። ምንም እንኳን ቤተክርስቲያን ብዙ ብልቶችና ስጦታዎች ቢኖራትም አንድ አካል በመሆኑዋ እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ፣ አንድ አካል እንድንሆን ይህንኑ አንዱን መንፈስ ጠጥተናል። ስለሆነም በመንፈስ ቅዱስ ያገኘነውን አንድነት እንድንጠብቅ ያሳስበናል 12፤4-26)።

ስለ ልዩነታችንም [*Diversity*] ደግሞ አስመልክቶ፣ በክርስቶስ አካል ውስጥ የተለያየ ብልቶች በመሆናችን እግዚአብሔርም — አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፣ ሁለተኛም ነቢያትን፣ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፣ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፣ ቀጥሎም የመፈወስ ስጦታን፣ እርዳታን፣ አገዛዝንና ልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችን አድርጎአል በማለት ይናገራል (12፤27-31)። ስለሆነም እግዚአብሔር አንድነቱ በሦስትነቱ፣ ሦስትነቱ ደግሞ አንድነቱ ተጠቃሎ የሚኖር እንደሆነና ስጦታዎቹንም እንደሰጠን እኛም ደግሞ ልዩነታችንን [Diversity] ይዘን በመቅረብ በአንድነት መሥራት ይኖርብናል።

እነዚህ ሁሉ የተለያዩ ስጦታዎች ቤተክርስቲያንን ለማነጽ በአንድነት ተጋጥመው መሥራት አለባቸው። ምንም እንኳን በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብንናገር፣ ደግሞ በተሰጠን የእምነት ስጦታ ተራሮችን ማፍለስ ብንችል፣ ወይንም ምስጢርንና እውቀትን የመግለጥ ስጦታ ቢኖረን በመከከላችን ያለውን መከፋፈል አጥፍተን፣ በኅብረትና በአንድነት ለመኖር የሚያስችለንን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነው ፍቅር ከሌለን ልክ እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚንቆረቆረው ጽናጽል ነን። የክርስትና ዋናው ቁም ነገር ስጦታዎቻችንን ለሰዎች እዩልን ማለት ሳይሆን የመንፈስ ፍሬን አፍርቶ መገኘት እንደሆነ ከዚህ ክፍል እንማራለን (12፤29-3፤1-13)።

በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ አንዳንዶች በልሳን በመጸለያቸውና አንዳንድ ስጦታዎችንም በመቀበላቸው ራሳቸውን በጣም «መንፈሳዊ» አድርጎ በመውሰድ ባሎች ከሚሰቶቻቸው ጋር መተኛትን እንኳን እስከ መከልከል ደርሰው ነበር (7፤1-7)። ስጦታዎቹም ስለ ነበራቸው የእግዚአብሔርን መንግሥት

(ግራንድ ራፒድስ፣ ቤከር ቡክ ሃውስ፣ 1987) 24-25።

አሁን በሚኖሩት ኑሮ በሙላት ያገኙ መስሎአቸውም ነበር። በዚህም ምክንያት ወደፊት የሚመጣ የሙታን ትንሣኤ አይኖርም በሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ውስጥ ተዘፈው ። ጳውሎስም ይህንን አስመልክቶ «ሙታን የማይነሱ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሣማ ?» ክርስቶስ ካልተነሳ ደግሞ ኃጢአታችሁን ይቅር ለማለት ስለማይችል «አሁንም በኃጢአታችሁ አላችሁ» በማለት «በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን» በማለት አሰ ተሳሰባቸውን አረመው (15፤1-58)።

የጳውሎስ የሕይወት ልምምድ እንደሚያሳየን ከሆነ በመንፈስ መኖር ማለት በድካም (በሕመም፣ በችግር ወዘተ) መኖር ሲሆን ይህም ማለት ደግሞ በርሱ ደካማነት የእግዚአብሔር ኃይል ይገለጣል። እርሱ ደካማ ሲሆን እግዚአብሔር በርሱ ይበረታል፤ ስለ ክርስቶስ ሲደክም፣ ሲንገላታ፣ በችግር፣ በጭንቀት ና በሕመም ደስ ይለዋል ምክንያቱም በድካሙ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በሙላት ስለሚገለጥ ኃይለኛ ያደርገዋል (2ቆሮ 12፤9-11)። በተቃራኒው ይህ ዓይነቱ የሕይወት ልምምድና መረዳት በቆሮንቶስ ላሉ፣ ከሁሉም የላቁ መንፈሳውያን አድርገው ራሳቸውን ለወሰዱት መሪዎች የማይጥም ነው። ምክንያቱም እንደ እነርሱ አስተሳሰብ መንፈሳዊ ሰው በድካም መታወቅ የለበትምና ነው (2ቆሮ 11፤ 1-11)።

14፤1-40

በዚህ ምዕራፍ ጳውሎስ እንደገና «ፍቅርን ተከታተሉ፣ መንፈሳዊ ስጦታ ንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ» በማለት ሊኖሩት የሚገባው ኑሮ በፍቅር የተሞላ ሆኖ ስሌላው ወንድም በማስብና በመተናነጽ እንጂ መንፈሳ ዊ ጡንቻን በማሳየት መሆን እንደሌለበት ይመክራል። ስለሆነም በልሳን መጸለ ይን አማኞች በግል ሕይወታቸውና በጓደኞቹ እንዲለማመዱና በጎብረት በሚሰበ ሰቡበት ጊዜ ሊጠቀሙበት የሚገባቸው ጉባኤውን ሊያንጽ በሚችል መንገድ መሆን እንዳለበት ያስገንዝባቸዋል። ትንቢት የሚናገር ጉባኤውን ለማነጽ፣ ለመምከርና ለማጽናናት ይናገራል። ምልክትነቱ ለሚያምኑት ቢሆንም የማያምኑ ትን ሰዎች ልብ በመመርመር ይወቅሳል፣ በልባቸውም የተሰወረውን ነገር በመግ

ለጥ ለእግዚአብሔር እንዲንበረከኩ ያደርጋል (24-25)። በልሳን የሚናገር ደግሞ ለእግዚአብሔር ይናገራል፣ ምልክትነቱም ለማያምኑት ነው እንጂ ለሚያምኑት አይደለም (ኢሳ 28፤11)። በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፣ በመንፈስም ምስ ጢርን ይገልጻል (20-22)።

ትንቢት በልሳን መልክ ይሁን ወይም በቀጥታ ይምጣ መልእክቱ በሌ ሎች ነቢያት መለየት ወይም መመርመር አለበት። በነገራችን ላይ ጳውሎስ ከሁለት ወይም ከሦስት በላይ የትንቢት መልእክት በአንድ ስብሰባ ጊዜ እይፈቅ ድም (ቁ. 26-33)። በልሳን የሚናገር ቢኖር ንግግሩን ይተርጉም ወይም ደግሞ ሌላ ሰው ይተርጉመው። ነገር ግን ትርጉም የሌለው ከሆነ ጸጥ ብሎ ስራሱና ለእግዚአብሔር መናገር አለበት (ቁ. 5፤ 27-28)።

ከላይ እንደተመለከትነው ሁለት ዓይነት የልሳን አጠቃቀም አለ – አን ደኛው በልሳን መጸለይ ሲሆን ይህም በግል ሕይወታችን የምንለማመደው ነው። የልሳን ጸሎት የመንፈስ ጸሎት በመሆኑ ራሳችንን ያንጸናል (ጳውሎስ ራሱ ከሁላ ቸው ይልቅ በልሳን ስለሚናገር እግዚአብሔርን ያመሰግናል፣ ቁ. 3፤ 18)። ሁለተ ኛው ደግሞ በልሳን የትንቢትን መልእክት መናገር ሲሆን የምንጠቀምበትም ጉባ ኤውን ለማነጽ በመሆኑ ሙተርጎም አለበት (27-28)። በልሳን መናገር ለሁሉም አማኞች የተሰጠ ስጦታ ነው (ምንም እንኳን ሁሉም አማኞች ባይኖራቸውም፣ ኢዩ. 2፤28-30)። መንፈሱን በሙላት ያገኘ ሁሉ የትንቢትን ስጦታ ሊቀበል ይችላል (ሐዋ 2፤17-18፤ 1ተሰሎ 5፤19-22፤ 2ተሰሎ 2፤2፤ ሮሜ 12፤6)። ስጦታ ውም በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ወይም ግፊት በጉባኤ ወይም በጎብረት መከከል የሚመጣ መልእክት ነው (29-33)።

«በክርስቶስም ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፥ ደግሞም ያተመን የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው።»

2ቆሮንቶስ 1፥21-22

11

መንፈስ ቅዱስና የቆሮንቶስ ሰዎች (2)

የቆሮንቶስ አማኞችን ቲቶ በጎበኛቸው ጊዜ ለጳውሎስ የወቀሳ ደብዳቤ በርሱ እጅ አከውለት ነበር (2፥12-13፤ 7፥6)። በደብዳቤውም፥ 1ኛ. የመልእክቶቹን አሳብ ለመረዳት አስቸጋሪ እንደሆነ (12-14)፣ 2ኛ. ሊጎበኛቸው አስቦ ለምን አሳቡን እንደቀየረ (15-23)፤ 3ኛ. በሥልጣኑ ሊጫናቸው እንደሚፈልግ በወቀሳቸው ጠቅሰውታል (24-24)።[85] ጳውሎስ ለዚህ ወቀሳ መልስ ሲሰጥ — በእግዚአብሔር ቅድስናና ቅንነት እንደሚመላለስ በመናገር ስለ መልእክቱም ከሚያስተውሉትና ከሚያነቡት በስተቀር ከዚህ በኋላ

ሌላ ከባድ መልእክት እንደማይጽፍላቸው ይነግራቸዋል።

ወደ እነሱ ሳይሄድ የቀረበትን ጉዳይ ደግሞ ሲናገር — «ለእናንተ የሚነገረው ቃላችን እምነና አይደለም አይሆንም» በማለት በርሱ የሚነገረው ቃል እምን እንደሆነ ይናገራል። እርሱ የሚያስበው በዓለማዊ ልማድ ስላልሆነ ቃሉ እምን ነው። ምክንያቱም ወደ እነርሱ ዳግም ያልሄደበት ምክንያት ደግሞ እንደገና በኃጢአት የተያዙትን በማሰብ ቤሐዘን ወደ እነርሱ እንዳይመጣ፤ ከዚያም እነርሱንም በመቅጣት ልቡ እንዳያዝን በማሰብ መሆኑ ነበር እንጂ ሃሳበ ወላዋይ ሆኖ አልነበረም። በሌላ አነጋገር አለመሄዱ ለእነርሱ እንዴት እንደሚራራ ያሳያል። በመጨረሻም ርሱ፥ በሰልዋኖስና በጢሞቴዎስ በኩል የተሰበከው የእግዚአብሔር ልጅም አምን ነው (ማለትም ወደ እነርሱ ለመሄድ አስቦ ቢቀርም እንኳ እግዚአብሔር ግን ታማኝ ስለሆነ እንደርሱ አሳቡን አይቀይርም። እግዚአብሔር የገባውን ተስፋ ሁሉ በርሱና በነጢሞቴዎስ በተሰበከው በልጁ በኩል ስለሚፈጽመው ሁሉ አሜን ነው)።

በመቀጠልም ስለዚህ ክቡር አገልግሎት ያጸናቸው፥ የቀባቸው፥ ያተማቸውና መንፈሱንም ልባቸው የሰጠ እግዚአብሔር እንጂ ሰው እንዳልሆነ ይናገራል (15-22)። ይህም አባባል የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ያሳየናል —

- *መጽናት* – እግዚአብሔር ታማኝ ስለሆነና አሳቡን የሚቀይር ስላልሆነ ማለትም አሜን ስለሆነ፥ (ቁ 19) እስከ መጨረሻው ድረስ ልጆቹን በመካከላቸው በተሰበከው በክርስቶስ ኢየሱስ ያቆማቸዋል፥ ይጠብቃቸዋልም።[86] ይህም ዋስትናችን በመሆኑ እንደ ታላቅ የሆነን ተስፋ ይሞላብናል።
- *ቅባት* — መቀባታችን ደግሞ የክርስቶስ እንድንሆን እደረገን (1ዮሐ 2፥20፤27)። ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ በመቀባቱ መሢሕ ወይም ክርስቶስ ተባለ ትርጓሜውም የተቀባ ማለት ነው (በተለየ መንገድ)።

---

[85] ኢንዳ ኢል በለሽል፥ *ሰከንድ ኮረንቲያንስ* (ዶውነርስ ግሮቭ፥ ኢንተርቫርሲቲ ፕረስ፤ 1996) 60-61።

[86] ፖል ባርኔት፥ *ዘ ሰከንድ ኤፒስትል ቱ ዘ ኮረንቲያንስ* (ግራንድ ራፒድስ፥ ኤርድመንስ አሳታሚ ድርጅት፤ 1997) 111-113።

የሐዋርያነት ሥልጣንህን ተጠቅመህ ትጫነናለህ ተብሎ ለቀረበበት ክስ ደግሞ ሲመልስ ለደስታችሁ ከእናንተ ጋር የምንሠራ ነን እንጂ በእምነታችሁ በእናንተ ላይ የምንገዛ አይደለንም በማለት ግንም ግንን ሊገዛ እንደማይችል ይገልጽላቸዋል (24)። እንደሚታወቀው ሁሉ የመጀመሪያውን መልእክት ሲጽፍላቸው ጋጢአት የሠሩትን ቤተክርስቲያን እንድትገሰጽና ራሱዋን እንድታጠራ ነበር (1 ቆር 4፤14-5፤1-13)። ታዲያ ይህንን ማድረጉ ስለሚወዳቸው እንጂ በእነርሱ ላይ ሊገዛ አለመሆኑን ሲናገር–«በብዙ መከራና ከልብ ጭንቀት በብዙም እንባ ጽፌላችሁ ነበርና፤ ይህም እናንተን አብዝቼ የምወድበትን ፍቅር እንድታውቁ እንጂ እንዳሳዝናችሁ አይደለም።» (2 ቆር 2፤4) በማለት መንፈሳዊ ቅጣት እግዚአብሔርን ከመውደድ የሚመጣ ሥነሥርዓት እንጂ ከዋላቻና ሥልጣንን ተገን በማድረግ የመጣ አለመሆኑን አብራርቶታል።

3፤1-18

ሐዋርያው አገልግሎቱን የሚታወሙትን ሰዎች በማጋለጥ አርሱና አብረውት የሚያገለግሉት እንደ አንዳንዶቹ የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚ ሸቅጡት እንዳይደሉ ይናገርና በቅንነት ከእግዚአብሔር የተላኩ መሆናቸውን ይመሰክራል (2፤16-17)። አርሱ ራሱን አያመሰግንም ወይንም እንደ ተቃዋሚዎ ቹ ሁሉ ስለ ራሱ በመጻፍ መልእክት አይልክም። ምክንያቱም የርሱ አውነተ ኛነት የሚለካው በአገልግሎት ፍሬው ነው። የአገልግሎት ፍሬው ከሆኑት ውስጥ ደግሞ እንዱ አነርሱ እንደ መሆናቸው መጠን ሕይወታቸው ስለ አርሱ ማንነት ይናገራል ማለት ነው። ስለሆነም እነርሱ «በልብ ጽላት የተጻፈ...የክ ርስቶስ መልእክት» ናቸው (ቁ 1-2)።

በመጨረሻም ተቃዋሚዎች ጳውሎስን በመቃወም የጻፉት ደብዳቤ በእጅ የተጻፈ ሲሆን፥ አርሱ ግን የራሱን ማንነት የሚገልጽ የመከላከያ ደብዳቤ አይ ጽፍም። ምክንያቱም ስለ ርሱ ማንነት የሚገልጸው ምስክርነት በመንፈስ በሰዎ ች ልብ ውስጥ የተጻፈ ስለሆነ ነው። ይህም ማለት በርሱ ስብከት መንፈስ ቅዱስ የሰዎችን ሕይወት በመቀየር ልባቸውን አትሞአቸዋልና ነው። ስለሆነም የአገልግሎቱ ፍሬ ስለ አርሱ ማንነት ይናገራል።

ስለዚህም እግዚአብሔር ልጆቹን ከልጁ ጋር አንድ እንዲሆኑ በማ ድረግ በመንፈሱ ይቀባቸዋል።[87]

- *ጎትመት —* በጥንቱ የጽርአ–ሮሜ ክፍል ውስጥ ዕቃ ካንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ በሚላክበት ጊዜ በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ ውስጥ ይደረግና የባለቤቱ ማኅተም ይመታበታል። ይህም የባለቤትነትንና የዕቃውን ትክክለኛነት ማረጋገጫ ስለሆነ ከተላከለት ሰው በስተቀ ር ማንም ሰው ሊከፍተው አይፈቀድለትም ነበር። ሐዋርያውም ይህንን ያነጋገር ዘይቤ በመጠቀም እግዚአብሔር በመንፈሱ ስላተ መን ማንም ወይም ምንም ነገር ሊነካን አይችልም ምክንያቱም የእግዚብሔር የባለቤትነቱ ልዩ ማኅተም አለብንና ነው ብሎ ይናገራል። እዚህ ላይ ማኅተም የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱሳ ችን ውስጥ በሌላም ስፍራ ተጠቅሶ እናያለን (ኤፌ 1፤13፤ 4፤30፤ ሮሜ 15፤28፤ 1ቆሮ 9፤2፤ ሮሜ 4፤11፤ 2ጢሞቴ 2፤19)።
- *የመንፈሱ መያዣ –* ይህ አባባል ደግሞ በውል ላይ ያተኮረ የዕቃ ግዢና ልውውጥ ስሌትን የሚያሳይ ሲሆን ሰዎች አንድን ዕቃ ለመ ግዛት ሲፈልጉ ሙሉ ዋጋውን ለመሉ ከፍለው እስኪ ወሰዱ ድረስ ሌላ ሰው መጥቶ እንዳይወስድባቸው ሲሉ ቀብዲ ይከፍላሉ። እዚ ህም ላይ ጳውሎስ ሲናገር እግዚአብሔር የመንፈሱን መያዣ በልባ ችን በማስቀመጥ፥ በዕለተ ምጽአት ጠቅልሎ የራሱ እስከሚያደ ርገን ድረስ ቀብዲ ከፍሎብናል በማለት በዋጋ እንደተገዛን ይነግረና ል። ይህም ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ ታላቅ የሆነ እምነት እንዲኖረን ያበረታታናል። ቀብዲም የተከፈለልን መንፈስ ቅዱስን በልባችን በማስቀመጥ ስለሆነ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሆንን (1ተሰሎ 4፤8፤ 1ቆሮ 6፤19፤ ገላ 4፤6 ፤ ሮሜ 8፤9-26)።

[87] ፊተ ጎደስ ሊምፓመሪንግ ፕሬዘንስ ፤292።

የቆሮንቶስ አማኞች በርሱ አገልግሎት ከርሰቶስን በማግኘታቸው መንፈ
ሱን ስለተቀበሉ እግዚአብሔር ድንጋዱን ልብ አውጥቶ የሥጋ ልብን ሰጣቸው
(ሕዝ 11፥19፤ 36፥26)። ስለዚህም ይህ አዲስ ልብ የሚያስችላቸው በድሮው
በሲና በተሰጠው የድንጋይ ጽላት (በሕግ ኩነኔ ሥር) እንዲኖሩ ሳይሆን ነገር ግን
(ሕይወትን በሚሰጠው በመንፈሱ) በልባቸው በተጻፈው ጽላት ነው (ዘጸ 34፥1)።
ስለዚህም እነርሱ የርሱ መልክእት ሆኑ ማለት በእጅ ያልተጻፈ የክርስቶስ መል
እክት ሆኑ ማለት ነው። ወይም በሌላ አነጋገር የጳውሎስና አብረውት ወንጌ
ልን የሚሰብኩት የቃሉ አገልጋዮች እውነተኛነትን የሚመሰክረው የክርስቶስ መን
ፈስ ሲሆን፥ ይህም በአገልግሎታቸው አማካኝነት በዳኑት ሰዎች ውስጥ በመሆን
ነው (ቁ 3)።

ስለዚህም ይላል ሐዋርያው ሲናገር «ብታታችን ከእግዚአብሔር ነው
እንጂ፥ በገዛ እጃችን እንደሚሆን እንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደ
ለንም።» በማለት እግዚአብሔር በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ
ኪዳን አገልጋዮች አድርጎ እንደጠራቸው ይናገራል (4-5)። የአዲስ ኪዳንም
አገልጋዮች በመሆናቸው ወንጌልን የሚሰብኩበትን ብቃት ያገኙት ከእግዚአብሔር
መንፈስ በሚገኝ ኃይል ነው። በመቀጠልም ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ሕይ
ወትን ይሰጣል ብሎአል። በርግጥም ሕጉ ቅዱስና በጎ ቢሆንም የማይጠብቀው
ሁሉ ከእርግማን በታች ነው፥ እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ–«የዚህን ሕግ ቃሎች
ያደርግ ዘንድ የማያጸና ርጉም ይሁን» (ዘዳግ 27፥26)። ታዲያ ማንምሕግን
ሙሉ ለሙሉ ሊጠብቅ ስላልቻለ ሰው ሁሉ ከእርግማን በታች ሆነ። ስለዚህም
ነው ጳውሎስ «ፊደል ይገድላል» ብሎ የሚናገረው።

ታዲያ ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸው ሰውን ሁሉ ከሞት እር
ግማን ሥር ያስቀመጠው አገልግሎት በክብር ከሆነ፥ የመንፈስ አገልግሎት እን
ዴት በክብር አይሆንም? ያ የኩነኔ አገልግሎት (ክብሩን ያጣው፥ እንዲሁም
የተሻረው አገልግሎት) በክብር ከሆነ የጽድቅ፥ አጅግ የሚበልጥ፥ የከበረና ጸንቶ
የሚኖረው አገልግሎት አጅግ ይልቅ በክብር ሆኖአል በማለት የመንፈስ ቅዱስ
አገልግሎትን ከሕግ አገልግሎት አጅግ የላቀ መሆኑን ይነግረናል። ከዚህ በፊት
እንደተነጋገርነው ሕጉ የተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ቢሆንም ከመንፈስ

ቅዱስ ጋር አብሮ ስላልታደለ በሰው ላይ መፍረድ እንጂ ነፃ ለማድረግ ኃይል
ያጣ በመሆኑ ደካማና የማይጠቅም ነበር።

ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ የሊየሱስን ሞትና ትንሣኤ ይዞ የመጣ የጽድቅ
አገልግሎት በመሆኑ አማኞችን ከሕግ በላይ (ኩነኔና ተገዥነት) እንዲኖሩ ያስ
ችላቸዋል። ስለሆነም መንፈሱ ያላቸው የሙሴ መጋረጃ በለ ተገፈፈላቸው ወደ
እግዚአብሔር ለመቅረብ በመቻላቸው የእግዚአብሔርን ክብር ያያሉ (ወደ
አርሱ በድፍረት መግባት ስለቻሉ፥ ዕብ 10፥19-20)። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር
ሲነጋገር መሸፈኛውን ከፊቱ ያነሳ ነበር፤ ወደ ሕዝቡ ሲመጣ ግን ፊቱን (ፊቱ
ላይ የሚታየውን የእግዚአብሔር ክብር) ይሸፍን ነበር (ዘጸ 34፥34)። ጳውሎስ
ግን የእግዚአብሔር ክብር የሆነውን የሊየሱስን ቢያንጸባርቅም (ስለለበሰው)
ፊቱን አይሸፍንም። ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ አርነት አለና አማኞች የጌታን
ክብር በነጻነት ያገኙታል፥ የርሱንም መልክ ይመስሉ ዘንድ ከክብር ወደ ክብር
አብረውት (ከጳውሎስ ጋር) ይለወጣሉ (7-18)።

6፥6-7

የጳውሎስ ተቃዋሚዎች ራሳቸውን የሚያመሰግኑና የሚያወድሱ እንዲ
ሁም በትዕቢት የተሞሉ ናቸው (11፥1-12፥12ን ተመልከት)። የርሱ ምስጋና ግን
ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለሆነ ራሱን አያመሰግንም። የሚመካውም በድክመ
ውስጥ በሚሠራው በእግዚአብሔር ኃይል ነው (4፥7)። ምክንያቱም የሰው ድክ
ምና የእግዚአብሔር ብርቱነት እጅ ለእጅ እንደሚጨዱ ያውቃል (4፥2፤ 6፥3-4)።

በተጨማሪም አገልግሎቱ እንዳይነቀፍ በእንዳች ነገር ማሰናከያን እንዳያ
ኖር በጥንቃቄ የሚመላለስ አገልጋይ ሲሆን ራሱንም የሚያቀርበው በብዙ መጽና
ት፥ መከራን በመታገስ እንዲሁም ጽድቅ በተሞላበት ኑሮ (በመንፈስ ፍሬ) ነው
(ቁ 4-5)። እንደዚህ ዓይነቱን ሕይወት እንዲኖር የሚያስችለው የመንፈስ ቅዱስ
ሰጦታና ኃይል ነው። ምክንያቱም በንጽህና መሄድና የመንፈስን ፍሬ ማፍራት
የሚቻለው በመንፈስ ቅዱስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀሰው የእውነት
ቃል የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሲሆን ፍቅር፥ ትዕግስትና ቸርነት ደግሞ የመንፈስ
ቅዱስ ፍሬዎች ናቸው (ቁ 6-8))። በመጨረሻም መንፈስ ቅዱስ እነዚ

ህን ሁሉ መከራና ችግር በድል አድራጊነት እንዲወጣው በማድረግ ወደር የማይገኝለት እውነተኛ አገልጋይ መሆኑን አሳይቶአል (8-10)።

6፤16-7፤1

በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ የቆሮንቶስ አማኞች ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ መጠመድ እንደሌለባቸው ያሰስባቸዋል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ከጣዖት ጋር ምንም ግንኙነት ስለሌለው ነው። ጌታ «በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፤ አምላካቸውም እሆናለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ» (ሌዋ 26፤11-12) ብሎ በተናገረው መሠረት በመካከላችንና በውስጣችን ስለሚኖር ቤተ መቅደሱ ነንና ከዓለም ተለይተን በመውጣት ልንቀደስ ይገባናል (ኢሳ 52፤11)። ተለይተንም ስንወጣ «እኔም እቀበላችኋለሁ፥ ለእናን ተም አባት እሆናለሁ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ» (2ሳሙ 7፤14) በማለት ታላቅ የሆነን ማበረታቻና ተስፋ በመስጠት ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን ማነጻት እንዳለብን ይመክረናል። ስለሆነም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በሁለት እግር ማነከስ ወይም በሁለት ቢላዋ መብላት አይቻልም — «...የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።» ተብሎ እንደተጻፈ ነው (ኢያሱ 24፤15)።

12፤1-12

ምንም እንኳን በቆሮንቶስ አማኞች መካከል የሐዋርያነት ሥልጣን በመከከላቸው በምልክት፥ በድንቅና በተአምራትም ሁሉ ቢደረግም ራሳቸውን የላቁ መንፈሳውያን አድርገው የወሰዱት መሪዎች የጳውሎስን የአካል ድካምና ሕመም ሊቀበሉት አልቻሉም። ምክንያቱም በእነርሱ አስተሳሰብ አማኝ ለዚያውም ሐዋርያ እንዴት አድርጎ ይታመማል? በእነርሱ አባባል የድል ሕይወት ማለት ከበሽታና ከችግር ፍጹም ነፃ የሆነ ሕይወት ማለት ነው (1ቆሮ 3፤1-3፤ 10፤10)[88]።

[88] ሲንዳ ኤል በለርኤ፥ *ለከንድ ኮሪንቲያንስ* 312-315። ሉቃስ ቤቶፋርያት ሥራ ላይ እንደዘገበውና ጳውሎስም እንደጻፈው አነ ጳውሎስ ወንጌልን ለመስበክ በሠሩባቸው ከተሞች ሁሉ ድንቅና ተአምራ

በተቃራኒው ጳውሎስን የመሰለ ለእገልግሎት የተጠራ፥ እስከ ሦስኛው ሰማይ ድረስ የተነጠቀና ሰውም ሊናገር የማይገባውን ቃል የሰማ ሐዋርያ የክርስትናን ሕይወት የተለማመደው በድካም፥ በመንገላታት፥ እንዲሁም በብዙ ስደት ነው። እርሱ ግን በዚህ ሁሉ ደስ ይለዋል ምክንያቱም በርሱ ድካም የእግዚአብሔር ኃይል ይገለጣልና ነው። ስለዚህም የርሱ ድካም በድንቅና በተአምራት እንዲሁም ኃይልን በመገለጥ ስለ ነበር የሐዋርያነቱን ሥልጣን ከለልክ እጅግ አጸናው፥ አገነነውም።

13፤13-14— ሥላሴያዊ ባርኮት

በዚህ የመደምደሚያ ክፍል ውስጥ — 1ኛ. የኢየሱስ ጸጋ 2ኛ. የእግዚአብሔር ፍቅር 3ኛ. የመንፈስ ቅዱስን ኅብረት በመጥቀስ መሠረታዊ የሆነውን የክርስትናን ዶክትሪን ይገልጣል። ይህም አብ ለሰው ልጅ ከሰው ታላቅ ፍቅር የተነሳ የጠፋውን ሰው ለማድን እቅድን አዘጋጀ (ሮሜ 1፤7፤ 5፤18-21፤ ዮሐ 3፤16)። የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ደግሞ ይሄንን ፍቅር (ሥጋ በመልበስ፥ መከራን በመቀበልና በመሰቀል በመሞት) ገለጠው (2ቆሮ 5፤14-15)። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ አማኞች ይሄንን ፍቅርና ጸጋ እንዲቀበሉ ያደርጋል። በሌላ አነጋገር ሞቶ ከተነሳው ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ በማድረግ በመጀመሪያ ከአብና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ከዚያም ከአማኞች ጋር ኅብረትና አንድነትን በማጠናከር ቤተ ክርስቲያንን ያንፃል (1ዮሐ 1፤3)።

ት እንዳደረጉ ተቅሰአል (ሐዋ 13፤6-12፤ 14፤3፤ 8-10፤ 16፤16-18፤ 19፤11-12፤ 20፤9-12፤ 28፤1-10፤ 1ተሰ 1፤5፤ 1ቆሮ 2፤4፤ ። በዚህ በቆሮንቶስ ዬተክርስቲያንም የተደረገው ምልክት፥ ድንቅና ተአምራት የወንጌሉን ቃል እውነተኛነት ስለሚያጸናው መንፈሱንም ይዘው የመጡትን ሐዋርያትና መንፈሳውያን እውነተኛነት ያጸናዋል።

«ልጆችም ሰለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚመኝ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ።»

ገላትያ 4፥6

12

መንፈስ ቅዱስና የገላትያ ሰዎች

ጳውሎስ በመጀመሪያው ሚሲዮ ናዊ ጉዞው በእንጾኪያ ከለችው ቤተክርስቲያን ተነስቶ ወደ ገላትያ ግዛት በመሄ ድና ወንጌልን በመስበክ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አቋቋመ (ሐዋ 13-14)። ነገር ግን እርሱ ወደ አንጾኪያ በተመለሰ ጊዜ ከይሁዲ ሐይማኖት የሆኑት ተቃ ዋሚዎች ወደ ገላትያ በመሄድ በሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁና ሕግን ካልጠበቃ ችሁ አትድኑም በማለት ማኅበረ ምእመናኑን አናወጡት (ሐዋ 15፥1-2)። ሐዋርያውም ይህንን አስመልክቶ — «በክርስቶስ ጸጋ እናንተን ከጠራችሁ ከእርሱ ወደ

ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ ... ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን።» (1፥6-9) በማለት ለስህተቱ ትምህርት ያለውን ተቃውሞ በአሰፈሪ ቃላት ገልጸታል።

በእምነት መንፈስን የተቀበለ ሰው ከሕግ የማስገደድ ሥልጣን ነጻ ወጥ ቶአልና የሕግ ሥራን ሊጠብቅ አይገባውም፤ ምክንያቱም ሕግና መንፈስ ተቃዋ ሚዎች ናቸውና። ከዚህ በፊት እንደተነጋገርነው ሕግ ሁሉንም ሰው ባለመታዘዝ ምክንያት ከእርግማን ሥር አደረገው። ስለዚህም ሕግ ሰውን ባሪያ ሲያደርግ መንፈስ ግን አርነት ያወጣል። በሌላ አነጋገር በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተሰጠው መንፈስ ቅዱስ የሕግን ኃይል በመሻር ኃይለ-አልባ አደረገው።

በመሠረቱ ሰውን የሚለውጠው ከመስማት የሚመጣ፥ ከመንፈስ የሚገኝ እምነት እንጂ የሕግ ሥራ አይደለም (3፥2-5፤ 4፥6)። ይህም የመንፈስ ሰጦታ ለአብርሃም ቃል የተገባለት ተስፋ ፍጻሜ ነው (3፥14)። ስለዚህም ጳውሎስ የሰበከላቸው ወንጌል ሕጉ-አልቦ ወንጌል ነው።[89] ሕገ-አልቦ ያደረገውም ምክንያት በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ የተገኘና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመጣ ነጻ ሰጦታ መሆኑ ነው (ማለትም የሕግን ሥራ በመጠበቅ የሚገኝ ሳይሆን በእምነት በሚሆን መስማት ነው)። ይህ የመንፈስ አገልግሎት ከሕግ ተገዥነት ሰውን ግላቀቅ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን አማኞችን በመንፈስ እንዲኖሩ፥ በመንፈስ እንዲ መሩና የመንፈስን ፍሬ እንዲያፈሩ ያደርጋቸዋል (5፥18፤ 24-25)።

3፥1-5

ለገላትያ ሰዎች ክርስቶስ ተሰብኮላቸው ነበር፤ እነርሱም ቃሉን በሰሙና በመንፈስ ቅዱስ የተደረገውን ታምራት ባዩ ጊዜ ጌታን በእምነት ተቀበ ሉት። መንፈስን የተቀበሉት በእምነት እንጂ በሕግ ሥራ ሰለ አይደለ አሁን

---

89 ሕጉ-አልቦ ወንጌል ሰል ምን ማለቱ ነው ጳውሎስ የሰበከው ወንጌል በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተገኘ ነጻ ሰጦታ ነው። ነጻ ሰጦታም ሰለሆነ ለመዳን የሚፈልግ ሰው በኢየሱስ ማመን እንጂ የሕግን ሥራ መስራት አያስፈልገውም። ይህንን ሰል ሕግ አያስፈልግ ማለቱ አይደለም ። ነገር ግን አንድ ጊዜ ወደ ጌታ ከመጣን በኋላ ኃይልን በሚሰጠን በመንፈስ ቅዱስ የጽድቅን ፍሬ

ወደ ሕግ ሥራ መዞራቸው ጳውሎስን አሳዝኖታል (1-5)። መንፈስንም በመቀበላቸው ከክርስቶስ ጋር አንድ አካል ያደርጋቸዋል፥ መዳናቸውን ያረጋግጥላቸዋል እንደገናም የክርስቶስ ለመሆናቸው መታወቂያቸው ነው። የሚያሳዝነው ነገር በመንፈስ የጀመሩትን ጉዞ በመንፈስ መጨረስ ሲገባቸው እነርሱ ግን ወደ ሕግ ሥራ ዘወር አሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ሕጉ ሁሉ ባንድ ትዕዛዝ ተፈጽሞአል ይህም — «ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ» በሚለው ነው። ይህም ትዕዛዝ ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አንዱ በሆነው በፍቅር ተጠቃልሎ ተፈጽሞአል (5፥13-15)። ስለሆነም ወደ ክርስቶስ የሚያቀርበን እምነት እንጂ የሕግን ሥራ መጠበቅ አይደለም።

3፥13-14

ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ በእንጨት ላይ በመሰቀል ከሕግ እርግማን በመዋጁቱ ለአብርሃም ተስፋ የተገባለትን መንፈስ ቅዱስን በእምነት ልንቀበል ቻልን። እንደሚታወቀው አብርሃም ራሱ የጸደቀው በእግዚአብሔር ስላመነ ነበር፤ ስለዚህም ከእምነት የሆኑቱ ሁሉ የአብርሃም ልጆች ናቸው (ዘፍ 15፥6)። በእምነቱ የጸደቀ ይኖራል ማለትም ሰው በማመኑ ምክንያት ይጸድቃል፥ በመጽደቁም ደግሞ በሕይወት ይኖራል (የዘላለም ሕይወትን ያገኛል) እንጂ ሕግን በመፈጸም አይደለም (ዕንባ 2፥4)። ምክንያቱም ለመኖር ሲባል ብቻ ከለ እምነት ሕግን መጠበቅ ይቻላል — ሕጉ ምግባርን እንጂ ልብን አይ መረምርምና ነው። በዚህ ክፍል ግልጽ ሆኖ እንደምናየው አሕዛብ ሁሉ ሲባረኩ የሚችሉት በአብርሃም ባርኮት በኩል ነው። ምክንያቱም የምድር አሕዛብ ሁሉ በእርሱ (በአብርሃም) ይባረካሉ ብሎ እግዚአብሔር ተናግሮአልና ነው (ዘፍ 12፥3፤ 18፥18)።[90]

(የመንፈስን ፍሬ) እያፈራን ስለምንኖር ለእግዚአብሔር ሕግ እንገዛለን። በሌላ አነጋገር ሕግን የምንጠብቀው ስመዳን ሳይሆን ስለዳንን ነው።

90 የአብርሃም የመጀመሪያ ስሙ አብራም [አቭራም] ነበረ ትርጉሙም «ከፍ ያለ ወይም የከበረ አባት» ቢሆን እግዚአብሔር ግን ይህንን ስም በመቀየር አብርሃም ብሎታል። በአብራይስጡ አቭረሃም ማ

3፥21-4፥4-7

በእምነት መዳን ሳይመጣ በፊት ከሕግ በታች ተዘግቶብን በባርነት ነበርን። ሕጉ ሁሉንም ሰው ከኃጢአት በታች ስለ ዘጋው ወደ ፊት ሊገለጥ ስላለው የእግዚአብሔር ጽድቅ በተስፋ እንጠባበቅ ነበር። ስለዚህም ሕጉ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ (የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ) ልጁን በመላክ ከሕግ ሞግዚት በታች ተዘግቶብን የነበርነውን ነጻ አወጣን። ታዲያ አሁን ሕግን በመፈጸም ሳይሆን በእምነት በኩል ክርስቶስን ስለ ለበስነው የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል። የርሱ ከሆንን ደግሞ የአብርሃም ዘርና የተስፋው ቃል ወራሾች ነን ማለት ነው (3፥21-29)።

ልጆችም በመሆናችን እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮህ የልጁን መንፈስ በልባችን ውስጥ አስቀመጠ። ይህም ማለት ማለትም ሊየሱስ በልባችን ውስጥ ሆኖ አባዬ ብሎ አባቱን ሲጣራ ስለምንሰማ ልጆች መሆናችንን በዚያ እናውቃለን። ስለዚህም ልጆች መሆናችን ካወቅን ደግሞ የሕግ ባሪያዎች አለመሆናችንን እናውቃለን ማለት ነው። በተጨማሪም ልጆች ደግሞ ከሆንን የእግዚአብሔር ወራሾች ነን ማለት ነው (4፥4-7)።

ከዚህ በታች መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጆች ስለ መሆናችን የሚመሰክርልንን መረጃዎች አስመልክቶ በዚህ ክፍልና በሮሜ መልእክት ያለውን ለማነጻጸር እሞክራለሁ፡ —

ለት የብዙዎች አባት ማለት ነው። ለዚህ ነው እግዚአብሔር ስሙን በመቀየር የብዙዎች ወይም የሕ

ሮሜ 8፥14-17	ገላ 4፥6-7
*እግዚአብሔር መንፈሱን ላከ *አባ አባት ብለን እንድንሁ	የልጁን መንፈስ በውስጣችን ላከው አባዬ ብሎ የሚጮህ የልጁ መንፈስ
*ልጅ ስለመሆናችን መንፈስ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል	ልጁ አባዬ ብሎ ይጣራል፥ እኛም እንሰማዋለን
*ከኃጢአት ባርነት ነጻ መውጣታችንን እናውቃለን *ወራሽ መሆናችንን ያረጋግጣልናል	ከሕግ ባርነት ነጻ መሆናች እናውቃለን ወራሽ መሆናችንን ያረጋግጣልናል

ሰአላዊ መግለጫ ቁ. 5

ስለዚህም የአብርሃም እውነተኛ ልጆች መንፈስ ቅዱስ በልባቸው ያላ ቸው ናቸው (ሊየሱስን የጣል አዳኝ አድርገው የተቀበሉ ማለት ነው)። ኢይሁ ዳዊ ሆነ ወይም አሕዛብ ሁሉም ይህን መንፈስ ሊኖራቸው ይገባል። የወደደንና ስለ እኛ ራሱን አሳልፎ በመሰቀል የሰጠው በመንፈሱ ውስጥ ይኖራል። አርሱ አባቱን «አባ፥ አባት» ብሎ በልባችን ውስጥ ሲጣራ እንሰማዋለን። እኛም ደግሞ ከርሱ ጋር አብረን ወራሾች ስለ ሆንን በዚያው መንፈስ እግዚአብሔርን «አባ፥ አባት» ብለን እንጠራዋለን።

5፥1-26

በነጻነት እንድንኖር ክርስቶስ ነጻ አወጣን እንጂ ተመልሰን ይህን ነጻነት በመጠቀም ከሕግ ባርነት ሥር ልንወድቅ አይገባንም። እግዚአብሔር መንፈ ሱን በውስጣችን ያስቀመጠው በርሱ ባገኘነውን ነጻነት አርሱን በመውደድና በማ

ገሎች ሁሉ አባት አደረገው፥ በርሱም በኩል የሱ ልጅ በሙሉ ተዋረዱ።

ምለክ ተደስተን እንድንኖር ነው። ነገር ግን ክርስቶስን መከተልና በሕግ ሥራ ለመጽደቅ መሞከር ሁለቱ በፍጹም በአንድነት የማይሄዱ ነገሮች ናቸውና የገላ ትያ አማኞች ከሁለቱ አንዱን መምረጥ ነበረባቸው (ቁ 1-3)። ሕግን ሁሉ በሚ ፈጽመው፥ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በሆነው በፍቅር ሆኖ የሚሠራ አምነት እንጂ የሕግን ሥራ መጠበቅ ወይም አለመጠበቅ ምንም አይጠቅምም (ቁ 6,13-14)።

ግንም በሕግ ሥራ ሊጸድቅ የሚሞክር ቢኖር ከክርስቶስ ተለይቶ ከጸ ጋው ወድቋል በማለት እውነቱን ይናገራል። እኛ በመንፈስ ሊገለጥ ያለውን የጽድቅ ተስፋ በአምነት እንጠባበቃለን በማለት የጽድቃችን ፍሬ ገና ጎህ ቀደደ እንጂ ሙሉ ለሙሉ እንዳልተጠቃለለ [Consummate] አስቀምጦታል። ይህም የሚሆነው በመጨረሻው ቀን ሲሆን አስከዚያ ግን ይህንን ሕጉአልባ የሆነውን፥ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ያገኘነውን ጽድቅ መንፈስ በሚሰጠን ኃይል መጠበቅ አለብን (4-8)።

አማኝ መንፈስ በሚሰጠው ኃይል በመጠቀም የሥጋን ምኞት መግደል አለበት። የሥጋ ሥራ ፍቅር የለውምና እርስ በርስ ያንካስሳል፥ ያጠፋፋልም (ቁ 13, 15)። በፍቅር የሚመላለስ ግን በመንፈስ ይመላለሳልና ልክ እንደ ጌታው እርሱም የሁሉም ባሪያ በመሆን ሕግን ይፈጽማል። በዚያን ጊዜ የእግዚ አብሔርን መንግሥት አሠራር በግልጽ ያልተረዱትን የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ብንመለከት ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ወጥቶ የእስራኤልን መንግሥት የሚመሠ ርት መስሎአቸው ስለነበር ቁልፍ የሆኑ የሥልጣን ቦታዎችን ተሽቀዳድሞ ለመያ ዝ በዝግጅት ላይ ነበሩ። ያዕቆብና ዮሐንስ ራሳቸውም ከዚያም ደግሞ እናታ ቸውን አማላጅ በመላክ ሥልጣኑን ሲጨብጥ በግራና በቀኝ እንዲያስቀምጣቸው ይወተውቱት ነበር። ሁሉም ደግሞ ማነው ከእኛ ውስጥ ታላቅ እየተባባሉ ይከ ራከሩ ነበር። ኢየሱስ ግን ሕጻናትን ወደ እነርሱ አምጥቶ እንደ እነዚህ ሕጻናት ተመልሳችሁ የዋሆች ካልሆናችሁና ራሳችሁን ባዶ ካላደረጋችሁ መንግ ሥተ ሰማያት አትገቡም በማለት ገሰጻቸው (ማቴ 18፥1-5፤ ሉቃ 9፥33-37, 46-48፤ ማር 10፥ 35-37)።

በመጨረሻውም እራት ላይ እንዲሁ ኢየሱስ እግራቸውን በማጠብ «እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ ይገባችኋል።» (ዮሐ 13፥3-18) በማለት አገልጋይ የተ

ጠራው ሥልጣኑን ተገን በማድረግ፣ በየምኩራቡ እየዞረ የከበፊታ ስፍራን በመፈ ለግ ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ ሳይሆን ነገር ግን ፎጣ በትከሻው ላይ ይዞ በመዞ ር ራሱን ዝቅ አድርጎ እግር በማጠብ የሁሉም አገልጋይ ለመሆን እንደሆነ አሰ ተማራቸው። ይህንኑ ትምህርት ደግሞ ጌታ መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ ወሰዶ በዚህ ክፍል ውስጥ እንደገና በማሰተማር በፍቅር የማይኖር አማኝ የሕግ ዕዳ እንዳለበት ያሳስበናል። ስለዚህም አማኝ በመንፈስ በመመላለስ የክርስቶስን ሕግ መፈጸም አለበት።

በመንፈስም የሚመላለሱ ሥጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋር ስለሚሰቅሉ የመንፈስን ፍሬ ያፈራሉ። ፍሬዎቹም — ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃትና ራስን መግዛት ናቸው (ቁ. 23)። ጳውሎስ ስጢሞቴዎስና ለቲቶ የጻፈውን መልእክት ብንመለከት ለቤተክርስቲያን መሪነት የሚያበቃ መመዘኛ አውጥቶ ሰጥቶአቸዋል። እነዚህም መመዘኛዎች የተመረኮ ዙት በጸጋ ስጦታዎች ብዛትና ጥልቀት ሳይሆን አማኞች ባፈሩአቸው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ነው (1ጢሞ 3፥1-13፤ ቲቶ 1፥5-16)።

ምንም እንኳን አማኞች ያሳቸውን የጸጋ ስጦታ ይዞ በመቅረብ የክርስቶ ስን አካል ለማነጽ መሳተፍ ቢገባቸውም የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ አፍርተው አለሳ ልተገኙ ድረስ ለአገልግሎት ብቁ መሆን አይችሉም። ስለዚህም ለቃሉና ለመ ንፈስ ቅዱስ በመታዘዝ የመንፈስን ፍሬ አፍርተን የእግዚአብሔርን አሳብ ልናገል ግል ይገባናል እንጂ ስጦታዎቻችንን በአመጸኝነት ምክንያት ልናባክናቸው አይገባ ንም።

ከዚህ በታች እነዚህን ፍሬዎች በዝርዝር እንመለከታለን: —

1) ፍቅር

ከሁሉም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ፍቅር ይበልጣል። ኢየሱስ ለደቀመዛ መርቱ እርስ በርሳቸው ይዋደዱ ዘንድ አዲስ ትዕዛዝ ሰጣቸው (ዮሐ 13፥34-335 ፤ 15፥12)። የሕግን ትዕዛዝ የምንፈጽመው የሕግን ሥራ በመሥራት ሳይሆን ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሠራልን ሥራ በማመን በፍቅር ስንመላለስ ብቻ ነው። በ1ቆሮ 13፥13 ላይ ፍቅር ከእምነትና ከተስፋ ጋር አብሮ ተጠቅሶ አል ነገር ግን ከሁለቱም ፍቅር ይበልጣል። ምክንያቱም የጸጋ ስጦታዎች ቢሆኑ

ጌታ ሲመጣ ይቀራሉ፣ እምነትና ተስፋን የወለድን እንደሆነ ደግሞ ጌታን ፊት ለፊት ስናየው በዚያን ጊዜ ተስፋችን ይፈጸማል። ተስፋችንም ስለሚፈጸም የሚያስፈልገን ፍጹም የሆነ ፍቅር እንጂ እምነት አይደለም። ምክንያቱም እም ነት ተስፋ የምናደርገውን ነገር እንደሚፈጸም የሚያስረግጥልን፣ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳን እንጂ በእጃችን ውስጥ ስላለ ነገርና ስለ ምናየው ነገር የሚረ ዳን አይደለምና ነው (ዕብ 11፥1-3)።

የቱንም ያህል የጸጋ ስጦታ ይኑረን፣ በእምነታችን ታላላቅ ተአምራትን እናድርግ ወይም በአገልግሎታችን ብዙ እንታወቅ ፍቅር ግን ከሌለን ባዶውን እንደሚጮህ ቆርቆሮ ወይም እንደሚንሸዋሸው ጽናጽል ነን (1ቆሮ 13፥1-2)። ፍቅር ይታገሳል፣ ቸርነትን ያደርጋል፣ አይቀናም፣ አይመካም፣ አይታበይም፣ የማ ይገባውን አያደርግም፣ የራሱን አይፈልግም፣ አይበሳጭም፣ በደልን አይቆጥ ርም፣ ከአውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ አመጻ ደስ አይለውም፣ ሁሉን ይታገሳል፣ ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፣ በሁሉ ይጸናል (1ቆሮ 13፥ 1-7)።

ይቅርታ የፍቅር መሠረታዊ አካል በመሆኑ እግዚአብሔር እኛን ይቅር እንዳለን ሁሉ እኛም አርስ በርሳችን ይቅር ልንባባል ይገባናል። ከይቅርታ ይልቅ ብቀላ እንደ ጀብዱ በሚቆጠርበት ኅብረተሰብ ውስጥ ለምንኖር ለእንደ እኛ ዓይ ነቱ ሰው ፍቅርን ለመፈጸም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ላይ በብርቱ መደገፍ ያስፈ ልገናል። ምክንያቱም የወጣነው ከዚያ ኅብረተሰብ ውስጥና የምንኖረውም በዚ ያው ኅብረተሰብ ውስጥ ስለሆነ ነው (ምንም እንኳን የጌታ እንጂ የዚያ ኅብረተ ሰብ ባንሆንም)። የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስተምረን ከሆነ ቤተክርስቲያን የምትኖርበት ማኅበረተሰብ / ኅብረተሰብ እንዳንድ ባሕልና ወግ መንፈሳዊ አድገ ቱዋን ከመጎተት ወደ ኋላ ያስቡት ጊዜ የለም። ምክንያቱም ኃጢአት ፍጥረትንና ሥርዓትንም ጨምሮ አሳድፍታልና ነው (ዘፍጥ 3፥1-21፤ ሮሜ 3፥11-18፤ 8፥18-22)።

ሰይጣንም ደግሞ ለእግዚአብሔር መንግሥት የማይመቸውን የአንድን ኅብረተሰብ ባሕልና ወግ በመጠቀም ቤተክርስቲያንን ይዋጋታል። ዶ/ር ክሊንተን አርነልድስ «መንፈሳዊ ጦርነት» በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ ሲጽፉ አንድ አማኝ ወደ ጌታ ሲመጣ ከኃጢአት ነጻ መውጣቱን ብቻ ሳይሆን ለክርስቶስ

ወንጌል እንቅፋት ከሆኑትንና ለእድገት ከማይመቹት ባሕል፣ ወግና የአኗኗር ዘይ ቤዎች ተጽእኖና አሰራት ነጻ መውጣቱን ማረጋገጥ አለበት ብለዋል።[91] ስለዚህም ቤተክርስቲያን እነዚህን ጎታች የሆኑ፣ ስጠላት አመቺ በር በመክፈት እርሱዋን የሚያስመቱትን ባሕላዊ ልምምዶችን በማጥናት ዒላማ ውስጥ አስገብታ መንፈ ሳዊ ውጊያን ልትዋጋ ይገባታል። በዚች በአጭር ሕይወቱና አገልግሎቱ ውስጥ ያየውት ነገር ቢኖር እኛ ኢትዮጵያውያን በመጀመሪያ ይቅርታ ይከብደናል። ይቅር ካልን ደግሞ በደልን መቁጠር ልምዳችን ነው። ስለዚህም በዚህ ጉዳይ ላይ መንፈሰ ቅዱስ በጥቂያችንና በግል ሕይወታችን እንዲሠራ አጥብቀን ልንጸ ልይ ይገባናል።

በተጨማሪም ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረን ጸሎት ላይ በመጀመሪያ እግዚአብሔር በደላችንን ይቅር እንዲለን ከመጠየቃ ችን በፊት ማድረግ የሚገባን ነገር ተጠቅሶአል፤ ይህም የበደሉንን ይቅር ማለት ነው። በማቴዎስ ምዕራፍ ስድስት ቁጥር አሥራ ሁለት ላይ «እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን» የሚለውን አባባል በቀጥታ የግሪኩን ቃል የተመለከትን እንደሆነ «እኛም የበደሉንን ይቅር ስንልለን በደላችንን ይቅር በለን» የሚለውን ትርጉም ይሰጠናል[92]። ኢየሱስም ጸሎቱን ካስተማራቸው በኋላ የይቅርታን አስፈላጊነት ሲገልጽ «ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፣ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና፤ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸ ውን ይቅር ባትሉ፣ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።» (ማቴ6፣1 4-15) ብሎአል።

በዚሁ መንፈል ምዕራፍ አምስት ላይም እንዲሁ ለአምልኮወደ እግዚአ ብሔር ፊት ከመቅረባችን በፊት አስቀድመን ከወንድሞቻችን ጋር ያለንን ቅሬታና በደል ማስወገድና እርቅን ማስፈን እንደሚገባን ጌታችን ያስተምረናል (ማቴ 5

---

91 ክሊንተን አርነልድስ፣ *ሰይጣን ኩሐለችንስ አባውት ስፐሪቾአል ምርፈር* (ግራንድራፒድስ፣ ዜ ኩር ቡክ ሃውስ፣ 1997) 187።

92 የግሪኩ ቃል ይቅር እንዳልን የሚለውን ለፈቀሜን ሲለው ይህም የመጣው ለፈሰሰ ከሚለው ቃል ነው ትርጓሜውም ይቅር ማለት ነው። ስለሆነም ለፈቀሜን የሚለው ቃል «ተፈጸሚ ግሥ [ፐርፈክት ቴንስ]» ሲሆን የሚያሳየውም የአንድን ነገር መፈጸም ወይም መደምደም ነው። በዚህም መሠረት ፣23-24)። ስለዚህም ይቅርታን ስመጠየቅ መጠት የሚኖረን እንኳን ስሎቹን ይቅር ስንል ብቻ መሆኑን ማስተዋልና መለማመድ ለመንፈሳዊ ጤንነት እጅግ አስፈላጊ ነው።

2) ደስታ

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለሆነ ማለትም ቅዱስ መንፈሱን በልባችን በማድረጉ ደስታንና ሃሴትን ይሞላብናል (ሮሜ 14፣17)። እኛም ደግሞ በርሱ ስለምንታመን፣ በማዳኑ ደስ ስለሚለን፣ ረዳታችን ስለሆነ፣ ቃል ኪዳኑን ስለሚያ ሰብ፣ የጽድቁ ፍርድ ለዘላለም ስለሆነ፣ ሁሉንም ነገር ስለሚቆጣጠርና ባጠቃላይ ስላደረገልን ነገር ሁሉ በደስታና በእምልኮ ሆነን ሁሌ በፊቱ እንቀርባለን። ዳዊት በመዝሙሩ «በእንተ የሚታመኑት ሁሉ ግን ደስ ይላቸዋል፤ ለዘላለሙ ደስ ይላቸዋል፣ እነርሱንም ትጠብቃለህ። ስምህንም የሚወድዱ ሁሉ በእንተ ይመካሉ» ይላል (መዝ 5፣11፤ 9፣14፤ (13)፣5፤ (32)፣ 11፤ (42)፣ 4፤ (63)፣ 7፤ (105)፣ 43፤ 119፣162፤ 149፣ 2)። የእግዚአብሔር ሕዝብ ደስተኛ ሕዝብ ነው። በምንም ዓይነት ነገር ውስጥ ብናልፍ በተለይ ደግሞ ክርስቶስ ያደረገልንና ወደ ፊት የሚጠብቀንን ክብር ስናስብ ሁሌ ደስተኞች እንሆናለን (ፊልጵ 4፣4-7፤ 1ተሰሎ 5፣16-18፤ ያዕቆ 5፣113)።

3) ሰላም

እኛ አሕዛብ ከእስራኤል መንግሥት ርቀን፣ ለተስፋውም ቃል ኪዳን እንግዶች ሆነን፣ በዚህም ዓለም ተስፋን አጥተን ከእግዚአብሔርም ሕይወት ተስ ይተን ነበር። ምክንያቱም በኃጢአት ምክንያት ሁላችንም የእግዚአብሔር ጠላቶች ነበርንና ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በመጀመሪያ ቀርበው ለነበሩት (ለእይ ሁድ) ከዚያም ለእኛ ርቀን ለነበርን በደሙ ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቅ ለእነርሱና ለእኛ ሰላምን የምሥራች ብሎ ሰበከ። በመስቀሉ ደምም የጥልን ግርግዳ አፍርሶ ሰላማችንም ሆነ፣ በርሱም ሰላምን አገኘን (ኤፌ 2፣11-17፤ 6፣15 ፤ ሮሜ 5፣1፤)።

ማቴዎስ ስድስት ቁጥር አሥራ ሁለት ሲተረጎም «እኛም የበደሉንን ይቅር እንዳልን» የሚለውን ይሰ

ከእግዚአብሔር ጋር ባስታረቀን ሰላም፣ በውስጣችን በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት አድሞንነትን፣ ቂመኝነትን፣ ክፍፍልን፣ መለያየትንና ጠብን አስወግደን እርስ በርሳችን ይቅር ተባብለንና አንተ ትብስ አንቺ ትብሺ ተጭበስን በፍቅር እንድንኖር ያደርገናል (ያዕቆ 3፥14-18፤ ሮሜ 14፥19፤ ኤፌ 2፥14-15፤ 4፥3፤ ቆላ 3፥15፤ 1ተሰሎ 5፥13)። በተጨማሪም ከአማኞች ጋር ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ከማያምኑት ጋር እንኳን ቢቻለን በሰላም ልንኖር ይገባናል። ለምን ቢባል ሊየሱስን ከመከተላችን በስተቀር በሌላ ነገር ማሰናከያን ለማንም ልናኖር አይገባንምና ነው (ሮሜ 12፥18፤ 1ቆሮ 7፥15፤ 2ተሰሎ 3፥16)።

ሰላም ወደ አንድነት ስለሚያመጣን በቤተክርስቲያን ውስጥ የመንፈስን አንድነት እንድንጠብቅ ይረዳናል። አንድነታችንን ጠበቅን ማለት ደግሞ ጌታችን ሊየሱስ ክርስቶስ ወደዚች ዓለም የመጣው በአባቱ ተልኮ እንደሆነና አብም እርሱን በወደደበት ፍቅር እኛንም እንደወደደን ለዓለም እናሳያለን (ኤፌ 4፥3፤ ዮሐ 17፥24)። ስለዚህም አማኞች ልባችንን ለሚለውጠው ለጌታ መንፈስ ቅዱስ በመክፈት፣ ሰላም የሚሰፍንበትን መንገድ በመፈለግ በክርስቶስ አካል ውስጥ የመንፈስን አንድነትና ኅብረት ልንጠብቅ ይገባናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር «በክርስቶስ አንዳች ምክር ቢሆን፣ የፍቅር መጽናናት ቢሆን፣ የመንፈስ ኅብረት ቢሆን፣ ምሕረትና ርህራሄ ቢሆኑ፣ ደስታዬን ፈጽሙልኝ፤ በአንድ አሳብ ተሰማሙ፣ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ በማለት የልቡን ጭንቀትና ጸሎት ይናገራል (ፊል 2፥1-3)።

በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚነሱትን ልዩነቶችና አለመግባባት ራሳችንን ዝቅ በማድረግና እውነትን በፍቅር በመግለጽ መንገርና እርቅ የሚሰፍንበትን መንገድ መፈለግ እንጂ እግዚአብሔር እንደሌላቸው ሰዎችና እንደ ፖለቲከኞች በጥላቻና በጩኸት ችግራችንን ልንፈታ አይገባንም። በተለይ ደግሞ እንደኛ ላለ ልዩነትን በሰላማዊ መንገድ ሳይሆን በጩኸና በዱላ መፍታት ወግ በሆነበት ኅብረተሰብ ውስጥ ያደግንና የምንኖር ሰዎች ስዚህ ጉዳይ ልዩ ትኩረት መስጠት አለብን። በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚነሱ ልዩነቶች በመነጋገር ቢቻል ልዩነቱን

ጠፍ ማለት ነው።

መፍታት፤ ካልተቻለም ደግሞ ልዩነቱ መሠረታዊ የሆነ የክርስትናን ዶክትሪን አስከልተቃወመ ድረስ በልዩነት ውስጥ ተዋድደን ልንኖር ይገባናል።

በአንድ ወቅት በቤተክርስቲያናችን ውስጥ መለያየት በተፈጠረበት ጊዜ ከአንደኛው ወገን የሆኑቱ ሌሎቹን ካልደበደብን በማለት ያዙን ልቀቁን እያሉ ሲገባበዙ አይተናል። ለምን በዱላ ልዩነታቸውን መግለጽ እንደፈለጉም ሲናገሩ «ምን እናድርግ ብላችሁ ነው፤ የጴጥሮስ ቅናት ይዞን እኮ ነው» የሚል መልስ ነበር ይሰጡ የነበሩት። ማወቅ የሚገባን ነገር ቢኖር ምንም እንኳን ጴጥሮስ ከለማወቅ የተነሳ ጌታውን ከሦስት ዓመት በላይ እየተከታተሉ ሲያሳድዱት የነበሩትን ከሃዲዎች ለመቋቋምና ጌታውን ለማስጣል ሲፎክ ቢመዝም የወሰደው እርምጃ ትክክል ሰላልሆነ ጌታ ራሱ ገሰጸታል (ዮሐ 18፥10-11፤ ሉቃ 22፥47-53፤ ማር 14፥ 47-49፤ ማቴ 26፥ 51-54)።

መቼም ሊዘሉዋት ያሰቡዋትን አሞራ ጅግራ ናት ይሉዋታል እንዲሉ ራሳችንን መግዛት ያቃተን እንደሆን በጴጥሮስ እያሳበብን የጡጫ አምሮታችንን በወገኖቻችን ላይ ልንወጣ አልተፈቀደልንም። ሁል ጊዜ ልናስታውስ የሚገባን ነገር ቢኖር ሁላችንም (ማለትም ከእኛ ጋር ልዩነት ያላቸውንም ጨምሮ) አንድ አባት፣ አንድ ጌታና አንድ መንፈስ እንዳለንና ሁላችንም ከክርስቶስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በአንዱ መንፈስ እንደተጠመቅን ነው (ፊል 2፥5-11፤ 4፥2-3፤ 2ጢሞ 2፥19-18፤ 1ዮሐ 1፥3 ን ተመልከት)።

4) ትዕግሥት

ትዕግሥትን በሁለት መንገድ እናየዋለን — እንደኛ እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን የሰው ልጅ በዘመናት ውስጥ በመታገስ፣ ሳያጠፋው ልጁን በመላክ ከዘላለም ሞት አዳነው (ሮሜ 2፥4፤ 9፥22)። እንግዲህ እግዚአብሔር እኛን ከታገሰን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንቻቻልና አንዳችን ሌላውን ልንታገስ ይገባናል (ቆላ 3፥12-113፤ 1ተሰሎ 5፥14)። እርስ በርሳችን ከታገስን ደግሞ ለይቅርታ መንገድን እንከፍታለን። ይቅር ከተባባልን ደግሞ የፍጻሜ ግቡሪያ የሆነውን ፍቅርን እንለብሰዋለን (ቆላ 3፥13)። ሁለተኛው ደግሞ ጌታችን መከራን ታግሶ ከሞት ካዳነን፣ እኛ ደግሞ ስለ ስሙ የሚደርስብንን መከራ በመታገስ የተሰጠንን የወንጌል ባለ አደራነት በታማኝነት ልንወጣው ይገባናል (ቆላ 1፥11፤

ያዕቆ 5፥10-11፤ ሮሜ 12፥12)። ጳውሎስ በቆላስያስ መልእክቱ ላይ የእግዚአብሔር ምርጦችና ቅዱሳን ስለሆንን ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትሕትናን፥ የዋህነትንና ትዕግስትን እንድንለብስ ይመክረናል (ቆላ 3፥12-14)። ስለዚህም እኛ ከፈቀድንለት መንፈስ ቅዱስ ይህንን ፍሬ እንድናፈራ (ትዕግስትን እንድንለብስ) በማድረግ የክርስቶስን አካል ይገነባታል። ካለዚያ ግን ራቁታችን ሆነን እንዳን ገኝ እንጠንቀቅ።

5) ቸርነት

የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ በመምራት እንደ አዳነን ሁሉ (ሮሜ 2፥4፤ 11፥22፤ ኤፌ 2፥7፤ ቲቶ 3፥4)) እኛም ለሚጠሉን በተለይ ደግሞ ለሚያሳ ድዱን ቸርነትን ማሳየት አለብን (2ቆሮ 6፥6)። ክርስቶስን ሳናገኝ በፊት ቸርነት ማድረግን አናውቅም ነበር (ሮሜ 3፥12)፤ አሁን ግን ቸርነት ተደርጎልን ድነናልና እርስ በራሳችንም ምሕረትን በማሳየት (ማለትም ሳንፈራረድ ሆደ ሰፊ በመሆን) አንድ ላይ ልንኖር ይገባናል። ይህንንም የሚያስችለን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው።

6) በጎነት

በጎነት የእግዚአብሔርን ታዛዥነት የሚያሳይ መሰረያ ነው (ሮሜ 15፥14፤ 2ተ ሰሎ 1፥11)[93]። ይህም ፍሬ ክፉን ነገር በመጸየፍ መልካምን ነገርን እንድናደርግ ይረዳናል። በጎነት ከጽድቅና ከእውነት ጋር በመሆን ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመርን እንድንኖር ይረዳናል (ኤፌ 5፥9፤ ቆላስ 1፥10)። እንግዲህ በጎነት በታሉ ላይ የተገለጹትን መልካም የሆኑትን ነገሮች ማድረግን፥ በቁሳቁስም እር ዳታ ይሁን ግብረገብነት ያላቸውን ነገሮችን ማድረግን ይጠቀልላል።

7) እምነት

እምነት ማለት በእግዚአብሔር ላይ ሙሉ ለሙሉ መደገፍና እርሱን ማመን ወይም እርሱ የተናገረውን መቀበል ማለት ነው። እግዚአብሔር ያዘጋ

[93] ኪነር፥ *ሰዶ ከራሽል ኩመችን ለባውት ዘ ሆሊ ስፒሪት* ፤ 160።

ጀልንን የዘላለም ሕይወት ልንወርስ የቻልነው በእምነት እንጂ ሕግን በመጠበቅ ወይም ወደ እርሱ ሊያቀርበን የሚችል ሥራ በመሥራት አይደለም። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ ከዚህ ዓይነቱ ሕጋዊነት ርቀን በዚህ ዓይነት እምነት እንድን ቀጥል በማድረግ ከእምነት ወደ እምነት ያሸጋግረናል (ገላት 3፥2-5፥5)።

8) የውሃት

የውሃት ማለት የራስን ሳይፈልጉ፥ በንጹህና በቅን ልብ ፍቅርን ማሳየት እንዲሁም በዝግታ መንፈስ ሌሎችን ማገልገልን ይጨምራል። በየውሃት መንፈስ ሰዎችን ማገልገል ቁጣን ያርቃል፥ ሰዎችን አሳባቸውን ካለምንም እንቅፋት ሊገ ልጹ ስለሚረዳቸው ወዳጅነታቸውን ያጠናክራል። በስህተትም የተገኙትን አማ ኞች ፍርድን በተሞላ ንግግር ከመሰበር ይልቅ በክርስቶስ የዋህነት ምሕረትን በማ ሳየት ከገቡበት ችግር ልናወጣቸው ይገባናል (1ቆሮ 4፥21፤ 2ጢሞ 2፥25፤ ያዕቆ 1፥21፤ 3፥13፤ 1ጴጥ 3፥15፤ ምሳ 15፥1)። ስለዚህም እኛ አማኞች እርስ በርሳ ችን በየውሃት መንፈስ በመተናነጽ፥ እንዲሁም ደግሞ በኃጢአት የወደቁትን ምሕረት በበዛበት መንገድ ማትናት ይገባናል (ገላ 6፥1፤ 1ቆሮ 4፥21)።

9) ራስን መግዛት

ራስን መግዛት ማለት በሁሉም ነገር ላይ ምግብም ሆነ መጠጥ ወይም ግብረሥጋ ግንኙነትም ሆነ ወይም ማናቸው ነገር ሳይሰለጥንብን ወይም ባሪያዎች ሳያደርገን በነጻነት የመኖር አቅም ማለት ነው (1ቆሮ 7፥9)። እንደገናም ራስን መግዛት እግዚአብሔርን ለመምሰል ራሳችንን ማለማመድን ይጨምራል (1ቆሮ 9 ፥25)። ይህም ቃሉን ለማንበብ፥ ለመጸለይ እንዲሁም ለመጾምና ለመጸለይ ራሳ ችንን ማለማመድንም አብሮ ያካትታል። ሁሉም ተፈቅዶልናል ነገር ግን ምንም ነገር አይሰለጥንብንም ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠን ኃይል ዓለማዊ ምኞትንና ኃጢአትን በመካድ ወይንም እንቢ በማለት በጽድቅና እግዚአብሔርን በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንኖራለን (ቲቶ 3፥11-14)። የዚህ ዓይነቱ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሌለው ሰው ለሚቀርብበት ፈተና እንቢ ማለት ያስቸግረዋል (አቅም ያጥረዋል)።

6፤7-10

ሰው የሚዘራውን ያንኑ ያጭዳልና፥ በመንፈስ የሚዘራ ሥጋን ከከፋ ምኞቱና መሻቱ ጋር ሰቅሎ መንፈስ በሚሰጠው ኃይል ስለሚኖር የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ ያጭዳል (5፤23)። በሥጋ የሚዘራ ግን በሥጋ ሥራ ስለሚመላለስ ኃጢአትን ያጭዳል (5፤1921)፤ ኃጢአተኛም ስለሆነ የእግዚአብሔርንም መንግሥት አይወርስም። ነገር ግን በመንፈስ ኃይል የሚመላለሱት ሕይወትን በሚሰጠው በመንፈስ ቅዱስ የዘላለም ሕይወትን እዲወርሱ አሰከ መጨረሻው ያጸናቸዋል (ገላ 5፤25፤ 2ቆሮ 3፤6)። ስለዚህም ጊዜው የመንፈስ ቅዱስ የሥራ ጊዜ ነውና ይህንን የመንፈስ ፍሬ በውቅቱ መገለጡትና ማጨድ አለብን እንጂ ልንዘል አይገባንም።

«በክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።»

ኤፌሶን 1፤3

13

መንፈስ ቅዱስና የኤፌሶን ሰዎች

ጳውሎስ መልእክቱን በባርኮት ከከፈተ በኋላ በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከንን እግዚአብሔርን ያመሰግናል። ይህም እግዚአብሔር አብ በክርስቶስ በኩል የሰጠንን ደህንነትና የመንፈስ ቅዱስን ባርኮት ያሳየናል። ባርኮቱም የተከናወነው ክርስቶስ በአብ ቀኝ ባለበት በሰማያዊ ስፍራ ሲሆን ጊዜውም ኢየሱስ ካረገ በኋላ ነበር (መንፈስ ቅዱስ የወረደው ኢየሱስ ወደ አብ ካረገ በኋላ ነው)። ጸጋውን በጥበብና በአእምሮ በማብዛት የፈቃዱን ምስጢር ይኸውም በሰማይና በምድር

ያለውን በክርስቶስ ለመጠቅለል እንደሆነ አስታወቀን (9-11)። በክርስቶስ አስቀድመው ተስፋ ያደረጉት አይሁዳውያንና እኛም በትውልዳችን አሕዛብ የሆንን ደግሞ የእውነትን ቃል ሰምተን በክርስቶስ ስላመንን በተሰፋው መንፈስ ታተምን። ይህም የመንፈስ ሳትመት እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ጠቅልሎ እስኪ ዋጅ ድረስ የርስታችን መያዣ ነው (2ቆሮ 1፥21-22፤ ገላ 3፥14)።

1፥17-20

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ስለ እነርሱ እያመሰገነ የክብር አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣቸው በጸሎቱ ይለምናል። እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሰጦታዎች የሆኑት ጥበብና መገለጥ የልባቸው ዓይኖች እንዲበሩ ያደርጓቸዋል። የልባቸው ዓይኖች ደግሞ ሲበሩ – 1ኛ. የመጥራቱ ተስፋ ምን እንደሆነ፤ 2ኛ. በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የክብር ባለጠግነት ምን እንደሆነ፤ 3ኛ. ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንደሆነ ያውቃሉ።

መንፈስ ቅዱስ የሚገልጥልን የኃይሉ ታላቅነት ምስጢር ምንድነው ቢባል — 1ኛ. ክርስቶስን ሲያስነሳው ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይ ከፍ እንዳደረገው፤ 2ኛ. ይህም ደግሞ በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ ይሆን ዘንድ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው ያሳየውን የብርታቱ ጉልበት ምን እንደሆነ ነው (21-22)። ስለዚህም የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ የእግዚአብሔርን የብርታት ጉልበትና ጥልቅ አሳብ እየመረመረ ስለሚነግረን እርሱን እንድናውቀው ይረዳናል። እርሱን ባወቅነው መጠን ደግሞ ለርሱ ያለን አክብሮትና ፍቅር ስለሚጨምር ወዳጅነታችን እየጠነከረ ይሄዳል።

2፥11-18

እኛ በተፈጥሮአችን አሕዛብ የሆንን ከእስራኤል መንግሥት ርቀንና ለእስራኤላውያን ከተገባው የተስፋው ቃልኪዳን እንግዶች ሆነንና በዚህ ዓለም ተስፋን አጥተንና ከእግዚአብሔር ተለይተን ያለ ክርስቶስ ነበርን። አሁን ግን በክርስቶስ ደም ኃጢአታችን ታጥቦ ወደርሱ ቀርበናል። እርሱ ሰላማችን ስለሆነ በእግዚአብሔርና በእኛ፥ እንዲሁም በእኛና በአይሁድ መካከል የነበረውን የጥል

ግድግዳ በሥጋው በማፍረስ ከሁለታቸው (ማለትም ከአይሁድና ከአሕዛብ) አንድን ሰው በመፍጠር በእዋጅ የተነገሩትን የትዕዛዛትን ሕግ ሻረ[94] (11-16)። ርቀን ለነበርነውና ቀርበው ለነበሩት (አይሁድ) ሰላምን የምሥራች ብሎ ሰበከ፥ ከእግዚአብሔርም ጋር አስታረቀን (ሮሜ 5፥2)፤ ከዚያም ለሁለታችንም አንዱን መንፈስ ሰጠን። መንፈሱም ሰላለን እርሱ በሠራው ሥራ ወደ አብ መግባት ቻልን (1ቆሮ 12፥13)።

2፥19-22

በሐዋርያትና በነቢያት መመረት ላይ ታንጸናል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ሕንፃም ስለሆንን በጌታ እየተጋጠምን ቅዱስ ቤተመቅደስ ስለሆን እንሠራለን። የእግዚአብሔርም ቤተመቅደስ ያደረገን ነገር ቢኖር የመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖር ነው ። መንፈስም ኅብረትን ስለሚጠብቅ በአንድነት ተጋጥመን እግዚአብሔርን እንድናመልከውና በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግ ይረዳናል።

3፥3-7

የጳውሎስ የወንጌል አገልጋይነት ሰፋቱና ጥልቀቱ የተወሰነው በእግዚአብሔር ኃይል አመራርና አንደተሰጠው የጸጋ ሰጦታ መጠን ነበር እንጂ በራሱ ብርታትና ጉልበት አልነበረም። ይህንንም ጉዳይ አሰመልክቶ ሲናገር «ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለ ጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ...ከዘላለም የተሰወረውን የምስጢር ሥርዓት ምን እንደ ሆነ እገልጥ ዘንድ።» (ቁጥ 8-9) በማለት ስለ ጥሪው ታላቅነት ይናገራል። ታዲያ ይህን ምስጢር የገለጠለት መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ጨምሮ ገልጸታል (ቁ 6)። በዚህ ክፍል ላይ «እስቀድሜ በአጭሩ እንደ ጻፍሁ፥ ይህን ምስጢር በመግለጥ አስታወቀኝ» በማለት ሲገልጽ

94

የጠቀ ግድግዳ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረው ክፍፍል ነበር። በሙሴ ሕግ መሰረት ከአምልኮ ሥርዓት እንስቶ እስከ አመጋገብ ሥርዓት ድረስ አይዳውያኑ የተሰጣቸውን ትእዛዝ ተከትለው መኖር ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም በመበል ሥርዓቱ መሰረት እንዳይረክሱ ሲሉ ከአሕዛብ ጋር በእንድነት ቀርበው አይበሉም ነበር። ክርስቶስ ኢየሱስ በሞቱ እንደዚህ የመሳሰሉትን የሕግና ባሕላ

ይሆን ምስጢር የተገለጠው ለቅዱሳን ሐዋርያትና ለነቢያት መሆኑንም ጭምር ገልጸታል። ይህ «ምስጢር» 1፥9-10 ላይ እንደተመለከትነው የእግዚአብሔር በሰማይና በምድር ያሉትን በክርስቶስ የመጠቅለል እቅድ ነው። በዚህ ክፍል ደግሞ ይህንኑ አሳብ እንዲህ ሲል አብራርቶታል – 1ኛ. አሕዛብ አብረው (ከአይሁድ ጋር) እንዲወርሱ፥ 2ኛ. በአንድ አካልም አብረው እንዲሆኑ፥ 3ኛ. በወንጌልም መሰበክ በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነ የተስፋ ቃል አብረው እንዲካፈሉ ነው።

የቆላስያስ መልእክትን ደግሞ ስናይ ይህንንም ምስጢር የቆላስያስ ሰዎች የሚረዱት የጳውሎስን መልእክት ሲያነቡ ነው (ቁ 3፤ ቆላስ 1፥25-27)። ወደ ዋናው ነጥባችን ስንመጣ ይህ መገለጥ ለጳውሎስ የተሰጠው በደማስቆ መንገድ ላይ (ክርስቲያኖችን ለማሳደድ ሲሄድ) ኢየሱስ ከተገለጠለት በኋላ ነበር። ስለ እርሱም እግዚአብሔር ሲናገር «በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ እቃ ነው።» (ሐዋ 9፥15-16) ብሎለታል። ስለዚሁ ስለ ተሰጠው መገለጥ ደግሞ ጳውሎስ ራሱ ሲናገር «በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፣ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም» ብሎአል (ገላ 1፥15-17)። እንግዲህ ከላይ እንደተመለከትነው የምስጢሩ መገለጥ የመጣለት በመንፈስ ቅዱስ ሲሆን ይህንን መገለጥ ደግሞ የሚሰብከው በተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር (ቁ. 7)።

3፥14-21

ሐዋርያው በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብራት የሚንበረከክበት ዋናው ምክንያት – 1ኛ. በመንፈሱ በኃይል በውስጥ ሰውነታቸው እንዲጠነክሩ ሲሆን፥ 2ኛ. ደግሞ ክርስቶስ በልባቸው በእምነት እንዲኖር ነው። እነዚህ ሁለቱ መሠረታዊ ነገሮች ካሉአቸው ሥርና መሠረታቸው በፍቅር ይጸናል ማለት ነው። ሥርና መሠረታቸው ደግሞ በፍቅር ከጸና ደግሞ 1ኛ. ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ፥ ከፍታው፥ እንዲሁም ጥልቅነቱ ምን

ቂ ተጽእኖዎች በመጥር ሁለቱንም በእንደገት አምጥቶ ካለምንም እንቅፋት ወደ አብ ፊት እንዲቀ

ያህል መሆኑን ለማስተዋል ከመታወቅ የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ የበረቱ ይሆናሉ። 2ኛ. እስከ እግዚአብሔር ፍጹም ሙላት ደርሰው እንዲሞሉ ያስችላቸዋል። ከዚህ እንደምንረዳው የጳውሎስ ጸሎት ባጭሩ በመንፈስ ቅዱስ ይሞሉ ዘንድ ነው። እግዚአብሔርም ደግሞ ይህንን መንፈስ ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ በላይ እጅግ አብልጦ ይሰጠናል።

4፥1-6

በዚህ ክፍል ደግሞ በተጠሩበት መጠራታቸው በሚገባ እንዲመላለሱ ይለምናቸዋል። ይህም ደግሞ በትህትና፣ በየዋህነት፣ በትዕግስት፣ በፍቅርና እንዲሁም በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት በመጠበቅ እንዲመላለሱ ነው። እነዚህም በገላትያ ምዕራፍ አምስት ላይ ያየናቸው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ናቸው። በሌላ አነጋገር የሚለምናቸው ነገር የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ እንዲያፈሩ ነው። የመንፈስን አንድነት የሚጠብቁበትም ዋናው ምክንያት በአንድ ተስፋ ስለ ተጠሩ ነው። በአንድ ተስፋ እንደተጠሩ ሁሉ ደግሞ አንድ አካል፣ አንድ መንፈስ፣ አንድ ጌታ፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ጥምቀትና አንድ አምላክ አለ። ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ በማፍራት የመንፈስን አንድነትና ኅብረት በሰላም ማሰሪያ መጠበቅ አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው።

አንዳንድ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ሰም («እኛ ጋር ሪቫይቫል አለ ወደ እኛ ኑ» በማለት ሰዎችን ከቤተክርስቲያን ውስጥ በማውጣትና እንዲሁም ሕዝቡን በመከፋፈል ወደ ራሳቸው ስብሰባ ይወስዷቸው) እግዚአብሔር በክቡር ደሙ የዋጀውን ጉባኤ ሲያውኩና ሲከፋፍሉ ማየቱ በጣም ያሳዝናል። ራሳቸውን «የመንፈሳዊ እንቅስቃሴ» መሪ [ሪቫይቫሊስት] በማድረግ በንጽህና ትምህርት የሚጸኑትንና የእግዚአብሔር እርሻ የሆኑትን ግኅበረ ምዕመናንን ሰላማቸውን በማወክ መንጋውን ሲከፍሉና ሲበትኑ ያየን «ጌታ መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ በዚህ ሰንት ግፍ ተሰራ!» ብለን ያለቀስንባቸው ጊዜያቶች እንዳሉ እግዚአብሔር ራሱ ምስክራችን ነው። መቼም ቢሆን መንፈስ ቅዱስ የሚጠላውን የክፍፍል ሥራ እየሠራን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎትን እንዲሰጥ ማድረግ እንችልም። ጌታ

ርጽ አደረገ።

መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን በመቀየርም ሆነ በተብረታችንም መከከለA በመሆን በሰላም ማሰሪያ የአካሉን አንድነት ይጠብቃA እንጂ ከፋፋይ አይደለምና ነው።

የዚህ ክፍA አጣብብ እንደሚያሳየን ከሆነ «ሰላም» የሚለው ቃA ከሌሎች ጋር የሚኖረን ግንኙነት፣ ከጠብና ከጥላቻ እንዲሁም ከመከፋፈA የሚጠብቀን የመንፈስ ፍሬ ነው። ክርስቶስ ሰላማችን ሆኖ በመስቀሉ ኃይA በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር፣ በመቀጠልም ከእርስ በርሳችን ጋር የነበረውን የጠብ ግድግዳ በማፍረስ ሰላምን ካወጀልን ዘንዳ እኛ ደግሞ ይሄንን ከክርስቶስ የተቀበልነውን ሰላም በውስጣችን በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ አንጠብቅ ይገባናA እንጂ ያንን የፈረሰውን የጠብ ግድግዳ እንደገና አንገነባው አልተፈቀደልንም (2፣16-17፤ ሮሜ 14፣17፤ 15፣13)።

4፣8-16

ሐዋርያው በመዝሙር (68)፣ 18 ላይ ያለውን «ወደ ላይ አረግህ ምርኮን ማረክህ፣ ስጦታዎችንም ለሰዎች ሰጠህ» የሚለውን በመጥቀስ ክርስቶስ ሞትን አሸንፎ ከተነሳ በኋላ በክብር ወደ አባቱ እንዳረገ ጠቅሶአA። በማረጉም «ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው» ክርስቶስ ምርኮን ማርኮ ለሰዎች ስጦታዎችን እንደሰጠ ጠቅሶአA። እነዚህም ስጦታዎች እንዳንዶቹን ሐዋርያት፣ ሌሎቹን ነቢያት፣ ሌሎቹን ወንጌA ሰባኪነት፣ ሌሎቹን አረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ለቤተክርስቲያን ሰጠ።

የሰጠበትም ዋና ዓላማ ሁላችን የእግዚአብሔርን Aጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት እንድንደርስ ነው። ወደዚህ እንድነት ደረስን ማለት ደግሞ ሙሉ ሰው ወደ መሆን፣ የክርስቶስ ሙላት ወደ ሚሆን ሙላት በመድረስ፣ እንዲሁም በአገልግሎት በርትተን ለክርስቶስ አካA በመሆን እንደ ሕንጻ አንድንሠራ ነው። የክርስቶስ ሕንጻ ሆነን ከተሠራን ደግሞ (ክርስቶስ የሕንጻው ራስ ስለሆነ) እውነትን በመያዝ፣ ራሳችንን በፍቅር እያነጽን ራስ ወደ ሆነው ወደ እርሱ እናድጋለን እንጂ በትምህርተ ነፋስ በመናወጥም ወዲያና ወዲህ እየተነሳፈፍን እንደገና ተመልሰን ሕጻናት አንሆንም። ስለዚህም ቤተክርስቲያን በመንፈሳዊ ጤንነት እንድታድግ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ስጦታዎች እንደሚያስፈልጉት አጠያያቂ አይደለም።

4፣17-32

በዚህ ክፍA አሕዛብ በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱ የኢፌሶን ሰዎች ደግሞ እንደዚሁ እንዳይመላለሱ ይመክራቸዋA። አነርሱ እውነት በኢየሱስ እንዳለ ስለ ተማሩ አሮጌውን ሰው በማስወገድ በአዕምሮአቸው እየታደሱ፣ ስለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው መልበስ ይገባቸዋA (ቁ 17-24)። አዲሱን ሰው ከለበሱ ደግሞ ውሸትን በማስወገድ እርስ በርሳቸው በእውነትን ሊነጋገሩ ይገባቸዋA። አትስረቅ በማለትም ሌብነት በጸድቃን ጉባኤ ቦታ እንደሌለው ይነግርና በመቀጠልም ከመስረቅ ይልቅ ሥራን በመሥራት በጉባኤያቸው የተቸገሩትን መርዳት እንደሚጠቅም ይመክራA። ቀጥሎም ተቆጡ ኃጢአትን አታድርጉ፣ በቁጣችሁ ላይ ፀሃይ አይግባ (የተቆጣናቸውን ሰዎች ሳይመሽ ሳይነጋ ይቅርታ ልንጠይቅ ይገባናA። ነገር ግን ይህን ካላደረግን ኃጢአትን ስለ ምንሠራ በግA ሕይወታችንና በተብረታችን ጉብቶ እንዲፈተፍት ሰዲያብሰለ እድA እንሰጠዋለን)[95] በማለት ከወንድሞቻችን ጋር ፊት ለፊት በመነጋገር ልዩነቶቻችንን መፍታት እንደሚገባን ይመክረናA።

እንዴት ባለም ሁኔታ እርስ በርሳችን ፊት ለፊት መነጋገርም እንደሚገባን ሲገልጽ — ንግግራችን ለሚሰሙን ጸጋን በመስጠት የሚያንጽ እንጂ ሰውን የሚያፈርስ ክፉ ቃA መሆን እንደሌለበትና እርስ በርሳችን ቸሮች፣ ርህሩሆች በመሆን እግዚአብሔር ይቅር እንዳለን እኛም ይቅር በመባባA መነጋገር ይገባናA ብሎአA። በመቀጠልም መራርነት፣ ንዴት፣ ቁጣ፣ ጩኸት፣ መሳደብና ክፋት ሁሉ ለቤዛ ቀን የታተምንበትን በውስጣችን ያለውን የእግዚአብሔር መንፈስ ያሳዝነዋA ብሎአA።

እኛ ኢትዮጵያውያኖች ባብዛኛው ጊዜ ፊት ለፊት በመነጋገር ልዩነቶቻችንን ለመፍታት ስንቸገር እንታያለን። ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት ምናA

95

ስለዚህ ጉዳይ የበለጠ ማብራሪያ የሚፈልግ ሰው የሚከተለውን መጽሐፍ ቢያነብ ጠቃሚ የሆኑ ሃሳቦችን ሊያገኝ ይችላA — ዎልተር ኤA ሊይሬልድ፣ ኤፌሶንስ (ዎውንስቦሮ፣ ኢንተርቫርሲቲ ፕረስ 1997) 116-122።

ባትም በባሕላችን ሰውን ፊት ለፊት ከማናገር ይልቅ አማላጅን በመላክ ወይም በሰምታ መልክ ቅሬታን በተዘዋዋሪ መንገድ ማሰማት የተለመደ ነገር ስለሆነ ይሆናል። ስለዚህም ይህ ባሕላዊ ተጽእኖ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እስካልተሰበረ ድረስ አማኝ እርስ በርሱ ቅሬታውንና በደሉን ለመነጋገር ይቸገራል። ፊት ለፊ ትም ተነጋግሮ ልዩነትን ማስወገድ ካለተቻለ ደግሞ አማኙ በቂም፥ በጥላቻና ውሉ አድሮ በአድመኝነትና በቡድን መከፋፈል ውስጥ ራሱን ያገኘዋል። ስለሆ ነም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሊኖር ስሚገባው ፍቅር፥ ሰላምና አንድነት እን ቅፋት ይሆናል ማለት ነው።

የሥነልቡና ጠበብት እንደሚነግሩን ከሆነ በሰዎች መካከል ያለ (በግንኙ ነት መሐል) ያልተፈታ ችግር ሄዶ ሄዶ መራርነትን፥ ቁጣን፥ ንዴትን፥ ብስጭ ትን፥ ጥላቻን፥ ሃሜትን ወዘተ በማስከተል የሰውን ልቡና ያዘብጠዋል፥ መንፈሳዊ ሕይወቱንም ወደ ጨለማ ውስጥ ይከተዋል (1ዮሐ 2፥9-11)።[96] ይህ ደግሞ በክር ስቶስ አካል ውስጥ መለያየትን ከዚያም መከፋፈልን ስለሚያመጣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ያሳዝነዋል። ስለዚህም በወንድሞቻችንና በእህቶቻችን ላይ ያለንን ቅሬታ ሳይውል ሳያድር፥ ፊት ለፊት በመቅረብ ፍቅር በተሞላበት ሁኔታ ቸርችና ርህሩሆች ሆነን በመነጋገር ልንፈታ ይገባናል (ማቴ 18፥15-17)። ጥላቻ መንፈሳዊ ነቀርሳ በመሆኑ አማኝ ዕለት ዕለት ልቡን ከፍቶ በማሳየት መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳውና የተደበቀ ጥላቻ እንኳን ካለ እንዲመረምረው ራሱን ማቅረብ አለበት።

የእግዚአብሔር ሕዝብ የመንፈስን አንድነት በሰላም ማሰሪያ በመጠበቅ የጽድቅ ፍሬ ማፍራት አለበት። የእስራኤል ሕዝብ ኃጢአትን በመሥራት ይከ ተላቸው የነበረውን መንፈስ አሳዘኑት፥ እርሱም ተመልሶ ጠላት ሆናቸው (ኢሳ 63፥10)። ከዚህም ክፍል ውስጥና ከእስራኤል ታሪክ የምንማረው ነገር

96

ከሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ውስጥ ያልተፈታ ችግር ወይም ግጭት ሁሉ የሥጉልቡና መንፈሳዊ ተጽእኖን በሚያመጣ የሰውን ባሕርይና መንፈሳዊነት ይነካል። የእግዚአብሔር ቃል የፀደቁትን በ ቀን አልፍ ጊዜ (ቁጥር የለውም) ይቅር እንድልና የበደሉንን ደግሞ በመጀመሪያ ግንኙ ከዚያም ባ ይሰሙን ሁለት ሰዎችን ከእኛ ጋር በመውሰድ ማነጋገር እንደሚገባ ሲያስተምረን መንገር እ ንጂ በቂምና በጥላቻ ኃጢአት እንድንታሰር አይመክረንም (ማቴ 18፥15-22)። ይቅር ስለመባባል ከ ተጠቀሱት የክርስቲያን የሥጉልቡና መጻሕፍት ጠቃሚ ሆኖ ያገኘሁት እንደሚከተለው ነው፦ ርበርት

ምንድነው ቢባል— አዲሲቱዋ ኢየሩሳሌም ሲያስገባን አብሮን የወጣውን መንፈስ በመከፋፈልና ጽድቅ በሌለው ኑሮ ልናሳዝነው የተገባ አይደለም።

5፥18-21

ቀኖቹን በመዋጀት የጌታ ፍቃድ ምን እንደሆነ ማስተዋል ይገባናል እንጂ እንደ ሞኞች ጊዜያችንን በዋዛ ፈዛዛ ማሳለፍ የለብንም። የጌታ ፈቃድ በመንፈስ እንድንሞላ ነው እንጂ በወይን ጠጅ እንድንሞላ ወይም በመጠጥ እን ድንሰከር አይደለም። በጥንቱ የሚዲትሬንያኑ ክፍል ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ወይንጠጅ መጠጣት የወይን ጠጅ አምላክ በሆነው በዲዮኒሰስ ይሞላል ብለው ያምናሉ። ታዲያ የዚህ ዲዮኒሰስ የተባለው አምላክ ተከታዮች ወይን ጠጅን ከጠጡ በኋላ አምላካቸውን ለማስደሰት ሲሉ ዝሙትን ይፈጽማሉ።[97] የሐዋር ያው ነጥብ ምንድነው — ድሮ አሕዛብ በነበሩበት ጊዜ ማለትም ወደ ሌሎች አማልእክት ተሰበው በነበሩበት ጊዜ ያደርጉት የነበረውን «በወይን ጠጅ አምላክ» መሞላት አሁን በክርስቶስ ውስጥ ላለ ጸድቅ ተገቢ ሰላልሆነ ሊያደር ጉት እንደማይገባቸው ነው የሚናገረው።

በወይን ጠጅ የሚሞሉት ሕይወታቸውን በማባከን ጊዜአቸውን በከንቱ ሲያሳልፉ ማለትም ልባቸውን በማሳት በስካር ተነድተው ስተለያዩ ኃጢአቶች ራሳቸውን አሳልፈው ሲሰጡ፥ በመንፈስ ዕለት ዕለት የሚሞሉት ግን ጊዜያቸውን በመዋጀት እግዚአብሔርን እያመሰኩ ያሳልፋታል። መንፈስም አምልኮን ስለሚ መራ በመዝሙርና በዝማሬ እንዲሁም በመንፈሳዊ ቅኔ ለጌታ እንድንቀኝና እንድ ዘምር በማድረግ ምስጋና የበዛለት የአምልኮ ሕይወት እንድንኖር ያደርገናል። ስለዚህም በመንፈስ ቅዱስ እንጂ በወይን ጠጅ አንሞላ። ምክንያቱም የተጠ ራነው እግዚአብሔርን በኑሮአችንና በቃላችን ለማምለክ ነው እንጂ ዋበብ እንደ ሌላቸው ሰዎች በመጠጥ የታሰረና የባከነ ሕይወት እንድንኖር አይደለምና።

መከረ እና ዶናልድ ሳፓ፥ *ዘ ሰርች ፎር ፐሰናሊቲ ሪለስ ፍሮም ዘ ተርሜንትስ ኦቭ ተከሲክ ኦንሮርጊ ቭክስ* (አን አርቦር፥ ሰርቸንት ፕብሊኬሽን፤ 1996)።

[97] ኪነር፥ *ዘ ኢይ ቪ ፕ ባይብል ባክግራውንድ ኮሜንተሪ ኦቭ ዘ ኒው ቴስተመንት* (ዶውነርስ ግሮቭ፥ ኢንተርቫርሲቲ ፕረስ፤ 1993) 550።

6፥10-20

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ሲናገር የዲያብሎስን ሽንገላ ለመቃወም እንች ል ዘንድ በጌታና በኃይሉ ችሎት እንድንበረታ ይመክረናል። በ1፥3 ላይ እንደ ምናስታውሰው የተባረክንበት መንፈሳዊ ባርኮት በመንፈስ ቅዱስ ከሰማያዊ ስፍራ መምጣቱን ነግሮናል። ከዚያም በመቀጠል እግዚአብሔር የኃይሉ ታላቅነት ምን እንደሆነ ይታወቅ ዘንድ ክርስቶስን ከሙታን አስነሣው ብሎአል (1፥20)። ከዚያም ደግሞ ከአለቅነትና ከሥልጣናት ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይ ከፍ አድርጎ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ አስቀመጠው (1፥21-22)። በማይታዘዙት ላይ አለቃ በሆነው በዲያብሎስ ስር የነበርንውን እኛን በክርስቶስ ትንሣኤ በመሳተፋ ችን ነጻ አውጥቶ ከርሱ ጋር በሰማያዊ ስፍራ አስቀመጠን (2፥2-7)።

አሕዛብና አይሁድ ከእምነት በተገኘ ደህንነት በአንድነት ሆነው እግዚአ ብሔርን እንደሚወርሱት ምስጢሩ በቤተክርስቲያን በኩል የተገለጠው በሰማያዊ ስፍራ ነው (3፥3-12)። ክርስቶስም ወደ ላይ ከፍ ባለ ጊዜ ስጦታዎችን ለቤተክር ስቲያን የሰጠው በዚሁ በሰማያዊ ስፍራ ሲሆን ስጦታውም የተሰጣት ከዲያብሎስ የሚመጣውን የስህተት ትምህርት እንድትቃወም ነው (4፥7-16)። ስለዚህም ይህንን የደህንነትን ታላቅ ምስጢርና በጸጋ ስጦታዎች የተሞሉ አገልጋዮችን በሰ ማያዊ ስፍራ የተቀበለችውና ራሱዋም በሰማያዊ ስፍራ ከጌታዋ ጋር የተቀመ ጠችው ቤተክርስቲያን አሁን ደግሞ ይህንን ታላቅ ምስጢር ሊዋጋ የመጣውን ዲያብሎስና ሠራዊቱን በሰማያዊ ስፍራ መንፈሳዊ ጦርነትን ልትገጥመው ይገ ባታል።

መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር ሳይሆን በሰማያዊ ስፍራ ካሉ የክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ስለሆነ በክፋው ቀን ለመቃወምና ሁሉንም የጠላትን ውጊያ አሸንፈን በድል ለመቆም እንድንችል የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ መልበስ ይኖርብናል። በዚህ ክፍል ሁለት ዓይነት የጦር ዕቃዎች ተጠቅሰዋል –

1. ለመከላከል የሚጠቅም ሲሆን ይህም –

- ወገባችንን በእውነት መታጠቅ (በተገለጠልን የእግዚአብሔር እውነት መኖር)
- የጽድቅን ጥሩር መልበስ (ኃጢአታችንን በመናዘዝ የቅድስናን ኑሮ መኖር)
- የሰላምን ወንጌል ተጫምተን መቆም (እርቀ-እግዚአብሔር የሚያመጣውን የምሥራች ቃል ላልሰሙት ማዳረስ) ነው።

2. የማጥቂያ መሳሪያ ሲሆን የሚንቦለቦሉትን የክፉውን ፍላጻዎችለማጥፋት ይጠ ቅመናል ይህም —

- የእምነትን ጋሻ ማንሳት (በእምነት እንደ ዳንነው ሁሉ አሁንም ሩጫችንን በእምነት መጨረስ ይኖርብናል፥ ካለ እምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት አይቻልምና፤ እንዲሁም ደግሞ ጋሻችን እግዚአብሔር ነው (መዝ 7፥10)።
- የመዳንን ራስ ቁር መልበስ (በጦርነት ውስጥ ወታደር ጭንቅላቱን በመሸፈን ወይም በመደበቅ ይዋጋል ምክንያቱም ጭንቅላቱን የተመታ ሰው ቶሎ የመሞት እድል አለውና፤ እንደዚሁም ሁሉ ደህንነታችን የክርስትና ሕይወታ ችን ጭንቅላት ነው። ሐዋርያው በዚህ በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ደህንነታ ችሁን ታጣላችሁ ለማለት ፈልጎ ሳይሆን ነገር ግን በጌታ ያገኘነውን ደህንነት በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ እንድንይዘው ነው። ከዚያም ይህንን ደህንነት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለሌሎች እንሰብክለን። አማኝ የሚያድነውን ወንጌል ይዞ በመንፈስ ኃይል ጨለማን ሰንጥቆ በመግባት በዚያ ለተቀመጡት የምሥራቹን ቃል ያበራላቸዋል። የያዘውም ቃል ብርሃን ስለሆነ ጨለማ አይሸንፈውም (ዮሐ 1፥5፤ ፊል 2፥12፤ 1ተሰሎ 5፥8)።
- የመንፈስ ሰይፍ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ሊኖርብን ይገባል። ይህም ማለት ቃሉን ማጥናትና በቃሉ ውስጥ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው (ኢያሱ 1፥7-9)
- በጸሎትና በልመና ዘወትር በመንፈስ ቅዱስ የተመራ ጸሎት ማቅረብ ሲሆን ይህም ስለ ቅዱሳንና ወንጌልን በመስበክ ሥራ ላይ ለተሰማሩትም ጭምር በመጸለይ ነው። [98]

98

ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ጎለም ጥቦች ማለትም በሰማያዊ ስፍራ ካለ የክፋት መንፈሳዊ ሠራዊት ጋር ቤተክርስቲያን ያለባትን ጦርነት አስመልክቶ ዶ/ር ክሊንተን አርነልድ ኢፊዚያንስ በ ተባለው መጽሐፋቸው ውስጥ ጠለቅና ሰፉ ባለ መልኩ አስቀምጠውታል። ይህንን የምዕራፍ 6 ክፍል ጠለቅ ብሎ ለማወቅ የፈለገ ሰው የርሳቸውን መጽሐፍ ቢያነብ ብዙ ጠቃሚ የሆነ እውቀትን ይገ

«ለኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና።»

ፊልጵስዩስ 3፥3

14

መንፈስ ቅዱስና የፊልጵስዩስ ሰዎች

አፍሮዲጡ ወደ ጳውሎስ ሰመታን ይዞ በመጣ ጊዜ በኢዎድያንና በሲንጢኬ መካከል በቤተክርስቲያን አንዳንድ አለ መግባባት አንዳለ ነገርት ነበር (4፥2)። ሐዋርያውም ፍቅራቸው በእውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲመጣና በእንድ ልብ ሰለ ወንጌል ሃይማኖት አብረው እየተጋደሉ በእንድ መንፈስ በመቆም ለክርስቶስ ወንጌል አን

ያል።— ከሊንተን ኢ አርኖልድ፣ *ኤፌሶንስ፣ ፓወር ኤንድ ማጂክ ዘ ኮንሊፐት ኦቭ ፓወር ኢን ሲይት ኦቭ ኢትስ ሂስቶሪካል ሲቲንግ* (ግራንድራፒድስ፡ ቤከር ቡክ ሃውስ፤ 1992) 65-67።

ደሚገባ እንዲኖሩ ይመክራቸዋል (1፥11, 27)። በእንድ መንፈስ መቆም ማለት አማኞቹ የመንፈስን ጎብረት በመጠበቅ የሚኖራቸው የመንፈስ ቅዱስ አምላድ ወደ አንድነት ያመጣቸዋል ማለት ነው። በአንድነት መኖር ማለት ደግሞ ለክር ስቶስ ወንጌል እንደሚገባ መኖር ማለት ነው።[99] ምንም እንኳን ደህንነት የግል ውሳኔ ቢሆንም አንድ ጊዜ ወደ ክርስቶስ አካል ከመጣን በኋላ ግን የምንኖረው ኑሮ በአንድነትና በጎብረት ላይ የተመረኮዘ ነው። ምክንያቱም መንፈሳዊ ቤት ሆነን የምንሠራው በአንድነት ተጋጥመን ራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ በአን ድነት ሆነን ስናድግ ነው።

2፥1-11

በክርስቶስ አንዳች ምክር ቢሆን — የፍቅር መጽናት ቢሆን፥ የመንፈስ ጎብረት ቢሆን፥ ምሕረትና ርህራሄ ቢሆኑ በአንድ አሳብ በመስማማት ደስታውን እንዲፈጽሙለት ይነግራቸዋል። በአንድ አሳብ መስማማታቸው ደግሞ አንድ ፍቅር፥ አንድ አሳብና አንድ ልብ እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል። ይህም አንድ ነት ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በክንቱ ውዳሴ ተነሳስቶ የማይረባ ነገር በማድረግ ሳይሆን ነገር ግን አያንዳንዱ ባልንጀራውን ከራሱ እንዲሻል በትህትና በመቁጠርና ለራሱ የሚጠቅመውን ሳይሆን ለባልንጀራው የሚጠቅመውን በመፈ ለግ የሚገኝ ነው። ይህም ደግሞ ቀድሞ በክርስቶስ የነበረ አሳብ ነው — እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ባለ ለራሱ የሚጠቅመውን ነገር ሳይሆን ነገር ግን ለእኛ የሚጠቅመንን ነገር ሊሰጠን ፈልጎ ራሱን በማዋረድ የሰውን ሥጋ ደርቦ መጣ (ሰው ሆኖ መጣ)። ከዚያም ወደ ቀራንዮ በመሄድ የመስቀል ሞት ሞቶ ከኃጢአትና ከሞት ባርነት ነፃ አወጣን።

ስለሆነም እኛም ከጌታችን በመማር መንፈስ በሚሰጠን ኃይል ሌሎች ወንድሞቻችንን ከእኛ እንደሚሻሉ በመቁጠር ለናገለግላቸው ይገባናል እንጂ በክንቱ ውዳሴ በመነሳት፥ በትዕቢት በመነሣትና አድልዎ በተሞላበት ሁኔታ ለወ ገኔ ይጠቅማል በማለት የክርስቶስን አካል ልንነዳ አይገባንም። ወገናዊነት ሂደ ሂደ መከፋፈልን በማምጣት የክርስቶስን አካል ያቆስላል። በመንፈስ እግዚአ

[99] ራ፡ *ጎደስ ኢምፓወሪንግ ፕሬዘንስ* 746።

ብሔርን የሚያመልክ ሰው በክርስቶስ ከመመካት በስተቀር ሌላ የሚመካበት ነገር ሊኖረው አይገባም። «እኔ የአገሌ ወገን ነኝ»፥ «የእኔ ዘር ከማንም ዘር ይበል ጣል»፥ «የእኔ እምነት ከማንም በላይ ነው»፥ «የእኔ እውቀት ከማንም ይበል ጣል» ወዘተ. እየተባባልን በከንቱ ውዳሴም ተነስተን፣ በትዕቢት፥ በቂምና በጥላቻ በመሞላት ጌታን ልናሳዝነው የተገባ አይደለም። ምክንያቱም መከፋፈል ባለበት በአንድ ልብ ስለ ወንጌል ሃይማኖት መጋደልና በአንድ መንፈስ መቆም ፈጽሞ አይቻልም።

መመካት ቢያስፈልግ ሐዋርያው ጳውሎስ በሥጋ የሚመካበት ብዙ ነገር ነበረው። ስለ ግርዘት ብትጠይቁ፥ በሰምንተኛው ቀን የተገረዘ፤ ስለ ዘር ብትጠይቁ፥ የአብርሃም ዘር አሰራኤላዊ የሆነ፤ ስለ ነገድ ብትጠይቁ ከአሰራኤል አባቶች አንዱ የሆነው ያዕቆብ እጅግ አድርጎ ከሚወዳት ከራሔል የተወለደ፥ የመጀመሪያው የአሰራኤል ንጉሥ (ሳኦል) ከወጣበት ከብንያም ነገድና በሙሴ«በእግዚአብሔር የተወደደ» ተብሎ ከተመረቀው ነገድ የወጣ ብንያማዊ ነበር (ዘዳ 33፥12)፤ ስለ አስተዳደግ ብትጠይቁ፥ በስደት ሳይሆን ነገር ግን በተስፋይቱ ምድር ሕጉንና የአባቶችን ወግና ቋንቋ አጥንቶ ያደገ ዕብራዊ ነበር[100]፤ ስለ ሕግ ብትጠይቁ፥ አሰራኤልን ከሚመሩት የሕግና የሃይማኖት ሊቃውንት ከሆኑት ከፈሪሳው ያን አንዱ ፈሪሳዊ የሆነ ለዛውም ከታላቁ ሊቀ ሊቃውንት ከገማልያል እግር ሥር ቁጭ ብሎ የተማረ ነበር (ሐዋ 22፥3)፤ ስለ ቅንዓት ብትጠይቁ፥ ቤተክርስቲያንን አሳዳጅ ለዚያውም የመጀመሪያው ሰደት በቤተክርስቲያን ላያ በተነሳ ጊዜ ማለትም አስጠፋኖስ ሲገደል ዋነኛው ተባባሪና አስተባባሪ ነበር፤ ከሕግ ስለሚገኝ ጽድቅ ብትጠይቁ ያለነቀፋ ነበር።

እንግዲህ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በሥጋ ለሚመካ ሰው ታላቅ የሆኑ ክንውኖች ሲሆኑ በኅብረተሰቡ ውስጥም ጥሩ የሆነን የክብሬታ ስፍራን የሚያስጡ

100

በዚያን ጊዜ ይኖሩ የነበሩት አይሁዶች በሁለት ዓይነት መንገድ ይጠራሉ — አነርሱም የይሁዳ አይሁድና የግሪክ አይሁድ ይባላሉ። የይሁዳ አይሁድ ይእስራኤል ምድር ያደጉና በምኩራቦቻቸው የዕብራይስጥን ቋንቋ ሲጠቀሙ የአረማውያንን ቋንቋ ደግሞ ለመግባቢያነት የሚጠቀሙ ናቸው። የግሪክ አይሁዶች ግን የሚናገሩትም ሆነ በምኩራቦቻቸው የሚጠቀሙበት ቋንቋ የግሪክ ቋንቋ ነው (ሰፕቱጂንት ማለትም ወደ ግሪክ የተተረጎመውን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ነው) (ሐዋ 6፥1፤ 2ቆሮ 11፥25)። — ኤፍ ኤፍ ብሩስ፣ *ፖል ኤፖስትል ኦቭ ዚ ሃርት ሬት ፍሪ* (ግሬንድ ራፒድስ፣ ኤርድመንስ 1996) 42።

ናቸው። ነገር ግን ለጳውሎስ ረብ የነበረውን ነገር ሁሉ ስለ ክርስቶስ ሲል እንደ ጉዳት ይቆጥረዋል። ይህም ማለትም ጳውሎስ በክርስቶስ ጽድቅ ውስጥ ለመገኘትና የትንሣኤውን ኃይል ለማወቅ ሁሉንም ነገር እንደ ጉድፍ ወይም እንደ እዳሪ ይቆጥራቸዋል (ፊልጵ 3፥3-11)። ምክንያቱም ጳውሎስ በመንፈስ እግዚአብሔርን የሚያመልክ ሰው ስለበር ከክርስቶስ በስተቀር የሚመካበት ሌላ ነገር የለውም።

ስለዚህም እኛም ደግሞ ራሳችንን ዝቅ በማድረግና በየዋሃት መንፈስ በመሆን ለራሳችን የሚጠቅመውን ሳይሆን ነገር ግን ለወንድሞቻችን የሚጠቅመውን በመፈለግ ማገልገል አለብን። ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ መኖር ማለት ሌሎች ከእኛ እንደሚሻሉ በማሰብ ራሳችንን መሥዋዕት አድርገን በማቅረብ ማገልገል ማለት ነው እንጂ በወገናዊነትና በቡድን ክፍፍል ውስጥ ገብተን፣ በከንቱ ውዳሴም በመመካትና ለወገኔ ይጠቅማል የምንለውን በመሥራት አይደለም። በመሠረቱ ፍቅራችን በእውቀትና በማስተዋል ከሁሉ ይልቅ እያደገ ሲበዛ ይገባዋል — ይህም ደግሞ በክርስቶስ አስቀድሞ የነበረ አሳብ ነው።

«... የፈቃዱን እውቀት መንፈሳዊ ጥበብና አስምርን ሁሉ እንዲሞላባችሁ አየለመንን፣ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም።»

ቆላስይስ 1፥9-10

15

መንፈስ ቅዱስና የቆላስይስ ሰዎች

ኤጳፍራ የቆላስይስ አማኞች ያላ ቸውን ፍቅር ለጳውሎስ በነገረው ጊዜ ጳውሎስም ነገሩ ደስ ስላሰኘው «በመንፈስ ስለሚሆን ፍቅራችሁ አስታወቀን» በማለት ገልጸታል። ይህም የሚያሳየን የቆላ ስይስ አማኞች ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬ አንዱ የሆነውን ፍቅርን እንዳፈሩ ነው (ገላት 5፥22፤ ሮሜ 15፥30)። የሐዋርያውም የልብ ምኞቱና ጸሎቱ 1ኛ. በመን ፈስ ቅዱስ በሚሆን የፈቃዱን እውቀት እንዲሞሉ 2ኛ. ለጌታ እንደሚገባ በመ መላለስ በነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ እንዲያሰኙ ነው። ታዲያ ይህንን ሊያ

ደርጉ የሚችሉት አራት ነገሮችን በመፈጸም ነው — ሀ) በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬን በማፍራት ለ) በእግዚአብሔር እውቀት በማደግ ሐ) በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየ በረቱ ከደስታ ጋር፣ በመጽናትና በመታገስ መ) በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እን ድንከፈል ያበቃንን አብን በማመስገን ነው።

ባጠቃላይ ከላይ እንደተመለከትነው የጳውሎስ ጸሎት የቆላስይስ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲሞሉና በርሱም ችሎትና ኃይል እንዲ በረቱ ነው። በሌላ አነጋገር ጸሎቱ በመንፈስ እንዲመላለሱ ነው፤ ምክንያቱም ከአብና ከወልድ ወሰዶ የሚነግረን፣ የሚያስተምረን እንዲሁም የቅድስና ኑሮን እንድንኖር የሚያስችለን መንፈስ ቅዱስ ነውና (ዮሐ 16፥14-15፤ 2ተሰሎ 2፥13፤ ሮሜ 8፥13፤ ቲቶ 3፥5)።

3፥1-17

ከክርስቶስ ጋር ሞተን ከተነሳን ሕይወታችን ከርሱ ጋር ተሰውሮአልና ያለነው በላይ በሰማይ ነው። ስለዚህም በሰማይ ካለን ደግሞ ሰማያዊ የሆነን ኑሮ መኖር አለብን፤ ይህም ደግሞ በቅድስና መኖራችን ነው። ከክርስቶስም ጋር አብረን በመሞታችንና በመነሳታችን፣ በምድር ያሉትን ብልቶቻችንን በመግ ደል አርጌውን ሰው ከሥራው ጋር አስወግደናልና ነው። ስለዚህም አግዚአ ብሔርን ለመምሰል የሚያስችለንን፣ ዕለት ዕለት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ስለለበስነው የመንፈስን ፍሬ በማፍራት ልንኖር ይገባናል (ቁ 1-13)። በሌላም በኩል ደግሞ ክርስቶስ ይቅር እንዳለን እኛም ደግሞ ይቅር ልንባባል ይገባናል፤ ይህንንም ለማድረግ የምንችለው የፍጹሚ ግሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ስንለብሰው ነው።

እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ሕይወታችን አብሮ ከተሰወረ – 1ኛ. በአንድ አካል የተጠራንበት የክርስቶስ ሰላም በልባችን መግዛት አለበት። 2ኛ. የእግዚአ ብሔር ቃል በሙላት ሊኖረን ይገባል። 3ኛ. በጥበብ ማስተማርና የተሳሳቱትን ደግሞ በጥበብ መገሰጽ አለብን። 4ኛ. በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔም በጸጋው በልባችን ለእግዚአብሔር እየዘመርን ሁሉ ልናመልከው ይገባናል (ቁ 14 -17)። እንግዲህ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የክርስትና ፍሬዎች ሁሉ የሚገኙት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው።

«መንፈስን አታጥፉ፤ ትንቢትንም አትናቁ፤
ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ፤ ከማናቸውም ክፉ ነገር ራቁ።»
1 ተሰሎንቄ 5፥19-22

16

መንፈስ ቅዱስና የተሰሎንቄ ሰዎች

አንደኛ ተሰሎንቄ

የተሰሎንቄን አማኞች በእምነታቸው ያጸናቸው ዘንድ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ወደ እነርሱ ላከው (3፥2)። ጢሞቴዎስም እነርሱን ጎብኝቶና አገልግሎ ወደ ጳውሎስ በተመለሰ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ያፈሩትን ፍቅርና እምነት የምሥራች ብሎ በነገረው ጊዜ ጳውሎስ እጅግ ተጽናና፥ እግዚአብሔርንም ስለ እነርሱ አመሰገነ (1፥2-3፤ 3፥6-8)። ሐዋርያው ጳውሎስም በመጀመሪያ ወደ እነርሱ ይዘት የሄደው ወንጌል በማቅለሙ ቃል የተ

ለበጠ ሳይሆን ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በመግለጥ ስለ ነበር ትልቅ የሆነ የኃጢአት ወቀሳንና እውነትን የመረዳት እውቀት በማምጣቱ ከተጣበቁበት የጣዖት አምልኮ ወጥተው የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅና በማመን በኩል ወደ ሚገኘው ደህንነት መጡ (ቁ 5 እና 10)።

ኃይሉንም በመቀበላቸው በጌታ ምክንያት የደረሰባቸውን ስደትና መከራ እንደ ጌታ ኢየሱስና እንደነ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ከሚገኝ ሃሴትና ደስታ ተቀበሉት። እምነታቸውም በመቄዶንያና በአካያ ላሉት እንዲሁም ለሌሎች አማኞች ምሳሌ ሆነ (1፥6-9፤ 2ቆሮ 8፥2፤ ሮሜ 5፥3-5፤ ሐዋ 5፥41፤ ያዕቆ 1፥2 ፤ 1ጴጥ 1፥6)። ስለ ስሙ የሚመጣን መከራና ስደት በእውነት የቆመች የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ልትጋፈጠው የሚገባት አንዱ የክርስትና ሕይወት ጉዞ ነው። አማኝ በመከራው ደስተኛ የሚሆነው ወደ ፊት ከጌታው ጋር በክብር የሚነግሥበትን ሕይወት አሁን በተሞላው መንፈስ ስለሚቀምሰው ነው። ስለዚህም ያንን ወደፊት የሚመጣውን ክብር አያስበ የአሁኑን ዘመን ሰቃይ በደስታ ይቀበላል።[101]

4፥8

የተሰሎንቄ አማኞች ጌታን በተቀበሉ ጊዜ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ መመላለስ እንደሚገባቸውና እንዴትስ እግዚአብሔርን ማስደሰት እንደሚችሉ ትዕዛዝን ከጳውሎስ እጅ ተቀብለው ነበር (4፥1-2)። በዚህ ክፍል ደግሞ የሐዋርያው ቀረነገር በቅድስና መኖራቸው ሲሆን ይህም የእግዚአብሔር ፍቃድ እንደሆነና ኃጢአትን እግዚአብሔር እንደሚጠላ ተናግሮአል። እግዚአብሔር የጠራን ለርኩሰት ሳይሆን በቅድስና ለመኖር ነው። ስለዚህም ይህንን ትእዛዝ በመጣል በኃጢአት የሚመላለስ ክርስቲያን ሰውን የጣለ ሳይሆን እንዲቀድሰን መንፈሱን በውስጣችን ያኖረውን እግዚአብሔርን ነው የጣለ በማለት የኃጢአትን አስከፊ ገጽታ አስቀምጦታል (ቁ 3-8)። መንፈስ ቅዱስ ሰውን ዳግም እንዲወለድ ብቻ ሳይሆን የሚያደርገው ነገር ግን ከዚያም በኋላ ባሕርይን በመለወጥ ፍሬ እንድናፈራ እያደረገ እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተን እንድንኖር ያስችለናል።

[101] ራእ ገደለ ኢምፓወሪንግ ፕሬዘንስ ፤ 47።

ስለዚህም በጋጢአት የሚመላለስ አማኝ ሊቀድሰው የሚችለውን መንፈስ ቅዱስን የማይፈልግ ነው።

5፤19-22

የዚህ ክፍል አገባብ እንደሚያሳየን ከሆነ ሐዋርያው የተሰሎንቄ አማኞች የመንፈስ ፍሬ እንዲበዛላቸው ይመክራቸዋል። ይህም — እርስ በርሳቸው በሰላም መኖር፣ ትዕግስት፣ ሩሕሩህነት፣ መልካሙን ለማድረግ መትጋትና ደስታ እንዲበዛላቸው ነው (5፤12-16)። ከዚያም ሳያቋርጡ እንዲጸልዩና በሁሉ እንዲ ያመሰግኑ በመምከር ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእነርሱ እንደሆነ ተናግሮአል (ቁ 17-18)። በመቀጠልም የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ጥንቃቄና ማስተዋል በተሞላበት ሁኔታ መያዝ እንደሚገባቸው እንጂ መጣል እንደሌለ ባቸው ሲነግራቸው – «መንፈስን አታጥፉ» ካለ በኋላ የመንፈስ ፍንደቃንና [Ecstasy] ትንቢትን ከመናቅ ወይም ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ስም የሚመጣን ማንኛውንም ዓይነት ትንቢት ከመቀበል በፊት ከእውነት እንደሆነና እንዳልሆነ መፈተን፣ ከዚያም መልካሙን መያዝና ክፉውን ማስወገድ እንደሚገባ ይመክራቸ ዋል። ብዙ አሳቾች የበግ ለምድ ለብሰው በሚወጡበት በዚህ ዘመን እኛም በዚህ ጉዳይ ላይ ልንጠነቀቅ ይገባናል።

በጉባኤያችን የሚመጡትን መልእክቶችና የሚደረጉትን ተአምራት አሜን ብለን ከመቀበላችን በፊት ራሳችንን ልንጠይቅ የሚገቡን ነገሮች አሉ፤ እነርሱም —

- በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ የመልእክቱን እውነተኛነት ለልባችን መስክሮልናል ወይ? (ሐዋ 16፤16-18፤ 1ቆሮ 12፤10) ።
- መልእክቱ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ይስማማል ወይ? (ዘዳግ 13፤1-5፤ 1ዮሐ 4፤1) (የእግዚአብሔር ቃል ትንቢትንና አገልግሎትን የመለኪያ ጠፍራችን ወይም ሚዛናችን ነው) ።
- መልእክቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ኢየሱስን በጉባኤው ውስጥ ያከብራል/ያሳላል ወይ? (ዮሐ 15፤26-27፤ 16፤14)።
- መልእክቱ ወቅታዊነት [Relevancy] አለው ወይ? ይህም ባጠቃላይ እግዚአ ብሔር ሰውን ለማዳን ያለውን አቅድና ዓላማ እንዲሁም ለዚያች ቤተክርስ

ቲያን በተለይ ያለውን አቅድና ዓላማ ያስፋፋል ወይ? ወይም በወቅቱ በአገ ርና በቤተክርስቲያን ውስጥ ላለው ችግር ወይም መልካም አገልግሎት አስተዋጽኦ ያደርጋል ወይ? ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል። እንደሚ ታወቀው አንዳንድ ሰዎች ለራሳቸው ክብርን ለማምጣት ሲሉ ወይም ደግሞ እንዲፈሩ ስለሚፈልጉ ያለውንና የሚታወቀውን እውነታ በትንቢት መልክ ያቀርባሉ። ምንም እንኳን መልእክቱ ቀጥተኛ የሆነን ጉዳት ባያመጣም ዞሮ ዞሮ ከእግዚአብሔር ያልሆነን መልእክት በማቅረባቸው ዋሽተዋልና ኃጢአትን ሰርተዋል (ኤር 23፤16-18)። ሌሎቹ ደግሞ ወገናዊነትን ማሳየት እነርሱን የሚደግፉአቸውንና የሚያሞጋግሱአቸውን በመምረጥ «በትንቢት» ያረሰሩሰዋቸዋል። ይህ ዓይነቱ መልእክት ከግነጽ ይልቅ መከፋፈልን በመ ፍጠር የመንፈስን ኅብረትና አንድነት ስለሚያደፈርስ አደገኛ ነው (ይህንን ስል ከእግዚአብሔር የሆነ መልእክት ለግለሰቦች መምጣት የለበትም ማለቴ እንዳልሆነ አንባቢው ሊረዳልኝ አፈልጋለሁ። እንደውም እግዚአብሔር የአገልጋዮቹን ሥልጣንና ኃላፊነት ለማጽናት፣ ለማበረታታት፣ ለመምከር፣ ለማስጠንቀቅ ወዘተ. መልእክት በጉባኤ ወይም በተበረቱ መሐል ይሰጣል፤ ዘዳግ 18፤20፤ ኤርም 28፤1-17ሐዋ 13፤1-3፤ 1ጢሞ 1፤18፤ 4፤14 ፊል 2፤3፤ 1ቆሮ 14፤3)።

- መልእክቱን ያቀረበው ሰው ሕይወትና አገልግሎት በቤተክርስቲያኑዋ ዘንድ (ወይም ደግሞ ከሌላ ቦታ የመጣ ከሆነ ከሚሳተፍበት ቤተክርስቲያን ዘንድ) ጥሩ የሕይወት ምስክርነት አለው ወይ? (ዘዳግ 13፤1-5፤ ኤርም 23፤14፤ 29፤21-23)።
- የቤተክርስቲያኒቱዋ ነቢያት ከዚያም መሪዎች መልእክቱን መርምረው ለይ ተውታል ወይም ይለዪታል ወይ? (ነቢያት ራሳቸው ቢሆኑ በቤተክርስቲያን መሪዎች ሊገመገሙ ይገባቸዋል፤ 1ቆሮ 14፤29)።
- በመጨረሻም ትንቢቱ መፈጸሙንና አለመፈጸሙን የመከታተል ኃላፊነት አለብን (ዘዳግ 18፤20-22)።

ከላይ የተጠቀሰውን መመሪያ ባለመከተል መልእክትን ሳይመረምሩና ሳይፈትኑ በመቀበል በሃሰት ትንቢት የቆሰሉትን ሰዎች ቤታቸው ይቁጠረው። በሌላው አንጻር ደግሞ መቼም ቅዠት ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም እንዲሉ

የሰሀተት አመራርን ፈርተን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ልናዳፍንና በተለይ ደግሞ የትንቢትን አገልግሎት ልንንቅ አይገባንም (ሮሜ 12፥6፤ 1ቆሮ 12፥10፤ 14፥1, 4-5)። ስለሆነም በመንፈስ ቅዱስ ላይ ተደግፈንና በቃሉ ተሞልተን ካገለገልን ከሰሀተት አመራር ሁሉ ሊጠብቀንና በድል መንሳቱ ሊያዘረን ፍጹም የታመነ አምላክ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ 10፥27-30 ባለው ክፍል ላይ ሲናገር «በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል» ካለ በኋላ በመቀጠልም «ከእኔም ማንም አይነጥቃቸውም። የሰጠኝ አብ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም» ብሎ ስለ ነገረን በቃሉ ላይ ታላቅ የሆነ እምነት አለን።

ሁለተኛ ተሰሎንቄ

የጳውሎስን የመጀመሪያውን የተሰሎንቄ መልእክት ያነበቡ አንዳንድ ሰዎች መልእክቱን በትክክል ባለመረዳታቸው ምክንያት የተነሳ አንዳንዶች ከመካከላቸው በመነሳት «የጳውሎስ መልእክት ሲተረጎም ይህንን ይመስላል፥ ይላል መንፈስ ቅዱስ...» በማለት ጳውሎስ የጌታ ቀን መጥቶአል ወይም ደግሞ ደርሶአል እንዳለ አድርገው በመተርጎማቸው ጉባኤውን አናወጡት (2፥1-2)።[102] ስለዚህም ሐዋርያው ሲናገር «ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለ መሰብሰባችን፥ በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደሚመጣ በመልእክት — የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ፥ ከአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እንለምናችሁአለን።» በማለት አረጋጋቸው።

ይህንን የሰሀተት ትንቢት የሰሙ አንዳንዶቹም እንግዲህ የጌታ ቀን ደርሶአል በማለት ሥራ እንኳን መሥራት በማቆማቸው በሌሎች ላይ ሸክም ሆኑ (1፥3-10)። ጳውሎስም ሲናገር «ከሀዲቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የአመፅ ሰው

[102] ፌ፥ ጎደሰ ኢምፓወሪንግ ፕሬዘንስ፤ 74።

አርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ»፥ የጌታ ቀን አይደርስም በማለት ሳይናወጡ ነገር ግን ጊዜውንና ወቅቱን እየመረመሩ፥ ሥራም እየሠሩ እንዲጠብቁ አሳሰባቸው። በተጨማሪም ጌታ ከሥልጣኑ መላእክት ጋር ከሰማይ በእሳት ነበልባል በሚገለጥበት ጊዜ መከራን እንደ አነርሱ ለተቀበሉ አረፍትን ብድራት አድርጎ እንደሚመልስ፣ መከራን ባመጡባቸው ሰዎች ላይ ደግሞ መከራን እንደሚፈርድና የጥፋት ልጅ የሆነውን ይህንን የአመፅ ሰው ከአፉ በሚወጣው መንፈስ እንደሚያጠፋው በመንገር በእንዴት ዓይነት ሁኔታ የጌታን ዳግም መምጣት መጠባበቅ እንደሚገባቸው ይመክራል (1፥5-8፤ 2፥1-2, 8፤ 3፥6-15)።

ስለዚህም ጌታ አምላክ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሃሳትንና እምነትን በአነርሱ በማፍራት ስመጪሻው ቀን ብቁ አድርጎ እንዲጠበቃቸው የዘወትር ጸሎቱ እንደሆነ ይናገራል። ነገር ግን መንፈስም በአነርሱ ውስጥ የሚሠራው ማለትም የሚቀድሳቸውና የሚለውጣቸው አነርሱ ፈቃደኛ ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው (1፥11-12፤ 2፥13-15)። በመጨረሻም በመንፈስ እንዲቀደሱና እውነትንም በማመን እንዲድኑ እግዚአብሔር ጠርቶአቸዋልና በቃልም ሆነ በመልእክቱ ከርሱ የሰሙትንና የተማሩትን እውነት ጸንቶ በመቆም መያዝ አለባቸው።

«ያን መንፈስም፣ በዚያው ጸድቀን በክርስቶስ ሕይወት ተሰፋ ወራሾች እንድንሆን፣ በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትረፍርፎ አፈሰሰው። ቃሉ የታመነ ነው።»

ቲቶ 3፥7-8

17

መንፈስ ቅዱስ በመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ

አንደኛ ጢሞቴዎስ

ጸውሎስ ወደ መቄዶንያ

በተሻገረ ጊዜ በኤፌሶን ተነስቶ የነበረውን የስህተት ትምህርት እንዲያስቆምና እንዲታወም ጢሞቴዎስን እዛ ትቶት ሄደ (1፥3-4)። በዚህ ክፍል ውስጥ እንደ ምንመለከተው ደግሞ የጢሞቴዎስ የአገልግሎት ጥሪ የተረጋገጠለትና የጸናለት በሽማግሌዎች እጅ መጫን ብቻ ሳይሆን ከመንፈስ ቅዱስ በሆነ ትንቢት ጭምር ነበር (1፥18)። ሐዋርያውም ይህንን ትንቢት እያስታወሰው በመንፈስ ቅዱስ

በመደገፍ መልካም ጦርነትን እንዲዋጋ ያበረታታዋል (4፥14)። ከ «መልካሙ ጦርነት» አንዱ በቤተክርስቲያኑ ተነስቶ የነበረውን የስህተት ትምህርት መቋቋም ነው። በቤተክርስቲያኑ የተነሱት እነዚህም መናፍቃውያን ሕሊናቸውንና በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት በመጣል ከእውነተኛው የወንጌል ትምህርት ለቀው ወጡ (ሰቱ) (1፥19-20)።

4፥1-2

በዚህ ክፍል ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ስለ ሃሰተኛ አስተማሪዎቹ ትንቢት ይናገራል። እንደሚታወቀው ሁሉ ስለዚች ቤተክርስቲያን ትንቢትን ሲናገር ይሄ ሁለተኛው ጊዜ ነው። በሐዋርያት ምዕራፍ ሀያ ላይ እንደምናየው የኤፌሶንን ቤተክርስቲያን መሪዎች አስጠርቶ «ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይሰቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሱ እኔ አውቃለሁ።» በማለት ትንቢት ነግሮአቸው ነበር (ሐዋ 20፥29-30)።

በዚህ ክፍል ደግሞ እነዚህ አስተማሪዎች በአጋንንት መንፈስ በመመራት ሃሰተኛ ትንቢትና ትምህርት እንደሚያስተምሩ ይተነብያል። እነዚህ መናፍቃውያን በእግዚአብሔር የተገለጠውንና በእምነት የሚያድነውን የክርስቶስ ኢየሱስን ጸጋ በማንቋሸሽ በሥራ መጽደቅን ያስተምራሉ፥ በሚያስቱ መናፍስትም መልእክትን ይናገራሉ። የስህተት ትምህርቱም ይዘት ውሸት የሞላበት፥ ሃይማኖትን የካደ፥ መጋባትን የሚከለክልና ሰዎች ከመብል እንዲርቁ በማዘዝ ራሳቸውን እንዲጎዱ የሚያደርግ ነው። ስለዚህም የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ ዚህ ያለውን ከሚያስቱ መናፍስት የሚመጣን መልእክትና ትምህርት በመፈተንና በመለየት ማጋለጥ ይኖርበታል (1ቆሮ 12፥10፤ 14፥29-32)።

ሁለተኛ ጢሞቴዎስ

4፥14 ፤ 2ጢሞ 2፥1-7

ከላይ እንደተመለከትነው ጢሞቴዎስ ወደ አገልግሎት ሲገባ ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር አብሮ የጸጋ ስጦታዎች ተሰጥቶት ነበር። ስለዚህም

ጕዳይ አስመልክቶ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲነግረው — «እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው እጅቼን በመጫኔ በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሳሳ አሳ ስብሃለሁ» (2ጢሞ 1፥6) በማለት ወጣቱን ወንጌላዊ ያበረታታዋል። ጢሞቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ኃይል የታጠቀ ቢሆን የሃሰተኛ አስተማሪዎችን ትምህርት ለማስቆም የተጠራ ወጣት አገልጋይ ነበር።

ከዚህ ክፍል እንደምንመለከተው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደሚዳፈ ነው ሁሉ ይቀጣጠልማል (1፥6፤1ተሰሎ 5፥19)። የሚዳፈነውም ስጦታዎቹን በመ ናቅና ችል በማለት ሲሆን፤ የሚቀጣጠለው ደግሞ ስጦታዎቹን አዘውትሮ በመያዝ የተሰጠውን የወንጌል ባላደራነት በመወጣት ነው። በተለይ ደግሞ ጢሞቴዎስ ተቃዋሚዎቹን ሳይፈራ በተሰጠው የጸጋ ስጦታ ኃይል የእውነትን ቃል ማስተማ ርና ሃሰተኞቹን መገሰጽ ነበረበት። ከዚህ የምንማረው ነገር — 1ኛ. እግዚአብ ሔር የኃይልና ራስን የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስን አንዳልሰጠን፤ 2ኛ. እውነትን በመያዝ ሐሰተኛ አስተማሪዎችንና ትምህርታቸውን ማጋለጥ እን ዳለብን፤ 3ኛ. አስፈላጊም ከሆነ እስከ ሞት ድረስ ታምነን መልካሙን ገድል መጋደል ነው።

1፥14

ሐዋርያው ለጢሞቴዎስ በክርስቶስ ባለ እምነትና ፍቅር ለማካኸት መልካሙን አደራ በእኛ ውስጥ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠብቅ ይመክ ረዋል። ይህም «መልካም አደራ» የክርስቶስ ወንጌል ነው (ቁ 11-12)። መል ካሙንም አደራ ሊየሱስ ክርስቶስ ለጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ እስከ መጨረሻው እንደሚጠብቅለት ሁሉ፥ ለጢሞቴዎስም እንዲሁ ያደርግለታል። መንፈስ ቅዱስም አገልጋዮቹን ኃይል እያስታጠቀ፥ እየለወጠና እየመራ አገልግሎታቸውን በታማኝነት እንዲወጡት ያደርጋል። ከዚህ በፊት እንዳየነው ሊየሱስ ክርስቶስ ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት ደቀመዛሙርቱ ኃይልን ሳይቀበሉ ከኢየሩሳሌም እንዳ ይወጡ ነግሮአቸው ነበር። ምክንያቱም ወንጌልን በሰው ኃይልና ጥበብ መሰበክ ስለማይቻል ነው (ሉቃ 24፥49፤ ሐዋ 1፥4)። በርግጥም ከለ መንፈስ ቅዱስ ኃይ ል፥ ድጋፍና ጥበቃ ማንም አገልጋይ ቢሆን መልካም ገድልን ተጋድያለሁ ሩጫው ንም ጨርሻለሁ ለማለት ፈጽሞ አይችልም።

በዚህ ክፍል ደግሞ በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንደሚ መጣ ይናገራል። ሰዎች ፈሪሐ እግዚአብሔር ስለ ሌላቸው በአመጸኝነት በእግ ዚአብሔር ቤት ውስጥ ይመላለሳሉ። በእውቀትና በእምነት ደካማ የሆኑትን ሰዎች እየፈለጉ አመጸኝነታቸውን ያስፋፋሉ። እነዚህ ሐሰተኞች ከውጪ ሲያ ዩአቸው የአምልኮ መልክ ያላቸው ይመስላሉ። የፈርዖን አስማተኞችና ጠን ቋዮች የነበሩት ኢያኔስና ኢያንበሬስ በፈርዖን ፊት አስማት በማድረግ ሙሴን እንደተቃወሙት ሁሉ፥ እነዚህም ሃሰተኞች እውነትንና የእውነትን አገልጋዮች ይቃወማሉ (ዘጸ 7፥11-12, 22፤ 8፥7)።[103]

በዚህ ክፍል እንደምናየው እግዚአብሔርን መምሰል ሦስት ነገሮችን ይጠይቃል — 1ኛ. እውነትን መረዳት 2ኛ. እግዚአብሔርን ማወቅና ማመን 3ኛ. እንደ እርሱ ፈቃድ መመላለስ (የቅድስና ሕይወት) ነው። እነዚህ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ግን ቤተክርስቲያን ይሄዳሉ ነገር ግን በዚህ ዓለም ተድላ የተታለ ሉና የተተበተቡ ስለሆኑ እንደቃሉ (በትእዛዙ) አይኖሩም። በትእዛዙም ስለማ ይሄዱ እግዚአብሔርን አያውቁትም። ስለማያውቁትም በርሱ ላይ የተመረኮዘ እምነት የላቸውም። እምነትም ስለሌላቸው ሊለውጥ፥ ሊቀድስና እውነትን ሊገልጥ ለሚችለው ለመንፈስ ቅዱስ ራሳቸውን አልሰጡም።

ስለዚህም ምንም እንኳን የአምልኮ መልክ ቢኖራቸውም (ቤተክርስቲ ያን ይሄዱ እንጂ) ሊለውጥ የሚችለውን የእግዚአብሔርን ኃይል የካዱ ናቸው። ኃይሉንም ስለካዱ በአመጸኝነት ሥራቸው በመቀጠል የእግዚአብሔርን እውነትና አገልጋዮች ይቃወማሉ። በመጨረሻም በኃጢአትና በአመጸኝነት ሥራ በእግዚአ ብሔር ቤት የሚመላለስ ሁሉ ሊቀድስና ሊለውጥ የሚቻለውን መንፈስ ቅዱስን የሚቃወም ስለሆነ የእግዚአብሔርን ኃይል የካደ ነው።

103

የኢያኔስና የኢያንበሬስ ስም በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ አልተጠቀሰም። ነገር ግን በአይሁዳው ያኑ ሥነጽሑፍ [ታርገም] ውስጥ የፈርዖን አስማተኞችና ጠንቋዮች መሆናቸው ተጠቅሶአል። አንዲ ሁም ደግሞ ፐሲኒና ኢፖሲየስ የተባሉት የአሕዛብ የጥንት ጸሐፍት ይህኑ ጠቅሰውታል። ኦሪገን የተባለውም የክርስቲያን ጸሐፊ እንዲሁ ስማቸውን ጠቅሶአል። ዎልተር ሎከ፥ ኢ ክሪቲካል ኢን

3፥16

የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ወይም መንፈስ ያለበት መጽሐፍ በጣም ጠቃሚ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣም ዳሩ ግን ቅዱሳን ሰዎች በእግዚአብሔር ተልከው በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት ተናገሩት (2ጴጥ 1፥21)። የእግዚአብሔርም እስትንፋስ ስለሆነ ዘላለማዊ ነው፥ ሕያው ነው፥ እውነት ነው [Absolute Truth]፥ አይለወጥም፥ አያረጅም፥ ስህተትም የለበትም። ሲናገረንም በኃይልና በሥልጣን ስለሚናገር ለትምህርት፥ ለተግሳጽ፥ ልብንም ለማቅናትና በጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማል።

ወደ ቲቶ

3፥5-8

በዚህ ክፍል ደግሞ ጳውሎስ ለቲቶ በጻፈው መልእክቱ ላይ አማኞች ለበጎ ሥራ የተዘጋጀንና በቅድስና ሕይወት የምንመላለስ መሆን እንደሚገባን ይናገራል። ቀድሞ ኃጢአተኞች በነበርን ጊዜ በአመፀኝነት እንደምንመላለሰው ዓይነት ኑሮ ልንኖር እንደማይገባን ይመክረናል (3፥1-3)። ድሮ የማናስተውል፥ የማንታዘዝ፥ የምንስት፥ ለልዩ ልዩ ተድላ የምንገዛ፥ በክፋትና በምቀኝነት የምንኖር፥ የምንጣላና እርስ በርሳችን የምንጠላላ ነበርን። አሁን ግን እግዚአብሔር በአዲስ ልደት በሚሆን መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ስለ አዳነን የምንኖረው ኑሮ የቅድስና ኑሮ መሆን ይገባዋል (ቈ 4-6፤ ኤፌ 5፥26)። እግዚአብሔር በምሕረቱ ቸር ስለሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ኃጢአታችንን አጥቦ ለአዲስ ልደት በማብቃት አደሰን [Regeneration and Renewal]።

ይህ መታጠብና መታደስ የተከናወነው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው። በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን እግዚአብሔር በመድኃኒታችን በኢየሱስ በኩል በእኛ ላይ መንፈሱን አትረፍርፎ አፈሰሰው (ቈ 6-7)። በትንቢተ ሕዝቅኤል ላይ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚያጥብ፥ እንደሚያጠራ ከዚያም አዲስን ልብ እንደሚሰጥ ይናገራል (36፥25-27)። ይህን ትንቢት በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተፈጽሞአል። በቆሮንቶስም መልእክት ላይ በጌታ ኢየሱስ ስም በአምላካችን መንፈስ እንደ ታጥብን፥ እንደ ተቀደስንና እንደ ጸደቅን ይናገራል (1ቆሮ 6፥11)።

በተጨማሪም በዚህ ክፍል ውስጥ ሥላሴ (ምስቱም አካላት) በማዳን ተግባር ውስጥ የተሳተፈውን መለኮታዊ ሚና እንመለከታለን — ኢየሱስ የሰውን ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኖ በመምጣት በሞቱ አዳነን፤ ይህም የአብ ፍቅርና ቸርነት ስለሆነ መንፈስ ቅዱስን በኢየሱስ በኩል አትረፍርፎ አፈሰሰው፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ይህንን ፍቅር በሕይወታችን እውን አደረገልን (ሐዋ 2፥33፤ ዮሐ 1፥16፤ 3፥34፤ 14፥20፤ ኢዩ 2፥28)።

ድ ኢክሰጀቲክል ኮሜንተሪ ኦን ዘ ፓስቶራል ኢፒስትልስ (ኒውዮርክ፥ ሃርፐር ስብራይዝርስ ሳንስ፥ 1924) 107።

«ይህ በጌታ በመጀመሪያ የተነገረ ነበርና፥ የሰሙትም ለእኛ አጸኑት፥ እግዚአብሔርም እንደ ፈቃዱ በምልክትና በድንቅ ነገር በልዩ ልዩ ተአምራትም መንፈስ ቅዱስንም በማከፋፈል አብሮ መሰከረለት።»

ዕብራውያን 2፤3-4

18

መንፈስ ቅዱስና የዕብራውያን ሰዎች

የዕብራውያን ጸሐፊ ከሰማነው፥

የእግዚአብሔር ልጅ ይዞት ከመጣው የወንጌል እውነት ፈቀቅ እንዳንል ያሳሰበ ናል። ይህንንም ወንጌልን ከሙሴ ሕግ ጋር በማነጻጸር በመላእክት የተነገረው ቃል[104] ቅጣትን ከመጣ «እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው እን

104

«በመላእክት የተነገረው ቃል» የሚለው አባባል በሲና ተራራ እግዚአብሔር ለሙሴ ሕግን ሲሰጠው መላእክትም ተሸኘው ነበር ብለው አይሁዳውያኑ ያምናሉ። ሙሴ ራሱ በዘዳግም ምዕራፍ ሰላሳ

ዴት እናመልጣለን?» በማለት የወንጌሉን ታላቅነት ያሳየናል። ይህም ወንጌል በመጀመሪያ በጌታ በራሱ የተነገረ ሲሆን ከዚያም የሰሙት ማለትም ሐዋርያት እንደመሰከሩት ይገልጻል (2፤1-4)። ወደ ላይ ከፍ ብለን በምዕራፍ አንድ ላይ ስንመለከት የእግዚአብሔር ልጅ ከመላእክት ሁሉ በላይ መሆኑን ይገልጻል። ከዚያም በመቀጠል ልጁ ከመላእክት በላይ ከሆነ በመላእክት መከከለኛነት በሲና ከተሰጠው ሕግ ይልቅ በልጁ የተሰጠው ወንጌል እጅግ የላቀ እንደሆነ ይመሰክራል (ዘዳ 33፤2)።

እግዚአብሔርም ይህንን ታላቅ ደህንነት የያዘውንና በልጁ የመጣውን ወንጌል መንፈስ ቅዱስን በማደልና ድንቅና ተአምራት በመሥራት መሰከረ። ግለትም መንፈስ ቅዱስ አብሮ ከወንጌል ጋር ሰለ ተሰጠ አገልጋዮቹ ድንቅና ተአምራት በማድረግ ታሉን አጸኑት። ስለሆነም ልጁ ይዞ የመጣውን፥ በመንፈስ ቅዱስ የታደለውንና የመጨረሻው የእግዚአብሔር መገለጥ የሆነውን ይህንን ታላቅ ደህንነት የጣለ ሰው የዘላለም ሕይወትን የጣለ በመሆኑ እጅግ ታላቅ የሆነ ቅጣት ይጠብቀዋል።

3፤7-11

የዕብራውያን ጸሐፊ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ኢየሱስንና ሙሴን ያነጻጽራ ቸዋል — ሙሴ በእግዚአብሔር ቤት ሁሉ እንደ ሎሌ የታመነ ነበር፥ ኢየሱስ ግን እንደ ልጅ በቤቱ የታመነ ነው። ስለዚህም ኢየሱስ የበላይ ነው ማለት ነው። የበላይም ከሆነ ደግሞ ከሙሴም ሕግ የበላይ ነው (ቁ 1-6)። ስለዚህም በክርስቶስ ያገኘነውን፥ የምንደፍርበትና የምንመካበትን የደህንነት ተስፋ አጽንተን ብንጠብቅ ቤቱ ነን በማለት በእምነታችን ጸንተን እንድንቆም ያበረታታናል።

ሦስት ቁጥር ሁለት ላይ «እግዚአብሔር ከሲና መጣ፥ በሴይርም ተገለጠ፤ ከፋራን ተራራ አበራላቸው፥ ከአእላፋትም ቅዱሳኑ መጣ፤ በስተ ቀኙም የእሳት ሕግ ነበረላቸው።» በማለት ሕጉ ሲሰጥ መላ እክትም አብረው እንደ ነበሩ ጽፏልል። ጳውሎስም በገላትያ 3፤19 ላይ ይህኑ ሃሳብ ጠቅሶታል። እስጢፋኖስም በሐዋርያት ሥራ ላይ «በመላእክት ሥርዓት ሕግን ተቀብላችሁ አልጠበቃችሁትም» በማለት የእስራኤልን መሪዎች ይወቅሳቸዋል (ሐዋ 7፤53)። በሁለቱ ኪዳናት መካከል የተጻፉትም የቀኖና መጻሕፍት እንዲሁ የመላእክትን መገኘት ጽፈዋል። እንግዲህ ማወቅ የሚገባን ነገር ቢኖር ሕጉን የሰጠው እግዚአብሔር ሲሆን ሕጉም ሲሰጥ መላእክት እግዚአብሔርን በማጀብ አብረውት ነበሩ እንጂ በሕጉና በእግዚአብሔር መካከል ያግዳሉ ማለት አይደለም።
ብሩስ፥ *ዘ ኤፒስትል ቶ ዘ ሂብሩስ* (ግራንድ ራፒድስ፥ ውልያም ኤርድመንስ፤ 1990) 66-67።

በመቀጠልም በምድረበዳ ይኳዙ የነበሩት ይከተላቸው የነበረውን መንፈስ ቅዱስ በአመፃቸው ምክንያት በማስመረራቸው እርሱም ተመልሶ ጠላት ሆና ቸው። በዚህም ምክንያት ወደ ተዘጋጀላቸው ዕረፍት ማስትም የከነዓን ምድር አልገቡም። ዛሬም እንዲሁ የኢየሱስን ድምጽ ከቃሉ የሰማንና ደህንነታችንን የተቀበልን ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረንን ማስጠንቀቂያ ስምተን ለርሱ በመገ ዛትና ለቃሉ ታዛዥ በመሆን ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት ስመግባት መትጋት አለ ብን። ወይም በሌላ አነጋገር ከርሱ የሰማነውንና በመንፈስ ቅዱሱ የተመስከረለ ትን እውነት እስከ መጨረሻው ድረስ አጥብቀን መያዝ ይገባናል (ዘጸ 17፡7፤ ዘኁ 20፡2-13፤ 14፡22-23፤ መዝ 94፡8-11፤ ዘዳ 8፡2)።

እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባን ነገር ቢኖር አሁን ወደ እግዚአብሔር ዕረ ፍት ገና አልገባንም ማለት አይደለም። ኢየሱስን አዳኙ አድርጎ የተቀበለ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት ገብቶአል (4፡8-10)። ቢሆንም ቅሉ ይህን አሁን የቀመስነውን የእግዚአብሔር ዕረፍት ሙሉ ለሙሉ የምናገኘውና የምንደሰትበት ጌታ ዳግም ሲመጣ ወይም ደግሞ እኛ ወደ ለርሱ ስንሄድ ነው (ከዓለም፣ ከሥጋ ና ከሰይጣን ፈተና ነጻ ሆነን)። ስለዚህም ደህንነታችን እግዚአብሔር ያዘጋ ጀልን ዕረፍት በመሆኑ እርሱ በሰባተኛው ቀን እንዳረፈ እንዲሁ እኛም በልጁ በኩል ባገኘነው ዕረፍት ዘና ብለን በነፃነት እንኖራለን።

10፡15-31

ኢየሱስ ሊቀ ካህናችንና መሥዋዕት በመሆን ራሱን በዘላለም መንፈስ ስለባቱ መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ (9፡14)። ስለ ኃጢአታችንም ሲል ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ከቀደሰን በኋላ በለባቱ ቀኝ በመቀመጥ የዘላለም ፍጹማን አድርጎናል (10፡12-14)። ይህንን የእግዚአብሔርን የማዳን እቅድ በተ መለከተ መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በኤርምያስ ውስጥ በመሆን ለስቀድሞ መስክሮ ታል (10፡15-16፤ ኤር 31፡31-34)። በመሆኑም ኢየሱስ በሞቱ ምክንያት በመረ ቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ አብ በድፍረት እንገባለን። ስለዚህም ይህንን ታላቅ ተስፋ እስከ መጨረሻው ድረስ አጥብቀን መያዝ ይኖርብናል።

የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ቢመስክሩበት ያለ ርሕራሄ እንደሚሞተው ሁሉ፣ የመጨረሻውን የእግዚአብሔር መገለጥ ይዞ የመ

ጣውን የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ፣ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረና የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ በፍርድ ቀን የሚበስ ቅጣት እንደሚቀበል ያስጠነቅቃል (ቁ 26-31)። ይህ ዓይነቱ አባባል በማቴዎስ ምዕራፍ አሥራ ሁለት ላይ የተመለከትነውን መንፈስ ቅዱስን መሳደብን ይመስ ላል። ሁለቱን እንድ የሚያደርጋቸው ኢየሱስ ይዞት የመጣውን የደህንነት ወንጌል አለመቀበል ነው (በማቴዎስ ምዕራፍ አሥራ ሁለት ላይ የተመለከትነው መንፈስ ቅዱስን በመቃወም ሲሆን፣ በዚህ ክፍል ደግሞ ወደ ሕግ ሥራ በመዘር ነው)።

«እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፥ ሁሉንም ታውቃላችሁ።»
1ዮሐንስ 2፥20

19

መንፈስ ቅዱስ በጴጥሮስና በዮሐንስ መልእክቶች ውስጥ

የጴጥሮስ መልእክት (1)

ሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክቱን የጻፈው «እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ፥ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡት» በተለያየ ቦታ ለተበተኑት መጻተኞች መሆኑን በመልእክቱ መግቢያ ላይ ተናግሮአል (ቁ1-2)። በመቀጠልም ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለማያልፍ ርስት ዳግም ተወለድን፥ ይህም ርስት በመጨረሻው ቀን ይገለጣል ካለ በኋላ እስከዚያ ድረስ ግን የእግዚአብሔር ኃይል እንደሚጠብቀን ይነግረናል (ቁ 3-5)። ይህም የሚያሳየን ምንድነው ቢባል — መንፈስ ቅዱስ እስራኤላውያንን ከግብጽ አውጥቶና በምድረበዳ ተከትሎ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዳገባቸው ሁሉ፥ እኛንም እንዲሁ በመቀደስና በመከተል የተስፋይቱ ምድር ወደ ሆነችው ወደ አዲሲቱዋ ኢየሩሳሌም በማድረስ የተዘጋጀልንን ርስት እንድንወርስ ያደርጋል።

1፥10-12

ለእኛ በመሢሑ በኩል ስለ ሚሰጠን ደህንነትና ጸጋ ትንቢት የተናገሩት የብሉይ ኪዳን ነቢያት ነገሩ መቼ እንደሚፈጸም ተግተው ቢመረምሩም እንኳን እርግጠኛ ጊዜውንና ሰዓቱን ራሳቸው አላወቁትም ነበር። መላእክቱም ራሳቸው መቼ እንደሚፈጸም ስለማያውቁ ጊዜውን ለማየት በጉጉት ይጠባበቁ ነበር በማለት እኛ የተለየን ትውልድ እንደሆንን ጸሐፊው ይናገራል። በእነርሱም የነበረው የክርስቶስ መንፈስ ስለ መምጣቱ፥ መከራ ስለ መቀበሉናና ስለ መከበሩ ነግሮአቸው ስለ ነበር ጊዜውን በመመርመር ለማወቅ ይተጉ ነበር።

ነገር ግን «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ»፥ በራሱ ሰዓት ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ በመምጣት በመሞቱና ትንሣኤው ድል ነስቶ ደህንነትንና የጸጋ ስጦታን ሰጠን። ከርሱ ጋር አብረን ብንሆን ደግሞ ወደ ፊትም ከርሱ ጋር አብረን እንክብራለን (ኤፌ 4፥7-13)። ይህ የደህንነት ወንጌልም የተሰበከልን ከሰማይ ቤተ ላክ በመንፈስ ቅዱስ ስለነበረ እግዚአብሔር በድንቅና በተአምራት ቃሉን ያጸና ነበር (ዕብ 2፥4)።

4፥12-14

ክርስቶስን በመቀበላችን ምክንያት እንደ እሳት ሊፈትነን የሚመጣውን መከራ በማየት ያልታሰበ መከራ እንደገጠመን አድርጎ በመውሰድ መደነቅ እንደ ሌለብን ይመክረናል። ፈተና የክርስትና ሕይወት አንዱ ጉዞ እንደመሆኑ መጠን ተዘጋጅተን መኖር ሲገባን ፈተናም ሲደርስብን በደስታ መቀበል አለብን። ምክንያቱም ስለ ስሙ መከራን ስንቀበል የክርስቶስን መከራ እየተካፈልን በመሆኑ ነው። የክርስቶስንም መከራ ስለምንካፈል የክብር መንፈስ በእኛ ላይ ስለ

ሚያርፍ ታጋሾችና ደስተኞች እንሆናለን። ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስ የመን ፈስ ፍሬ የሆኑትን ደስታንና ትዕግስትን እንድናፈራ ስለሚያደርገን ወደ ፊት የሚ ገለጠውን የክርስቶስ ክብር እያሰብን አሁን የሚደርስብንን መከራና ችግር እንድ ንቋቋመውና በደስታ እንድንቀበለው ያደርገናል።

የጴጥሮስ መልእክት (2)

የእግዚአብሔር ቃል በሰው ፈቃድ የተጻፈ ሳይሆን ቅዱሳን ሰዎች በእግ ዚአብሔር ተልከው በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩት። ስለዚህም እግዚአ ብሔር ከሰጠው ትርጉም ሌላ ማንም ሰው ለገዛ ራሱ እንደሚመች አድርጎ ሊተ ረጉም አልተፈቀደለትም። እንደውም ሰው በጨለማ በፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ሁሉ፥ ቃሉን በመጠንቀቅ ልንይዝና ልንተረጉም ይገባናል። ምክንያቱም በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ ስለሆነ ከማንኛውም ትንቢት ይልቅ እጅግ የጸና ነውና (1፥18-21)።

አንደኛው የዮሐንስ መልእክት

2፥18-27

ብዙዎች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች መነሳታቸው አሁን ያለንበት ጊዜ የመ ጨረሻው ሰዓት እንደሆነ ይጠቁመናል በማለት ሐዋርያው ይነግረናል። በመቀጠ ልም እነዚህ ሐሰተኞች በኢፌሶን ቤተክርስቲያን ውስጥ ኢየሱስን ክርስቶስ አይ ደለም በማለት የከሀዲት ትምህርታቸውን እንደተያያዙትም ይነግረናል። ይህም ትምህርተ ኦፋቄ «*አውቆታዊነት*» [Gnosticism] በመባል ይታወቃል።[105] ዮሐንስ

105

ናስቲሲዝም የሚለው ቃል የመጣው ግኖሲስ ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም እውቀት ማለ ት ነው። የዚህ ትምህርተ ኦፋቄ ዋና ሃሳብ እውቀት እንጂ እምነት አይደለም የሚያድነው የሚለው ነው። ስለዚህም የዚህ ሰሀተት ትምህርት ተከታዮች «እውቀትን» ከምንም ነገር በላይ አድርገው ስለሚመለከቱ «*አውቆታውያን*» ወይም *ናስቲስት* በመባል ይታወቃሉ። በተጨማሪም ደግሞ የኢየሱ ስን በሥጋ መገለጥና መሞት አይቀበሉም። የዚህ ትምህርት ዋና መሪ የሆነው የወጣው ከኢፌሶን ቤተክርስቲያን ውስጥ ሲሆን ስሙም ሴሪንቲየስ ይባላል።

መልእክቱን የጻፈው በኢፌሶን[106] ላሉት አማኞች ነው። በኢፌሶን ስለሚነሳው ትምህርተ ኦፋቄውም ጸውሎስ ትንቢትን ተናግሮ እንደነበር ተመልክተናል (ሐዋ 20፥29-30)። ስጠሞቴዎስም በጻፈው መልእክቱ ላይ እንዲሁ ይህንኑ ጉዳይ በማስመልከት አስጠንቅቆት ነበር (2ጢሞ 3፥1፤ 4፥3-4)። ዮሐንስም ስለ ትም ህርተ ኦፋቄውና አስተማሪዎቹ ሲናገር «ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለው ም፤ በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው» ብሎአል (1ዮሐ 2፥23)።

የኢፌሶን አማኞች ግን የተቀበሉት ቅዱስ ቅባት እውነትን ከውሸት በመለየት ያስተምራቸዋል። ቅባት የሚለውን ቃል በግሪኩ *ክሪዝማ* ሲለው ይህ ም በመንፈስ ቅዱስ መቀባታችንን ያሳያል። በብሉይ ኪዳን ዘመን ነገሥታት፥ ቀሳውስትና ነቢያት ለአገልግሎት ሲመረጡ ወይም ሲወጡ በዘይት ይቀባሉ (ሌዋ 8፥30፤ 1ሳሙ 10፥1፤ 16፥13፤ 1ነገ 1፥39፤ 19፥16፤ 2ነገ 9፥3፤ 11፥12፤ 23 ፥30)። በትንቢተ ኢሳይያስም ላይ መሢሑ በእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚ ቀባ ይነግረናል። ኢየሱስም ሲናገር ኢሳይያስ በመንፈስ ተመርቶ የተነበየው፥ የሚመጣው የተቀባው (መሢሕ) እርሱ ራሱ እንደሆነ መስክሮአል (ኢሳ 61፥1፤ ሉቃ 4፥17-19)። ጸውሎስም በቆሮንቶስ መልእክቱ ላይ «በክርስቶስ ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው» (2ቆሮ 1፥21) በማለት እርሱና የቆ ሮንቶስ አማኞች አብረው በመንፈስ እንደተቀቡ ገልጸዋል።

እንግዲህ ከላይ እንደተመለከትነው «ቅባቱ» በአዲስ ኪዳን ዘመን ለም ንኖር ለሁላችንም ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ባፈጸመው ሥራ የተሰጠን ስጦታ ነው። እግዚአብሔርም ቅባቱን በውስጣችን በማድረግ የርሱን በጎነት እንድንነግር የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናትና ለርስቱ የተለየ ቅዱስ ሕዝብ አደረገን። በመንፈስ ቅዱስ መቀባታችንም ስለ እግዚአብሔር ማወቅ የሚገባንን እውነት ያስተምረናል። ይህም ማለት ደግሞ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ፥ ስለ እግዚአብሔር ማንነት ሲያስተምረን ለአገልግሎትም ኃይልን ያስታጥቀ ናል። ኢየሱስም በዮሐንስ ወንጌል ላይ ሲናገር የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ

106

ከርሰን፣ ሙ፣ ሞሪስ፣ *ለን ኢንትሮዳክሽን ቱ ዘ ኔው ቴስተመንት* (ግራነድ ራፒድስ፣ ዞንደርቫን አሳ ታሚ ድርጅት፣ 1992) 450። የዘወዲያስ ልጅ የሆነው ዮሐንስ በእይወድ ጦርነት ጊዜ ወደ ኢፌሶን ስመኖር መጥቶ ነበር (66-70)። ዮሐንስም እዛ ስመቆየቱ የኢፌሶን ቤኖ የነበረው ፖሊክራትና አይ ሬኒየስ መስክረዋል። ስለዚህም የተጻፈው ለኢፌሶን ነው ማለት ነው።

ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራን፥ የሚሰማውን ሁሉ እንደሚናገር፥ እርሱን እን ደሚያከብረውና ከርሱ ወስዶ እንደሚነግረን የሰጠን ተስፋ ይህ ነው (ዮሐ 14፥ 16-17፤ 15፥26-27፤ 16፥13-15፤ ሐዋ 1፥4-8)።

3፥23-4፥6

በዚህ ክፍል ደግሞ በኢየሱስ የምናምን ሁሉ እርስ በርሳችን መዋደድ እንደሚገባን በማሳሰብ ይህንን ትእዛዝ የሚጠብቅ በክርስቶስ ይኖራል ክርስቶስም በርሱ ይኖራል ብሎአል። በክርስቶስ ውስጥ መኖራችንን በእኛ ውስጥ በሚኖ ረው በመንፈስ ቅዱስ እናውቃለን። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስም የፍቅርን ፍሬ እንድናፈራ በማድረግ በእግዚአብሔር ትእዛዝ እንድንኖር ያደርገናል። ትእዛዙ ንም ስንጠብቅ ደግሞ ያን ጊዜ በክርስቶስ ውስጥ መኖራችንን እናውቃለን ማለት ነው (3፥23-24)።

ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ስለ ወጡ መንፈስን ሁሉ መመ ርመር እንጂ ማመን እንደሌለብንም ያስጠነቅቀናል። ዮሐንስ ከእግዚአብሔር የሆነና ያልሆነ መንፈስን ለመለየት የሚጠቅሙ መመዘኛዎችን አውጥቶአል። የስህተትን አመራር የምንለየውም በውስጣችን ባለው በቅባቱ ነው። —

ሀ/ ከእግዚአብሔር የሆነው

* ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የሚያምን
* ኢየሱስ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ/መሢሕ ነው ብሎ የሚያም ን (2፥22)
* ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚያምን (5፥5)
* ከእግዚአብሔር የሆነውን የሚናገር (4፥5-6)

ለ/ ከእግዚአብሔር ያልሆነው (የስህተት አመራር)

* ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ አያምንም
* ኢየሱስ ክርስቶስ/መሢሕ ነው ብሎ አያምንም
* ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አይቀበልም
* አብና ወልድን ይክዳል
* ከዓለም የሆነውን ይናገራል ዓለሙም ይሰማዋል

በመጨረሻም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በሚታመን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል ከለ በኋላ በእኛ ውስጥ መኖሩንም የምናውቀው በመንፈስ ቅዱሱ ሲሆን ይህም መንፈስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነም ይመሰክራል በማለት ገልጸታል (4፥13-14፤ 5፥6-7)።

የዮሐንስ ራእይ

ሐዋርያው ዮሐንስ ኢየሱስ ተገልጦለት የትንቢቱን ቃልና ለሰባቱ አብ ያተ ክርቲያናት መልእክት እንዲጽፍ በነገረው ጊዜ በመንፈስ ነበር። የትንቢቱ ቃልና ለሰባቱ አብያተክርስቲያናት የተጻፉትም መልእክቶች በመንፈስ ቅዱስ እን ደተጻፉ ሲገልጽ «መንፈስ ለአብያተክርስቲያናት የሚለውን ያድ ያለው ይስማ» ይላል (2፥7, 11, 17, 29፤ 3፥6, 13, 22)፣ «ከሰማይም ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብሁለን ናቸው። መንፈስ — አዎን፥ ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ ሥራቸውም ይከተላቸዋል ይላል ብለህ ጻፍ የሚል ድምፅ ሰማሁ።» በማለት ይናገራል (14፥13)።

በመጨረሻም ጌታ ኢየሱስ «እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ....» (22፥12) ሲል መንፈሱና ቤተክርስቲያን ደግሞ «ና ይላሉ» (22፥17)። ከላይ እንደተመለ ከትነው መንፈስ ቅዱስ ነቢያቶች ቃሉን እንዲናገሩ መንዳት ብቻ ሳይሆን ከሕዝ ቡ ጋር በመሆን «ጌታ ኢየሱስ ና» ይላል። እንግዲህ በዘፍጥረት ላይ መንፈስ ቅዱስ በዉኃ ላይ ሰፍፎ ነበር፥ አሁን ደግሞ እዚህ «ጌታ ሆይ ና» ይላል። ከዚህ ምንን እንግራለን ቢባል — መጽሐፍ ቅዱሳችን በመንፈስ ቅዱስ ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚደመድም ነው።

«ወደ ላይ በመጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ»

ኤፌሶን 4፡8

20

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና አገልግሎት

(1ቆሮ 12፤ 13፤ 14፤ ሮሜ 12፡1-8፤ ኤፌ 4፡1-16፤
1ጴጥ 4፡7-11፤ 1ተሰ 5፡19-22)

እስካሁን ድረስ ባየናቸው ምዕራፎች ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተጠቀሱትን እንቀጻትና ስንኞች ከሞላ ጎደል ተንጋገረናል። አሁን ደግሞ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና አገልግሎታቸው በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ እንመለከታለን። እንግዲህ በቀጥታ ስለ አገልግሎት ከመነጋገራችን በፊት እነዚህ ስጦታዎች በአሁኑ ዘመን ይሠራሉ ወይ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንሞክራለን። በአሁኑ ዘመን ባለችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ስጦታዎችን

በተመለከተ ሁለት ዓይነት አስተሳሰብ አለ። አንደኛው ክፍል የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ከሞቱ በኋላ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ቆመዋል ሲል፤ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የለም፤ ስጦታዎቹ ቀድሞ እንደሚሠሩት ሁሉ አሁንም ይሠራሉ በማለት ያምናል።[107]

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በአሁኑ ጊዜ አይሰሩም የሚሉት የሚያቀርቡት መሠረታዊ የሆነው ምክንያት ከሞላ ጎደል እንደሚከተለው ነው —

- ኢየሱስ ሥልጣን የሰጠው ለሐዋርያት ብቻ ስለ ነበረ እነርሱ ያደርጉት የነበረውን ድንቅና ተአምራት እኛ ማድረግ አንችልም።
- ድንቅና ተአምራት የተደረገው የሐዋርያትን ሥል ጣን ለማጽናት ነበር።
- አሁን የእግዚአብሔር ቃል ተጠርዞ ስለተዘጋጀልን ሌላ ዓይነት መገለጥም ሆነ ተአምራት አያስፈልገንም። በሐዋርያት ዘመን ግን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ገና ስላልተጠረዙ ለመመሪያና እውነትን ለማጽኚያ ስጦታዎች አስፈላጊ ነበሩ።
- በ 1ቆሮ 13፡8 ላይ «ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል» የሚለውን በመውሰድ በአሁኑ ጊዜ ትንቢት ተሽሮ አል ወይም ቆሞዋል ይላሉ።[108]

በመሠረቱ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች ሐዋርያት ብቻ የተሰጠ ሥል ጣን ነው ብለን ካመንን ዘንድ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ለመስበክ የተሰጠው ሥልጣንና እደራ ለአሥራ አንዱ ደቀመዛሙርት በመሆኑ በአሁኑ ዘመን የምን ኖር ክርስቲያኖች ወንጌል ለመስበክ ሥልጣን የለንም ማለት ነው። ይህ ደግሞ ከኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ ጋር ይቃረናል። እንደ እውነቱ ከሆነ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሐዋርያት ከሞቱም በኋላ በቤተክርስቲያን ውስጥ ይሠሩ እንደ ነበሩ የቤተክርስቲያን ታሪክ ግልጽ አድርጎ ይነገረናል።

---

107 የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በአሁኑ ዘመን አይሰሩም ብለው ከሚያምኑት ዋና ዋናዎቹ ውስጥ ቢንጃሚን ዎርፊልድ፣ ጆን ማክአርተር፣ ሪቸርድ ግሪፊን፣ ቢንጃሚን በፈከሪድ መዙተ ሲሆኑ ብዙ ተከታዮችም አሉአቸው። እነዚህም ሰዎች አልፈው ተርፈው ስጦታዎቹን የሚጠቀሙትን ሰዎችና መሠረተ እምነትን ከስህተት አሰራር እንደሆነ አድርገው ይከሳሉ።

108 ጆን ማክአርተር፣ *ስፐሪትዋ ኢን ታንግስ* (ቺካጎ፣ ሙዲ ፕረስ፣ 1988) 43።

በእንደኛውና በሁለተኛው ክፍለ ዘመን የተጻፈ *ዲይዳኬ* ወይም *የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ትምህርት* በመባል የሚታወቀው መጽሐፍ የቤተክርስቲያን መመሪያ መጽሐፍ ነው። በዚህም መጽሐፍ ውስጥ ስለ ሰጦታዎች አጠቃቀም የወጣውን መመሪያ እናገኛለን። ግለትም ሰጦታው ያላቸው ሰዎች በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ማገልገል እንደሚገባቸው ተጠቅሶአል። እርሱም እንደዚህ ይላል –

«ነቢይ በመንፈስ ፍንደቃ ውስጥ እያለ አትረብሸው። ለመመርመር ብትፈልግ እንኳን አምልኮውን እስኪ ጨርስ ድረስ ጠብቀው። አንድ ነቢይ ደግሞ ወደ አንተ መጥቶ ቢሰብክና መልእክት ቢያቀርብ ነገር ግን የተናገረውን መልእክት እርሱ ራሱ የማይኖርበት ከሆነ ሃሰተኛ ነው። ደግሞም «በመንፈስ ሆኖ» ገንዘብ እንድትሰጠው ቢጠይቅህ ወይም ገንዘብ ስጠኝ ብሎ ቢናገር ያ ነቢይ ሐሰተኛ ነውና አትቀበለው።»[109]

በእንደኛው ክፍለ ዘመን ግለቂያ ላይ ይኖር የነበረው የሮሜው ቢሾፕ ክሊመንትም ለቆሮንቶስ ምዕመናን በጻፈው ደብዳቤ ላይ ደግሞ አማኞች መንፈሳዊ ሰጦታዎችን እንዲጠቀሙ ያበረታታቸዋል። ሰጦታዎቹም ለርስ በርስ መረዳዳትና ወደ አንድነት ለመምጣት አስፈላጊዎች ናቸው ብሎአል።[110] በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ ይኖር የነበረው የአንጾኪያው ቢሾፕ ኢግናጢዎስ [ኢግኔሺየስ] ለቢሾፕ ፖሊካርፕ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ሰጦታ እንዳይጎድለው ከእግዚአብሔር መገለጥን እንዲጠይቅ ይመክረዋል።[111]

በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ግለቂያ ላይ ይኖር የነበረው የሊዮን ቢሾፕ የነበረው አይሬኒየስ ናስቲሲዝም [Gnosticism] የተባለውን የስሀተት ትምህርት ለመቃወም በጻፈው መልእክት ላይ የጸጋ ሰጦታዎች ግለትም የፈውስ፣ አጋንንትን የማውጣት፣ የትንቢትና እውቀትን የመግለጽ ሰጦታዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደሚሠሩ ጠቅሶአል።[112] በአራተኛው ክፍለ ዘመንም ይኖር የነበረውና በሰሜን አፍሪካ በምትገኘው የካርቴጅ ቢሾፕ ጠርጡሊን [ተርቱሊያን] (ሥላሴ

[109]

ሳይረል ሲ ሪችርድሰን፣ *አርሊ ክርስቲያን ፋዘርስ* (ኒውዮርክ፣ ኮሊየር ቡክስ፣ 1970) 176-177።

[110] ሮበርት ኪዶ፣ *ኸሪማትስ ፒፍትስ ኢን ዘ አርሊ ቸርች* (ፒዩዲ፣ ሄንድሪክሰን፣ 1997), 11-12።

[111] ሳይረል ሪችርድሰን፣ 118።

[112] ኪይድ፣ 43-47 (Ireneus as quoted by Eusibus in Ecclesiastical History, 5, 7:6, Krisop Lake, (Loeb Classical Library), 1: 455) ።

የሚለውን ቃል ለቤተክርስቲያን ያበረከተው) የመንፈስ ቅዱስን ኃይልና የጸጋ ሰጦታዎችን እንደሚያከብር ጽፎአል።[113]

በመሠረቱ ሐዋርያቶች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ድንቅና ተአምራትን እያደረጉ ወንጌልን የሰበኩበት ዋና ዓላማ ሥልጣናቸውን ለማጽናት ሳይሆን የምሥራቹን ድምጽ እውነተኛነት ለማጽናትና[114] ወቀሳን በሰዎች ልብ ውስጥ በማምጣት ሰዎች እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ እውነት እንዲደርሱ ነው። ለምሳሌ የገላትያ አማኞች በእነ ጳውሎስ እጅ የተሠራውን ተአምራትና ድንቅ በማየት («ከእምነት ጋር በሆነ መስማት») የክርስቶስን ወንጌል ተቀበሉ (ገላ 3፥5)።

የትንቢት ሰጦታ ተሸሮአል ሊሚለው ደግሞ በ1ቆሮ 12-14 ያለውን ጠቅላላ አሳብ የተመለከትን እንደሆነ ጳውሎስን ያሳሰበው ጉዳይ ሰጦታዎቹን ከለ አግባብ የመጠቀሙ ጉዳይ ነበር። ስለሆነም በጉባኤ መሐል ለሌሎቹም ወገኖች በማሰብ ሰጦታዎቻችንን ልንጠቀም እንደሚገባ ይናገራል። ምንም እንኳን የጸጋ ሰጦታዎችን በብርቱ እንዲፈልጉ ቢያበረታታቸውም ቅሉ ከሁሉ የሚበልጠው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ አፍርቶ መገኘት ወይም በሌላ አነጋገር መንፈሳዊ መሆን [ፐኦማቲኮን] እንደሆነ ይገልጻል። የመንፈስም ፍሬ አፍርቶ መገኘት ሰጦታዎችን [ካሪዝማታ] ውጤታማ ያደርጋቸዋል ብሎአል። ስለዚህም ሐዋርያው «ከሁሉ የሚበልጥ መንገድ አሳያችኋለሁ» በማለት መንፈሳዊ የሚያደርገውን፣ ለዘላለም ጸንቶ የሚቆየውንና ከሁሉ የሚበልጠውን ፍቅርን እንዲከታተሉ ይነገራቸዋል (12፥31-13፥1-13።

ታዲያ ሕጉ ሁሉ የተፈጸመበት፣ የመንፈስ ፍሬ የሆነውን ይህንን ፍቅር ከሰጦታዎች ጋር ሲያነጻጽረው ወይም በሌላ አነጋገር መንፈሳዊነትን [ፐኦማቲኮን][115] እና የጸጋ ሰጦታን [ካሪዝማታ] ሲያነጻጽረው – «ትንቢትም

[113] ኪይድ፣ 68 (Turtulian, Passio S. Perpetuae (Martyrdom of St. Perpetuae), 1, ed. J.A Robinson (Text & Studies 1,2 Cambridge, 1891), 62.

[114]

ጄክ ዲር፣ *ሰርፕራይዝድ ባይ ዘ ፓወር ኦቭ ዘ ስፒሪት* (ግራንድ ራፒድስ፣ ዞንደርቫን አሳታሚ ድርጅት፣ 1993) 104።

[115]

በጸውሎስ አስተሳሰብ መንፈሳዊ መሆን ግለት የመንፈስ ቅዱስ ሕዝብ መሆን ግለት ነው። የመንፈስ ቅዱስ መሆን ደግሞ ለርሱ በመኖርና ከርሱ ፈቃድ ወሰጥ በማደር የመንፈስን ፍሬ ማፍራት መቻል ነው። የበአጠ ግብራያና የተለያዩ አስተያየቶችንና ግብራያዎችን ለማወት የሚፈልግ ሰው

ቢሆን ይሻራል፥ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፥ እውቀትም ቢሆን ይሻራል...» (ቁ 8-9) በግለት ፍቅር ከሁሉም እንደሚበልጥ ይናገራል። ታዲያ ፍቅር በዚህ ምድር ኑሮ ብቻ ሳይሆን በሚመጣውም ዓለም ቢሆን የሚቀጥል ፍሬ መሆኑን ለመግለጽ ነው የተጠቀመበት እንጂ እርሱና ሌሎቹም ሐዋርያት ከሞቱ በኋላ ስጦታዎች ያቆማሉ አላለም። ጳውሎስ ስጦታዎች ይቆማሉ እንዳለ አድርጎ መውሰድ በዚህም ክፍል ሆነ በሌሎቹ የጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ጨርሶ ያልተደገፈ አስተሳሰብ ነው።

የቆሮንቶስ ሰዎች ምንም እንኳን ስጦታዎቹ ቢኖራቸውም ጳውሎስ በም ዕራፍ አሥራ ሁለት መጀመሪያ ላይ «ስለ መንፈሳዊ ነገር ታውቁ ዘንድ እወዳለ ሁ» በማለት ከሁሉም የሚበልጠው ወይም የለንድ አማኝ መንፈሳዊነት የሚለ ካው ባለው የሥጦታ ብዛትና ትልቅነት ሳይሆን በመንፈሳዊነቱ (ማለትም ባፈራው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ) እንደሆነ ሲመክራቸው እንመለከታለን።

ለምሳሌ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስና ለቲቶ በጻፈው መልእክት ላይ የቤተክ ርስቲያን መሪ ሊሆኑ ስለሚገባቸው ሰዎች መመዘኛ የሚሆን ዝርዝር መመሪያዎ ች አውጥቶአል። ልብ ብለን እነዚህን መመሪያዎች የተመለከትን እንደሆነ እን ድም የጸጋ ሥጦታ እንደመመዘኛ ሆኖ አልተጠቀሰም። ነገር ግን የተጠቀሱት ነገሮች ቢኖሩ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ናቸው (1ጢሞ 3፥1-13፤ ቲቶ 2፥1-10)። ግወቅ የሚገባን ነገር ቢኖር የጸጋ ስጦታዎች የተሰጡን እግዚአብሔር ስለሚ ወደን (ኢየሱስ በመሰቀል በሠራው ሥራ) ሲሆን፥ መንፈሳዊ ለመሆን ግን እኛ እግዚአብሔርን መልበን ልንወደው ይገባናል። ይህም ደግሞ የሚሆነው ለሚለ ውጠን ለመንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ሙሉ ለሙሉ በመስጠት በትእዛዙ ለመኖር በንችል ነው (ዮሐ 14፥15፤ 15፥8-11፤ 1ዮሐ 2፥2-6፤ 3፥24፤ 4፥16-21 5፥1-5)።

እንግዲህ ወደ ዋናው ነጥባችን እንምጣና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሐዋርያት ዘመን ብቻ ነበር የሚሠሩት ስሚሉት፥ ቤተክርስቲያን ካለ ስጦታዎቹ መንቀሳቀስና የተሰጣትን የወንጌል ባለ አደራነት ክርስቶስ በሚፈልገው መንገድ ልትወጣው ትችላለች ወይ? ብለን መጠየቅ ይገባናል። እንደሚታወቀው ሁሉ

በዶ/ር ጎርደን ፊ እና በዶ/ር ካርሰን የተጻፉትን መጻሕፍት ማንበብ ይችላል፤ — ፊ፥ ጎርደ ኢም

የመንፈስ ቅዱስ በሙላት ለቤተክርስቲያን መሰጠት አስቀድሞ የነበረ የእግዚአብ ሔር እቅድ ነበር። ይሄንኑ እቅድ ነቢያቶች በተለያየ ጊዜያትና በብዙ ጎዳና ተንብየውት ነበር።

ሙሴ በምድረበዳ ለሁለተኛው ትውልድ ባደረገው ንግግር እግዚአብሔር አምላክ እንደርሱ ያለ ነቢይ እንደሚያስነሳ ተናግሮ ነበር ። ይህ «እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ» እርሱም ከዳዊት ዘር የሆነ ሲመጣ መንግሥቱን እንደሚመሠርት በአይሁዳውያኑ ዘንድ የታወቀና በጉጉት የሚጠበቅ ጉዳይ ነገር ነበር (ዘዳግ 18፥15፤ ኢሳ 9፤ 11፤ ዮሐ 1፥ 45-46፤ 5፥45-47)። ታዲያ ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚመሠረተው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ቅዱሳን መጻሕፍት ይነግሩናል (ኢሳ 35፥5-6፤ 61፥1-4)[116]።

በግቴዎስም ወንጌል ላይ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራትና ድንቅ ማድረግ ለደቀመዛሙርቱ እንደ አርአያነት እንደጠቀማቸው እናነባለን። ሉቃስም በሐዋርያት ሥራ ላይ ቢጽፍ ቤተክርስቲያን ወንጌልን በአራቱም ማዕዘን ለፍጥ ረት ሁሉ ከመስበኳ በፊት አብ በገባው የተሰፋ ቃል ግለትም በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞላች ይነግረናል። ጳውሎስም ደግሞ ቤተክርስቲያንን ከመንፈሳዊ ስጦታዎች ነጥሎ አያያትም። ምክንያቱም ከሰማይ የወረደን ወንጌል ከሰማይ በወረደ መንፈስ ብቻ መስበክ እንደሚቻል መረዳትን ያገኘ ሰው ነበርና ነው። የሁበራውያንም ጸሐፊ እግዚአብሔር ወንጌልን መንፈስ ቅዱስን አብሮ በግደል እንደሰጠ ተናግሮአል። ስለዚህም ቤተክርስቲያን ወንጌልን በመንፈስ ኃይልና ጉልበት ይዛ ሮጠች እንጂ በሰው ጥበብና የቴክኖሎጂ እውቀት አልነበረም።

ፓወርን ፕሬዘንስ 26-32፤ ካርሰን፥ *ቮዊንግ ዘ ስፒሪት* 22-30።
116

አይሁዳውያኑ እግዚአብሔር መንግሥቱን ሲመሠርት ደጉትና ተአምራት ይሠራል ብለው ይጠብቁ ነበር፤ ኢየሱስ ናዝሬት በሚገኘው ምኩራብ ተገቶ ከነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ ውስጥ ስለ መጪው፥ የእግዚአብሔር መንግሥትና መንፈስ ቅዱስ የሚናገረውን ምዕራፍ 61፥1-2 ላይ ያለውን በማንበብ «ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ» አላቸው (ሉቃ 4፥16-21)። በሌላ ጊዜ ደግሞ መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስ የሚመጣው መሢሕ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ፈልጎ ነበር። በዚህም ምክንያት ተከታዮቹን ወደ ኢየሱስ በመላክ «የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላ እንጠብቅ?» ብሎ ጠየቀው ቀው ጊዜ ኢየሱስ የመለሰለት ከኢሳይያስ መጽሐፍ 35፥5-6 ያለውን ነው። ምክንያቱም ይህን ክፍል አይሁዳውያኑ ከመሢሑ መምጣትና የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሪያ ጋር ስለሚያያዙት ነው። በይበልጥ ግብራሪያ ለሚፈልግ ከዚህ የሚከተለውን መጽሐፍ ማንበብ ይችላል — ጆርጅ ኢ. ላድ፥ *ሌ ቲለጂ ኦቭ ዘ ኔው ቴስተመንት* (ግራንድ ራፒድስ፡ ኤርድመን አሳታሚ ድርጅት፤ 1993) 54-64።

በዛሬ ዘመን የምንኖርን ክርስቲያኖች ከጥንት ዘመን ክርስቲያኖች ልዩ የሚያደርገን ምንም ነገር የለም፣ ልክ እነርሱ በመንፈስ ኃይል የሰላምን ወንጌል እንደ ሰበኩት ሁሉ እኛም እንዲሁ በመንፈስ ኃይል ተደግፈን መስበክ አለብን። የቴክኖሎጂና የእውቀት መራቀቅ የእግዚአብሔርን በሙላት መገኘት ሊተካው አይችልም፣ ችሎም አያውቅም። መርሳት የሌለብን ነገር ቢኖር የእግዚአብሔር ሞኝነት ከሰው ጥበብና እውቀት እጅግ ይጠበባልና ነው።

ዶ/ር ክሬግ ኪነር የሊየሱስ በማቴዎስ ወንጌል (10፥5-6) ላይ ተአምራት ማድረግ አንዲት አድርጎ ለደቀመዛሙርት አገልግሎት አርአያ እንደሆናቸው ሲገልጹ[117] —

- ደቀመዛሙርትን ሾሞ (ሥልጣንና ኃይል ሰጥቶ) ለአገልግሎት መላኩ ወደ ፊት ለሚጠቢቃቸው ለታላቁ ተልእኮ ምሳሌ ነው (ማቴ 28፥19)።
- ደቀመዛሙርቱ የሰበኩትም መጥምቁ ዮሐንስ የጀመረውንና ኢየሱስ የቀጠለውን የእግዚአብሔርን መንግሥት መምጣት ነው። ይህም መንግሥት በኃይል መምጣት በአሁኑ ዘመን ለምንኖር ለእኛም ጭምር ነው (ማቴ 3፥2፤ 4፥17፤ 9፥35፤ 10፥7)።
- የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣቱን የሚያበስረው የእግዚአብሔር ኃይል መገለጥ መሆኑን አይሁዳውያኑ ጠንቅቀው ያውቁ ስለነበር ኢየሱስም ሆነ ደቀመዛሙርቱ ይህንን መንግሥት መምጣቱን አውን ያደረጉት ኃይልን በመግለጥ ነበር (ማቴ 9፥35፤ 10፥8)።
- ይህም ድንቅና ተአምራት በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉትን ትንቢቶች መፈጸማቸውን በማሳየት አዲሱ የእግዚአብሔር ዘመን (የመጎብኘት) መምጣቱን ያረጋግጥልናል (ማቴ 11፥4-6፤ ኢሳ 35፥5-6)።
- በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አገልግሎት ሰዶትን ያስከትላል፤ ይህም አገልግሎት ለአንድ ጊዜ ተደርጎ የሚቆም ሳይሆን ኢየሱስ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ የሚቀጥል ክስተት ነው (ማቴ 10፥17-39፤ 23) በማለት ጠቅለል በማድረግ ቀምጠውታል።

[117] ኪነር፣ *ስለ ክርስቶስ ትመሰክሳለህ* ገጽ ሀሀ ሀሀ፣ በፒሬተ ፤87-88።

መንፈስ ቅዱስ በመረደበት በበዓለ ኀምሳ ቀን ጴጥሮስ ለተሰበሰበው ሕዝብ የመንፈስ ቅዱስ ሙላቱ በነቢዩ በኢዩኤል የተነገረው ትንቢት ፍጻሜ እንደ ሆነ ሲናገር —

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ — በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ራእይ ያያሉ፣ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤ ደግሞም በዚያች ወራት በ ወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ። ድን ቆችን በላይ በሰማይ፣ ምልክቶችንም በታች በምድር አሰጣለሁ፤ ደምም እሳት ም የጢስ ጭጋግም ይሆናል። ታላቅ የሆነ የተሰማም የጌታ ቀን ሳይመጣ ፀሐይ ወደ ጨለማ ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣሉ። የጌታን ስም የሚጠራም ሁሉ ይድ ናል። ... የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና»


(ሐዋ 2፥17-21, 39፤ ኢዩ 2፥28-32)

ቀደም ብለን እንደተነጋገርነው ሁሉ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሰጦታ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለአባታችን ለአብርሃም «የምድር ወገኖች ሁሉ በእንተ ይባረካሉ» ብሎ ቃል የገባለት የተስፋ ቃል ሲሆን፥ በነቢያቱም አፍ እንዲሁ የተስፋውን ቃል በተደጋጋሚ በማብሰር በጉጉት እንድንጠባበቅ አድርጎናል። ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ሰጦታዎቹ በእንደኛው ክፍለ ዘመን ለኖሩት ክርስቲያኖች ብቻ የተሰጠ ስጦታ አይደለም። ለዚሁም መረጃ የሚሆነን በሐዋርያት ሥራ ላይ የተጠቀሰውን እንመልከት —

1) መንፈስ በሥጋ ለባሹ ላይ ይፈሳል

- የሚፈሰው በመጨረሻው ዘመን ነው ብሎአል (ይህም የመጨረሻው ዘመን የሚባለውም መንፈስ ከወረደበት ቀን አንስቶ እስከ ጌታ ምጽአት ያለው ጊዜ ነው።)
- የዘር ልዩነት የለበትም (አይሁድ ሆነ አሕዛብ)
- የመደብ ልዩነት የለበትም (ሀብታም ሆነ ደሃ፣ ገዢ ሆነ ተገዢ)
- የጸታ ልዩነት የለበትም (በብሉይ ኪዳን ጊዜ ለክህነት አገልግሎት የሚሾሙት ወንዶች ብቻ ነበሩ፤ አሁን ግን ሁሉም የንጉሥ ካህናት

ዓምሳ ቀን ጀምሮ እስከ ጌታ ዳግም ምጽአት ድረስ ያለው ጊዜ የመጨረሻው ዘመን በመባል ይታወቃል። ይህም የመጨረሻው ዘመን ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ስጦታ የምትሰራበት ጊዜ ነው።



ስእላዊ መግለጫ ቁ. 6

ስጦታዎቹ እነማን ናቸው

1ቆሮ 12፥8-11

እውቀትን መናገር፥ ጥበብን መናገር፥ እምነት፥ የመፈወስ ስጦታ፥ ተአምራት ማድረግ፥ ትንቢት፥ መናፍስትን መለየት፣ በተለየ ልሳን መልእክት ማምጣትና የልሳን ትርጉም።

1ቆሮ 12፥28

ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ አስተማሪዎች፥ ተአምራት አድራጊዎች፥ አርዳታ ሰጪዎች (የሚረዱ)፥ መንፈሳዊ መሪ [Guidance] የተለየ ልሳን (በጉባኤ መሐል መልክት የሚያመጣ)።

ሮሜ 12፥6-8

ትንቢት፥ አገልግሎት፥ ማስተማር፥ ምክር [Exhortation]፥ ልግስና፥ መሪነት [Leadership]፥ ቸርነትን የሚያደርግ።

አንዲሆን ተጠርቶአል። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ ልዩነት ሳያደርግ በሁሉም ላይ ይወርዳል)

- ❖ የእድሜ ልዩነት የለበትም (እንደ አይሁዳውያኑ ሕግ ዕድሜአችን ለሳሳ ዓመት እስኪሞላው መጠበቅ የለብንም)

2) መላቱም ለልጅ ልጅና ለአሕዛብ ጭምር ነው (ማለትም ለዚያ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ከትውልድ እስከ ትውልድ ድረስ ነው)።

3) ታላቁ የጌታ ቀን እስኪመጣ ድረስ ቤተክርስቲያን በመንፈሱ ትሞላለች፥ ተሞልታለችም።

ስለሆነም ከበዓለ ዓምሳ ቀን አንስቶ እስከ ጌታ ዳግም ምጽአት ድረስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ ይሠራሉ እንጂ በመ ሐሉ የተቋረጠ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የለም (መንፈስ ቅዱስ ያቆመበት ጊዜ የለም)። በተጨማሪም ኢሳይያስና ሚክያስ እግዚአብሔር እስከ መጨረ ሻው ቀን ድረስ መንፈሱን እንደሚያፈስ ይነግሩናል (ኢሳ 2፥2፤ 44፥3፤ ሚክ 4 ፥1)።

በመጨረሻም የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ኢየሱስ በአብ ቀኝ በክብር መቀመጡን ያሳየናል (ሐዋ 2፥33-35፤ መዝ (110)፥1)። ስለዚህ ጌታችን ዳግም እስከሚመጣ ድረስ መንፈስ ቅዱስ እርሱን በመወከል በሙሉ ኃይልና ስልጣን በቤተክርስቲያን ውስጥ ይሠራል። ዶ/ር ማርቲን ሎይድ-ጆንስ «ጆይ አንስፒክ ብል» በተባለው መጽሐፋቸው ላይ «እግዚአብሔር ዓለሙን ስለወደደ አንድያ ልጁን ሰጠን፤ ታዲያ ይህንን በልጁ በኩል የተዘጋጀልንን በረከት (የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት) አለመቀበል እግዚአብሔርን እንደመሳደብ ይቆጠራል» በማለት የባርኮቱን ታላቅነት ገልጸውታል።[118]

ይህ ክፍል የምናየው ስእላዊ መግለጫ በትንቢተ ኢዩኤል ላይ ያለ ውን ማለትም ጴጥሮስ በበዓለ ዓምሳ ቀን የጠቀሰውን ታል ያሳየናል (ኢዩ 2፥28-32)። በስእላዊው መግለጫ ላይ እንደምናየው መንፈስ ቅዱስ ከወረደበት ከበዓለ

118

ማርቲን ሎይድ-ጆንስ፥ *ጆይ ለንደክሰል፥ ፓወር ኤንድ ሪሊጅን ኢን ዘ ሆሊ ስፒሪት* (ዊተን፥ ሄርል ድ ዌው ፕብሊሸርስ፤ 1984) 16።

<u>ኤፌ 4፥11</u>

ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ ወንጌላውያን፥ መጋቢዎችና አስተማሪዎች።

<u>1ጴጥ 4፥11</u>

አገልግሎት [Service] ና ሰባኪ።

ከዚህ በመቀጠል ግውቅ ያስፈልገና ብዬ ያሰብኳቸውን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ዎች ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር እንመለከታቸዋለን፤[119] —

1. *ትንቢት*

እግዚአብሔር ለሕዝቡ እውነትን ለመግለጥና የሚመጣውን ዘመንና ሁኔታ ለመጠቆም ትንቢትን ይሰጣል። ይህም እውነትን የመግለጥ አገልግሎት አንዳንድ ጊዜ ትንቢታዊ ሲሆን ሌላ ጊዜ ደግሞ የተደበቀን ነገር ወደ ብርሃን በማውጣት ኃጢአትናን የሰሀተትን ሥራ በማጋለጥ ነው። ትንቢትን በተመለከተ ወደ ፊት ሊሆኑ ስላላቸው ነገሮች ተገልጦ የምናገኘው በሐዋ 21፥9-11፤ 11፥27-30፤ ሮሜ 15፥26 ሲሆን፥ የእውነትን መንገድ ማሳየት ደግሞ በቲቶ 1፥12፤ 1ቆሮ 14፥3-4፤ ሐዋ 15፥32 ውስጥ ነው። ትንቢቱን የሚናገረውም ሰው ከእግዚአ ብሔር የተቀበለውን መልእክት ነው። የአነጋገሩም መንገድ አንዳንዴ በቀጥታ መነዳት ሲናገር አንዳንዴም ደግሞ እግዚአብሔር በልቡ ውስጥ የገለጠለትን እውነት በመናገር ነው።

የትንቢት መልእክት በተለያየ ዓይነት መንገድ ሊመጣ ይችላል፤ ይህም — በራእይ መልክ፥ በሕልም፥ ድምጽን በመስማት፥ ፍንደቃ በተሞላበት ሁኔታ፥ ልብ ውስጥ በሚቀመጥ መልእክት ወዘተ. ሊሆን ይችላል (2ሳሙ 23፥2-3፤ ሆሴ1፥2፤ ኤር 25፥15፤ 27፥2፤ 1ዜና 25፥1-8፤ 1ነገ 17፥13-14፤ 2ነገ 4፥3-4)።

119

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚጥቀሱን አንዳንድ ጠቃሚ አሳቦችን ዶ/ር ጀምስ ከሊንተን ከጻፉት «ስፕሪቹአል ጊፍትስ» ከተባለው መጽሐፍ ተውሻለሁ። — ጀምስ ሮበርት ከሊንተን፥ *ስፕሪቹአል ጊፍትስ* (ዊሸርሎጅ ካሊፉ፥ ሞራይዘን ሃውስ ፑብሊሸርስ፤ 1985) 53-91።

የመልእክቱም ይዘት ቃሉን በማብራራት፥ ኃጢአትን በመውቀስ፥ በመምከር፥ በማነጽ፥በማጽናናት፥ የወደፊቱን ነገር ለመጠቆምና ለማሰጠንቀቅ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን መውሰድ ስለሚገባት አቋምና እርምጃ ሊሆን ይችላል።

ትንቢትን የሚያቀርቡት ሰዎች በምን ዓይነት ሁኔታ ማቅረብ አለባቸው የሚለው ነገር ብዙውን ጊዜ የሃላብ መለያየትን ሲያመጣ ይታያል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን ትንቢትን የሚናገር እንዴት ሆኖ እንደሚናገር ግለትም የለም ልኮ ሥርዓትን ሳይረብሽ ተራ ጠበቆና ተደማምጦ ከመናገር በስተቀር ቆሞ ይናገር ወይም ቁጭ ብሎ ወይም እየዘለለ የተጠቀሰ የአመራር ደንብ የለም። እግዚአብሔር ሉዓላዊ እንደመሆኑ መጠን በፈቀደው ዓይነትና መንገድ መጠቀም ይችላል። ለምሳሌ መንፈስ ቅዱስ በንጉሥ ሳኦል ላይ በወረደበት ጊዜ ወደ አርማቴም አገር ወደ ነዋትዘራማ እስኪመጣ ድረስ ትንቢት ይናገር ነበር። በሳሙኤልም ፊት ልብሱን አውልቆ ራቁቱን ትንቢት ይናገር ነበር፤ ራቁቱንም ወድቆ ቀንና ሌሊት በዚያ አድሮአል (1ሳሙ 19፥23-24)።

አንዳንዴም የነቢያት ጉባኤ ቀኑን ሙሉ እግዚአብሔርን እያመለኩና እየፈነደቁ ትንቢትን ይናገሩ ነበር (1ሳሙ 10፥5-6, 9-13)። ቢጨማሪም የአሦር ንጉሥ ሳርጎን አዛጦንን በያዛት ጊዜ እግዚአብሔር የእሞጽን ልጅ ኢሳይያስን — «ሂድ፥ ማቅህን ከወገብህ አውጣ ጫማህንም ከእግርህ አውልቅ» ብሎ በተናገረ ው ጊዜ በግብፅና በኢትዮጵያ ላይ ለምልክትና ለተአምራት እንዲሆን ራቁቱን ለሦስት ዓመት እንደ ዜደ እንመለከታለን (ኢሳ 20፥1-6)።

በመሠረቱ የትንቢት አገልግሎት ዓላማው አማኞችን ብቻ መገንባት ሳይ ሆን ያልዳኑትንም ሰዎች በመውቀስ፥ ልባቸውን በመመርመርና የተሰወረውን በመ ግለጥ ለእግዚአብሔር እንዲንበረከኩ ያደርጋል (1ቆሮ 14፥23-25)። በመጨረ ሻም ማንኛውም ዓይነት ትንቢት ከእውነት መሆኑንና አለመሆኑን፥ ከዚያም በኋ ላ ደግሞ መፈጸሙንና አለመፈጸሙን ነቢያትና መሪዎች መለየት አለባቸው። የመልእክቱን ይዘት መለየቱ የሚጠቅመው ዋናው ምክንያት መልእክቱ ከእግዚአ ብሔር ይሁን፥ ከሥጋ ወይንስ ከሰህተት አመራር ለመለየት ነው (በአንደኛው የተ ሰጡንቄ መልእክት ሥር ለማብራራት እንደሞክርሁት)።

በመጨረሻም ምንም እንኳን በሐዋርያት ሥራ ላይ አንዳንዶቹ በመን ፈስ ቅዱስ በተጠመቁ ጊዜ ትንቢት ቢናገሩም የነቢይነት አገልግሎት ግን የተለየ

ስጦታ ነው — ነቢይነት ሥልጣንን ሲያሳይ ትንቢት መናገር ግን ስጦታነቱን ብቻ ነው የሚያሳየው (ሐዋ 2፥4፤ 19፥7)። ጳውሎስም በመልእክቱ የቆሮንቶስ አማኞች ሁሉም ትንቢትን ቢናገሩ ይወድ ነበር። ነገር ግን አንደ አውነቱ ከሆነ ሁሉም ትንቢት አይናገሩም ነበር (1ቆሮ 14፥5፤ 31)። ስለዚህም ነቢያት ለተጠሩበት አገልግሎት ብቻ ሆነ ተብለው የተለዩ አገልጋዮች ናቸው (ሐዋ 11፥28፤ 21፥10፤ ኤፌ 4፥11)። ስለሆነም ከትንቢት ሌላም የእግዚአብሔርን ቃል በአውቀትና በጥበብ የመገለጥ ስጦታና የፈውስም ስጦታ ሊኖራቸው ይችላል (ኤፌ 2፥20፤ 4፥11)። ታዲያ ነቢያትን እንዴት አድርገን እንለያቸዋለን የሚለውን ጥያቄ ከዚህ በመቀጠል እንነጋገራለን: —

ሀ/ የእግዚአብሔር ነቢይ ማነው

1. በእግዚአብሔር የተጠራ ነው (ዘዳ 13፥1-5፤ ኤር 1፥5))
2. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞላ ሥልጣንና መገለጥን ከእግዚአብሔር የተቀበለ ነው (ዘዳ 18፥19-22፤ ዘኁ 11፥17፤ ሕዝቅ 3፥12-14፤ 8፥3፤ 11፥1፤5፣24፤ 43፥5፤ 1ሳሙ 19፥20፤ 2ዜና 20፥14)
3. የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ነው (ከእግዚአብሔር የሆነውን ብቻ ይናገራል፣ እግዚአብሔርን እንጂ ራሱን አይሰብክም) (ዘዳግ 18፥18-19፤ ዘጸ 4፥10-16)።
4. በእግዚአብሔር ስም መልእክቱን ይናገራል (ዘዳ 18፥ 20፤ ኤር 26፥16)
5. ስለንጋው ግድ የሚለው ነው (ኢሳ 40፥11፤ ዮሐ 10፥1-18)።
6.. የተናገረው ቃል ሳይፈጸም አንዲት በመሬት ላይ ጠብ አይልም (ዘዳ 18፥20-22፤ 1ሳሙ 3፥19-20፤ 1ነገ 13፥26፤ 16፥2፤ 2ነገ 24፥2፤ ኤርም 28፥15-17፤ ሕዝቅ 33፥33)።
7. ትንቢትን ብቻ በመናገር የተወሰነ ሳይሆን የአውቀትንና የጥበብን ቃል በመግለጥ ሊያገለግል ይችላል። አብዛኛው የብሉይ ኪዳን ነቢያት በፈውስ፣ ተአምራትና ድንቅ በማድረግ አንዲሁም በመገለጥ ያገለግሉ ነበር።
8. እግዚአብሔርን የሚወድ፣ የሚፈራና የሚያከብር ነው

ለ/ የነቢያት አገልግሎት

1. የእግዚአብሔርን መልእክት ሳይጨምሩና ሳይቀንሱ ለሕዝቡ ማድረስ
2. ሕዝቡ በቅድስና ከእግዚአብሔር ጋር መራመዱን ማረጋገጥ
3. ኃጢትንና ስህተትን መገሰጽ፣ ማረም፣ ማሳተከከልና ማነጽ
4. ሕዝቡን ለንስሐ መጥራትና ማነቃቃት
5. ሐሰተኛ ነቢያትን ማጋለጥና መገሰጽ
6. የዘመኑን ተጨባጭ አውነታ ማስተማር፣ የመጨረሻውን ዘመን ማመልከትና ለጌታ ቀን የሕዝቡን ልብ ማዘጋጀት
7. ለሕዝቡ መጸለይ
8. እግዚአብሔርን የማይፈሩትንና ሕዝብን የሚያሳስቱ መሪዎችን መምከር፣ መውቀስና መገሰጽ

ሐ/ ሐሰተኛ ነቢያትንና መልእክታቸውን መለየት


(ዘዳግ 13፥1-5፤ 18፥21-22፤ ኤር 2፥8, 26፤ 23፥13፤ 6፥13፤ 8፥10፤ 14፥13-16፤ 23፥16-17፤ 27-28፤ 1ቆሮ 14፥29፤ 1ተሰሎ 5፥19-20)


1. የሚመሩት ወይም የሚናገሩት ከእግዚአብሔር በሚገኝ መገለጥ ሳይሆን ከራሳቸው ምኞት ወይም ከረቀቀ የሰይጣን አሠራር ከሚገኝ ምሪትና መገለጥ ነው።
2. ለሰው ጆሮ የሚጥምን መልእክት ፈልገው ማቅረብ ሥራቸው ነው። ተቀባይነትን ለማግኘት ሲሉ ሕዝቡ ወንስሐ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ በሚገባው ሰዓት እንኳን (ሕዝቡ በእምላኩ ላይ ባመፀበት ጊዜ ወደ ንሰሐ ከመጥራት ይልቅ ምንም ችግር እንዳልተፈጠረ በመውሰድ) ሰላምን፣ ተስፋንና ብልጽግናን ይሰብካሉ፤ ይህም ደግሞ Vox populi በመባል ይታወቃል። ለምሳሌ በነቢዩ ኤርምያስ ዘመን የነበሩት ሐሰተኛ ነቢያት የሕዝቡን ድጋፍ ለማግኘት ሰላም ሳይሆን ሰላም ይሆናል እያሉ ይተነብዩ ነበር፤ ኤርምያስ ግን ሕዝቡን ወደ ንሰሐ በመጥራቱና የእግዚአብሔርን ፍርድ በመናገሩ መከራን ተቀበለ (ኤርም 28፥1-2፤ 15፤ 27፥1-11፤ 18፥18)።
3. የሚናገሩት ቃል ከእግዚአብሔር የተገኘ መገለጥ እንዳልሆነ ስለሚያውቁ ሰዎችን ለማጥመድ ወይም ለመማረክ የተለያየ ዓይነት ዘዴንና እጅ ዋጮዘ

ዛን ይጠቀማሉ፤ ይህም Realpolitik ይባላል። ሞያተኞችም ስለሆኑ የሚገዳቸው የራሳቸው ክበርና ዋቅም እንጂ የመንጋው ጉዳይ አይደለም።

4. በመልእክታቸው የሰዎችን ልቡና መቆጣጠርና ግስፈራራትን ያዘወትራሉ
5. እግዚአብሔርን ከማስደሰት ይልቅ ሰውን ወይም የሰውን ሥርዓት ለማስደሰት ይጥራሉ፤ ሃሳባቸው ምድራዊ ስለሆነ ሄዶ ሄዶ ሰዎችን በሚያስጥምና በሚያፈርስ በብዙ ፈተና ይወድቃሉ (መጨረሻቸው አያምርም)።
6. በአማልክቶቻቸው ስም ሊናገሩ ይችላሉ (ከተናገሩም ማንነታቸው ተለየ ማለት ነው)፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ስም ተናግረው ትንቢቱ ካልተፈጸመ ሐሰተኛ ናቸው።
7. በእግዚአብሔር ስም ተናግረው ትንቢቱ ቢፈጸም እንኳን የሚያምኑበትና የሚያስተምሩት ትምህርት ስህተት ከሆነ ሐሰተኞች ናቸው። ይህም ማለት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይጠጋ ትምህርት ያስተምራሉ።
8. በሕይወታቸው የመንፈስ ፍሬ አይታይባቸውም ወይም ደግሞ ሕይወታቸው ሰውር በሆነ የኃጢአት ነቀዝ የተበላ ነው፤ ኢየሱስም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ ብሎአል (ማቴ 7፥15-23፤ ሉቃ 6፥44፤ ኤርም 23፥14)።

ነቢያትንና መልእክታቸውን መለየት





ስእላዊ መግለጫ ቁ. 7

2 *ማስተማር*

ይህ ስጦታ ያላቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ወይም መመሪያ በመስጠት ያገለግላሉ (ማቴ 5-7፤ ዮሐ 6፥59፤ ሐዋ 18፥11፤ 1ቆሮ 4፥17፤ 1ጢሞ 2፥12)። አውቀትን የሚቀስሙና ራሳቸውን የሚያስተምሩ ሲሆኑ ሌሎች ሰዎች ከነርሱ ይማራሉ (ማቴ 11፥29፤ 28፥ 19፤ ሐዋ 14፥21)። አውነትን በመተርጎምና በማብራራት (ማር 24፥27፤ 1ቆሮ 12፥30)፥ ቃሉን በመተንተንና በመዘርዘር ሰዎች ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱት በማድረግ (ሐዋ 11፥4፤ 18፥26፤ 28፥3)፥ አውነትን ከሐሰት ለይቶ በማሳየት ሰዎችን የማሳመን ችሎታ አላቸው (ሐዋ 19፥9-10)። የአስተማሪነት ስጦታ ከትንቢት ቀጥሎ ትልቁን ቦታ የያዘ ስጦታ ሲሆን አማኝን በእግዚአብሔር አውነት በማነጽና የሰሀተትን ትምህ

ርት በማጋለጥ ቤተክርስቲያንን ይጠቅማል፥ ሙሉ ወደ መሆንም እንድትደርስ ያስችላታል።

3. *መጋቢነት/አረኛነት*

ይህ ስጦታ ከአስተማሪነት ስጦታ ጋር የተያያዘ ነው። መጋቢዎች መንጋውን ለመጠበቅና ለማነጽ የማስተማር ስጦታ ያላቸው ናቸው። በጉሮአቸውና በታላቸው በሰዎች ሕይወት ውስጥ በጎ ተጽእኖ የሚያደርጉ መሪዎች ናቸው። ለመንጋው የሚበጅ ራእይ አላቸው፣ ሥልጣናቸውን ከማን እንደተቀበሉት ስለሚያውቁ በእንድ ነገር ላይ ውሳኔ ለመስጠት አይቸገሩም። መንጋውን ከስህተት አሠራር ለመጠበቅ የተጉ ናቸው፤ መንጋውን በእግዚአብሔር አውነት ለመገንባት ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ (መንጋውን ያሰማራሉ)። በሚያሰማሩበትም ጊዜ መንጋው የተመጣጠነ መንፈሳዊ ምግብ ማግኘቱን ይከታተላሉ፣ የአባሎታቸውን ችግር ቶሎ መረዳትና አቅም በፈቀደው መጠን መርዳት ደስ የሚላቸው ናቸው። የአውነትን ቃል በሥልጣን ማዘዝ፥ ማስተማር፤ መምከር፥ ማበረታታትና ወደ ሰዎች ልብ የማምጣት ስጦታ አላቸው (ዮሐ 21፥16፤ ሐዋ 20፥17-28፤ ሮሜ 12፥8፤ 1ጢሞ 3፥5፤ 5፥17፤ ዕብ 13፥7, 17, 24፤ 1ጴጥ 5፥1-11፤ ኢሳ 40፥11)።

አረኞችም ስለሆኑ የአባላቶቻቸውን መንፈሳዊ እድገት ይከታተላሉ፤ የአባላቶቻቸውን የጸጋ ስጦታ ለይቶ በማወቅ ኮትኩተው የማሳደግ ኃላፊነት አለባቸው። በጸጋ ያደጉትን ደግሞ በተገቢው የአገልግሎት ዘርፍ በማሳተፍ አንድ ላይ እየተጋጠሙ የክርስቶስን አካል ሊገነቡ የሚችሉበትን መንገድ የመንፈስ ቅዱስ ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ይተልማሉ። ይህም ደግሞ የመንፈስን አንድነትና ሕብረት ለመጠበቅ ስለሚያመች ራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ሊየሱስ በአንድነት ለማደግ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።

በአጠቃላይ መጋቢዎች እነርሱም ልክ እንደ ጌታ ኢየሱስ መልካም አረኛ በመሆን መንጋውን በፍቅር እንጂ በኃይል አይገዙም። መንጋው በሚያሰማሩበት ጊዜ ደግሞ ወደ ለመለመ መስክ በመምራት ጠቦቶቹን በብብታቸው ሊሸከሙ የሚጠቡትን ደግሞ በቀስታ ይመራሉ። በመከራና በስደት እንዲሁም በችግር ምክንያት የላሉትን እጆችና የሰለሉትን ጉልበቶች ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ያቀናሉ። በኃጢአት ውስጥ የወደቁትን አባላት ደግሞ ፍቅር በተሞላበት መን

ገድ፥ በየዋሃት መንፈስ በመሆን ያቀናሉ እንጂ የፍርድን ቃል በመሰንዘር ሰውን አይሹብሩም ወይም አያስበረግጉም (እውነትን በፍቅር ይገልጻሉ) (ኢሳ 40፥10-11፤ 2ቆሮ 2፥5-11፤ ገላ 6፥1-5፤ ዕብ 12፥12-13፤)።

4. የእውቀትን ቃል መናገር [ከእግዚአብሔር የሚመጣ ቃል (ሉሳ) በእውቀት መግለጥ]

ይህ ዓይነቱ ስጦታ ያላቸው ሰዎች ሰማያዊ የሆነ መገለጥን ያገኙ ናቸው። የዚህ ዓይነቱ ስጦታ ባብዛኛው ጊዜ በፈውስ የጸሎት ስብሰባ ውስጥ ይከሰታል፤ እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር እንደ ፈቀደ መገለጡ ለግለሰቦች ሊመጣ ይችላል። የእመጣጡም መንገድ ሊለያይ ይችላል፤ ይህም — በራእይ መልክ ሊያዩ ይችላሉ፣ በሕልም ሊታያቸው ይችላል፣ በድምጽ መልክ ለልባቸው ሊመጣላቸው ይችላል፤ ወዘተ.። ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ ጴጥሮስ የሐናን ያን ኃጢአት በመገለጥ አውቆታል (ሐዋ 5፥1-4)፤ ወንጌልን ወደ አሕዛብ ይዞ እንዲሄድ በራእይና በድምጽ መገለጥ ተነገረው (ሐዋ 10፥9-23)። ጳውሎስ ከጌታ ባገኘው የራእይ መገለጥ ምክንያት ወንጌልን እየሰበከና እያስተማረ አንድ ወር ተኩል በቆሮንቶስ ቆየ (ሐዋ 18፥ 8-11)። ጳውሎስ ታስሮ በመርከብ ወደ ሮሜ ሲሄድ ባለ ማዕበል ተነስቶ አናወጣቸው። ነገር ግን እርሱ ባገኘው መገለጥ መሠረት ሰዎቹ ከማዕበሉ የተነሳ እንደማይሞቱ ተናገራቸው (ሐዋ 27፥9-12፤ 21-26)።

በመቀጠል ደግሞ እግዚአብሔር በዘመናችን ከሠራቸው ሥራዎች አንዱን አቀርባለሁ፤ —

በሳንዲያጎ ካሊፎርንያ ጆን ሬቦርግና ጄን ሬቦርግ የተባሉት ባለትዳር ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ተደላድለውና ተመቻችተው ይኖሩ ነበር። ጆን በአንድ የመድሀን ኩባንያ ውስጥ ሲሠራ ጄን ደግሞ አስተማሪ ነበረች። ሁለቱም ጌታን በጣም የሚወድዱና በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ የሚሳተፉ፤ በደስታና በሰላም የሚኖሩ ነበሩ። በ 1965 ዓም ባላሰቡት ሰዓት አንዳንድ ሁኔታዎች በጄን ላይ መከሰት ጀመሩ። ከሥራ ወደ ቤት ስትመጣ በጣም ድካም ይሰማታል፣ እንቅልፍ አልወሰድ ይላታል፣ ቀስ በቀስ ሰውነትዋ ይዝላል፤ ባጠቃላይ ሕይወቱዋ ጣዕሙን ያጣል። ሁኔታውን ለባለቤትዋ ታማክረውና በነገሩ ላይ ለመነጋገር

ወደ ቤተሰብ ሐኪም ጋር ይሄዳሉ፤ ይህ የሆነው በጥቅምት 1965 ዓም ነው። ሐኪሙም ሁሉን ነገር ከመረመሩ በኋላ ምንም ዓይነት በሽታ እንደሌለባት ይነ ግሩዋትና በቂ ዕረፍት እንድትወስድ በመምከር ያሰናበቱዋታል።

ነገር ግን ጄን ሕመሙ እየባሰባት ስለ ሄደ የምትወደውን የመምህርነት ሥራ እንኳን ለማቆም ተገደደች። በተለያዩ ጊዜያት የፈውስ ስጦታ ያላቸው አገልጋዮች ቢጸልዩላትም እንኳን ሊሻላት አልቻለም። ሕመምዋም እየጸናባት ሲሄድ ራሱዋን መንከባከብና የቤት ውስጥ ሥራ እንኳን መስራት ስላልቻለች ሠራተኛ መቅጠር ግድ ሆነባቸው። በመጨረሻም የአእምሮ ሐኪም ጋር ሲወሰዱዋት በልቡና ዝብጠት [Depression] በሽታ እንደምትሰቃይና ይህም በሽታ ደግሞ ወደ ከፍተኛ የአእምሮ በሽታ ደረጃ እንደ ደረሰ ስለተረጋገጠ ለሕክምና እንዲያመች ሲባል ሚሳሺስታ የተባለ በሳንዲያጎ የሚገኝ የአእምሮ በሽታ ሆስፒታል እንድትገባ ተገደደች።

እዚያ እያለች ሰይጣን በተለያየ መንገድ ይከሳት ነበር — «እግዚአብሔርን የሚወድና በፈውስ የሚያምን እንዳንቺ ያለ ሰው እንዴት በእንደዚህ ያለ በሽታ ይሰቃያል? ይቅርታ የማይገባውን ኃጢአት ስለ ሰራሽ ነው እንደዚህ የምትሰቃዪው» የሚሉት ይገኙበታል። ጆንም ኦሮውንና የጄንን የሕክምና ክፍያ በአንድ ሰው ደመወዝ ሊቋቋመው ስላልቻለ ቤቱን በመሸጥ ከሁለቱ ልጆቹ ጋር አፓርትመንት ተከራይቶ ገባ። በአጠቃላይ ትዳሩ፥ ቤተሰቡና ኦሮው ሁሉ ተመሰቃቀለ።

ይህ በንዲህ እንዳለ በጥቅምት 1968 ዓም ላይ የፈውስ ስጦታ ያለው ፖል ኬይን የተባለ ወንጌላዊ በሳንበርናንዲኖ በተዘጋጀ የወንጌል ስብሰባ ላይ ለመሰበክ ይመጣ ስለ ነበር እርሱን ለማግኘት የጄን አባትና እናት እዛ ድረስ ሄዱ። ከስብከትም በኋላ ሊፖል ኬይን ስለ ልጃቸው ከነገሩት በኋላ እንዲጸልይላቸው ጠየቁት። ፖል በመመለስ ጄን የት ሆስፒታል እንደሆነች ጠየቃቸው። ነገር ግን የጄን ባለቤት ጆን ለማንም መንገር ስላልፈለገ ለእነርሱም አልነገራቸውም ነበርና ሊፖልም ሊነግሩት አልቻሉም። እርሱም ለልጃቸው እን ደሚጸልይላት ነግሮአቸው ተለያዩ።

ጊዜው አኩለ ሌሊት ነበር ፖል የአምስት ቀን የወንጌል ስብከቱንና አገ ልግሎቱን ጨርሶ ወደ መጣበት አገር ለመመለስ ወደ መኪናው ይሄዳል።

ወደ መኪናውም ከ ሄደ በኋላ የመኪናውን ሞተር ከማስነሳቱ በፊት ለጂን ጸለየላት። በጸሎት ላይም እንዳለ ወደ ሰማይ ሲመለከት ሰማዩ ልክ እንደ ትልቅ ቴሌቪዥን ሆኖ ታየው። በቴሌቪዥኑ ውስጥም ጂንን በአንድ የአለምሮ በሽተኞች ሆስፒታል ውስጥ ያያታል፣ ከዚያም በልቡ ውስጥ እንዲህ የሚል ድምጽ ይመጣል – «ወደ ሳንዲያጎ ሂደህ ለዚች ሴት ብትጸልይ ለክብሬ ሰል አፈውሳታለሁ፣ ምስክርነቱዋንም ብዙ ሴቶችን ለማጽናናት እጠቀምበታለሁ።»

በነጋታው ፖል ከጌታ በተቀበለው መገለጥ መሠረት ጂንን ለማየት ወደ ሳንዲያጎ እየነዳ ሲሄድ ሳለ ሳንዲያጎ ከመግባቱ በፊት አንድ ቦታ ላይ እንዲያቆም በልቡ ይሰማዋል። መኪናውንም ካቆመ በኋላ የሕዝብ ስልክ ያለበት ቦታ ይሄድና የጂን እናትና አባት የሰጡትን ስልክ ይደውላል። ስልኩንም የጂን ልጅ የሆነችው ጂኒል ታነሳለች። ፖልም ለጂኒል እናቱዋ የተኛችበትን የሆስፒታል ስም እንድትነግረው ይጠይቃታል። እሱዋ ግን የሆስፒታሉን ስም ልትነግረው እንደማትችል ከገለጸችለት በኋላ በመቀጠልም ካለ አባቱዋ በስተቀር ማንም እናቱዋን ሊጎበኝ እንደማይፈቀድለት ትነግረዋለች። ፖልም መለሰና «አባትሽ የነገረሽን ትእዛዝ እንድትጥሺ አልፈልግም፤ ነገር ግን አንድ ግዜ ታገሺኝ፣ እሺ? ስልኩን አትዝጊው» ካላት በኋላ መጸለይ ጀመረ። በጸሎት ላይ እንዳለ አሁንም አንድ ትልቅ የሆነ ቴሌቪዥን ያያል፤ በውስጡም ያለው የሳንዲያጎ ጋዜጣ ሲሆን በጋዜጣውም ላይ «ሜሳቪስታ» የሚል ጽሑፍ አለበት። ከዚያም ለጂኒል «አናትሽ ያለችው ሜሳ ቪስታ ሆስፒታል ነው፣ ትክክል አይደለም?» ሲላት እርሱዋም መልሳ «አዎን፣ እዚያ ነው ያለቸው ትለዋለች»። እርሱም መልሶ እናቱዋን እግዚአብሔር እንደሚፈውሳትና እንደምትድን ይነግራትና ውበቱ ታል አጽናንቶአት ወደ ሆስፒታሉ ያመራል።

ሆስፒታሉ ከደረሰ በኋላ ሰሙን ላስተናጋጂዋ በመንገር የመጣበትም ምክንያት ጂንን ሊጎበኝ እንደሆነ ይነግራታል። የሚደንቀው ነገር ከጂን ስም ሥር ከለ ባልዋ በስተቀር ማንም ሊጎበኛት እንደማይችል ቢጸፍበትም ቅሉ ገብቶ እንዲያያት ተፈቀደለት። ጂን ደግሞ ፖል ወደ እርሱዋ ሲመጣ ስታየው «ጌታ ሆይ፣ ይህ መልአክ የሚመስል ሰው ማነው? ያንተን ክብር በርሱ ውስጥ አያለሁ፤ እንደርሱ ያለ ሰው መጥቶ ቢጎበኘኝ ደስ ባለኝ ነበር።» አያለች በልቡዋ አያሰበች አያለች ነርሱዋ «ጂን» ብላ ጠርታት ሰውዬው እርሱዋን ሊያያት እን

ደመጣ ነገረቻትና ትታቸው ሄደች። ፖልና ጂንም ለብቻቸው ይሆኑ ዘንድ ወደ አንድ ክፍል ሄዱ። ፖልም ራሱን ካስተዋወቀ በኋላ ኢየሱስ ወደ እርሱዋ እንደላከው ነገራት። ከዚያም በመቀጠል «ኢየሱስ እንዲፈውስሽ እጸልይልሻለሁ እንቺም ትፈወሻለሽ፣ በምስተኛውም ቀን ወደ ቤትሽ ትሄጃለሽ» አላት።

በመቀጠልም «ከመጸለዬ በፊት እግዚአብሔር ወደ አንቺ እንደላከኝ ታውቂ ዘንድ የሚረዳሽን አንዳንድ ነገሮች እነግርሻለሁ: — 1ኛ. ኢየሱስ እንድ ነገርሽ የነገረኝ ምንም ዓይነት ይቅር የማይባል ኃጢአት እንዳልሠራሽ ነው። 2ኛ. የአሥራ አራት አመት ልጅ በነበርሽ ጊዜ ከረጅቱን ለማሳለፍ ወደ አሬገን ግዛት ሄደሽ ነበር። አዚያም እያለሽ ጌታ ኢየሱስ ወደ ልብሽ መጥቶ እንዲስ ውጥሽና ከዚያም ሚሲዮናዊ እንዲያደርግሽ ጠይቀሽው ነበር» አላት። እርሱዋም በመደንገጥ «አዎ። የተናገርከው ነገር ትክክል ነው። ግን እንዴት ልታውቅ ቻልህ?» በማለት አድናቆቱዋን ገለጸችለት። እርሱም በመመለስ «ጌታ ባይገል ጥልኝ ኖሮ ባላወቅሁትም ነበር፣ አሁንም እንደነገርኩሽ ሚሲዮናዊ ሊያደርግሽ ይፈልጋል ነገር ግን አንቺ በምትጠብቂው መንገድ አይደለም።» ከለ በኋላ ዓይኑን በመጨፈን «ጂን፣ አሁን አንድ የለየር መንገድ ዩኒፎርም የለበሰ የአውሮፕላን አብራሪ ወይም ፖይለት እያለሁ እርሱም ያንቺ ጎረቤት ነው የሚሰቱም ስም ፖት ይባላል፤ የርሱ ስም ማን ነው?» ብሎ ጠየቃት። እርስዋም መልሳ «ስሙ አለን ሊንድመን ይባላል እርሱም የፒኤስኢ ከፕቴን ነው» አለችው። ፖል እንደገና «ሜርየን የምትባል ጎረቤት አለችሽ አይደል?» ሲል ጠየቃት። እርሱዋም መልሳ «አዎን» አለች። ፖልም መልሶ «ወደፊት ስፖትና ለሜሪየን ጌታ ያደረገልሽን ትነግሪያቸዋለሽ፣ ሕይወታቸውም በአንቺ ምስክርነት ይለወጣል። አለንንም ደግሞ ዩኒፎርሙን ለብሶ አንቺ ጌታ ያደረገልሽን ነገር ሁሉ ስትነግረው አያለሁ፤ ስለዚህም በአንቺ ምስክርነት ምክንያት ጌታን በመቀበል ይድናል» አላት።

በመጨረሻም ፖል ለጂን ሊጸልይላት ልክ የሞቱ ውኃ በሆድዋ ላይ እን ደተደረገ ነገር ተሰማት። እንደገናም ጨምድዶ የያዛት ደመና የመሰለ ነገር ሲለ ቃት ታወቃት። በደስታ ሰለ ተሞላች «ተፈወስኩኝ» በማለት ጮኸች። ፖልም በለሰለሰ ድምጽ «ገና ነው ትንሽ ይቀራል። እኔ ከዚህ ከሄድሁ በኋላ ዝቡጠቱ ተመልሶ ስመምጣት ይሞከራል፤ በዚያን ጊዜ ጌታ እግዚአብሔር ከመጽሐፍ

ቅዱስ ውስጥ ጥቅሶችን ይሰጥሻል ይህም ቃል ደግሞ ፈውስሽን ያጸናዋል። የክፉውን ድምጽ ስትሰሚ በእግዚአብሔር ቃል ተቃወሚው፥ በሦስተኛውም ቀን ቤትሽ ትሄጂያለሽ» ካላት በኋላ ተሰናብቶአት ሄደ።

ጀንም ከቤቱ ወጥታ ወደ ውጪ ዞር ዞር እያለች ሳለ ጌታ ቃሉን በልቡዋ ውስጥ አስቀመጠ። ይህም ቃል በኢሳይያስ 41፥10 ላይ ያለው «አኔ ከንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ አኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ፤ አበረታሃለሁ፥ አረዳሀግስ ሁ፥ በጽድቄም ቀኝ ደግፈ አይዝሃለሁ።» የሚለው ነው። በጣም የሚገርመው ነገር ልክ ይህንን ቃል ከጌታ ከተቀበለች በኋላ አንድ በረዶ የሚመስል እጅ ከጨለማ ውስጥ ወጥቶ ልቡዋን ለመያዝና የክስ ወሬን በመንዛት ተስፋዋን ሊያ ጨልም ሲሞክር ድምጹዋን ከፍ አድርጋ በመጮህ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል በማለት የተሰጣትን በኢሳይያስ 41፥10 ላይ ያለውን ቃል በቃል መለሰችለት። ያም ክፉ ነገር ወዲያው ለቋት ሄደ። በሚያስገርም ሁኔታ ስለ ተፈወሰች ሐኪ ሞቹም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በሦስተኛው ቀን ወደ ቤቱዋ ሰደዱዋት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔርን በምስክርነቱዋ እያገለገለች በደስታ ከቤተሰ ብዋ ጋር ኖረች።[120]

ምንም እንኳን የተለያዩ የፈውስ ስጦታ ያላቸው አገልጋዮች ለጀን ቢጸልዩላትም ቅሉ እግዚአብሔር ግን በራሱ መንገድና ሰዓት ቃሉን በመላክ ፈወሳት። የሕይወቱዋም ጉዞ «እግዚአብሔርን ለሚወዱትና እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።» የሚለውን ቃል ያስታውስ ናል (ሮሜ 8፥28)። በጣም ደስ የሚለው ነገር በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብንሄድ የንጋት ኮከብ የሆነው ኢየሱስ በጨለማው ላይ እያበራ፥ በበትሩና በም ርኩዙ ደግሞ እያጽናናንና እየደገፈን አብሮን ይጓዛል። አብሮንም ስለሚጓዝ ከአሸናፊዎች ሁሉ እንበልጣለንና ክፉን እንፈራም (መዝ (23)፥4፤ ሮሜ 8፥31 -39)።

120

ይህንን ታሪክ የወሰድሁት ዶ/ር ጃክ ዲር ከጻፉት መጽሐፍ ውስጥ ነው። — ጃክ ዲር፥ *ሰርፕራይዝ ድ ባይ ዘ ቮይስ ኦቭ ጎድ* (ግሬንድ ራፒድስ፥ ዞንደርቫን አሳታሚ ድርጅት፤ 1996) 343-357።

5. *የ፻በብን ቃል መናገር [ከእግዚአብሔር የሚመጣን ቃል (ሉቃስ) በ፻በብ መግ ለጥ]*

ይህ ስጦታ ያለው ሰው በግስተዋል የተሞላ ነው። የተወሳሰቡ የሚመስ ሉትን ችግሮች በእግዚአብሔር ቃል በመመርመርና በመገምገም መመሪያ ማው ጣት ይችላል። ለችግሮች ቅሰፈታዊ የሆነ መፍትሄ የመስጠት ችሎታ አለው። ከመናገሩ ወይም እሺ ከማለቱ በፊት ውስጡን ያደምጣል ማለትም ለመንፈስ ቅዱስ ንቁ የሆነ ልቡና አለው፣ የሁኔታዎችንና የነገሮችን አካሄድ ወይም መስመ ር ያስተውላል፤ ሰዎችን በመምከር ተግባር ላይ ደግሞ ችግራቸው ያለበትን ቦታ በመጠቆም ከገቡበት አዘቅት ውስጥ የሚያወጣቸውን መፍትሄ ይሰጣል። ባጠቃ ላይ አረጋመዱ በመንፈስ ቅዱስ የተለካ ነው። ይህ ስጦታ ለሁላችንም የሚሰ ጥበት ጊዜ አለ ይኸውም ስለ ክርስቶስ ስም ስንሰደድ ነው። በምንሰደድበትም ጊዜ የአባታችን መንፈስ በእኛ ላይ ስለሚሆን ምንና እንዴት እንደምንናገር ጥበ ብን ይሰጠናል (ማቴ 10፥19-20፤ 1ጴጥ 4፥14)።

ለዚህ ዓይነቱ ስጦታ ዋና ምሳሌ የሚሆነን በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አሥራ አምስት ላይ የምናየው የጥንቱዋን ቤተክርስቲያንን ሊከፋፍል የነበረውን ችግር እንዴት አድርጎ በመንፈስ ቅዱስ ጥበብ ያዕቆብ የመፍትሄ አሳብ አንዳቀ ረበ ነው (15፥19-21)። ጴጥሮስ ደግሞ በአይሁድ መሪዎች ፊት ቀርቦ በምን ኃይል ወይስ በማን ስም እርሱና ባልደረቦቹ ወንጌልን አ ንደሰበኩ ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠው መልስ ጥበብን በመግለጥ ስለ ነበር ይሰሙት የነበሩት ሁሉ ያል ተማሩና መጽሐፍን ያላወቁ ሰዎች በእንደዚህ አይነት ጥበብ በመናገራቸው አደነ ቁአቸው (ሐዋ 4፥5-14)።

እስጢፋኖስም እንዲሁ ጥበብን በመግለጥ ለተሰበሰበው ሕዝብና ለመሪ ዎቹ እውነትን በመናገሩ እንደተገደለ እናውቃለን (ሐዋ 7፥1-60)። የእግዚአብ ሔርም ቃል ስለ ሁኔታው ሲነግረን «አንዳንዶቹ ተነስተው እስጢፋኖስን ይከራከ ሩት ነበር፤ ይናገርበት የነበረውንም ጥበብና መንፈስ ይቃወሙ ዘንድ አልቻሉም» (ሐዋ 6፥8-10) ይላል። ጳውሎስም ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስና በርሱ ላይ ስላለው እምነት በተለያዩ ጊዜያት በሕዝብ፥ በአለቆችና በነገሥታት ፊት ጥበብን በመግ ለጥ እንደተናገረና መልስ እንደሰጠ ተገልጾአል (ሐዋ 22፥1፤ 23፥1፤ 24፥10፤ 25 ፥25፥6፤ 26፥1)።

6. *ምክር*

ይህ ስጦታ ያለው ሰው ሰዎችን እንደ ቃሉ እንዲሄዱ የመለመን፥ የመምከርና የመገሰጽ (ሐዋ 2፥40፤ ሮሜ 15፥30፤ 16፥17፤1ቆሮ 1፥10፤ 2ቆሮ 9፥5 ፤ 1ተሰሎ 4፥1፤ ዕብ 1፥25) አገልግሎት አለው። በመከራ ውስጥ ያሉትን ሰዎች የማጽናናትና የማበረታታት እንዲሁም የራሱንም ሆነ የሌሎችን ሰዎች የሕይወት ምስክርነት በመንገር ሰዎች እስከ ሞትም ድረስ የታመኑ እንዲሆኑ በማደፋፈር ሲያገለግል አገልግሎቱም የሰዎችን ልብ ይነካል (2ቆሮ 1፥4፤ ኤፌ 6፥22፤ ቆላ 4፥8፤ 1ተሰሎ 4፥18፤ 5፥11፤ ሐዋ 11፥23፤ 14፥22፤ 1ቆሮ 14፥31)። ቃሉንም ሲሰጥ በኃይልና በሥልጣን ይናገራል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው የእግዚአ ብሔርን እውነት ይዞ ለመቆም በጣም ደፋር ነው።

7. *በልሳን መልእክት ማቅረብና መተርጎም*

ይህ ስጦታ ያለው ሰው በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት ራሱ እንኳን ሊረ ዳው በማይችለው ልዩ በሆነ ቋንቋ ይናገራል። ቋንቋውንም የሚረዳው ስለሌለ መንፈስ ቅዱስ ለተናጋሪው ወይም ደግሞ ለሌላ ሰው ትርጉሙን ይሰጣል። በሐዋርያት ሥራ ላይ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ በልሳን መናገር ባህዛኛውን ጊዜ የሚታይ ነገር ነበር (2፥4፤ 10፥45-46፤ 19፥6)። ጳውሎስ ራሱ በልሳን ይናገራል ነገር ግን በግል ጸሎቱ ነው የሚጠቀምበት (1ቆሮ 14፥18)። የልሳኑ ትርጉም የማይታወቅ ከሆነ በግል ጸሎታችን ጊዜ ብቻ መጠቀም ይኖርብናል። ምክንያቱም በልሳን የሚናገር በመንፈስ ምስጢርን ይገልጸል እንጂ ለሌላው ሰው ምን እንደሆነ አይታወቅም። ሌላው ቀርቶ ለሚጸልየው ሰውዬ እንኳን ትርጉሙ አይታወቅም (1ቆሮ 14፥1-5,13-19)።

ጳውሎስ አገልጋዮች ለመጸለይ በተሰበሰቡበት ቦታ በልሳን መጸለይን የሚታወም አይመስልም (ለተለያዩ የአገልግሎት ስብሰባዎች)። እርሱ የተታወ መው ሰዎች ለአምልኮ በሚሰበሰቡት ጊዜ በጉባኤ መሐል የሚደረጉትን የልሳን ጸሎቶች (በልሳን መናገር) ነው። በአምልኮ ጊዜ በጉባኤ መሐል የሚደረጉ ነገ ሮች ለአምልኮ፣ ለግንዛ፣ ለመምከር፣ ለማጽናናትና ለመመስከር መሆን ይገባ ቸዋል እንጂ የሰዎችን አዛብ የሚከፋፍልና አገልግሎትን የሚረብሽ መሆን የለበ

ትም። ስለዚህም በጉባኤ መሐል የሚደረገው ነገር ሁሉ በሥርዓትና በአግባብ መሆን አለበት (1ቆሮ 14፥3-25፤ 1ሳሙ 10፥5-6፤ 19፥20)[121]።

8. *መናፍስትን መለየት*

ጳውሎስ በቆሮንቶስና በተሰሎንቄ መልእክት ላይ መንፈስን መለየት የተ ጠቀመበት ትንቢትን ለመመርመር ሲሆን ዮሐንስ ደግሞ የተጠቀመበት ሐሰተኛ ትምህርትን ለመለየት ነው (1ቆሮ 14፤ 1ተሰሎ 5፥19፤ ዮሐ 4፥1-6)። በብሉይ ኪዳን ዘመን ታላላቅ ነቢያት ወጣት ነቢያትን በማሰተማርና ትንቢታቸውን በመ መርመር ያሳድጓቸው ነበር (1ሳሙ 19፥20፤ 2ነገ 2፥15፤ 4፥38)። የሐዋርያት ዘመንም ነቢያት አንዱ የአንዱን ትንቢት በመመርመር የመልእክቱን ይዘትን ይገ መግመታል (1ቆሮ 14፥29)።

በሐዋርያት ሥራ ላይ ከተጠቀሱት መንፈስን የመለየት አገልግሎት ውስጥ ጳውሎስ ያጋጠመው አምምድ እንደ ጥሩ ማሰረጃ ሆኖ ሊቀርብ ይች ላል። ጳውሎስ ወንጌልን ሊሰብክ ወደ ፊልጵስዩስ በሄደ ጊዜ እንዲት የምዋርተ ኝነት መንፈስ ያለባት ሴት ተገናኝቻቸውና «የመዳንን መንገድ የሚነግሩአችሁ እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው» እያለች አያሌ ቀናት ትጮህ ነበር። መቼም መናፍስትን የመለየት ስጦታ ለሌለው ሰው መልእክቱዋን ቢያዳ ምጥ ምንም ስህተት አያገኝምበትም ይሆናል። ምክንያቱም ችግሩ ያለው ከመ ልእክቱ ጀርባ ስለሆነ ነው — ሰይጣን በእርሱዋ ውስጥ በመሆን ወንጌል ወደ ሰዉ ጆር እንዳይገባ በጩኸትዋ ያውክ ነበር (የዚህ ዓይነቱ ሥራ የረቀቀ የጠላ ት አሠራር ነው)። ጳውሎስ ግን ሴትዮዋን ዝም በይ አላላትም። ቃሉ የሚ ለው «ዘውር ብሎ ርኩሱን መንፈስ — ከእርስዋ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዣለሁ» አለው ነው። ምክንያቱም መንፈሱን ለይቶት ነበርና ነው (ሐዋ 16፥16-18)።

በተመሳሳይ ሁኔታ ጳውሎስ በርናባስና ዮሐንስ ወንጌልን ለመስበክ በመንፈስ ቅዱስ ተልከው ወደ ስልማና ቆጵሮስ በሄዱ ጊዜ በአይሁድ ምኩራ ቦች ቃሉን ይሰብኩ ነበር። በዚያም የአገሩ አገረ ገዥ ለሆነው ለሰርግዮስ

[121] ኪነር፥ *ሰረ ስሩቭል ኩመሰችነስ አላውት // ሆሊ ስፒሪተስ* 121-125።

ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል እየነገሩት ባለ በርያሱስ የተባለው ጠንቋይ ነቢይ አገረገሸውን ሊያጣምም ፈልጎ በተቃወማቸው ጊዜ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ «አንተ ተንኮል ሁሉ ክፋትም ሁሉ የሞላብህ፥ የዲያብሎስ ልጅ፥ የጽድቅም ሁሉ ጠላት፥ የቀናውን የጌታን መንገድ ለማጣመም አታርፍምን? አሁንም እነሆ፥ የጌታ እጅ በአንተ ላይ ናት፥ አውርም ትሆናለህ እስከ ጊዜውም ፀሐይን አታይም አለው።» አለው። እርሱም ወዲያውኑ ዓይነ ስውር ሆነ። ጳውሎስ ይህንን ያደረገው እውቀትን በመግለጥ ነበር (ሐዋ13፥4-12)። ሌላው መንፈሰን ለመለየት የሚጠቅመን መሳሪያ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቃሉም በሙላት ሲኖርብን ትንቢትንና የሰዠተት ትምህርትን ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል መመርመር እንችላለን (ዕብ 5፥14፤ 1ዮሐ 4፥1-3)።

9. *ለምንት*

ይህ ዓይነቱ ስጦታ ለመዳን ከሚያስፈልገው እምነት ይለያል። እግዚአብሔር ለሁሉም አማኝ በእኩል ውስጥ እንዲሳተፍ እምነትን ሰጥቶታል (ሮሜ 12፥3፣ 6)። የእምነት ስጦታ ግን ከዚህ ይለያል፥ ተራራን እንኳን ሊያፈልስ የሚችል ነው (1ቆሮ 13፥2)። «ተራራ ማፍለስ» በአይሁዳውያኑ ያንጋገር ዘይቤ የማይቻለውን ነገር ማድረግ ማለት ሲሆን ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰናፍጭ ቅንጣት እምነት ቢኖራቸው በሰው የማይቻለውን ነገር ማድረግ እንደሚችሉ ተነግሮአቸዋል (ማር 11፥223)። ስጦታውም ያላቸው ሰዎች ታላላቅ ድንቆችን ማድረግ ይችላሉ (እግዚአብሔር የፈቀደላቸውን ማለቱ ነው፤ ምክንያቱም እምነት ብቻውን ምንም ማድረግ አይቻለውም የእምነቱ ሰጪ የሆነው ካልፈቀደ በስ ተቀር)።

10. *ድንቅና ተአምራት አንዲሁም ፈውስ*

ይህ ስጦታ የእግዚአብሔርን ኃይል የመግለጥ ስጦታ ነው። የእምነትና የፈውስ ስጦታም ከዚህ ስጦታ ጋር አብረው ሊደመሩ ይችላሉ። ኢየሱስና ደቀመዛሙርት በታንኳ ሲጓዙ ማዕበል በተነሳ ጊዜ ኢየሱስ በታችኛው ክፍል ተኝቶ ነበር። በፍርሃት የተዋጡት ተከታዮቹ ኢየሱስ ማዕበሉን እንዲያስቆመው ከእንቅልፉ በቀሰቀሱት ጊዜ እምነት ስለጎደላቸው ወቀሳቸው። ምክንያቱም ራሳ

ቸው ማዕበሉን እንዲቆም ማዘዝ ሲችሉ ባለማድረጋቸው ወይም ደግሞ ኢየሱስ እያለ ጀልባው ይሰጥማል ብለው ማሰባቸው በእርሱ ላይ ያላቸውን የእምነት ማነስ አሳይቶአል (ማር 4፥40)። ያዕቆብ በመልእክቱ ደግሞ ኤልያስ ዝናብ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር እንዳይዘንብ በማድረጉ የእምነት ሰው እንደነበረ በመጥቀስ እኛም የርሱን አርአያ እንድንከተል ያበረታታናል (ያዕ 5፥17-18)። በሐዋርያት ሥራ ላይም እንዲሁ ሐዋርያት ታላላቅ ድንቅ ተአምራትን በማድረግ ደዌን በመፈወስና እስራትን በመፍታት ወንጌልን እንደሰበኩ እንመለከታለን (ሐዋ 4፥33፤ 5፥12፤ 6፥8፤ 8፥5-7፤ 13፥ 9-12፤ 16፥16-18፤ ሮሜ 2፥3)።

በዘመናችን ባለችው ቤተክርስቲያን ስለ ፈውስ ያለውን አስተሳሰብና ትምህርት መነጋገር አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በተለይ ደግሞ የብልጽግና ወንጌል ሰባኪዎች አማኝ መታመም የለበትም ስለሚሉ በክርስቶስ አካል ውስጥ ትልቅ የሆነን ችግር ይፈጥራሉ። በመጀመሪያ ይህንን ትምህርት በእግዚአብሔር ቃል ከማየታችን በፊት እግዚአብሔር ስምን ይፈውሰናል? የሚለውን ብንመለከት ለትምህርታችን ጠቃሚ የሆነን መንገድ ይከፍትልናል።

ሀ/ እግዚአብሔር ስምን ይፈውሰናል

1. *መሐሪ ስለሆነ ነው*

   (ማር 1፥4-42፤ 9፥22፤ ሉቃ 7፥11-17፤ 17፥13-14፤ ማቴ 9፥27፤ 15፥32፤ 20፥29-34፤ 15፥22-28፤ 17፥14-21)

2. *ራሱንና ልጁን ስለከበረ*

   (ዮሐ 11፥4, 40፤ ሐዋ 3፥12-13፤ 4፥21፤ ማቴ 15፥30-31፤ ሉቃ 5፥24-26፤ 7፥16፤ 13፥13,17፤ 18፥42-43፤ 19፥37)

3. *እምነታችንን በማየት*

   (ማቴ 9፥22፤ 15፥28፤ 9፥2፤ ሐዋ 14፥8-10)

4. *በቃልኪዳኑ መሠረት*

   (ያዕቆ 5፥14-18)

ለ/ መቼ ነው የምንፈወሰው

1. *ኢየሱስ ለመፈወስ የእግዚአብሔር ኃይል በሆነለት ጊዜ ፈወሰ (በአብ ጊዜና ሰዓት)*

(ሉቃ 5፥17፤ ዮሐ 5፥19፤ ሐዋ 3፥12-13)

2. *ኢየሱስ የሰዎችን እምነት በማየት ፈወሰ*

(ማር 6፥5-6፤ ማቴ 13፥58፤ 15፥21-28፤ ሐዋ 14፥9-10)

3. *መሐሪና ቸር ስለሆነ ፈወሰ*

የእስራኤል መሪዎች ኢየሱስን በእጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ስለ አሉት «ለዚህ አመንዝራ ትውልድ ከነቢዩ ዮናስ በስተቀር ምል ክት አይሰጠውም» በማለት በግልጽ መናገርና መፈወስ አቆመ (ማቴ 12፥38-42)። ነገር ግን ከዚያ ጊዜ በኋላ ለሰዎች በማዘንና በመራ ራት ፈውሶአቸዋል (ማር 5፥21-43፤ ማር 7፥31-37፤ 8፥22-26፤ ማቴ 17፥14-20)።

4. *ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን የሰበከው በብዙ ድካም (በሕመም) ነበር*

በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን የነበሩ ራሳቸውን የላቁ መንፈሳውያን አድ ርገው የወሰዱ አንዳንድ መሪዎች የጳውሎስን አገልግሎትና ሐዋርያ ነት የተቃወሙት ሕመም ስለ ነበረበት ነበር። በእነርሱ አስተሳሰብ መንፈሳዊ ሰው መታመም የለበትምና ነው። እንደሚታወቀው ሁሉ ለገላትያ አብያተክርስቲያናትም ወንጌልን ይዞ የሄደው በብዙ ሕመም ነበር (ገላ 4፥12-14)። ጳውሎስ ግን ይህ ድካም ከርሱ እንዲርቅ ሦስት ጊዜ ጌታን ለምኖት ነበር፤ ነገር ግን ጌታ መልሶ «ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካምህ ይፈጸማልና አለኝ» በማለት ይናገራል (1ቆሮ 2፥1-5፤ 1ቆሮ 12፥1-10)።

5. *የጳውሎስ የወንጌል ባልደረቦች ይታመሙ ነበር*

አፍሮዲጡ እስከ ሞት ድረስ ታሞ ነበር፤ ነገር ግን ወዲያውኑ በተአ ምራት አልተፈወሰም። ማለትም እንደማንኛውም ሰው ታሞ ተኝቶ ነበር (ፊል 2፥25-27)። ከጳውሎስ ጋር አብሮት ያገለግል የነበረው ጥሮፊሞስ ስለ ታመመ ጳውሎስ በሚሊጢን ትቶት መሄድ ግድ ሆነበ

ት (2ጢሞ 4፥20)፤ ጢሞቴዎስ ደግሞ ዕድሜውን በሙሉ በሆድ በሽ ታይስቃይ እንደነበረ የታወቀ ነው (1ጢሞ 5፥ 23)።

ታዲያ አንዳንድ ሰባኪዎች በተለይ ደግሞ ከብልጽግና ወንጌል ትምህ ርት ወገን የሆኑቱ በሽታ ከእግዚአብሔር አይደለም ብለው ሲያስተምሩ — ሩክር ሰቲያን በምንም ዓይነት መንገድ ሕመምን መቀበል የለበትም፤ ምክንያቱም ድህነ ትና ሕመም እርግማን ናቸው»[122] ይላሉ። ደግመውም ከርስቲያን ከታመመም እምነቱን በመጠቀም መፈወስ አለበት በማለት ያስተምራሉ[123]። ምንም እንኳን በሽታ፥ ድህነትና ሞት የመጡት ከአዳም ውድቀት በኋላ ቢሆንም ፍጥረትም አብሮን «ከጥፋት ባርነት ነጻ ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር አስኪደርስ ድረስ» አግኝ ሁሉ ከችግርና ከበሽታ ነጻ የሆነ ኑሮ ይኖራል ማለት አይቻልም።

በርግጥም ስመፈወስ የእግዚአብሔር ፈቃድና የእኛ እምነት አስፈላጊ ቢሆንም ፈውስ በሰው ፈቃድ አይመጣም። እግዚአብሔር በራሱ መለኮታዊ ፈቃድና ጊዜ ሁሉን ነገር ያከናውናል እንጂ በሞታው ስላስን ብቻ ከለ እግዚአብ ሔር ፈቃድ በፈቀደን መንገድ ሰዎችን መፈወስ እንችላለን ማለት ዘበት ነው።

በሽታ በተለያዩ ሁኔታዎች ሊመጣ ይችላል። ስለሆነም በመጀመሪያ የበሽታው መንስኤ ምን እንደሆነ ማወቅ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ መጸለይ እንዳ ለብን ይረዳናል። ይኸውም — 1) ከሰይጣን የሚመጣ በሽታ አለ (ማለትም ሰይ ጣን በቀጥታ መንገድ የሚያመጣብን፣ የክፋት ሁሉ ምንጭ ስለሆነ የእግዚአብ ሔርን ልጆች ከመዋጋት ያቋረጠበት ጊዜ የለም)። 2) እግዚአብሔር ፈቅዶት የሚያስቀምጠው በሽታ አለ (ጳውሎስና ጢሞቴዎስ እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይገባ ቸዋል)። 3) ራሳችን የምናመጣው በሽታ አለ (በኃጢአት ምክንያት)። 4) ሌሎች

122

ኬነት ኢ. ሄገን፣ *ሪዲምድ ፍርም ፆቨሪቲ ሲክስ ኢንድ ሰፐሪቾለ ዴዝ* (ቶልባ፣ ኬነት ሄገን ሚኒስትሪስ፣ 1993) 8።

123

ከብልጽግና ወንጌል ሰባኪዎች ዋነኞች የሆኑት ኬንዮን፣ ኬነት ሄገን፣ ኬኑትና ግሎሪያ ሀገላንድ፣ ፍሬደሪክ ፕሬይስ፣ ጄሪ ሰቨል፣ ጄሪ ዲፐላጉቲስ፣ ከሪፍሉ ዶላር፣ ቻርለስ ካፐስና የመሳሰሉት ናቸ ው። በሽታ መንፈሳዊነት ሳላስው ከርስቶስ ሲሉል በመውረድ በመንፈስ ምት ነጻ አውጥቶናል ብለው

ሰዎች የሚያመጡብን በሽታ አለ። 5) የምንኖረው በኃጢአት በወደቀ ዓለም ውስጥ ስለሆነ እንደማንኛውም ሰው ልንታመም እንችላለን። ነገር ግን የብል ጽግና ሰባኪዎች በአብዛኛውን ጊዜ የሚያቀርቡት መረጃ በኢሳይያስ ምዕራፍ ጎምሳ ሦስት ላይ ያለውን «በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ» የሚለውን ሲሆን፥ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት ከበሽታ ስለ ፈወሰን ልንታመም አይገባንም ይላሉ።

አንዳንዶቹ እንደውም ስመፈወስ ያበቃል በማለት ዝርዝር መመሪያ ያወ ጡም አሉ ይህም — 1) እንደምትፈወስ ተናገር 2) አመነው (በራስህ እምነት ላይ እምነት ይኑርህ) 3) እንደ ተፈወስህ አድርገህ ፈውሱን ተቀበል 4) ስሌሎች ም ተናገር የሚሉት ናቸው። በእነርሱ አባባል እነዚህን አራቱን ነገሮች ተከ ትሎ ያደረገ ሰው ይፈወሳል ብለው ያስተምራሉ።[124] የሚያሳዝነው ነገር ከበሽ ታው የማይፈወስ እማኝ እምነት እንደጎደለው አድርገው ስለሚወስዱ ብዙ ሰዎ ችን ግራ በመጋባትና በጭንቀት ውስጥ ሊጥሏቸው ችሎአል።

በርግጥም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚች ዓለም የአዝአብሔርን መንግ ሥት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይዞ በመምጣትና ስለ እኛ ኃጢአት በመሞት የዘላ ለም ሕይወትን ሲሰጠን፥ የፈውስንም በረከት እንደ ፈቃዱ እንድንቀበል አድር ጓል። ግቴዎስ በወንጌሉ ላይ እንደሚነግረን ኢየሱስ በዚች ምድር በሚመላ ለስበት ጊዜ (ማለትም ገና ወደ መስቀል ሳይሄድ) ደዌን እየፈወሰና መናፍስትን

ም ያምናሉ። ኬንዮን፡ *ጀለስ ዘ ሂለር* (ቢለትል፡ ኬንዮን ጎስፔል ፐብሊሺንግ ሶሳይቲ፤ 1943) 44, 6 7።

124

ሚስተር ኬነት ሄገን እንደሚሉት ከሆነ ኢየሱስ በራሱ ከተገለጠላቸው በኋላ ከላይ የተጠቀሱትን አራቱን ነጥብ ያዘለ መመሪያ ሰጣቸውና በእነዚህ የሚያምን የሚፈልገውን ሁሉ ከእነና ከአባቱ ይቶ በላል ለለኝ ይለሉ። — ኬነት ሄገን፡ *ያው ቶ ሪይት ዩር ለውን ቲሴት ዊዝ ጎድ* (ቶልሳ፡ ፈዝ ላይብረሪ፤ 1979) 5, 20, 21, 32። ሄገን፡ *ሃቭንግ ፈይዝ ሊን ዩር ፈይዝ* 1980። በይበልጥ ስለ ብልጽግና ወንጌል ስማወቅ የሚፈልግ ሰው ከዚህ የሚቀጥለውን መጽሐፍ ቢያነብ እጅግ ጠቃሚ የሆ ነ አውቶትን ይቀስማል። መጽሐፉንም የጻፉት ሰው በብልጽግና ወንጌል እንቅስቃሴ ውስጥ የነበሩ ለለነበሩ ብዙ ዋልት የሆነ መረጃ በማቅረብ ትምህርቱ አረም የበዛበት በመሆኑ የተሳሳተውን አስተሳሰ ብ አጋልጠውታል። መጽሐፉም እንደሚከተለው ይሆናል — ዲ አር መክኮነል፡ *ሊ ዲፍረንት ጀ ፓል፡ ሊ ሂስቶሪካል ሊንድ ቢብሊካል አናሊሰስ አቭ ምደርን ፈይዝ ሙቭመንት* (ግሀዲ፡ ሄነሪሪ ክሪን ፕብሊሸርስ፤ 1988)። እንዲሁም በሃንክ ሄነገራፍ የተጻፈው መጽሐፍ ስለ ብልጽግና ወንጌል ብዙ ጠቃሚ መረጃዎችን የያዘ ነው — ሃንክ ሄነገራፍ፡ *ክርስቲያኒቲ ሊን ክራይስስ* (ዩጂን፡ ሃርቬስ ት ሃውስ, 1993)። ፊ፡ *ዘ ዲዚዝ ኦቭ ዲ ሄልዝ ኢንድ ዌልዝ ሽፓል* (ቢቨርሊ፡ ፍሮንት ላይን ፤ 1985)። ዶ/ር ጎርደን ፊ በመጽሐፋቸው ላይ ታሳት የሆነን ትንቢታዊ ግስጠንቀቂያ ሲናገሩ — ግንም ይህንን የስህተት ትምህርት የሚያስተምር ሁሉ የሚያስፈራው የአዝአብሔር ፍርድ ይጠብቀ ዋል ምክንያቱም ፍርድ ከአዝአብሔር ቤት ይጀምራልና ነው በማለት ሰቶታቸውን ገልጸዋል።

በስሙ እያወጣ መጣ፥ ይህም በነቢዩ በኢሳይያስ «እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ» የተባለው ይፈጸም ዘንድ ነው ብሎአል (ኢሳ 53፥4፤ ማቴ 8፥16-17)። ጴጥሮስም ደግሞ የኢሳይያስን ትንቢት በመጥቀስ «ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ። እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና፥ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል።» በማለት የመገረፉ ቁስል ፈውስ እንደ በጎች ከተቅበዘበዝንበትና ከጠፋንበት አምጥቶን የዘላለም ሕይወትን እንደሰጠን አስቀምጦታል («የመገረፉን ቁስል» የተጠቀመበት ለደህንነት ነው እንጂ ለሥጋ ፈውስ አይደለም፥ ኢሳ 53፥5-6። 1ጴጥ 2፥24-25። ማቴዎስ ደግሞ «ደዌያችንን ተሸከመ» የሚለውን የተጠቀመበት ለሥጋ ፈውስ ነው)።

ስለዚህም ደዌያችን ልክ እንደ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ ተደምስሶል ናል ብለን ካመንን ሁሉም አማኝ ኢየሱስን ሲቀበል ወዲያውኑ ኃጢአቱ እንደ ሚደመሰስለት ሁሉ ከደዌም ነጻ መሆን ነበረበት ማለት ነው። ካልሆነስ በኢየ ሱስ ክርስቶስ ላይ ያለን ከዘላለም ሞት ያዳነን እምነት የሥጋን ፈውስ ለማም ጣት ብቁ አልሆነም ወይ? ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል። ታዲያ ይህንን ስንል እግዚአብሔር አይፈውስም ማለታችን ነው? በፍጹም አይደለም! እግዚአብ ሔር ሕዝቡን ትናንትም እንደ ፈወሰው ሁሉ ዛሬም ይፈውሳል፥ እግዚአብሔር እምላካችን ፈዋሽ አምላክ ነውና (ዘጸ 15፥26)።

በተለይ ደግሞ በአዲስ ኪዳን ዘመን ስምንኖረው ልጆቹ እግዚአብሔር በልጁ በኩል ፈውስን እንድንቀበል አድርጓል። መንፈሱንም በማፍሰስና ልዩ ልዩ ስጦታዎችን በመስጠት የድል ሕይወት እንድንኖር አስችሎናል። ቢሆንም ቅሉ ወደ ኢየሱስ ስንመጣ ከኃጢአትና ከሴጣን ባርነት ነጻ እንደምንወጣ እንጂ ከችግር፥ ከበሽታ እንዲሁም ከመከራ ፍጹም ነጻ የሆነ ኑሮ እንደምንኖር ቃል አልተገባልንም። እንደውም ጌታ «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ» በማለት ስሚመጣብን ችግርና መከራ ራሳችንን አዘጋጅተን እንድንኖር ነግሮናል (ዮሐ 1 5፥33)።

በመሠረቱ ኢየሱስ በመራው ሥራ በመንፈስ ቅዱሱ በኩል ወደ አብ መግባት አግኝተናልና ያለብንን ሸክምና ችግር ሁሉ ወደ እርሱ ይዘን ልንቀርብ ይገባናል እንጂ እንደ እርኩም አቀርቅረንና ቆዝመን ልንሄድ አይገባንም። እን

ደውም በዕብራውያን መልእክት ላይ ኢየሱስ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና ምሕረትን እንድንቀበልና በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ በማለት ያበረታታናል (ዕብ 2፥18፤ 4፥15-16)።

እግዚአብሔር ዛሬ በቤተክርስቲያን ላይ መንፈሱን በማፍሰስ ልዩ ልዩን ስጦታዎችን በመስጠትና ድንቅና ታምራትን በማድረግ ልጆቹን ከድል ወደ ድል ሲያሸጋግር፥ ያላመኑትን ደግሞ ወደ ዘላለም ሕይወት ያመጣቸዋል። መቼም ከለ እምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት ባይቻልም እምነታችን የፈለግነውን ነገር ወይም የምኞታችንን አባብ ሁሉ የሚሰጠን ልዩ ኃይል አይደለም። እንደውም በተቃራኒው እምነት ራሳችንን ለማስደሰት ሳይሆን ነገር ግን ለእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ አሜንና አዎን በማለት በተስፋ እንድንገዛ ያደርገናል። በመሆኑም ሁሉን ቻይ የሆነውን የጌቶች ሁሉ ጌታ እግዚአብሔርን እንደ ፈለግነው አንድና ዘው መረን አይለቅቀንም (በነገራችን ላይ እግዚአብሔር በግንም አይታዘዝም አይመራምም፥ ኢሳ 40፥12-17))።

በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ ባላቸው እምነት ምክንያት ንብረታቸውን ሁሉ ተቀምተው ከሮሜ የተባረሩትንና «ግማሽ በነቀፋና በጭንቅ እንደ መጫወቻ» የሆኑትን አይሁድ ክርስቲያኖች ለማጽናናት የዕብራውያን ጸሐፊ በመልእክቱ ላይ የእምነት አባቶችን በመጥቀስ የተስፋውን ቃል ለማግኘት መጽናት እንደሚ ያስፈልጋቸው ይነግራቸዋል (ዕብ 10፥32-39)። በመቀጠልም አንዳንዶቹ የተገላ ቸውን ተስፋ አላገኙም ሌሎቹ ደግሞ አግኝተዋል ብሎአል። ነገሩን ሲያብራራ ውም ግማሾቹ በእግዚአብሔር ስለ አምነታቸው ተመስክሮላቸው ሳለ የተገላቸ ውን ተስፋ አላገኙም — እንደውም በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እምነት እንዳ ንዶቹን መከሸቻ አደረጋቸው፥ እስከ ሞት ድረስ እስደበደባቸው፥ በእስራትና በመ ሀኒ ፈተናቸው፥ በመጋዝ አሰነጠቃቸው፥ ሁሉን አሳጣቸው፥ መከራን በመቀበል አሰጨነቃቸው፥ ምድር አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ እንዲሁም በዋ ሻና በጉድጓድ አቅበዘበዛቸው ሲል በዚያው እምነት ደግሞ ሌሎቹ የኤርትራን ባሕር ተሻገሩ፥ የኢያሪኮን ቅጥር አፈረሱ፥ ነገሥታትን ድል መቱ፥ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አገኙ፥ የአንበሶችን አፍ ዘጉ፥ የእሳትን ኃይል አጠፉ፥ ከሰይፍ

ስለት አመለጡ፥ ከድካማቸው በረቱ፥ በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ፥ ሴቶቹ ደግሞ የሞቱ ልጆቻቸው ከሞት ተነሡላቸው በማለት ይነግረናል (ዕብ 11፥1-38)።

በተጨማሪም እግዚአብሔር ሁሌ በመፈወስ ተግባር ላይ ሲሆን ፈውሱ መንፈሳዊ ፈውስ፥ የሥጋ ፈውስ፥ ወይም ደግሞ የልቡና ፈውስ ሊሆን ይችላል። ይሆንን ሁሉ ግን እርሱ እንደፈቀደ በራሱ ጊዜና ሰዓት፥ ራሱን በልጁ በኩል ሊገ ልጽ በፈቀደ መጠን ያደርገዋል። እኛ ማድረግ የሚገባን ነገር ምንድነው ቢባል ሳንታክት በእምነት ሆነን ልጁ ባስተማረን ጸሎት «ያንተ እንጂ የኔ ፈቃድ አይ ሁን» ብሎ በመጸለይና እግዚአብሔርን በሕይወታችን እግዚአብሔር እንዲሆን መፍቀድ ብቻ ነው (ሉቃ 22፥42፤ ማር 14፥36፤ ማቴ 26፥34)። ምንም እንኳን አምላካችን ለእኛ ካለው ታላቅ ፍቅር የተነሳ ሥጋን በመደረብ ተዋርዶ ቢመጣና ወዳጆቹና ወንድሞቹ ብሎ ቢጠራንም ለአምላክነቱ የሚገባውን አክብሮትና ፍር ሃት ልንነፍገው አይገባንም።

ስለ ስጦታዎች ማጠቃለያ

1. ስጦታዎቹ የሚሰጡን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው
2. ስጦታዎቹን ተግተን እንድንፈልግ ተነግሮናል
3. መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎቹን እንደወደደ ለቤተክርስቲያን ጥቅም ይሰጣል
4. እያንዳንዱ አማኝ ቢያንስ አንድ ስጦታ አለው
5. የስጦታውም ትልቅነትና ትንሽነት ካንዱ ወደ አንዱ ሊለያይ ይችላል
6. ምንም እንኳን መዳን የግል ውሳኔ ቢሆንም ቅሉ የክርስትና ኑሮ የጋራ ስለሆነ ስጦታዎቹን ይዘን በመምጣት ባንድነት ተጋግዘን አካላቱን መገንባት ይኖርብና ል። ቤተክርስቲያንም ወደ ሙሉ እድገት መድረስ የምትችለው ስጦታዎቹን በእንድነት ስንጠቀምባቸው ነው።
7. ስጦታዎቹን በእምነትና በፍቅር መጠቀም ይኖርብናል
8. ስጦታዎቻችንን በአገልግሎት ላይ በማዋል ማሳደግ አለብን
9. ሰጪው እግዚአብሔር እንደሆነ አውቀን በተዋረደ መንፈስ በመሆን ስጦታ ዎቹን ቤተክርስቲያንን ለማነጽ መጠቀም ይኖርብናል ይህም የመንፈስን ኅብረት መጠበቅን ያጠቃልላል። እኛ የማንረባ ባሪያዎች ስንሆን የተሰጠንን አደራ እን

ደተወጣን ብቻ ልንቆጥር ይገባናል እንጂ ራሳችንን ከሌሎች እንደምንበልጥና እንደምንሻል አድርገን ወሰደን በትዕቢት በመነፋት ስሥጋና ለሰይጣን ምክንያት እየሰጠን እግዚአብሔርን ልንበድል አይገባንም።

10. ስጦታዎች ሁሉ በኢየሱስ ላይ ያተኮሩና እርሱን የሚያከብሩ መሆን ይገባቸዋል
11. የአንድ አማኝ እውነተኛ መንፈሳዊነት የሚለካው ለኢየሱስ ጌትነት በመገዛት የመንፈስን ፍሬ በማፍራት እንጂ ባለው የስጦታዎች ትልቅነትና ብዛት አይደለም። ስለሆነም ስጦታዎቻችንን በቅድስናና እግዚአብሔርን በመምሰል ስንጠቀም አገልግሎታችን ይበልጥ ውጤታማ ይሆናል
12. ስጦታዎቻችንን በአግባቡና በሥርዓት መጠቀም ይኖርብናል። ስለሆነም እንዴት ባለ ሁኔታ መጠቀም እንደሚገባን ማስተዋል ይኖርብናል።
13. ትንቢትንና በልሳን መናገርን ደግሞ እንዳንከላከል ተነግሮናል
14. ሁሉም ስጦታዎች ለቤተክርስቲያን አስፈላጊ ናቸው
15. ስጦታዎቹም ከእግዚአብሔር ስለ ተሰጡን በሙሉ ሥልጣን ልንጠቀምባቸው ይገባናል

«ስለዚህ ምክንያት በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ራት አንበረከክሁሁ፤ በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደከብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይሰጣች ሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፥ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር በፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል ፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፤ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ።»

ኤፌሶን 3፤14-19

መዝጊያ

ፍቅር ካለ ስሜት ራሱን ሊገልጥ አይችልም

እንግዲህ እስካሁን ድረስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማንነትና መለኮታዊ ተልእኮ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ከፍሎች በማገናዘብ ተመልክተናል። ታዲያ መጽሐፉን ከመዝጋታችን በፊት ስለ መንፈስ ቅዱስ ጠቅለል ባለ መልኩ መነጋገር ያስፈልገናል። ከዚህ በፊት እንዳየነው ሁሉ ጌታ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለሆነ የርሱ መገኘት ማለት የእግዚአብሔር በኃይል መገኘት ማለት ነው። ከዘፍጥረት አንስቶ እስከ ጌታ ዳግም ምጽአት ድረስ መንፈስ ቅዱስ በሰው ልጅ ሕይወትና ታሪክ ውስጥ ያለው ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ያሳየናል። ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ከገባበት የኃጢአት አዘቅት ውስጥ ለማውጣት፥ ከሞት አድኖ የዘላለም ሕይወት ለመስጠት፥ እንዲሁም የእግዚአብ

ሔር ልጆች እንድንሆን በልጅነት ሥልጣን ሊሾመን ወደዚህች ዓለም የመጣው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲሆን አገልግሎቱንም የፈጸመው በዚሁ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር።

እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና በነቢያት በኩል ወደ ሩት ስለሚከናወነው ነገርና ስለ ክርስቶስ መምጣት ለአባቶቻችን ተናግሮ ነበር። መልእክቱን ያቀረቡት ነቢያት የመሢሑ መምጣትና የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ መቼ እንደሚፈጸም ስላላወቁ ይሆን የእግዚአብሔር መዳን ተግ ተው እየፈለጉ መረመሩት። መላእክቱ እንኳን ሳይቀር የትንቢቱን ፍጻሜ ሊመለ ከቱ ይመኙ ነበር (ዕብ 1፥1-3፤ 1ጴጥ 1፥10-20፤ ሉቃ 10፥23-24)። በዚህ በመ ጨረሻው ዘመን ስለምናር ለእኛ ግን በነቢያት በኩል ሳይሆን ነገር ግን ሁሉን ወራሽ ባደረገው፥ ዓለማትን በፈጠረበት፥ የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርይው ምሳሌ በሆነው፥ ሁሉንም ነገር በሥልጣኑ ቃል ደግፎ በያዘው፥ እንተ ልጁ ነህ እኔ ዛሬ ወልጂሃለሁ ባለው፥ እንዲሁም መላእክቱን መናፍስት አገልጋዮቹን ደግሞ የእ ሳት ነበልባል በሚያደርገው በውድ ልጁ በኩል ተናገረን።

የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ በመምጣት በሞትና ትንሣኤው ሰላምን ሰጠን። ይህም በመጀመሪያ ቀርበው ለነበሩት ለአይሁድ ከዚያም ርቀን ለነበርነው ለእኛ ሰላምን የምሥራች ብሎ ሰበከ፥ በርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን። የሚቀድሰውና የሚቀደሱት አንድ ናቸውና ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ በሞቱ ሞትንና ዲያብሎስን በመሻር በሕይወታችን ሙሉ በሞት ፍርሃት በባርነት ታስረን የነበርነውን እኛን ነፃ አወ ጣን። የምሥራቹንም ቃል በምልክትና በድንቅ በልዩ ልዩ ተአምራት አንዲ ሁም መንፈስ ቅዱሱን አብሮ በማደል መስክረ። መንፈሱንም በውስጣችን በማ ስቀመጥ እኛንም ከሰማያዊ ጥሪ ተካፋዮች አደረገን (ዕብ 1፤2፤ ኤፌ 2)።

ኢየሱስም ዲያብሎስንና ሞትን ድል አድርጎ ከሞት ከተነሳ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ አርሱ በሞቱና ትንሣኤው እውን ያደረገውን የሰላም ወንጌል ለመስ በክ ይዘው ከመውጣታቸው በፊት በኢየሩሳሌም ሆነው መንፈስ ቅዱስን እንዲጠ ብቁ ነገሮአቸው ስለነበር እነርሱም ይህንን ትእዛዝ በመቀበል መንፈሱን ተጠመ ቁ፥ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ለማዳረስ ወጡ። ይህ የሰላም ወንጌል የእግዚአ ብሔር ቃልና ኃይል በመሆኑ (ሮሜ 1፥17፤ 1ተሰሎ 2፥13፤ 1ጢሞ 2፥4) የመጣው

በመንፈስ ቅዱስ በሚሆን መገለጥ ነው (1ቆሮ 2፥10-16፤ ኤፌ 3፥5-7)። የእግዚ አብሔርም ኃይል ስለነ በጌታ ኢየሱስ አምነን ልባችንን ስንከፍት መንፈስ ቅዱስ አዲስ ፍጥረት አድርጎ ይለውጠናል። ይህንንም የሚያደርገው ለአዲስ ልደት በሚሆን እጥበት (1ቆሮ 6፥11፤ ሮሜ 12፥2፤ ቆላ 3፥10፤ ቲቶ 3፥5)፣ በመ ቀደስ (2ተሰሎ 2፥13፤ ሮሜ 15፥16፤ 1ቆሮ 6፥11)፣ ለቤዛ ቀን የሚሆንን ሳትመት ልባችንን በማተም (ኤፌ 1፥13፤4፥30፤ 2ቆሮ 1፥21-22)፣ በውስጣችን በማደር ቤተመቅደስ ሲያደርገን ፍሬን እንድናፈራም ይረዳናል (1ቆሮ 3፥16-17፤ 6፥19-20 ፤ ገላ5፥22-24፤ ፊል 4፥4-9፤ ቲቶ 2፥11-14)።

መለወጣችንንና የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ደግሞ የምናውቀው መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚነግረን ግለትም ተጨባጭ በሆነ መንገድ [Objective expe rience] ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በስሜታችንም በኩል [Subjective experience] እና ውቀሞለን። ምክንያቱም ጌታ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን በመሆን ይጸልይልናል (የልባን ጸሎት)፥ በማይናገር መቃተት ይማልድልናል፥ እግዚአብሔርን አባዬ ብለን እንድንጠራው ያደርገናል። ይህም ደግሞ የእግዚአብሔር ልጆች እንጂ የሕግና የኃጢአት ባሪያዎች አለመሆናችንን ያረጋግጥልናል፥ እንዲሁም የጌታች ንን ድምጽ እንድንሰማ ያስችለናል (ዮሐ 10፥14-16፤ ሮሜ 8፥14-17፤ 26-27፤ 1ቆሮ 6፥11፤ 12፥12፤ ገላ 3፥2-5፤ 4፥5-7፤ ኤፌ 1፥13-14፤ ቲቶ 3፥5-7)። ስለዚ ህም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እግዚአብሔርን በሕይወታችንም እንለማመደዋ ለን ማለት ነው።

ጸሎትን በተመለከተ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ እንድንጸልይ ይነግረናል (ኤፌ 6፥18-20፤ ይሁዳ 20)። ይህም በመንፈስ መጸለይ ማለት በል ባን መጸለይና በመንፈስ ቅዱስ የተመራ ጸሎትን ማቅረብ ነው። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን አሳብ ስለሚያውቅ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይጸልይልናል ወይም ደግሞ እንድንጸልይ ያደርገናል። ይህም ደግሞ ልባችንን በመምራት የምንጸልይባቸውን ርዕሶች በመስጠትና እንዴት እንደምንጸልይ በመምራት ነው (1ቆሮ 14፥15፤ ሮሜ 8፥14-17፤ 26-27፤ ገላ 4፥5-7)።

እምልክን በተመለከተ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በርሱ የተመራን አምልኮ ለእምላክችን እንድናቀርብ ይረዳናል። እግዚአብሔር መንፈስ ነውና የምናመል ከው ሁሉ በእውነትና በመንፈስ ማምለክ ይኖርብናል። አንዳንድ ሰዎች በአም

ልኮ ጊዜ ስሜት ቦታ የለውም ምክንያቱም እግዚአብሔርን ማምለክ መንፈስን ነው የሚጠይቀው ይላሉ። በመሠረቱ አሳባችንን፣ ስሜታችንን፣ ኃይላችንን እን ዲሁም ልባችንን አሰባስበን ስርሱ ካልሰገድን በምን ዓይነት ሁኔታ ልናመልክ እን ችላለን ? የቀደመችው ትእዛዝ እግዚአብሔር አምላካችንን በፍጹም ልባችን፣ በፍጹም ነፍሳችን፣ በፍጹም አሳባችን፣ እንዲሁም በፍጹም ኃይላችን እንድን ወደው ትነግረናለች (ዘዳ 6፥4፤ ማቴ 22፥37-38፤ ማር 12፥30-31፤ ሉቃ 10፥27-28)። ታዲያ ስሜታችንን ሳንጠቀም እንዴት እድርገን በፍጹም ነፍሳችን፣ አሳባ ችን፣ ልባችንና ኃይላችን ልንወደውና ልናመልከው እንችላለን? በመሠረቱ እግ ዚአብሔርን የምናመልክበት ዋናው ምክንያት ስለምንወደው ነው። አምልኮአ ችን ደግሞ የፍቅራችን መግለጫ መሆኑ እሙን ነው። ፍቅር ደግሞ ካለ ስሜት ራሱን ሊገልጥ አይችልም።[125] ስለዚህም ስሜታችን በአምልኮ ውስጥ ትልቅ ስፍራ አለው ማለት ነው። ምክንያቱም ስሜታችንን በመጠቀም ነው ፍቅራችንን የምንገልጸው። ይህንን ሰንል ደግሞ ቅጥ ያጣ የስሜት ሁካታ ይኑር ማለታችን አይደለም። ነገር ግን ጌታ መንፈስ ቅዱስ ስሜታችንንና መንፈሳችንን በመቀስ ቀስና በመመምራት በእግባቡና በሥርዓት አምላካችንን በፍጹምነት እንድናመ ልከው ይረዳናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት የመንፈስ አምልኮ ውስጥ አንዱ የሆነው ንጉሥ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ሠርቶ በጨረሰ ጊዜ በምረ ቃው ሥነሥርዓት ላይ የተከናወነው ነው። ንጉሡም ጸሎቱን በፈጸመ ጊዜ እሳት ከሰማይ ወረደ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና ሌላ መሥዋዕቱን በላ፤ የእግዚ አብሔርም ክብር ቤቱን ሞላው። የእግዚአብሔርም ክብር ቤቱን ሞልቶት ነበርና ካህናቱ ወደ እግዚአብሔር ቤት መግባት አልቻሉም። ይህንን ታላቅ ነገር ያዩት ሕዝብ ሁሉ በወለሉ ላይ በግምባራቸው በመደፋት «እርሱ መልካም ነውና፥

125

ፍቅር ሁለት ገጽታዎች አሉት አንርሱም ውስጣዊ ገጽታና ውጫዊ ገጽታ ናቸው። ውስጣዊ ገጽታ ማለት በስሜታችን በኩልና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ [Motive] የምንገለጠው ነው። ስምሌ ከእግ ዚአብሔር ጋር ያለን የአባትነትና የልጅነት ፍቅር በስሜት ላይ ያተኮረ ስለሆነ ውስጣዊ ነው። ውጫዊው ደግሞ በፍቃደኝነት፣ በምርጫና በውሳኔ ላይ የተመረኮዘ ነው። ይህም ምግባርን የተመለ ከተ ሲሆን ትእዛዙን እንደንፈጽምና ፍሬን እንድናፈራ ስለሚያደርገር እግዚአብሔርን መውደዳችንን እንገልጽበታለን።— ርበርትሰን ሙኪዲልኪን፣ *ለን ሊንትሮሳክሽን ቱ ዚብሊካል ኢቲክስ* (ሚተን፣ ቲንዳል ሃውስ ፓብሊሸርስ፤ 1989) 19-24።

ምሕረቱ ለዘላለም ነውና» እያሉ በመዘመር እግዚአብሔርን አመስኩት (2ዜና 7፥1-7)። እኛም በዚህ በመጨረሻው ዘመን የምንኖር፥ በጸጋ ላይ ጸጋ የተቀበ ልን አማኞች መላው አካላችንን በአምላካችን አግ ሥር በመጣል በፍቅርና በአክብሮት ሆነን በደስታና በፍንደቃ ልናመልከው ይገባናል።

በመጨረሻም እንግዲህ ጌታ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔርን በመንፈስ እንድናመልከው ሲረዳን (ፊል 3፥3)፥ አምልኮውም በተሰጠን በልዩ ልዩ የጸጋ ሰጦታ ሊሆን ይችላል (1ቆሮ 6፥25-26)፤ በመንፈስ ሆኖ በመዘመር ሊሆን ይች ላል (1ቆሮ 14፥15)፤ ወይም ደግሞ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔ በልባ ችን በመቀኘት ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም ደግሞ ሰውነታችንን እግዚአብሔ ርን ደስ የሚያሰኝ፥ ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርገን በማቅረብ ስናመልከው ይህም ደግሞ ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችን ነው (ሮሜ 12፥1-2)። ስለዚህ ሁሉ ግን ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንደወደደ ለጥቅም ያደርገዋል (ኤፌ 5፥19፤ ቆላ 3፥16)። ስለዚህም ዳዊት በመዝሙሩ ላይ *«ዋሳ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፥ አቤቱ፥ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍ ቃለች። ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች።»* (መዝ (42)፥1-2) እንዳለው ሁሉ እኛም ዕለት ዕለት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ልንጠግ ይገባናል።

ከብር ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ስለእግዚአብሔር አምላካችን ይሁን፤ አሜን።

Bibliography [የመጽሐፍ ሰንጠረዥ]

Allison, D. C. *'The Living Water."* SVTQ 30(1986): 143-157.

Arnold, Clinton E. *Ephesians: Power and Magic; The concept of power in Ephesians in light of its historical setting.* Cambridge: Cambridge University Press, 1989.

_____. *3 Crucial Question About Spiritual Warfare.* Grand Rapids: Baker Book House, 1997.

Avigad, N. *Discovering Jerusalem.* Nashville: Nelson, 1980.

Barnett, Paul. *The Second Epistle to the Corinthians.* Grand Rapids: Eerdmans, 1997.

Barron, Bruce. *The Health and Wealth Gospel: What is going on today in a movement that shaped the faith of millions?* Downers Grove: IVP, 1987.

Bauer, Walter, *A Greek-English Lexicon of the New Testament* and *Other Early Christian Literature.* Chicago: Chicago University Press, 1979.

Belleville, Linda L. *Second Corinthians.* Downers Grove: IVP, 1996.

Bittinger, A. *Gifts and Graces: A Commentary on 1 Corinthians 12-14.* Grand Rapids: Eerdmans, 1967.

Brown, Driver & Briggs. *A Hebrew and English Lexicon of the Old Testament.* Oxford: Clarendon Press.

Bruce, F. F. *Epistles to the Hebrews.* Grand Rapids: Eerdmans, 1990.

_____. *The Spirit in the Letter to the Galatians in Essays on Apostolic Themes: Studies in honor of Howard M. Errin.* Peabody: Hendrickson, 1985.

_____. *The Hard Sayings of Jesus.* Downers Grove: IVP, 1983.

_____. *The Gospel of John.* Grand Rapids: Eerdmans, 1983.

Bruner, Fredrick D. *A Theology of the Holy Spirit: The Pentecostal Experience and the New Testament Witness.* Grand Rapids: Eerdmans, 1970.

Carson, D. A. *Showing the Spirit: A Theological Exposition of 1 Corinthians 12-14.* Grand Rapids: Baker Book House, 1987.

Carson, Moo and Morris. *An Introduction to the New Testament.* Grand Rapids: Zondervan, 1992.

Copeland, Kenneth. *The Laws of Prosperity.* Fort Worth: Kenneth Copland Publication, 1989.

_____. *The force of Faith.* Forth Worth: KCP, 1983.

Cranfield, C.E.B. *The Epistle to the Romans V. 1 & V. 2.* Edinburgh: T&T Clark, 1994.

Daube, David. *The New Testament and Rabbinic Judaism.* London: 1956.

Deer, Jack. *Surprised by the Voice of God: How God* Speaks *Today Through Prophecies, Dreams and Vision.* Grand Rapids: Zondervan, 1996.

_____. *Surprised by the Power of the Spirit: Discovering How God Speaks and Heals Today.* Grand Rapids: Zondervan, 1993.

Dunn, James. *Jesus and the Spirit.* London: SCM, 1975.

_____. *Baptism in the Holy Spirit.* Naperville: SCM, 1970.

Ellis, E. E. *Prophecy and Hermeneutic in Early Christianity: New Testament essays.* Grand Rapids: Eardmans, 1978.

Erickson, Millard. *Christian Theology.* Grand Rapids: baker Book House, 1994.

Fee, Gordon D. *Paul, the Spirit, and the People of God.* Peabody: Hendrickson, 1996.

_____. *God's Empowering Presence: The Holy Spirit in the Letters of Paul.* Peabody: Hendrickson, 1994.

_____. *Gospel and Spirit: Issues in New Testament Hermeneutics.* Peabody: Hendrickson, 1991.

_____. *The Disease of the Health and Wealth Gospels.* Beverly: Frontline Publishers, 1985.

_____. *The First Epistles to the Corinthians.* Grand Rapids: Eerdmans, 1987.

Gaffin, Richard B. *Perspectives on Pentecost: Studies in New Testament Teaching on the Gifts of the Holy Spirit.* Phillisburg: Presbyterian and Reformed, 1979.

Geisler, Norman. *Answering Islam: The Crescent in the Light of the Cross.* Grand Rapids: Baker Book House, 1993.

Green, Joel B. *The Gospel of Luke.* Grand Rapids: Eerdmans, 1997.

Green, Michael. *I Believe in the Holy Spirit.* Grand Rapids: Eerdmans, 1989.

Grudem, W. A. *"1 Corinthians 14:20-25: Prophesy and Tongues as signs of God's Attitudes."* WTJ 41(1979) 381-396.

_____. *The Gift of Prophecy in 1 Corinthians.* Washington: University Press of America, 1982.

Gundry, Robert H. *MARK: A Commentary on His Apology for the Cross.* Grand Rapids: Eerdmans, 1993.

Hagin, Kenneth. *Classic Sermons.* Tulsa: KHM, 1993.

_____. *Redeemed from Poverty, Sickness and Spiritual Death.* Tulsa: KHM, 1993.

_____. *Having Faith in Your Faith.* Tulsa: KHM, 1980.

_____. *How to Write Your Own Ticket With God.* Tulsa: Faith Library, 1980.

_____. *Key to Scriptural Healing.* Tulsa: Faith Library, 1977.

Hanegraaff, Hank. *Christianity in Crisis.* Eugene: Harvest House Publishers, 1993.

Hilderbrandt, Hilf. *An Old Testament Theology of the Spirit of God.* Peabody: Hendrickson, 1995.

Hoekma, Anthony. *Holy Spirit Baptism.* Grand Rapids: Eerdmans, 1972.

Horton, Michael. *The Agony of Deceit: What Some TV Preachers Are Really Teaching.* Chicago: Moody Press, 1990.

Horton, Stanley M. *What the Bible Says About the Holy Spirit.* Springfield: Gospel Publishing House, 1995.

Kaiser, O. *Issaiah 13-39: A Commentary.* Philadelphia: Westminster, 1974.

Kaiser, Walter Jr. *Toward Rediscovering the Old Testament.* Grand Rapids: Zondervan, 1991.

Keener, Craig S. *The SPIRIT in the GOSPELS and ACTS*: Divine Purity and Power. Peabody: Hendrickson, 1997.

_____. *Matthew.* Downers Grove: IVP, 1997.

_____. *3 Crucial Question About the Holy Spirit.* Grand Rapids: Baker Books, 1996.

_____. *IVP Bible Background Commentary of the New Testament.* Downers Grove: IVP, 1993.

Kenyon, E. W. *Identification: A Romans in Redemption.* Seattle: Kenyon Gospel Publishing, 1968.

_____. *Jesus the Healer.* Seattle: KGP, 1943.

Koch, K. *Is Daniel Also Among the Prophets? Interpreting the Prophets.* Philadelphia: Fortress, 1987.

Kydd, A. N. *Charismatic Gifts in the Early Church.* Peabody: Hendrickson, 1984.

Ladd, George E. *A THEOLOGY OF THE NEW TESTAMENT.* Grand Rapids: Eerdmans, 1996.

_____. *The Holy Spirit in Galatians, in current issues in Biblical and Patristic Interpretation.* Grand Rapids: Eerdmans, 1975.

Lane, William L. *The Gospel According to Mark.* Grand Rapids: Eerdmans, 1974.

Larkin, William Jr. *Acts.* Downers Grove: IVP, 1995.

Larkin, William & Williams, Joel. *Mission in the New Testament*. Maryknol, New York: Orbis Books, 1998.

Lederle, Henry I. *Treasures Old and New: Interpretations of "Spirit Baptism" in the Charismatic Renewal Movement*. Peabody: Hendrickson, 1988.

Liefeld, Walter L. *Ephesians*. Downers Grove: IVP, 1997.

Lloyd-Jones, Martyn. *Joy Unspeakable: Power and Renewal in the Holy Spirit*. Wheaton: Harold Shaw Publishers, 1984.

Lock, Walter. *A Critical and Exegetical Commentary on the Pastoral Epistle*. New York: Charles Scribner's Sons, 1924.

Lull, David J. *The Spirit in Galatia: Paul's Interpretation of Pneuma as Divine Power*. Chico, California: Scholars, 1980.

MacArthur, John F. *Charismatic Chaos*. Grand Rapids: Zondervan, 1992.

_____. *Speaking in Tongues*. Chicago: Moody Press, 1988.

MacGorman, J. W. *The Gifts of the Spirit: An Exposition of* 1 *Corinthians 12-14*. Nashville: Broadman, 1974.

Martin, Ralph P. *The Spirit and the Congregation: Studies in 1 Corinthians 12-15*. Grand Rapids: Eerdmans, 1984.

Marty, Martin E. A Short History of Christianity. Philadelphia: Fortress, 1987.

McConnel, D. R. *A different Gospel: A Historical and Biblical Analysis of the Modern Faith Movement*. Peabody: Hendrickson, 1988.

McGee, Garry B. *Initial Evidence: Historical and Biblical Perspectives on the Pentecostal Doctrine of Spirit. Baptism*. Peabody: Hendrickson, 1991.

McGee, Robert & Sapaugh, Donald. *The Search for Peace: Release from the Torments of Toxic Unforgiveness*. Ann Arbor, Michigan: Servant publication, 1996.

McGrath, Alster. *"I Believe" Exploring the Apostles Creed*. Downers Grove: IVP, 1997.

McQuilkin, Robertson. *An Introduction to Biblical Ethics*. Wheaton: Tyndal House Publishers, 1989

Meier, John P. Matthew: *New Testament Message 3*. Wilmington: Glazer, 1980.

Mills, Watson E. *The Holy Spirit: A Bibliography*. Peabody: Hendrickson, 1988.

Moo, Douglas. *The Wycliff Exegetical Commentary on Romans 1-8* Chicago: moody Press, 1991.

Noll, Mark A. *Turning Points: Decisive Moments in the History of Christianity*. Grand Rapids: Baker Books, 1997.

Oswalt, John N. *The Book of Isaiah Chapters 40-66*. Grand Rapids: Eerdmans, 1998.

Pearlman, M. *The Zealots of Massada*. New York: Scribner's, 1961.

Pink, Arthur W. *The Holy Spirit.* Grand Rapids: Baker Book House, 1970.

Price, Frederick. *Ever Increasing Faith Messenger.* Newsletter, Crenshaw Christian Center, Inglewood, California.

_____. *Is Healing for All?* Tulsa: Harrison House, 1976.

_____. *How Faith Works.* Tulsa: Harrison House, 1976.

Richardson, Cyril C. *Early Christian Fathers.* New York: Macmillan Publishing Company, 1970.

Obinson, J. A. *Turtulian: Passio S. Perpetuae (Martyrdom of St. Perpetuae).* Cambridge (Text & Studies 1,2), 1891.

Schatzmann, Siegfriend. *A Pauline Theology of Charismata.* Peabody: Hendrickson, 1987.

Showers, Ronald E. *The Most High God: A Commentary on the Book of Daniel.* New Jersey: The Friends of Israel Gospel Ministry, 1982.

Stott. John R. *The Baptism and Fullness of the Holy Spirit.* Downers Grove: IVP, 1964.

Stronstand, Roger. *The Charismatic Theology of St. Luke.* Peabody: Hendrickson, 1994.

Synan, Vinson. *The Holiness-Pentecostal Movement in the United States.* Grand Rapids: Eerdmans, 1971.

The Zondervan Pictorial Encyclopedia of the Bible Vol. 2. Merrill Tenney (Gen. Editor). Grand Rapids: Regency Reference Library.

Thomas, Robert & Gundry, Stanley. *A Harmony of the Gospels.* San Francisco: Harper, 1978.

Vangemeren, Willem A. *Interpreting the Prophetic Word.* Grand Rapids: Zondervan, 1990.

Walvoord, John F. *Daniel: The Key to Prophetic Revelation.* Chicago: Moody Press, 1971.

_____. *The Holy Spirit.* Findlay, Ohio: Dunham Publishing Company, 1958.

Warfield, Benjamin B. *Counterfeit Miracles.* Edinburgh: The Banner of Truth Trust, 1918, reprint 1972.

Westcott, B. F. *The Gospel According to St. John.* Grand Rapids: Eerdmans, 1973.

Wimber, John. *Power Evangelism.* San Francisco: Harper & Row, 1986.

Wolf, H. W. *Joel and Amos.* Philadelphia: Fortress, 1977.

Wood, Leon. *A Survey of Israel's History.* Grand Rapids: Zondervan, 1986.

_____. *The Holy Spirit in the Old Testament.* Grand Rapids: Zondervan, 1976.